# አርማጌዶን፥ የነዳጅ ዘይትና የመካከለኛው ምሥራቅ ውዝግብ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መካከለኛው ምሥራቅ እና የምዕራብ ሥልጣኔ ማብቂያ የሚነግረን ነገር

ዶክተር ጆን ኤፍ. ዋልቮርድ
Dr. John F. Walvoord

ተርጓሚ ሰሎሞን ደጀኔ

ልዩ ረዳት
ትፍስህት ለማ

Published by
LAPSLEY/BROOKS FOUNDATION
Dallas, Texas --- Addis Ababa
U.S.A. Ethiopia

1995 - 1988

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
1987 (1995 እ.አ.አ.)

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
"Armagedon, Oil and the Middle East Crisis"
by Dr. John F. Walvoord
Copyright 1974, 1976, 1990
Zondervan Press
Grand Rapids. U.S.A.
ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን፥
የታተመውም በደራሲው ፈቃድ ነው።

የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን
ስልክ 201464 ፖስታ 41221
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Publisher
Lapsley/Brooks Foundation
Dallas, Texas, U.S.A.

# ምስጋና

ይህ የትርጉም ሥራ ዳር እንዲደርስ ሞያዊ እርዳታ በመስጠት ረገድ የተሳተፉትን ኢትዮጵያውያን፥ እንዲሁም የቴክኒክ እርዳታ በመስጠትና በማበረታታት የረዱንን ሚስተር ፍራንክ ኪንዝመን፥ ዶ/ር ቤን ሄይል እና ጂን አሊሰንን ከልብ እናመሰግናለን።

# የመጽሐፍ ማውጫ

መቅድም ............................ 11

1. ጥያቄዎች ስለ ወደፊቱ .................... 17

አስደናቂው ሀያኛ ምዕተ ዓመት / ፈጣን ለውጥ / አይቀሬው ቀውስ / የነቢያቱ ድምፅ / "ጊዜያቱ" በማለቅ ላይ ናቸው / መልስ ፍለጋ

2. የአርማጌዶን የጊዜ ሠሌዳ .................. 21

ትንቢቱ ግልጥና ጥርት ያለ ነው / የአውሮፓው ኅብረት ለውጥና የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት / የሰባቱ ዓመታት ቅድመ ሁኔታዎች / የሮም ግዛት ማንሰራራት / እስራኤል ሕልውናዋ ይጠበቅ ይሆን? / ነዳጅ ዘይት እና የሥልጣን ሽኩቻ / አዲሱ ጭለማ ዘመን / እስከ አርማጌዶን ድረስ ያለው የሁኔታዎች ቅደም ተከተል / ከሦስተኛው የዓለም ጦርነት ወደ አርማጌዶን

3. የእስራኤልና የዓረቦች ግጭት ............... 27

የተስፋ ጭላንጭል / ነጻነት-ምድሪቱ-ብልጽግና / የዓረቦች ዓላማ-እስራኤልን ማጥፋት / በ1956ቱ ጦርነት የዓረቦች ማፈግፈግ / ሩሲያ ለእስራኤሎች ተፃራሪ ሆና ቆመች / ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እርዳታ ማጣት / የስድስቱ ቀን ጦርነት / ተአምራዊው የእስራኤል ድል / ሩሲያ ጦርነት እንዲቆም ጥሪ አደረገች / የ1967ቱ ጦርነት የመጨረሻ ቀኖች / አሜሪካና እንግሊዝ ጣልቃ ገብተዋል በሚል በናስር የተናፈሰ ወሬ / የ1967 ጦርነት ውጤቶች / ሩሲያ ግብፅንና ሶሪያን እንደገና አስታጠቀቻቸው / ግብፅ ከሩሲያ ጋር ያላትን ግንኙነት አቋረጠች / ሩሲያ የተቋረጠ ግንኙነትዋን አደሰች / ነዳጅ ዘይት ለማስፈራሪያነት ሲውል / ለ1973 ጦርነት ዝግጅት / የዓረቦች ጊዜያዊ ድል / የዓለም ኅብረተሰብ አስተያየት / የጦርነቱ ጉዳት መጠን / በለስ ለእስራኤል ሲቀና / የሩሲያ የተኩስ አቁም ግፊት / የካምፕ ዴቪድ ስምምነት / የሊባኖስ መወረር / ኢራን- አዲሷ እስላማዊት ሪፐብሊክ / የሳዳም ሑሴን በኢራቅ ውስጥ ሥልጣን መያዝ / ኢራቅ ኩዌትን ወረረች / ተአምራዊው የእስራኤል መትረፍ / ማስጠንቀቂያ/ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነቱ እንደገና ተረጋገጠ

4. ነዳጅ ዘይት በማስፈራሪያነት ................ 43

አዲሱ የዓረብ ኅብረት / የዓለም የኃይል ምንጭ ቀውስ / የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት ዋነኛ ሚና / የ1973ቱ ማዕቀብ / አሜሪካ ነዳጅ ዘይት የማምረት አቅሟና ዕቀባውን ብቻዋን መወጣቷ / እስራኤል ማንን ትመን? / የመጨረሻው ዘመን ትንቢት ሲፈጸም / የአሜሪካ እና ሩሲያ ማሸቆልቆል / የመካከለኛው ምሥራቅ ትንቢታዊ ዕጣ-ፈንታ / የሚቀጥለው ቀውስ- ምን ያህል ሩቅ ነው?

5. ፍልስጥኤም- የተስፋና የጭንቅ ምድር .......... 51

ትንቢት በምድራዊ ሰው ዓይን / ትንቢታዊ ጥያቄዎች ስለ ተስፋይቱ ምድር / አብራም- የተስፋ ሰው / የምድሪቱ ተስፋ / ምድሪቱን ከመውረስ መዘግየታቸው / ከምድሪቱ የመጀመሪያው ጉዟቸው / እስራኤል በግብፅ / ወደ ተስፋይቱ ምድር የመጀመሪያው መመለስ / በመታዘዝ ወዲያው ውርስን ማግኘት / ሁለተኛው ጉዞ- ምርኮው / ሁለተኛው የመመለስ ተስፋ / የዳንኤል ጸሎት፥ ሁለተኛው መመለስ / ቤተ መቅደሱ እንደገና ተሠራ / ቤተ መቅደሱ በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ / የቤተ መቅደሱ መፍረስ / ሦስተኛው ጉዞ / ለመጨረሻ ጊዜ ስለመመለሳቸው የተነገረ ትንቢታዊ ተስፋ / የተበተኑት እስራኤላውያን ስደት / የሦስተኛው መመለስ ጅማሬ / የ1917ቱ የባልፎር መግለጫ / በ1948 የእስራኤል መንግሥት መመሥረት / የእስራኤልና የዓረቦች ጦርነት (1948-1949) / ትንቢቶቹ ተፈጽመው ይሆን? / በቀላሉ የሚገኝ ክብር የለም / የመመለሱን ተስፋ የሚፈጽመው አዲስ መንግሥት ይሆናል / መድረኩ ሲመቻች

6. የነቢያት ከተማ......................... 67

የተከበሩ ትዝታዎች / የፍጻሜው ከተማ / ጥንታዊው የኢየሩሳሌም ታሪክ / የእስራኤል ሕይወትና ተስፋ ማዕከል / ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጣው መሢሕ / ተቀባይነት ያጣው ንጉሥ / ኢየሱስ የሃይማኖት መሪዎችን ተቃወመ / የኢየሩሳሌምን መጥፋት ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ / የደቀ መዛሙርቱ ጥያቄዎች / ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄዎች የኢየሱስ መልሶች / የአሁኑ ዘመን በኢየሱስ አገላለጥ / የኢየሱስ ትንቢቶች ትክክለኛነት

7. ኢየሩሳሌምን በአንክሮ ተመልከቱ ............ 75

የኢየሩሳሌም የወደፊት ዕጣ ምንድነው? / የ1967 ዓመተ ምሕረቱ ጦርነት / የዓለም ታሪክ ንድፈ-አሳብ ከዳንኤል ትንቢት አንጻር / በዳንኤል ትንቢታዊ ራእይ ውስጥ ያለው የጊዜ ክፍተት / የዳንኤል ትንቢቶች ማረጋገጫ በዮሐንስ / የቅድስቲቱ ከተማ ርኩሰት / የኢየሩሳሌም አይቀሬው ትንቢት

8. የዓለም የሃይማኖት ማዕበል ከፍ እያለ መሄድ ..... 85

የሃይማኖት ሚና በመጨረሻው ሰዓት / የመካከለኛው ምሥራቅ የሃይማኖት ውጥረት / ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ላይ ያላት የይገባኛል ጥያቄ / የተባበረ የዓለም ሃይማኖቶች ጥረት ሊኖር ይችል ይሆን? / ሁሉን አቀፍ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ጅማሬ / ትንቢታዊ ማስጠንቀቂያ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት / የመናፍስት ትምህርት መስፋፋት / ቀጥሎስ ምን ይሆናል? / ሁሉን አቀፍ የሆነች ቤተ ክርስቲያን መከሠት / እግዚአብሔርን አለማመን ለመጨረሻው የዓለም ሃይማኖት ቁልፍ መሆኑ / ሆኖም አያውቅ

9. አውሮፓን መለወጥ ...................... 95

አዲስ የዓለም ሥርዓት / የሩሲያ በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ላይ ማየል / የሶቪየት ኃይል ማክተም / አዲስ እውነታ በምሥራቅ አውሮፓ / ነዳጅ ዘይት በብዛት የሚፈልግ ማነው? / ፋብሪካዎቹ ቢቆሙ / የአሥሩ መንግሥታት ኅብረት መድረክ / ወሳኙ ቁም ነገር

10. መጪው የመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም ...... 101

ዓለም ስለ ሰላም የሚያስጨንቀው ሁካታ / ሰላምና የመጨረሻው ሂደት/ የሮማውያን አገዛዝ ማንሠራራት / በመለወጥ ላይ ያለችው አውሮፓ ሚና / የእስራኤል ለድርድር ዝግጁ መሆን / አዲስ የዓለም መሪ ብቅ ማለት / ቃል ኪዳኑ ሲፈርስ / የሰላሙን አለቃ መጠበቅ

11. ያላቋረጠው የሩሲያ ጣልቃ ገብነት ሥጋት ..... 107

የሩሲያ ወረራ ፍርሃት / የሩሲያ ኃይል እየቀነሰ መሄድ / የሩሲያ ዲፕሎማሲያዊ ቁማር / ሩሲያ ወደፊት ከመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮች ውጭ መሆኗ / ሩሲያ እስራኤልን ለመውረር ስትነሣ / የሩሲያ

ውድቀት / የሩሲያ ወረራ በቅርብ ይፈጸም ይሆን? / የሩሲያ ክስረት- የክርስቶስ ተቃዋሚው መጠቀም

12. መጭው አምባገነን የዓለም ገዥ ............ 115

የወራሪዎች የዘመናት ሕልም / በማነስ ላይ ያለችው ዓለም / የቦምቡ መምጣት / የዓለም መንግሥት - የሰው ልጆች የመጨረሻ ተስፋ / ስለ ዓለማችን ታላላቅ መንግሥታት ነቢዩ ዳንኤል የተናገረው ትንቢት / የሮም መንግሥት መነሣትና መውደቅ / የአራተኛው መንግሥት ማንሰራራት / የመጪው አምባገነን የመጀመሪያ እርምጃ / የዳንኤልን ሰባ ሱባዔ ለመረዳት / አርባ ሁለት የፍዳ ወራት / ለዓለም አገዛዝ የሚያገለግሉ ሁኔታዎች ዛሬም አሉ / የዓለም አምባገነንነት ዛሬም ይቻላል

13. የዓለም የጥፋት ቀን..................... 125

ሊመጣ ያለው የኑክሊየር መዓት / እየጨመረ የመጣው የአካባቢ ብክለት / የሕዝብ ብዛትና ረኃብ / የሥርዓት አልባነት ሥጋት / መጪው "የያዕቆብ መከራ" ጊዜ / የመከራው ወቅት፤ ከዳንኤል እይታ አንጻር / ታላቁ የዓለም የመከራ ዘመን / ስለ ታላቁ መከራ የክርስቶስ ትንቢት / የሰው ዘር እየጠፋ ነው / አስገራሚው የእግዚአብሔር ሕዝቦች መትረፍ / የራእይ መጽሐፍ ዝርዝሮች / ሰባቱ አስፈሪ ማኅተሞች / ሰባቱ የጥፋት መለከቶች / የመጨረሻዎቹ ሰባት የመቅሠፍት ጽዋዎች

14. አርማጌዶን፥ የዓለም የሞት ሽረት ትግል ...... 135

አዲሱ የዓለም መንግሥት ዓዋጅ / ወደ ፍርድ መጣደፍ / የሦስተኛው የዓለም ጦርነት ፍንዳታ / ከደቡብና ከሰሜን ዓመፅ / የኮሚኒስት ቻይና እንቅስቃሴ / የሰይጣን ጦር ዕቅድ / ሰይጣናዊ ሚልሳዊነት / ታላቁ የእግዚአብሔር ቀን ውጊያ / አርማጌዶን / እግዚአብሔርን ሰድቦ መሞት

15. የክርስቶስ ዳግም ምጽአት................ 141

ከግርግም ወደ ሥልጣንና ክብር / መብረቅ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ / የመላው ዓለም ድንጋጤ / በነጩ ፈረስ ላይ የተቀመጠው

/ የሦስተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ / በአካል መመለሱ / ግልጥና በክብር የተሞላ መመለስ / ከሰማይ ሠራዊት ጋር ስለ መመለሱ / ምድርን የሚያናውጥ ምጽአት / በመንግሥታት ላይ ለመፍረድ መምጣት / ጽዮን ላይ ሆኖ ለመግዛት መመለስ / በሕይወት ያሉ አይሁዶች እንደገና ለፍርድ ሲሰባሰቡ / በሕይወት የተረፉ ሌሎች ሕዝቦችም ለፍርድ ይቀርባሉ / ከጥፋት ወደ ፍጹማዊነት / ለአሁኑ ትውልድ ተገቢ ጥያቄ

16. ሊታወስ የሚገባ ተስፋ ....................153

ለጭንቀት ቀን አጽናኙ ተስፋ / ከዳግም ምጽአቱ የሚለየው አዲስ ተስፋ / መነጠቅ፤ ዋናው የሐዋርያት ትምህርት / መነጠቁ በጌታ የሞቱትን ክርስቲያኖችም ይጨምራል / የክንውኖችን ቅደም ተከተል መረዳት / ትንሣኤን ለማዘዝ የክርስቶስ ሥልጣን / በአየር ላይ በአንድነት መገናኘት / የመነጠቅ መጽናኛነት / መነጠቅና አዲስ አካል-ለሕያዋን / መነጠቁ ከመጨረሻ ሰዓት ድርጊቶች በፊት ይከናወናል / በጉጉት መኖር

17. የሚቀጥለውስ? ........................161

ተከታዩን እንቅስቃሴ በአንክሮ መጠበቅ / የእግዚአብሔር ትክክለኛ ጊዜ / ለምንድነው ክርስቶስ መምጫውን ያዘገየው? / ግልጥ የተስፋ መልእክት / ስለ ጌታ መመለስ ምልክቶች አሉ? / ሦስቱ ዋና ዋና የትንቢት ክፍሎች / ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገሩ ትንቢቶች ማገናዘቢያ/ ስለ መንግሥታት የተነገሩትን ትንቢቶች ማገናዘቢያ / ስለ እስራኤል የተነገረ ትንቢት ማገናዘቢያ / የተወሳሰበው የድርጅቶች ገጽታ / የመጨረሻው መድረክ ዝግጁ ነው

መረጃዎች ..........................181

የእንግሊዝኛ ቃላት ዝርዝር

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማውጫ

# ማሳሰቢያ

- የመጽሐፉ ተርጓሚ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ ክፍሎችን ግልጥ ለማድረግ ሲል በደራሲው ፍቃድ አንዳንድ ማብራሪያዎችን ጨምሯል።

- ተጨማሪ ጥናት ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎችን ለመርዳት ሲባል አንዳንድ ስሞችና አገላለጦች በጽሑፉ ለመጀመሪያ ጊዜ በተከሰቱ ወቅት በእንግሊዝኛ በቅንፍ ተመልክተዋል። አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም የቃላቱ የአማርኛ አነባበብ በቅንፉ ውስጥ ታክሏል። የሁሉም ቃላት ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተል በመጽሐፉ መጨረሻ ይገኛል።

- የተጠቀሱት ጊዜያት የተመለከቱት በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ነው።

- "መጽሐፍ ቅዱስ" እና "ቅዱሳት መጻሕፍት" የሚሉትን ቃላት በማፈራረቅ ተጠቅመንባቸዋል። የሚያካትቱትም የብሉይ ኪዳንን ሠላሳ ዘጠኝ መጻሕፍትና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን ሃያ ሰባት መጻሕፍት ነው።

- በዚህ መጽሐፍ፥ ከመዝሙረ ዳዊት ከምዕራፍ 10-146 ውስጥ የተጠቀሱ ጥቅሶች ሁሉ ከድሮው (1954 ዓ.ም.) መጽሐፍ ቅዱስ በቅንፍ የተጠቀሱትን ምዕራፎች ያመለክታሉ።

- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ ከሚገኙበት የገጽ ቁጥር ጋር በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ በ"ጥቅስ ማውጫ" ላይ ቀርበዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይህንን ማውጫ ለጥናታቸው ጠቃሚ ሆኖ ያገኙታል ብለን እናምናለን።

# መቅድም

በ1973 ዓ.ም. ነዳጅ ዘይት በመካከለኛው ምሥራቅ የፖለቲካ መሣሪያ ሆነ። የነዳጅ ማዕቀብ በፐርሺያ ባሕረ-ሰላጤ የሚገኘውን የነዳጅ ሀብት ለተቆጣጠሩ አገሮች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኃይል ሲሰጣቸው፥ ሌላውን የዓለም ክፍል አስደነገጠው።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ዓለም እንደ አሁኑ ያለ የነዳጅ ድፍድፍ ችግር ገጥሟት አያውቅም። አሁን ግን ለመጀመሪያ ጊዜ የመካከለኛው ምሥራቅ ግጭት በእያንዳንዱ ሰው ላይ ተጽዕኖ አድርጓል።

የነዳጁ ዕቀባ በ1973 ዓ.ም. ለ6 ወራት ቢራዘም ኑሮ የአውሮፓንና የጃፓንን ኢኮኖሚ ለውድቀት ይዳርገው ነበር። የራሷ የነዳጅ ምርት የነበራት አሜሪካን እንኳን፥ ከውጭ በምታስመጣው ነዳጅ የምትረዳ በመሆኗ ማዕቀቡን ለረጅም ጊዜ ልትታገሠው አልቻለችም።

የነዳጅ ዘይት ዋጋ ሽቅብ ቢወጣም፥ ጥቂት ቆይቶ ዕቀባው ስለአበቃ ዓለም እንደገና ዕፎይ አለች።

እስራኤል ግን ከአካባቢው ችግር ጋር ትታገል ነበር። የፍልስጥኤም ችግር በዓረቦችና በእስራኤል መካከል ያለውን ጥላቻ አከፋው። የስደተኛ መጠለያዎችም የሽብር ፈጣሪዎች መመልመያ ጣቢያዎች ሆኑ። ሊባኖስ በእርስ በርሱ ጦርነት ፈራረሰች፤ እስራኤልና ሶሪያ ወደ ግጭት አመሩ። ያም ቢሆን መሣሪያ የሚያማዝዘው ጦርነት ከፐርሺያ ባሕረ-ሰላጤ ሚዳዎች የራቀ ስለነበር፥ ነዳጅ ዘይት የግጭቱ አንድ አካል አልነበረም። የአሜሪካን የባሕር ኃይል ወደ ባሕረ-ሰላጤው በመጠጋት ኃይሉን አሳየ።

በኢራንና በኢራቅ መካከል ይደረግ የነበረው ጦርነትም ቀስ በቀስ ጋብ አለ። ነዳጅ ዘይት ወደ ምዕራብ እንዳይጓዝ ለማገድ በጊዜው ከልቡ የሞከረ ስላልነበረ፥ የዓለም ኢንዱስትሪዎች ችግር አልገጠማቸውም።

ዓለምን አሥግቷት የነበረው ጥፋት ዋል አደር ሲል እንደገና ፊቱን መለስ አደረገና ሰላም የሰፈነ መሰለ። የዓረቡ ዓለም የተባበረ በመምሰል በአካባቢው ሰላምን ለማረጋገጥ እንደሚችል ገለጠ። የነዳጅ ዘይትም ወደየአቅጣጫው መጓጓዙን ቀጠለ። ምዕራቡ ዓለም፥ በተለይም አሜሪካ ከምንጊዜውም ይልቅ በዚህ ከውጭ በምታስገባው ነዳጅ ላይ የምትደገፍ ነበረች።

በኢራቅና በኢራን መካከል በተፈጠረው የጦርነት-አቁም ፋታ ዓለም ዘና ብላ ሳለ፥ በ1990 ሳዳም ሑሴን [Saddam Hussein] ኩዌትን በወረራ ያዙና

መካከለኛው ምሥራቅ እንደገና አደገኛ ወቅት ውስጥ ገባ። የዓረቦች የውሸት ኅብረትም ፈራረሰ። የምዕራቡ ዓለም ሠራዊት ሳውዲ ዓረቢያና አጎራባቾችዋ የሆኑትን የነዳጅ ባለጸጋ አገሮች ከጦርነቱ ጥፋት ለመከላከል በፍጥነት ወደ አካባቢው ተንቀሳቀሰ። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ የዓረቢያ የነዳጅ ማምረቻ ሜዳዎች በወታደርና በዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ተጥለቀለቁ።

ሳዳም ሑሴን ድፍረት በተሞላበት መሠሪነት ምዕራቡን ዓለም የሚያስፈራሩበት ጠንካራ ጦር ለመመሥረት ሞከሩ። የሩቅ ዓላማቸው ግን እስራኤልን ማጥፋት ነበር።

ዓረቦችና እስራኤል አብሯቸው በኖረው ግጭት ሳቢያ አደገኛ ወደሆነው ዓለም አቀፍ ጦርነት ያመሩ ጀመር። አንድ እብድ ሰው፥ የአገር መሪም ይሁን ሽብር ፈጣሪ፥ በቀላሉ ዓለምን በሞላ የሚያሳትፍ ጦርነት የሚቀሰቅስ በትር ሊሰነዝር ይችላል።

በአካባቢው የነዳጅ መኖር፥ መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን ትንቢቱ መካከለኛው ምሥራቅን የትኩረት ማዕከል ያደረገበትን ምክንያት ያስረዳል። ይህ ብቻ አይደለም፤ አካባቢው የአርማጌዶን ጦርነት የፍልሚያ አውድማና እኛ የምናውቀው የምዕራቡ ዓለም ሥልጣኔ ማከተሚያ እንደሚሆንና እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ የሚሆነውን ነገር ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ይገልጣል።

የእያንዳንዱ ዕለት አርዕስተ ዜናዎች ወደፊት ምን ይፈጸም ይሆን? የሚል ጥያቄ ያነሣሉ። ዓለም እንዲህ የበዙ አስፈሪ እድገቶችና ፈጣን ለውጦች አይታ አታውቅም። በዚህ ጊዜ ታዲያ ክርስቲያን ሊያደርገው የሚገባ ነገር፥ መጽሐፍ ቅዱስን መመርመርና ወደፊት ስለሚከናወኑ ታላላቅ ሁኔታዎች መረዳት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እስከዛሬ ያለውን ዓለም ታሪክ፥ የምድራችንን አፈጣጠር፥ የሰውን ዘር አጀማመርና እግዚአብሔር ከእስራኤልና ባጠቃላይም ከዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያብራራ ዘገባ አለው። አዲስ ኪዳን ጠቃሚ የሆነውን የኢየሱስ ልደት፥ ሕይወቱን፥ ሞቱንና ትንሣኤውን ያስገነዝባል። የክርስቶስና የሐዋርያቱ ትምህርት ለቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ያለፈውን ብቻ ሳይሆን፥ ወደፊት ስለሚሆነውም ነገር ትንቢታዊ እይታና እውነት አስጨብጧታል።

የዚህ ቅዱስ ቃል ማዕከላዊ መልእክት በጥንቃቄ የሚገልጠው የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት ሲሆን፥ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቀድመው

ስለሚፈጸሙ ጠቃሚ ክንውኖችም ብዙ ትንቢቶች ተነግረዋል። እነዚህ ትንቢቶችና ክንውኖች ቅደም ተከተላቸውን በሥርዓት ሲይዙ፥ በቅርቡ በዓለም ስለሚፈጸመው ሁኔታ ትንቢታዊ አጀንዳ ይሆናሉ። አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችና ጠበብት፥ ዓለም በታሪክ ግዙፍ ወደሆነው ጦርነት፥ ማለት ወደ አርማጌዶንና ወደ ሥልጣኔ ማከተሚያ ጥፋት በማምራት ላይ መሆኗን ከእግዚአብሔር ቃለ ትንቢት በመረዳት አምነዋል።

የመካከለኛው ምሥራቅ ያላቋረጠ ውጥረትና አስገራሚው የአውሮፓ እድገት፥ ወደ መጨረሻው፥ ወደ ግዙፉና ወደ አውዳሚው የዓለም ጦርነት (ብዙዎች ከአርማጌዶኑ ውጊያ ጋር ያዛምዱታል) የሚያመራ ይሆን? በማለት ይጠይቃሉ። የአሁኑ የዓለም ሁኔታ ወደ እልቂቱ ለሚያመሩት ዓበይት ትንቢታዊ ክንውኖች ምቹ ነው? እንዲያ ከሆነ ታዲያ ከእንግዲህ የሚቀጥለው ምንድነው? የእስራኤል የወደፊት ዕጣስ፥ ምን ይሆናል? በነዳጅ ሳቢያ የሚደረገው ግጭቱ በምን አኳኋን ነው በወደፊቱ የዓለም ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርገው? ወደ አርማጌዶን በመቃረብ ሂደት የሚከሠቱት ክንውኖችስ ምንድናቸው?

ይህ መጽሐፍ ስለ መካከለኛው ምሥራቅ ለተነገሩ ትንቢቶች የተለየ ትኩረት በመስጠት እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል። ዓለማችን ወደ አዲስ ችግር በመሸጋገር ላይ ስለመሆኗ ሁሉም ይስማማል። መጪዎቹ ቀናት የፈጣን ለውጥና የአስደናቂ እድገት ተስፋ ይፈነጥቃሉ። ስለመጪው ጊዜ ለሚነሡ ጠቃሚ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚችለው ግን፥ እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።

አብዛኛው ዓለም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለሆነው ትንቢት የሚሰጠው ትኩረት ውሱን ነው። ብዙዎቹ እግዚአብሔርን እንደሌለ ቆጥረውታል። እግዚአብሔር ካለ በሌላ አገር እንደሚኖርና፥ ከጭሰኞቹ ግብር እንደማይሰበስብ ባለ ርስት ይቆጠራል ይላሉ። መንግሥታትና ግለሰቦች በጻድቁና ሁሉን አድራጊ በሆነው እግዚአብሔር ፊት ለፍርድ የሚቀርቡ መሆኑን ለማመን አይፈልጉም። ቁሳዊ አመለካከት ባጠቃው ዘመናዊ ዓለማችን የሚገኙ አንዳንድ ክርስቲያን ተብዬዎችም፥ በዓለማዊ ጣጣ ተተብትበው ዘላለማዊውን ጸጋ ቸል ይሉታል። የወደፊት ተጠያቂነት ጉዳይ በሕይወታቸው ተጽዕኖ እንዲኖረው አይፈቅዱም።

የሀኛውን ክፍለ-ዘመን አስገራሚ ክንውኖች ስናጤን፥ ስለመጪው ጊዜ የተነገሩት ትንቢቶች ከዚህ ቀደም እንደተፈጸሙት ትንቢቶች ሁሉ ቃል በቃል የሚከናወኑ መሆናቸውን ያመለክታሉ። በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት፥ በእግዚአብሔር አጀንዳ ላይ የአርማጌዶን ጦርነት ከፊታችን ስለሆነ፥ ታሪክ

ወደተነበየለት ፍጻሜ በማምራት ላይ የመሆኑ ማስጠንቀቂያ ጥሞና የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኗል።

በዚህ መጽሐፍ የቀረቡት እውነቶች እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ሆኖ ታሪክን የሚቆጣጠር መሆኑን የሚያስገነዝቡ ሊሆኑ ይገባል። በሱ ጊዜ ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፤ ልሳናት ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ መሆኑን ይናገራሉ። ለብዙዎቹ ግን ያ ጊዜ ዘላለማዊ ግባቸውን ለመለወጥ የዘገየ ይሆንባቸዋል።

የሀያኛው መቶ መጨረሻ አሥር ዓመት፥ ለሁለት ሦስተኛው የዓለም ክፍል የሚታደለው የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት፥ የዘመናዊው ዓለም ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ዋና መሣሪያ መሆኑን ከመነሻው አረጋግጧል። መላው ዓለም በመካከለኛው ምሥራቅ ባለው ክንውን ውስጥ ጠቃሚ ድርሻ አለው። የአካባቢው ሰላም በብዙ መልኩ ከአሜሪካ ይልቅ ለአዲሲቱ አውሮፓ ኃያልነትና ብልጽግና ይበልጥ ይጠቅማል። ዛሬ አብዛኛው ዓለም በመካከለኛው ምሥራቅ ግጭት ውስጥ ስለገባ ብልጽግናው በአንዳንድ ሁኔታዎች በሰላምና ከክልሉ በሚመጣ የማያቋርጥ የነዳጅ ዕደላ ዋስትና ላይ የሚደገፍ ሆኗል። ይህ ነው ግልጥ ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት። መካከለኛው ምሥራቅ ወደ አርማጌዶን የሚያመራ የጦርነት አውድማ፥ ለክርስቶስ ዳግም ምጽአትና የተተነበየው የዓለም ታሪክ ፍጻሜ ትዕይንት መድረክ ነው። ዓለም ትኩረቱን በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ ማድረጉ፥ እስራኤል የጥንት ምድሯ ባለቤት መሆኗ፥ እና ዓለም የሰላም ዋስትና የሚሰጣት ሰው በምትፈልግበት ሁኔታ ላይ መሆኗ፥ የፍጻሜውን ጊዜ የሚያሟሉ ሁኔታዎች መሳካታቸውን ያመለክታል።

እነዚህ ማስረጃዎች እውነት ከሆኑ፥ የአሁኑ ጊዜ ክንውኖች ለእምነትና ለንስሐ፥ በእያንዳንዱ መንግሥትና ግለሰብ ላይ የመጨረሻ ፈራጅ ወደሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ፊትን የመመለሻ ጥሪ አቅራቢዎች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መሠረት እግዚአብሔር ባስገራሚ ሁኔታ በሰው ታሪክ ውስጥ ጣልቃ የሚገባበት ጊዜ ቅርብ ይሆን ይሆናል።

ይህ መጽሐፍ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች መስክ የብዙ ዓመታት ልዩ ምርምራዊ ጥናት የተደረገበትና፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለጣዎችን አስመልክቶ የተጻፉ ሌሎች መጻሕፍት ውጤትና ቀጣይ ሲሆን፥ ዓላማውም ስለመጪው ጊዜ ለሚቀርቡ ትክክለኛ ጥያቄዎች ግልጥ በሆነ ቋንቋ መልስ መስጠት ነው። ትንቢት የተወሳሰበ ጉዳይ ቢሆንም፥ የሚፈልግ ሁሉ ዋና ዋና ጭብጦቹን ሊረዳቸው ይችላል። ጠለቅ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች ግን፥ ይህ

መጽሐፍ ከዚያም በላይ ጠቃሚ የሆነና በዘመናዊው ዓለም በሚገጥሙ ትንቢታዊ ጥያቄዎች ላይ ተጨማሪ ብርሃን የሚፈነጥቅ ሆኖ ያገኙታል።

ይህን መጽሐፍ የሚያነቡ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛው አዳኝና ጌታ መሆኑን ተረድተው ወደ እርሱ ይቀርባሉ ተብሎ ይታመናል። ታሪክ ወደ ፍጻሜው በማምራት ላይ ስለመሆኑም ብልህነት የታከለበት ግንዛቤ ይኖራቸዋል። ይህ ድምዳሜ ትክክል ከሆነ፥ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅና፥ የጌታ በርሱ ላመኑት መምጣት በቅርቡ እንደሚፈጸም መጠበቅ ያለበት ጉዳይ ነው።

ጆን. ኤፍ. ዋልቮርድ

# 1

# ጥያቄዎች ስለ ወደፊቱ

## ♦ አስደናቂው ሀያኛ ምዕተ ዓመት

በማንኛውም መለኪያ ቢታይ፥ ሀያኛው ምዕተ ዓመት ለማመን የሚያዳግቱ ሁኔታዎች የተከናወኑበት ክፍለ-ዘመን ነው። በዚህ ዘመን መጀመሪያ ውስጡን የኤሌክትሪክ ኃይል መጠቀሚያዎች እንደ ራዲዮ፥ ቴሌቪዥን፥ አይሮፕላን፥ ሚሳይል (ተወንጫፊ መሣሪያ)፥ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች፥ ኮምፒውተሮች፥ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች፥ እና አቶሚክ ፈንጂዎች የመሳሰሉት አልነበሩም። ቴክኖሎጂ የሰውን ልጅ ወደ ዘመናዊው ዓለም በማሸጋገሩ፥ ጥንት በዓለማችን በአንድ ዘመን ይታይ የነበረ ለውጥ አሁን በአንድ ዓመት ይከወናል።

## ♦ ፈጣን ለውጥ

ባለፈው ምዕተ ዓመት፥ ዘመናችንን ያጥለቀለቁ ሳይንሳዊ ክስተቶችና ማኅበራዊ እድገቶች በግልጥ ታይተዋል። ሳይንሳዊ ግኝቶች ሁሉንም የጥናት መስክ ዳስሰዋል። የኤሌክትሪክ ግኝት፥ ምድራዊ ሕይወትን በአስደናቂ ሁኔታ ለውጧል። ራዲዮ፥ ቴፕ፥ ቴሌቪዥን፥ ፎቶ ኮፒ፥ የፋክስ መረጃ ልውውጥ፥ ኮምፒውተሮችና፥ የሳተላይት ግንኙነት ዓለማችንን በመረጃ እንድትጥለቀለቅ አድርገዋታል። መኪና፥ አውሮፕላንና ሌሎች መጓጓዣዎች እየተመረቱ በሰፊው መሰራጨታቸው የዓለምን መጓጓዣ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ለውጠውታል። ስለሆነም ዛሬ ዓለም በክልል ብቻ የምትለይ አንዲት ትልቅ መንደር ሆናለች። ባህልና የሕዝብ መቀራረብ የመስፈኑን ያህልም የሕዝቦች የማንነት መታወቂያ እየጠፋ ነው። የማንነትን መለያም አሳንሶታል። በቅርቡም የሕዋው ጉዞ በጣም ተራ ጉዳይ ይሆናል። የሕዋ ጣቢያዎችም አዲሶቹ የጋራ ግንባሮቻችን ይሆናሉ።

ዘመናዊው ቴክኖሎጂ ጦርነትን ይበልጥ አጥፊና አውዳሚ አድርጎታል። አውዳሚነቱን የሚያሳዩ የኑክሊየርና የኬሚካል ጦር መሣሪያዎች በዓለም ላይ በሁሉም አቅጣጫ በመስፋፋት ላይ ናቸው። የኑክሊየር መሣሪያ መስፋፋት ከአሥርተ-ዓመታት በፊት ዓለምን እንዳሠጋት ሁሉ፥ ዛሬም የኬሚካልና የባክቴሪዮሎጂካል የጦር መሣሪያዎች መስፋፋት ያካባቢ ግጭቶችን በመቀስቀስ ዓለምን ሥጋት ላይ ጥሏታል።

የዚህ ሁሉ ውጤት ተዳምሮም አስደናቂ ማኅበራዊ ለውጥ አስከትሎአል። ፈጣን የቴክኖሎጂ እድገት የሰዎችን አብሮ መኖር ባህል ቢያዳብርም፥ አንዳንዴ ከለውጡ ጋር አብሮ መራመዱ ከአቅም በላይ ሆኗል።

በሁሉም የሕይወት አቅጣጫ የሞራል (ግብረ ገብነት) ማዘመም ይታያል። በመንግሥትና በተለያዩ የንግድ ሥራ ዘርፍ ምግባረ ብልሹነት ተስፋፍቷል። ቤተ ክርስቲያን ሳትቀር ይህ ቅሌት በተከታታይ ገጥሟታል። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ቤተሰባዊ ሕይወት ተበላሽቷል። ውርጃ፥ የተመሳሳይ ጾታ ወሲባዊ ግንኙነት፥ ለአደንዛዥ ዕፆች ተገዢነት፥ ወንጀል፥ ድህነት፥ ረኃብና ሌሎችም ችግሮች በሞራል አንጻር ሲታዩ የቴክኖሎጂውን እድገት ባዶና ፍሬ-አልባ አድርገውታል።

## ♦ አይቀሬው ቀውስ

በፍጥነት እያደገ የመጣው ዘመናዊ የሕይወት እንቅስቃሴ፥ ዓለምን ከማትወጣበት አሥጊ ቀውስ ውስጥ እየዘፈቃት ነው። ይህ ሁሉ የቴክኖሎጂ እድገት፥ እንዲሁም ዘመናዊው አኗኗራችን ኤሌክትሪክና መጓጓዣን ለማሟላት በኃይል ሰጪ ነገሮች ላይ ይደገፋል። ብልጽግናችንም በማያቋርጥ የነዳጅ ዘይት አቅርቦት ላይ የተመሠረተ ሆኗል። ለምሳሌ የአሜሪካ ፍጆታ በዓለም ከሚመረተው የነዳጅ ዘይት 39 ከመቶ ነው። ያለ ነዳጅ ዘይት በዓለም አሉ የሚባሉ ትላልቅ ባለ ኢንዱስትሪ አገሮች ኢኮኖሚ ይወድቃል። የምስተኛው ዓለም አገሮችም፥ ነዳጅ ዘይት በመጠነኛ ዋጋ ካላገኙና አቅርቦቱ ከተናጋባቸው ከእጅ ወደ አፍ የሆነው ኢኮኖሚያቸው ይፈራርሳል። ለዚህ ነው የመካከለኛው ምሥራቅ ቀውስ ለዓለም ቀውስ ዋነኛ መንሥኤ ሆኖ የተገኘው።

ታዲያ፥ በዚህ ሁኔታ በዓለማችን ያንዣበበውን ውጥረት እስከ መቼ በጥንቃቄ መያዝ ይቻላል? ዓለምስ በደም መጨማለቅን ለማስወገድ እስከ መቼ ትታገላለች? ሰው ከዚህ በፊት በነበረው ትውልድ ሊታሰብ የማይቻል መሣሪያ ለራሱ ማጥፊያ በጥበቡ ሠርቶ አውጥቶአል። ዓለም ወደማትወጣው ግዙፍ ቀውስ በማምራት ላይ ነች። ስለ ጥፋት የተነበዩት ነቢያት ትክክል ይሆኑ? ዓለምስ ወደ አርማጌዶን በመገስገስ ላይ ናት? ኃጢአተኞች ከአምላክ ፍርዳቸውን የሚቀበሉበትና የሰው ዘር ታሪክ መደምደሚያ (ማብቂያ) እየተቃረበ ይሆን?

## ♦ የነቢያቱ ድምፅ

ትንቢት፥ በኮከብ ቆጠራ፥ መናፍስት በመጥራትና በመሳሰሉት ነገሮች የሚገለጥ አይደለም። የሃይማኖት ሰዎች ትንቢትን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ታሪክ ያለው ዕቅድ መግለጫ ራእይ አድርገው ይመለከቱ ነበር። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም የብዙዎቹን ነቢያት ሕይወትና ሥራ ዘግበዋል፦ የሙሴ፥

የኢሳይያስ፥ የኤርምያስ፥ የሕዝቅኤል፥ የዳንኤል፥ የሆሴዕ፥ የኢዩኤል፥ የሚክያስንና ሌሎችንም። እነዚህ ሰዎች ወደፊት ሊመጣ ስላለው ሁኔታ፥ እንዲሁም በየዘመናቱ ብቅ ስለሚሉት ኃያላን መነሣትና መውደቅ ጠቅሰው፥ መሪዎቹም የታሪክ አሻራቸውን በመካከለኛው ምሥራቅ ትተው እንደሚያልፉ ግልጥ ባለ ዝርዝር ተንብየው ነበር። ከነቢያቱ አንዳንዶቹ የተናገሩት ትንቢት ሲፈጸም የማየት ዕድል ገጥሟቸዋል። የብዙዎቹ አስገራሚ ትንቢቶች ዛሬም በመፈጸም ላይ ናቸው።

ኢየሱስ ራሱም ቢሆን ነቢይ ነበር። የሙሴን፥ የኢሳይያስን፥ የዳንኤልን፥ የኤርምያስንና የሚክያስን መጻሕፍት በመጥቀስና ብዙውን ጊዜ የራሱን ትርጉምና አሳብ አክሎ በማብራራት ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ተንብይዋል። ቃሉም በዘመናት ተፈትኖ እውነትነቱ ተረጋግጧል። ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም መውደቅ (ሉቃስ 21፡20-24) የተናገረው ትንቢት ግልጥና የማያሻማ ስለነበር፥ ከተማይቱ በ70 ዓ.ም. በቲቶ [Titus] አማካይነት ከመውደሟ በፊት የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ከጥፋቱ ለማምለጥ ችላለች። ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ እስራኤል ሕዝብ በጥንቃቄ የተነገሩ ትንቢቶች ያኔ እንደሆነው ሁሉ፥ ዛሬም እንደ ሰንሰለት ተያይዘው የሥልጣኔያችን መብቂያ መቃረቡንና በቅደም ተከተል በመፈጸም ላይ ያሉ ክንውኖችን የሚያሳዩ ዓይነተኛ ምልክቶች ናቸው።

## ♦ “ጊዜያቱ” በማለቅ ላይ ናቸው

ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያንን ስደት፥ የኢየሩሳሌምን ውድቀት፥ የቤተ መቅደሱን መውደም፥ አይሁዶች በዓለም ሁሉ እንደሚበተኑና ቤተ ክርስቲያን ይህን ሁሉ ተቋቁማ በአስደናቂ ሁኔታ እንደምታድግ አስቀድሞ ተንብዮ ነበር። እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ሁሉ፥ ኢየሱስም እስራኤላውያን እንደገና ወደ ርስታቸው እንደሚሰበሰቡና መንግሥታቸውንም እንደሚመሠርቱ አመልክቶአል። ይህ ሁሉ፥ ታሪክ ያረጋገጠው ሐቅ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ትንቢት በሚገባ የተረዱ ሁሉ በኢየሩሳሌምና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚከናወኑ ሁኔታዎች የሥልጣኔ ማክተሚያና የአሕዛብ ዘመን ማብቂያ ምልክቶች እንደሆኑ ኢየሱስ አስጠንቅቋል። ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁዳውያንን አስመልክቶ ሲናገር፥ “...በሰይፍ ስለትም ይወድቃሉ፤ ወደ አሕዛብ ሁሉም ይማረካሉ፤ የአሕዛብም ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች” አለ (ሉቃስ 21፡24)።

ዛሬ አራት ሚሊዮን የሚሆኑ አይሁዳውያን ወደ ምድራቸው (ርስታቸው) ተመልሰዋል። ይህ ቁጥር በሙሴ መሪነት ከግብፅ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡት ሁለት ሚሊዮን ሰዎች እጥፍ ሲሆን፥ በታሪኳም ትልቁ እንቅስቃሴ ነው። ብዙዎች የተጨቃጨቁባትና የተደራደሩባት ኢየሩሳሌም

በ1967 ዓ.ም. በአይሁዶች እጅ ብትገባም፥ ከተማይቱን አስመልክቶ የሚካሄደው ፖለቲካዊ ጦርነት ዛሬም እልባት አላገኘም። የቅድስቲቱ ከተማ የወደፊት ተስፋ ምንድነው? አስቀድሞ እንደተነገረው የአሕዛብ ዘመን በትክክል እያከተመ ከሆነ፥ የሚቀጥለው ሁኔታ ምን ይመስል ይሆን? ስለ አካባቢው የወደፊት ሁኔታ በእርግጠኛነት ለመናገር ይቻል ይሆን? ከሆነስ፥ የተስፋ ወይስ የጥፋት ማስጠንቀቂያ?

## ◆ መልስ ፍለጋ

ዘመናዊው ሰው ከመቼውም ይልቅ ስለ ወደፊቱ የተለያዩ ጥያቄዎች በማቅረብ ላይ ነው። ጥያቄዎቹ ከፍተኛ ትኩረት የሚሹ ሲሆኑ፥ ለነሱም ቀጥተኛና ትክክለኛ መልስ ሊሰጠን የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ስለሆነም፥ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የት እንዳለንና በቅርቡ የሚፈጸሙት ታላላቅ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ግንዛቤ ይኖረን ዘንድ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ ቀደም የማይቻሉ የሚመስሉ ትንቢቶች ዛሬ እንደገና በመመርመር ላይ ናቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን ጥናት በተመለከተ ሁለት የተለያዩ አስተሳሰቦች መኖራቸውን ማስተዋል ይኖርብናል። አንደኛው፥ ትንቢቶችን በቸልታ መመልከት ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ መተርጎም ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተፈጽመዋል። በሚገባ ስንገመግማቸው፥ የተፈጸሙት ቃል በቃል እንደሆነ እንረዳለን። ባለፉት ጊዜያት ከተፈጸሙት ትንቢቶች ምሳሌነት ስንመለከት፥ ትንቢቶቹን በቸልታ ማለፍ ወይም ቃል በቃል እንደሚፈጸሙ መጠራጠር ፍጹም የማይቻል ነው።

ሁለተኛው አስተሳሰብ ደግሞ፥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ከሚገባ በላይ በማጋነን፥ ወይም ቃል በቃል በመውሰድ ወቅታዊ ከሆኑ የዘመናችን ክሥተቶች ጋር ለማያያዝ የሚደረግ ሙከራ ነው። ስለ ጌታ ምጽአት፥ ወይም ስለ ዓለም ፍጻሜ ቀኑን ወስነን ለመናገር ምንም ዓይነት የቅዱሳት መጻሕፍት ድጋፍ የለንም። የቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢትን የሚመረምር ማንኛውም ሰው ባንድ በኩል እግዚአብሔር የገለጣቸውን ነገሮች በጥንቃቄ እየመረመረ፥ በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ መልስ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች እንዳሉ በጥንቃቄ ማስተዋል ይኖርበታል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ትክክለኛና መሠረታዊ የአተረጓጎም መመሪያዎችን በተረዱ መጠን፥ በዓለም በሚሆነውና ከዘመናት በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ በተተነበየው ሁኔታ ውስጥ እውን የሆነ ክንውን እንዳለ አብልጠው ይረዳሉ። የተለያየ የሕይወት አቅጣጫን የሚከተሉና የተለያየ ሃይማኖታዊ እምነት ያላቸው ሰዎች ሁሉ፥ “ወደፊት ምን ያጋጥመን ይሆን?” የሚል ጥያቄ ያነሣሉ።

# 2

# የአርማጌዶን የጊዜ ሠሌዳ

## ♦ ትንቢቱ ግልጥና ጥርት ያለ ነው

ራሳቸውን "ነቢይ" ብለው የሚጠሩ የዘመናችን ሰዎች ትንቢት፥ ጭፍንና የተድበሰበሰ ነው። ትንቢታቸውን ከወቅቱ ሁኔታዎች ጋር ለማስማማት ስለሚጥሩ ነው ይህ የሆነው። በተቃራኒው ደግሞ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ትንቢቶች የተድበሰበሱ ሳይሆኑ፥ ግልጥና እርስ በርሳቸው የተደጋገፉ ናቸው። ምንም እንኳን አንዳንድ ጥቃቅን የአተረጓጎም ልዩነቶች ቢኖሩም፥ አጠቃላይ መልእክቱ ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ ግልጥና ጥርት ያለ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጨረሻውና አሰቃቂው የዓለም ጦርነት ብቻ አይደለም የሚናገረው። ወደ አርማጌዶን ጦርነት የሚመሩ ሁኔታዎችን የጊዜ ሰሌዳቸው እንኳን ሳይቀር ነው የሚገልጣቸው። "አርማጌዶን" ማንኛውም ሰው ፍርሃቱን (ሥጋቱን) የሚያመለክትበት የዓለም ፍጻሜ መግለጫ ሆኗል። ነቢያት አርማጌዶንን በይበልጥ በማብራራት፥ ጦርነቱ ዓለም ራሷን በራሷ የምታጠፋበትና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚደረግ የመጨረሻው አስከፊ እልቂት እንደሆነ አመልክተዋል።

ይህ አስቸጋሪና አስደንጋጭ ጦርነት፥ በአብዛኛው መልኩ በዕለታዊ ጋዜጦች ርእስነት ከሚወጡ ዜናዎች ጋር የሚመሳሰልበት ሁኔታ አለ። ይህ ታሪክ አውዳሚ ጦርነት፥ በተወሰነለት ጊዜና በተተነበየለት ስፍራ ይደረጋል።

አርማጌዶን የሚለው ቃል ከዕብራይስጥ የመጣ ሲሆን፥ ትርጉሙም "የመጊዶ ተራራ" ማለት ነው። ይህ አነስተኛ ተራራ የሚገኘው ከፍልስጥኤም በስተሰሜን ያለው ሰፊ ሸለቆ ከሚያበቃበት ስፍራ ላይ ነው። በዚህ ስፍራ ባለፉት ዘመናት ብዙ ጦርነቶች ተካሂደዋል፤ ወደፊትም ከፍተኛ ግጭት የሚደረግበት የጦር አውድማ ነው።

## ♦ የአውሮፓው ኅብረት ለውጥና የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት

እ.ኤ.አ. በ1989 እና 1990 ከተከናወኑት አስገራሚ ለውጦች አንዱና ዋነኛው በምሥራቁ የአውሮፓ ክፍል የኮሚኒዝም ሥርዓት መፍረስና በምትኩም የዲሞክራሲ ሥርዓት ማቆጥቆጡ ነበር። ምንም እንኳን ይህ አስገራሚ የታሪክ

ሂደት በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ባይተነበይ፥ በመጨረሻው ዘመን፥ በተለይም በሰባቱ ዓመታት ወቅት፥ ኅብረት የሚፈጥሩ አሥር መንግሥታት እንደሚነሡ ከተነገረው ትንቢት ጋር የተያያዘ ነው። ኅብረቱ ዋና ዋናዎቹን የአውሮፓ አገሮች የሚያቅፍ መሆኑ አያጠራጥርም። ለመካከለኛው ምሥራቅ ሰላምና መረጋጋትን፥ ለወቅቱ የአካባቢው ብጥብጥ ደግሞ አንድ እልባትን ለማስገኘት ሙከራ የሚደረገውም በእነዚህ አሥር መንግሥታት አማካይነት ነው።

## ♦ የሰባቱ ዓመታት ቅድመ ሁኔታዎች

የመጨረሻው ትንቢታዊ ፍጻሜ የሚከናወነው በቀናት ሳይሆን፥ በዓመታት ልዩነት ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተተነበየው፥ ቀደም ብሎ፥ የዓለምን ፍጻሜ የሚወስኑ ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ይከናወናሉ። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች አሁንም በፍጥነት በመሟላት ላይ ናቸው። ቅድመ ሁኔታዎቹ እንደተሟሉም ሌሎች ግልጥ ሁኔታዎች የሚከናወኑበት የጊዜ ሰሌዳ ይጀመራል። ይህም የጊዜ ሰሌዳ በመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት ለሚፈጸሙት ጉዳዮች ዝግጅት የሚደረግበትን አጭር ወቅት ያጠቃልላል። ከሰባቱ ዓመታት፥ የመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመታት ተኩሉ ወደ አርማጌዶን የሚያመራ፥ ተወዳዳሪ የሌለው ጥፋትና ጦርነት የሚካሄድባቸው ይሆናሉ።

## ♦ የሮም ግዛት ማንሰራራት

ከነዚህ ሰባት ዓመታት በፊት፥ በአሥር ቀንዶች የተመሰሉት የአሥር መንግሥታት ኅብረት ይመሠረታል (ዳን. 7፡8)። ተመሳሳይ የሆነው የመጨረሻ መንግሥት አገዛዝ ገለጣ በራእይ 13፡1 ላይ ተጠቅሷል። በአገር ደረጃ ተለይተው ባይቀመጡም የነዚህ የመጨረሻዎቹ መንግሥታት ኅብረት ለሮም ግዛት ማንሰራራት ምክንያት ይሆናል። ይህ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 7 ከተጠቀሱት አራዊት አራተኛዋን አውሬ ያመለክታል። እነዚህ አገሮች፥ ምናልባት አንዳንድ የአውሮፓ መንግሥታትን፥ የምዕራብ እስያንና፥ የሰሜን አፍሪካ አገሮችን ይጨምሩ ይሆናል። ይህ አስፈላጊና ትኩረት የሚገባው ጉዳይ የክርስቶስ ምጽአት የመጨረሻዎቹ ዓመታት ለመጀመራቸው ዓይነተኛ ምልክት ሊሆነን ይችላል። የሚታየው ክንውን ሁሉ ለመጨረሻው ዘመን በር ከፋችና የመጀመሪያ ሂደት ነው። ይህ የመንግሥታት ኅብረት ለመካከለኛው ምሥራቅ የሰላም ዋስትና ለመስጠት ሲል፥ ከእስራኤል ጋር የሰባት ዓመታት የሰላምና የጥበቃ ቃል ኪዳን ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ አስፈላጊው ይሆናል።

## ♦ እስራኤል ሕልውናዋ ይጠበቅ ይሆን?

የአርማጌዶንን የቀን ቀመር በትክክል ለማገናዘብ የታሪክና የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት አስፈላጊ ይሆናል። እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ ራሷን የቻለች መንግሥት ሆና እንደገና ማንሰራራቷ አስፈላጊ ጅምር ነበር። ከዚያም፥ በዓረቦችና በእስራኤል መካከል የሚካሄደውና እስከዛሬ መፍትሔ ያልተገኘለት ጦርነት ተጀመረ፤ አሜሪካና ሩሲያ በዚህ ጦርነት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ የሚል ሥጋት ሰፍኖ ቆየ። እስራኤል በጦርነቱ እንደማትጠፋ፥ የኋላ ኋላ ግን የቃል ኪዳን አጋሮቿ ቃላቸውን እንደሚያጥፉባት ትንቢት ያመለክታል። ወደፊት በሚደረገው የሰላም ድርድር መሠረትም ከፍላጎቷ ውጭ የተደረገ ውሳኔን ለመቀበል ትገደዳለች። ዓረቦች የነዳጅ ክምችታቸውን ለማስፈራሪያነት በመጠቀም ላይ ሲሆኑ፥ በመካከለኛው ምሥራቅ አዲስ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥምረት እየታየ ነው። አሜሪካንም ሆነ ሩሲያ በአካባቢው ያላቸው የበላይነት በአውሮፓ ይወሰዳል።

## ♦ ነዳጅ ዘይት እና የሥልጣን ሽኩቻ

አስገራሚው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ኃይል አሰላለፍ ክሥተት በዓለም አቀፍ ደረጃ በሂደት ላይ ነው። የወደፊት ሁኔታው ደግሞ ቀጥሎ ያለውን መልክ ሊይዝ ይችላል፡- የደለበ የነዳጅ ዘይት ሀብት ያላቸው ዓረቦች፥ እንዲሁም በእርሻና በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ምዕራባውያን አገሮች ግንባር ይፈጥራሉ። ይህ ከነውን፥ አሜሪካም ሆነች ሩሲያ በአካባቢው ያላቸውን የኢኮኖሚ የበላይነት ያዳከመዋል። አሜሪካ ለባሕረ-ሰላጤው አካባቢ መከላከያ በምታወጣው ከፍተኛ ወጪና፥ ከአውሮፓውያን ወዳጆቿ ድጋፍ ከማጣቷ የተነሣ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ትዘፈቅና አሁን በዓለም ላይ ያላትን የበላይነት ታጣ ይሆናል። ሩሲያም በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ያፈሰሰችላቸው ዓረቦች አንቅረው ተፍተዋታል፤ በአውሮፓ በመታየት ላይ ካለው ለውጥ የተነሣም ተዳክማለች። በዚህ ሳቢያ ሁኔታውን በታዛቢነት ከመመልከት ሌላ ምርጫ አይኖራትም። የሜዲትራኒያን ክልል አገሮች አዲስ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ኃይል ለማሰባሰብ፥ የየአገሮቹን የገንዘብ ምንዛሪ ሽቅብ ለማውጣትና ቁልቁል ለማውረድ፥ የዓለምን ንግድ ለመቆጣጠርና ብዙውን የኃይል ክምችት ለማስተዳደር በኮንፌዴሬሽን ደረጃ ኅብረት ይፈጥራሉ።

## ♦ አዲሱ ጭለማ ዘመን

በልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ማመንና፥ በዓለማችን እየተከሠቱ ያሉ እንግዳ ነገሮች መስፋፋት ከተረትነትና እንደ ጨዋታ ከመቆጠር አልፈው የሰውን

ልጅ የሚያስፈሩ ይሆናሉ። ስለ ጥንቆላና ሰይጣን አምልኮ የተጻፉ መጻሕፍት፣ መጽሔቶችና ፊልሞች የምዕራቡን ዓለም ትኩረት ይሻማሉ። ሰይጣናዊ አምልኮና እስካሁን የማይታወቁ አዳዲስ የሃይማኖት ቡድኖች ግንባር ቀደም ዜና በመሆን ላይ ናቸው።

ትኩረት የሚሰጠው ሌላ አስደንጋጭ የወደፊት ጉዳይ ደግሞ በሥነ-መለኮታዊያን አጠራር የቤተ ክርስቲያን ንጥቀት መሟላት- ክርስቲያኖች በቅጽበት ከዚህ ዓለም መወሰዳቸው ይሆናል (1ኛ ተሰ. 4፡13-18)። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ "እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፣ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ" (ዮሐ. 14፡3) በማለት የተናገረው ተስፋ ፍጻሜ ነው። የሞቱት ክርስቲያኖች ያኔ ይነሣሉ፣ በሕይወት ያሉት እውነተኛ ክርስቲያኖች ደግሞ ሥጋዊውን (አካላዊውን) ሞት ሳይቀምሱ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይነጠቃሉ። ይህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በቅፅበት ከአካባቢው የመሰወራቸው ሁኔታ በሌላው ሕዝብ ዘንድ ግራ መጋባትን ይፈጥራል። በክርስትና ሽፋን የተዋቀረች ቤተ ክርስቲያን፣ ወይም ድርጅት፣ እውነተኛ ክርስቲያኖች ከውስጧ ሲነጠቁ፣ በፖለቲካ ጥቅመኞች እጅ ትወድቃለች። ጥንቆላ፣ ሰይጣናዊ አምልኮና የርኩሳን መናፍስት ሥራ በመላው ዓለም ይሰፍናል። በጨለማው ዘመን እንደታየው ሁሉ፣ ይህ ጊዜም ዓለማውያን መንግሥታት ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ተባብረውና ተቀናጅተው የሚሠሩበት ይሆናል።

## ♦ እስከ አርማጌዶን ድረስ ያለው የሁኔታዎች ቅደም ተከተል

ከሌላው የዓለም ክፍል ይልቅ በቅድሚያ መካከለኛው ምሥራቅ ከፍተኛ ቀውስ የሚደርስበት መሆኑ በግልጥ ሊታወቅ ይገባል። ከዚሁ ጋር መንግሥታት በአካባቢው የበላይነትን ለመጨበጥ ከሚያደርጉት ሽኩቻ የተነሣ አዲስ ሥርዓት ይሰፍንና ለአሥሩ መንግሥታት መድረክ ያዘጋጅላቸዋል፤ የአካባቢው ሁኔታ ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ ሰላማዊ መፍትሔ የሚያገኘውም በእነዚሁ መንግሥታት አማካይነት በተጽዕኖ ነው። የአሥሩ መንግሥታት መመሥረት የመድረኩ መዘጋጀት ሲሆን፣ ሰባቱ ዓመታት መቆጠር የሚጀምሩት ደግሞ፣ ከእስራኤል ጋር የመጨረሻ የሰላም ውል ከሚፈራረሙበት ዕለት አንሥቶ ነው። በዚህ ጊዜ የዓለም አቀፍ የኃይል ሚዛን በአውሮፓ አገሮች ኅብረት ላይ እየተሰበሰበ ይሄዳል። የመካከለኛው ምሥራቅን ችግር በሰላም ለመፍታት ከሚጥሩት መሪዎች መካከል አንድ ዓለም አቀፍ መሪ ይነሣና፣ በእስራኤልና በአክራሪ ዓረብ አገሮች መካከል ስምምነት እንዲኖር ያደርጋል። ይህ ዘመን የሐሰት ሰላም የሰፈነበት፣ ትጥቅን ለማስፈታት እንቅስቃሴ የሚደረግበት፣ እንዲሁም አዲስ ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመዘርጋት

ግፊት የሚደረግበት ይሆናል። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜያት፥ የኅብረቱ መሪ ሥልጣኑን እስኪያጠናክር ድረስ ጸጥታ የሚሰፍንባቸው ናቸው።

የሚቀጥሉት (መጨረሻዎቹ) ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜያት ደግሞ፥ ሊታሰብ የማይቻልና የማያቋርጥ እጅግ አስከፊ ጥፋት የሚከሠትባቸው ይሆናሉ። ይህ ዘመን ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ግን፥ ሩሲያ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያለ ኃይልዋን ይዛ ከመካከለኛው ምሥራቅ ሥልጣን ለመቀራመት የበኩልዋን ጥረት ታደርጋለች። ሆኖም ሠራዊቷ በልዕለ-ኃይላት ድባቅ ይመታል (ሕዝ. 38፡39)። ከዚህ በኋላ የኃይል ሚዛኑ የሚዲትራኒያን አካባቢ ኅብረት ተቆጣጣሪ ወደሚሆነው አዲስ መሪ ይዛወራል። ይህ መሪ፥ ሰይጣን ወቅቱን ጠብቆ የሚያስነሣው ሰው ሲሆን፥ ትጥቋን ፈትታ በሰላም የምትኖረዋን እስራኤል ለማጥፋት ይሞክራል። እንደ ባቢሎናውያንና እንደ ሮማውያን መንግሥታት ራሱን ጣዖት በማድረግ፥ ዓለም ሁሉ እንዲሰግድለት ያዝዛል። አይሁዶች፥ ስመ-ክርስቲያኖች (ያልተነጠቁት) እና ከሁሉም ወገን የተውጣጡ አነስተኛ ቡድኖች ሂትለር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አይሁዶችን ካሰቃየበት የከፋ ስቃይና እልቂት ይደርስባቸዋል።

ዓለማችን ሳይንቲስቶች መፍትሔ በማያገኙላት አኳኋን ከቁጥጥር ውጪ ትሆናለች። በሺህ የሚቆጠሩ ሰማዕታትን የሚያስገኘው የሰው ልጅ ድርጊት እና የእግዚአብሔር ድርጊት በመዋሃድ በዓለምና በከዋክብት ሥርዓት (ሶላር ሲስተም) ላይ ትልቅ ሁከትን ይፈጥራሉ ። ከዋክብት ይወድቃሉ፥ ፕላኔቶች ከሥርዓታቸው ውጪ ይበራሉ። ከፍተኛ የአየር ንብረት ለውጥም ይሆናል (ራእይ 16፡13-14፤ 16፡8-9)። ያልተለመደ ሙቀትና ቅዝቃዜ፥ ጎርፍና፥ ሌሎችም ጥፋቶች የዓለምን አዝመራ ያወድማሉ (ራእይ 6፡6-8)። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች በረኃብ ያልቃሉ (ማቴ. 24፡7)። ዘመናዊ መድኃኒቶች ቢኖሩም፥ በአዲስ ወረርሽኝ መቅሠፍት ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ሕይወት ይቀሠፋል። የሰባቱ ዓመት መጨረሻ ሲቃረብ፥ የምድር ነውጥ የዓለምን ታላላቅ ከተሞች እንዳልነበሩ ያደርጋቸዋል። ተራሮችና ደሴቶች በባሕር ይዋጣሉ (ራእይ 16፡17-20)። በጥፋት ላይ ጥፋት ተደራርቦ በአጭር ጊዜ አስከፊ እልቂት ይደርስና፥ በቢሊዮን ከሚቆጠረው የዓለም ሕዝብ እጅግ ጥቂቱ ብቻ ይቀራል።

## ♦ ከሦስተኛው የዓለም ጦርነት ወደ አርማጌዶን

ከዚህ ሁሉ አስከፊ መዓት በኋላ ሳይታሰብ የዓለም ጦርነት ይቀሰቀሳል። በብዙ መቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩና ለሥልጣን ሽሚያ የሚሻኮቱ መንግሥታት ወታደሮች ቅድስቲቱን ከተማ ይከቧትና (ራእይ 16፡13-16) ከሌሉ በታሪክ

ተወዳዳሪ የሌለው የጦርነት አውድማ ይሆናል። በሚሊዮን የሚቆጠር የደቡብ ሠራዊት አፍሪካን ወክሎ ወደ ጦርነቱ ይተማል (ዳን. 11፡40)። ሌላው ሩሲያንና አውሮፓን ወክሎ ከሰሜን የሚመጣ ሠራዊት ደግሞ፥ ፍልስጥኤም ላይ ይሰፍራል (ዳን. 11፡40)። ውጥረቱን ለማባባስ፥ ሩቅ ምሥራቃውያንና ቻይና የኤፍራጥስን ወንዝ አቋርጠው በመምጣት የጦርነቱ ተሳታፊዎች ይሆናሉ (ዳን. 11፡44፤ ራእይ 9፡15-16፤ 16፡12)። በዚህ አስጨናቂ ጦርነት ታይቶ በማይታወቅ መጠን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይሞታሉ። ይህን ነው መጽሐፍ ቅዱስ አርማጌዶን ብሎ የሚገልጠው። ጦርነቱ ሊያበቃ ጥቂት ሲቀረውና አሸናፊው ሳይለይ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥልጣንና በታላቅ ክብር ከሰማይ ይመጣል። በራእይ ምዕራፍ 19 ላይ እንደተገለጠው፥ አመጣጡ፥ በሚሊዮን በሚቆጠሩ መላእክትና ቅዱሳን ታጅቦ ነው። የነገሥታት ንጉሥና የዓለም ፈራጅ ሆኖ የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ ደምስሶ፥ የራሱን የጽድቅና የሰላም መንግሥት በምድር ላይ ያሰፍናል።

የትንቢት አጥኚዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢትና በብዙ ጠቋሚ ዘገባዎች ላይ በመንተራስ፥ ዓለም ወደ አርማጌዶን እየገሰገሰች ነው ብለው ይደመድማሉ። ለዚህ ድምዳሜ ያበቃቸው ምልክት ምንድነው? ዓለማችንስ ምን ያህል ወደ ፍጻሜ እየተቃረበች ይሆን? ግለሰቦችስ እንዲህ ካለው ሁኔታ አንጻር ተስፋቸው ምንድነው? የዘመኑ ትውልድስ ከዚህ ጥፋት ለመዳን ምን ማድረግ አለበት? ለነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መልሱ እግዚአብሔር ስለ መጨረሻው ዘመን ባለው ትንቢታዊ ዕቅድ፥ ስለ እስራኤል፥ ስለ ዓለምና ስለ ቤተ ክርስቲያን በተናገረው ውስጥ ተካትቷል። በዚህ የታሪክ መድረክ ላይ የምትገኘው እና ከዓለም ሕዝብ ብዛት አንጻር እጅግ የምታንሰው፥ ነገር ግን ከፊታችን ያለውን የመጨረሻ የዓለም እልቂት ለኳሽ የሆነችው እስራኤል ናት።

# 3

# የእስራኤልና የዓረቦች ግጭት

## ♦ የተስፋ ጭላንጭል

ኢየሩሳሌምና በሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዶች በሮማውያን ወታደሮች በ70 ዓ.ም. ከወደሙ አያሌ ምዕተ ዓመታት ተቆጥረዋል። እነዚህ ለአይሁዶች የኀዘንና የልብ ስብራት ዘመናት ነበሩ። ኢየሱስና ነቢያት እንደተነበዩት ሁሉ፥ አይሁዶች በዓለም ዙሪያ ተበትነዋል፤ በሮማውያን ሰይፍ ተጨፍጭፈዋል። ሐሰተኛ እምነትን ለማጥፋት በተደረገው ሙከራም ብዙ አይሁዳውያን በተሳሳቱ ክርስቲያኖች ተገድለዋል፤ በጀርመኖች የመርዝ ጋዝ ያለ ርኅራኄ አልቀዋል። ስለዚህ ጥፋት ብቻ አልነበረም ነቢያት የተናገሩት፥ ስለ አዲሱ የተስፋ ዘመንም ገልጠዋል። አይሁድ እንደ አንድ ሕዝብ ሆነውና ሕልውናቸውን ጠብቀው እንዲታገሉ የረዳቸው ከነዚህ የተስፋ ጭላንጭሎች የመነጨ ብርታት ነበር።

## ♦ ነጻነት - ምድሪቱ - ብልጽግና

ነቢያቱ አጉል ሕልመኞች አልነበሩም፤ እስራኤላውያን ብሩህ ተስፋ እንደሚጠብቃቸው ተናግረዋል። በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠው አይሁዳውያን ከመከራና ችግር እንደሚድኑ ብቻ ሳይሆን፥ ነጻነታቸውንና መሬታቸውን በማግኘት በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የበለፀገ መንግሥት እንደሚመሠርቱ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ተችዎች ከእግዚአብሔር ለአብርሃም በተሰጡት ተስፋዎች፥ ሙሴና በሌሎች ነቢያትም በተነገሩ ትንቢቶች ሲያፌዙ ኖረዋል። እነዚህ ትንቢቶች ከእግዚአብሔር የተሰጡ እውነቶች መሆናቸውን ግን ሊገነዘቡ ይገባል።

ከ1948 አንሥቶ ያለውን የእስራኤል ታሪክ ስንመለከት እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ እንደታደጋት እንረዳለን። ምንም እንኳን ኢየሱስን እንደ መሢሕ ባትቀበለው፥ ስለ እርሷ ያለውን ትንቢታዊ ቃል ለመጠበቅ ሲል እስካሁን በተአምር አቆይቷታል። ተደጋጋሚ ወታደራዊ ጥቃት ቢደረግባትም ሕልውናዋን አስጠብቃለች፤ የጥንት ርስቷ በነበረው ስፍራ ላይ ይበልጥ እንድትስፋፋና እንድትደላደል አድርጎአታል። የእነዚህ ጦርነቶች ዘገባ ከትንቢቶች መፈጸም አኳያ ሲታይ የድርጊቱን አስደናቂነት ያጎላዋል።

ከአብርሃም ጀምሮ በዘመናችን እስካሉት እምነታቸው አጥብቀው የያዙ አይሁዳውያን ድረስ ያሉት አይሁዳውያን የሚያምኑባቸውና ድጋፍ የሚሆናቸው እነዚህ ተስፋዎች ናቸው። እነዚህ ትንቢቶች በተለያየ የዓለም ክልል ላሉ አይሁዳውያን ጥልቅ ትርጉምና መልእክት ነው ያላቸው። በ1956 እና 1967 እስራኤልን የሚያጠፉ ጦርነት በታወጀ ዕለት የኢየሩሳሌም ራዲዮ ጣቢያ የነቢዩ አሞጽን ትንቢት ጠቅሶ የሚከተለውን መልእክት አስተላልፎ ነበር፦

> "የሕዝቤን የእስራኤልን ምርኮ እመልሳለሁ፤ የፈረሱትንም ከተሞች ሠርተው ይቀመጡባቸዋል፤ ወይንንም ይተክላሉ፤ የወይን ጠጅንም ይጠጣሉ፤ አታክልቱንም ያበጃሉ፤ ፍሬውንም ይበላሉ። በምድራቸውም እተክላቸዋለሁ፥ ከእንግዲህ ወዲህ ከሰጠኋቸው ከምድራቸው አይነቀሉም ይላል አምላክህ እግዚአብሔር" (አሞጽ 9፥ 14-15)።

ስለ እስራኤል የተነገረው ትንቢት ግልጥ ነበር። ወደፊት በተስፋይቱ ምድር እንደገና እንደምትመሠረትና ማንም ሊበግራት እንደማይችል ተነግሮላታል። በ1948 የእስራኤል ልደት የተስፋው መፈጸም ጅማሬ ይሆን? ከሆነ ምንም ችግር ይግጠማት፥ ማንኛውም ኃያል መንግሥት ወይም ሠራዊት ይነሣባት፥ ከእንግዲህ እስራኤልን ወደ ባሕር ገፍተው ሊጥሏት አይችሉም።

## ♦ የዓረቦች ዓላማ- እስራኤልን ማጥፋት

የእስራኤልን በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ መኖር ዓረቦች ልክ በቀዶ ጥገና ብቻ ሊወገድ እንደሚችል አስከፊ ሕመም ነው የሚመለከቱት። እግዚአብሔር የተስፋይቱን ምድር እንደሚያወርሳቸው ተስፋ የሰጣቸው ቢሆ ንም፥ ዓረቦች ግን እስራኤላውያንን ሜዲትራኒያን ባሕር ውስጥ ለማስጠምና ኢየሩሳሌምን ጨምሮ አካባቢውን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ጽኑ ፍላጎት አላቸው። ይዋል ይደር እንጂ፥ በሕዝብ ብዛትና በሀብት ከምችት የበለጸገው የዓረብ ዓለም ይህን ምኞቱን እውን ለማድረግ መነሣቱ አይቀርም።

## ♦ በ1956ቱ ጦርነት የዓረቦች ማፈግፈግ

እስራኤል በ1948 ዓ.ም. ሕልውናዋን ካስከበረች ወዲህ፥ እሷም ሆነች የዓረቡ ዓለም ብዛት ያለው የጦር መሣሪያ በማከማቸት ላይ ናቸው። በጥቅምት ወር 1956 ዓ.ም. ቀልጣፎቹ የእስራኤል ወታደሮች በቀላሉ የጋዛን ሰርጥ ወረሩ። እስራኤል በኃያላን መንግሥታት ባትገታ ኖሮ ግብፅም ወዲያውኑ በፈጣኖቹ የእስራኤል ወታደሮች እጅ ትወድቅ ነበር።

## ♦ ሩሲያ ለእስራኤሎች ተፃራሪ ሆና ቆመች

ከ1956 ዓ.ም. ወዲህ ያሉት ዓመታት ለእስራኤል አመቺ አልነበሩም። በምዕራብ ከግብፅ፥ በሰሜን ከሶሪያ፥ በምሥራቅ ከዮርዳኖስ በየጊዜው ጥቃት ይሰነዘርባት ጀመር። ግብፅ በጀማል አብደል ናስር መሪነት ከሶቪየት ኅብረት ጋር የጠበቀ ግንኙነት መሠረተች። ሶቪየት ደግሞ በቢሊዮን ዶላር የሚገመት የጦር መሣሪያ ለግብፅ ሰጠቻት። በብዙ ሺህ የሚገመቱ ሩሲያውያን የጦር አማካሪዎችም ወደ ግብፅ ገቡ። የሩሲያ በዚህ አኳኋን በዓረቦች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት፥ ችግር አስከትሎ አሜሪካና እንግሊዝም ጣልቃ ባይገቡ ኖሮ መካከለኛው ምሥራቅ በኮሚኒስቶች ቁጥጥር ሥር ይሆን ነበር። በ1958 ዓ.ም. እንደተደረገው ሁሉ፥ የአሜሪካ ባሕር ኃይል በሊባኖስ ሲሰፍር፥ የእንግሊዝ ጦር ኃይሎችም ለዮርዳኖሱ ንጉሥ ሑሴን [King Hussein] ድጋፍ ሰጡ። ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለአካባቢው የተሰጠ ምንም እርዳታ አልነበረም።

## ♦ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እርዳታ ማጣት

በጀማል አብዱል ናስር [Gamal Abdul Nasser] የሚመራው የዓረብ ዓለም በእስራኤል ላይ የጦርነት ሴራ ቀጠለ። ምንም እንኳን ሌላ ጦርነት ያስነሣል የሚል ሥጋት ቢኖርባቸው፥ ናስር በሶሪያ አክራሪዎች ግፊት እስራኤል ላይ የሚቃጣውን ማንኛውንም ጥቃት ደገፉ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እስራኤል ላይ የሚደረገውን ትንኮሳ በቸልታ ነበር የሚመለከተው። ከ1949 ዓ.ም. ጀምሮ እስራኤል 100,000 ጊዜ ድንበሯ እየተጣሰ የደረሰባትን ጥቃት ዝርዝር ለማሳተም የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ለነበሩት ዩ ታንት [U Thant] አቅርባ ነበር። እርሳቸው ግን ዝርዝሩ እጅግ የበዛ ነው በማለት ሳይቀበሏት ቀሩ። በእነዚህ ሁኔታዎች ሳቢያ አገሪቱ ከማኅበሩ እርዳታ እንደማታገኝ ግልጥ ሆነ። ጥቃቱ ሲብሰባት ሴስ ሰሙ የምትባለዋን አነስተኛ የዮርዳኖስ ከተማ ወርራ እንዳልነበረች አደረገቻት። የዓረቦችን ትንኮሳ በቸልታ ሲመለከት የነበረው የመንግሥታቱ ማኅበር ይህን ድርጊቷን አወገዘ። በነዚህ ሁኔታዎች ሳቢያ አገሪቱ ከማኅበሩ እርዳታ እንደማታገኝ ግልጥ ሆነ።

## ♦ የስድስቱ ቀን ጦርነት

ሩሲያ በሁኔታው ለመጠቀም ያላደረገችው ጥረት አልነበረም። በ1967 ዓ.ም. ለግብፅና ለሶሪያ "እስራኤል ለጦርነት በመዘጋጀት ላይ ናት" እያለች

የተጋነነ ጥቆማ ታቀርብላቸው ጀመር። ከዚህ የተነሣ ነበር ፕሬዚደንት ናስር እስራኤልን የማጥፊያ ጊዜ አሁን ነው የሚል እምነት አድሮባቸው የነበረው። የዓረቦች ዓላማ፥ ከፍተኛ ጦርነት አድርጎ እያንዳንዱን እስራኤላዊ ማጥፋትና አካባቢውን እንደገና በቁጥጥራቸው ሥር ማድረግ እንደሆነ ይፋ ወጣ። እነሱም ሆኑ እስራኤል ከየአቅጣጫው አሳሳቢ መረጃ ይደርሳቸው ጀመር። በመጨረሻም ግብፃውያን አካባ [Aqaba] ባሕረ-ሰላጤ ውስጥ የምትገኘውንና ኤላት [Eilat] የተሰኘችውን የእስራኤል ወደብ ዘጉ።

እስራኤል ይህን ሁሉ ካጤነች በኋላ ሕልውናዋን ለማስጠበቅ ብቸኛው መፍትሔ አስቀድማ ማጥቃት መሆኑን አመነችበት። ስለዚህም ሰኔ 5 ቀን 1967 ዓ.ም. ጎህ ከመቅደዱ በፊት አይሮፕላኖችዋ ዝቅ ብለው ከሰሜንና ከሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመብረር የግብፅን አየር ኃይል ድባቅ መቱት። ባሕር ሰርጓጅ [Torpedo/ቶርፒዶ] ኮማንዶዎችዋም አብዛኛውን የግብፅ ባሕር ኃይል አወደሙ።

## ♦ ተአምራዊው የእስራኤል ድል

ቀጥሎ የተደረገው ጦርነት የዓረቡን ዓለም ክፉኛ ነበር የጎዳው። የእስራኤልን ጥፋት ለማየት የቋመጡት ዓረቦች በተቃራኒው የራሳቸውን ጦር መፍረክረክ ተመለከቱ። ዘመናዊው የእስራኤል ታንከኛ ወደ ሲና በረሀ ገሰገሰ። የጦሩ የግስጋሴና የማጥቃት ስልት በመጽሐፍ ቅዱስና በአይሁድ ታሪክ እንደተገለጠው ጥንት አካባቢውን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ከተጠቀሙበት የጦርነት ስልት ጋር ይመሳሰል ነበር። ይህን የተመለከተችው ሩሲያ የረጅም ጊዜ ዕቅዷ ሁሉ እንዳልሠመረላትና የዓረቡን ዓለም ለማስታጠቅ ያወጣችው ሦስት ቢሊዮን ዶላር አንዳችም ውጤት እንዳላስገኘላት በሁለተኛው ቀን ተረዳች። የዮርዳኖስና የግብፅ ሠራዊት በጦርነቱ ተሽመደመደ፤ የሶሪያም ጦር እግሬ አውጪኝ አለ። ያ ሁኔታ ቢቀጥል ኖሮ ካይሮ፥ አማንና ደማስቆ በጥቂት ሰዓት ውስጥ ለእስራኤል ጦር ጥቃት ይዳረጉ ነበር። ስለ እግዚአብሔርም ሆነ ስለ መንፈሳዊ ነገር ደንታ ያልነበራቸው አይሁዳውያን እንኳን ሳይቀሩ ይህን ሲመለከቱ፥ ስለ ተአምራዊው አምላካዊ ማዳን ይወያዩ ጀመር።

## ♦ ሩሲያ ጦርነት እንዲቆም ጥሪ አደረገች

በ1956 እንደተደረገው፥ አሁንም ድሉ ወደ እስራኤል ማጋደል ሲጀምር፥ ጦርነቱ እንዲቆም ጥሪ ቀረበ። ሩሲያ በመጀመሪያ ድሉ የዓረቦች ይሆናል ብላ በመገመት ውጊያው እንዲቀጥል ትደግፍ ነበር፤ በኋላ ነው፥ የዓረቦች ብቸኛ ተስፋ የጦርነቱ መቆም መሆኑ ግልጥ የሆነላት።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መጀመሪያ ጦርነቱ እንዳይቀሰቀስ ምንም ጥረት ያላደረገውን ያህል፥ እስራኤል ጥቃቱን ማቆም አለባት እያለ ይወተውት ጀመር። እስራኤል ደግሞ ጦርነቱ የሚቆመው አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉላት ብቻ እንደሆነ ግልፀ አደረገች። ይኸውም ራስዋን የቻለች ሉዓላዊት አገር መሆንዋ እንዲታወቅላትና ለአካባቢው ሰላምም አስተማማኝ ውል እንዲደረግ መጠየቅ ነበር።

## ♦ የ1967ቱ ጦርነት የመጨረሻ ቀኖች

ዓረቦች ድል የመሆናቸውን ሐቅ መቀበሉ ቸገራቸው፤ ውጊያው በቀጠለ መጠን ደግሞ እስራኤል ግዛቷን አስፋፋች። በቅዱስ ስፍራዎች ላይ ጥቃት ላለማድረስ እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግም ኢየሩሳሌምን እጇ አስገባች። ወታደሮቿ ጥንታዊው ቤተ መቅደስ የነበረበትን ስፍራና "የለቅሶ ግንብ" በመባል የሚታወቀውን ለመጀመሪያ ጊዜ እጃቸው ሲያስገቡ፥ ይህ ነው የማይባል ደስታ ነበር የተሰማቸው፤ በደስታ አለቀሱ።

ጄኔራል ሞሼ ዳያንም [Moshe Dayan] አይሁዶች ወደ ቅድስት አገራቸው መመለሳቸውን፥ ከእንግዲህም ማንም እንደማያስወጣቸውና ወደኋላም እንደማያፈገፍጉ በማሳወቅ ጋዜጣዊ መግለጫቸውን ለዓለም አሰሙ። ቀደም ሲል የ1948ቱ የጦር አቁም ስምምነት ወደ "ለቅሶ ግንብ" ለመቅረብ እንደሚችሉ ዋስትና ቢሰጣቸውም ውሉ ተግባራዊ አልሆነም ነበር።

የእስራኤል ወታደሮች ወዲያውኑ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ገሰገሱ፤ የዮርዳኖስ መንግሥት ሠራዊት አፈገፈገ። እስራኤል ዛሬም እንኳን በ"ምዕራብ ዳርቻ" [West Bank/ዌስት ባንክ] ላይ ያላት የይገባኛል ጥያቄ እርሷ ራሷ ባላነሣችው ጦርነት አካባቢውን በቁጥጥሯ ሥር ካደረገች ወዲህ የተጀመረ ነው። የዓለም መገናኛ ብዙኃን ግን ይህን ሐቅ መቀበል አይፈልጉም። ዮርዳኖስ በፍጥነት ለሽንፈት የተዳረገችው፥ የአየር እርዳታ አደርግልሻለሁ ያለቻት ግብፅ ቃሏን ባለማክበርዋ ነበር። የሶሪያና የግብፅ ወታደሮች ምንም እንኳን ሩሲያ በተለያየ መልኩ ከፍተኛ እገዛ ብታደርግላቸውም የእስራኤልን ጦር መቋቋሙ አልሆነላቸውም።

የታሰበው ሁሉ በዚህ አኳኋን እንዳልሆነ ሲሆን ጊዜ፥ ዮርዳኖስ ሠራዊቷ ጦርነት እንዲያቆም ረቡዕ ዕለት አዘዘች፤ በማግስቱ ሐሙስ ደግሞ ግብፅ በአሳቡ መስማማትዋን ገለጠች። ሶሪያ ብቻ ነበረች፥ አስከፊ ጉዳት ቢደርስባትም ጦርነቱን ብቻዋን የቀጠለችው። ሆኖም እስራኤልን በቦምብ ትደበድብበት የነበረው የጎላን ተራራ በአስደናቂ ተጋድሎ በእስራኤላውያን

ቁጥጥር ሥር ዋለባት። ይህ ድል የመሆኛዋ የመጀመሪያ ቀን ሆነና፤ ጦርነቱ በስድስት ቀን አበቃ። ውጊያው የእስራኤልን የጦር ችሎታ ያስመሰከረ ቢመስልም፥ እግዚአብሔር ለእስራኤል በገባው ተስፋ መሠረት የማዳን እጆቹን ያሳየበት ጦርነትም ነበር።

## ♦ አሜሪካና እንግሊዝ ጣልቃ ገብተዋል በሚል በናስር የተናፈሰ ወሬ

ናስር እስራኤልን ለማጥፋት የነበራቸው ሕልም እንዳልሠመረላቸው ሲያዩ ለደረሰባቸው ታላቅ ሽንፈት እንግሊዝንና አሜሪካንን በጣልቃ ገብነት ወነጀሉ። ይሁን እንጂ፥ የኋላ ኋላ ይህ ውንጀላ ፍጹም ሐሰት መሆኑ ተረጋግጦአል። ጦርነቱ ያበቃ ዕለት ነበር ፕሬዚደንቱ ሥልጣን መልቀቃቸውን ያስታወቁት። የግብፅ ወታደሮች ያ ሁሉ ቅሌት የደረሰባቸው በናስር መሪነት እንደሆነ ቢታወቅም፥ ሕዝቡ ወደ ሥልጣን እንዲመለሱ ተማፀናቸው። እሳቸውም እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ለሽንፈታቸው ምክንያት የሆነው የእንግሊዝና የአሜሪካ ጣልቃ ገብነት እንደሆነ ሲያወሩ ኖሩ።

## ♦ የ1967 ጦርነት ውጤቶች

ጦርነቱ፥ የእስራኤልን ግዛት የቆዳ ስፋት ከስምንት ሺህ ወደ ሠላሳ አራት ሺህ እስኩዌር ማይሎች* ከፍ እንዲልና የሕዝቧም ቁጥር በእጥፍ እንዲጨምር አድርጓል። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ አይሁድ ከተነገሩት ትንቢቶች አኳያ የኢየሩሳሌም ተመልሳ በአይሁዶች እጅ መግባት ትልቁ ነጥብ ነው። ይህ ብቻም አይደለም፤ ለጊዜውም ቢሆን ሌላ ጦርነት እንዳይነሣ አድርጓል። በጦርነቱ ሳቢያ ከዓረቦች ሠላሳ አምስት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ሲያልቁ፥ ከእስራኤል ደግሞ አንድ ሺህ የማይሞሉ ሰዎች ሞተዋል። በዚህ ጦርነት እስራኤል ዝናዋ ከፍ ያለ ሲሆን፥ በዚያው መጠን የጠላቶችዋ የጦር ኃይል ተንኮታኮተ። ተአምራዊው የ1967 ጦርነት የመጨረሻው ባይሆንም፥ "ከእንግዲህ ወዲህ... ከሰጠኋቸው ከምድራቸው አይነቀሉም" (አሞጽ 9፡15) የሚለውን የነቢያት ትንቢት ዓለም ተገንዝቦታል።

## ♦ ሩሲያ ግብፅንና ሶሪያን እንደገና አስታጠቀቻቸው

የ1967 ዓመተ ምሕረቱ አስቃቂ ጦርነት ውጤት አሁን እንደ ታሪክ ቢወራም፥ በትንቢታዊ ትርጉም የተሞላ ነው። ቀጥሎ ባሉት ዓመታት ሩሲያ ግብፅን፥ ሶሪያንና ሌሎች ዓረብ አገሮችን በጦር መሣሪያ ማስታጠቅ ቀጠለች።

---

* አንድ እስኩዌር ማይል 2,671,895 ካሬ ሜትር ወይም 267 ሄክታር ነው።

ብዛት ያለው የኢኮኖሚ እርዳታም ሰጠቻቸው። በ1972 ዓ.ም. ሀያ ሺህ ከፍተኛ የሩሲያ የጦር መኮንኖች ግብፅ ውስጥ ነበሩ። በውጪው ሲታይ የሩሲያ ዓላማ ግብፅ እስራኤልን ለመውጋት ያላትን ፍላጎት መግታት ቢመስልም፥ የሩቅ ጊዜ ዕቅዷና ዝግጅቷ ግን ለጦርነት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነበር። ሆኖም የሩሲያ ወታደሮች ቁጥር እየበረከተ መምጣት ለግብፅ መሪዎች የራሳቸውን ወታደር ለመቆጣጠርና የጦር ስልት ለመቀየስ፥ እንዲሁም ውሳኔ ለማስተላለፍ አዳጋች ሆኖባቸው ነበር።

## ♦ ግብፅ ከሩሲያ ጋር ያላትን ግንኙነት አቋረጠች

ሐምሌ 1972 ዓ.ም. 90 ደቂቃ በፈጀው የፕሬዚደንት አንዋር ሳዳት [Anwar Sadat] ንግግር፥ ግብፃውያን ወታደሮቻቸውን፥ ሰፈራቸውንና መሣሪያቸውን ለመቆጣጠር ብቃት እንዳላቸው ገልጠው፥ የሩሲያ የጦር አማካሪዎች አገራቸውን ለቀው እንዲወጡ አዘዙ። ይህ ሁኔታ ሩሲያ በመካከለኛው ምሥራቅ ለመቆየት ላላት ፍላጎት መሰናከል ቢሆንም፥ ዓረቦችን ደግሞ ይበልጥ በራሳቸው እንዲተማመኑና ነጻ ዘይታቸውን እንደ ማስፈራሪያ እንዲጠቀሙበት አድርጓቸዋል።

ሩሲያኖች የግብፅን ጦር ሠራዊት መናቃቸውና ጦሩን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት በግብፃውያን ዘንድ እንዳይታመኑ አድርጓቸዋል። ይህ ብቻ አይደለም፤ ግብፃውያን ከእስራኤል ጋር ባላቸው ወሳኝ ጦርነት ለድል የሚያበቃ ዘመናዊ መሣሪያ ሩሲያ እንደማታስታጥቃቸው በውል ተረድተዋል። በእነዚህ ሁኔታዎች ሳቢያ ከፊሎቹ የሩሲያ ወታደሮች ወደ አገራቸው ቢመለሱም፥ አሥራ አንድ ሺህ የሚሆኑት ማጥቂያና መከላከያ ወረዳዎችን ለማጠናከር በግብፅ ቀሩ። ሩሲያውያን ከግብፅ እንዲወጡ መደረጉን ግብፃውያን በደስታ ቢቀበሉትም አገሪቱ ትልቅ ችግር ላይ ነበረች። ዓረቦች ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ገና አዲስ የጦር ስልት አልቀየሱም፤ በዚህ ሳቢያ ወደዱም ጠሉ የሩሲያ ጥገኚነት አስፈልጓቸዋል።

## ♦ ሩሲያ የተቋረጠ ግንኙነትዋን አደሰች

ሩሲያውያን በበኩላቸው የረጅም ጊዜ ዕቅዶቻቸው ስላልተሳኩላቸው ለዘለቄታው የተከሏቸውን ከባድ የጦር መሣሪያዎች ይዘው በጥድፊያ ከግብፅ ወጡ። ከዚህም የተነሣ ግብፅ የመለዋወጫ ዕቃዎች እቅርቦት ቀነሰባት፤ ለጦር መሣሪያዎች የሚያስፈልጓትን የመለዋወጫ ዕቃዎችን፥ አረሮችን፥ የቴክኒክ አማካሪዎችና የኤኮኖሚ እርዳታ ለማግኘት ስትል ከሩሲያ ጥገኝነት መላቀቅ አልሆነላትም። በጊዜው ለዓረቦች የጦር መሣሪያ ሊያቀርቡ የሚችሉ የዓረብ

ወዳጆች ጥቂት ነበሩ። ግብፅ ደግሞ ይህን የጦር መሣሪያ ፍላጎት ለማሟላት አቅሙ የላትም። ይህ እንዲህ እያለ፥ በመካከሉ፥ ሩሲያ ለሌላ ዓረብ አገር ስፊ አቅርቦትና የኢኮኖሚ እርዳታ ታደርግ ጀመር። ቀስ በቀስም ለይስሙላ ያህል የግብፅና የሩሲያ ግንኙነት እንደገና ታደሰና የጦር መሣሪያ አቅርቦቱ እንደገና ቀጠለ። በዚህ ጊዜ ነው በግብፅና በሳውዲ ዓረቢያ መካከል አዲስ ኅብረት ተመሥርቶ ለዓረቡ ዓለም አዲስ የጦር ዕቅድ ለመንደፍ ጠቃሚ ውይይት መካሄድ የጀመረው።

## ♦ ነዳጅ ዘይት ለማስፈራሪያነት ሲውል

የመካከለኛው ምሥራቅ አዲስ ፖለቲካ ዓረቦችን ከሩሲያ ጥገኝነት ነጻ በማድረግና፥ ራሳቸውን ችለው ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቲክ ግንኙነት በመፍጠር ዕቅድ ላይ ያተኮረ ነበር። የዓረብ አገሮችና ኢራን የነዳጅ ዘይት ዋጋቸውን ወደ ሰማይ በማናርና ከነሱ ጋር ወዳጅነት በሌላቸው ላይም ማዕቀብ በመጣል በኢንዱስትሪ የበለጸጉ አገሮችን ማስፈራራት ጀመሩ። አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገውን እርዳታ እንድታቆም ለማስገደድ ሲባል የነዳጅ ዘይት አቅርቦት መቋረጥን እንደ ማስፈራሪያ በማቅረብ በ1973 ዓ.ም. በመስከረም ወር ተጽዕኖ ተደረገበት። ይህ እንደሚሆን አስቀድሞ ሲጠበቅ የቆየ ቢሆንም፥ ሁኔታው አዲስና አደገኛ አቅጣጫ ያዘ። በመላው ዓለም በነዳጅ ዘይት የመጠቀሙ ሁኔታ በፍጥነት እየጨመረ መምጣቱ ደግሞ ችግሩን አባባሰው። በአሜሪካ የነዳጅ ዘይት እጥረትና፥ የማጣራቱ ብቃት ማነስ የተነሣ ችግሩ ጊዜ የማይሰጥ ሆኖ ነበር። ሥነ-አካባቢ አጥኚዎች የአላስካውን የነዳጅ ዘይት ቧንቧ፥ የውቅያኖስ ውስጥ የነዳጅ ፍለጋ እና የኑክሊየር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ሥራ አቀዝቅዘውት ነበር። እነዚህ ሁሉ ታክሉበትና የነዳጅ ዘይት እጦት ዓለም አቀፍ ሥጋት አስከተለ። ሊቢያ በስሜታዊው መሪዋ በሙሐመድ ጋዳፊ [Muammar Kadafi] አማካይነት የነዳጅ ዘይት ኢንዱስትሪዎችዋን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር አደረገችና ወደ አውሮፓና አሜሪካ የሚላከውን የነዳጅ ዘይት መቆጣጠር ጀመረች። ይህ ሁሉ የሚደረገው፥ አሜሪካ እስራኤልን ከመርዳት እንድትታቀብ ለማስገደድ ነበር። የተዘነጋው ነገር ግን፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ስለ እስራኤል መጠበቅ ጉዳይ የሚናገረው ጠቃሚ መልእክት መኖሩን ነው።

## ♦ ለ1973 ጦርነት ዝግጅት

ግጭቱ ከመቀስቀሱ ቀደም ብሎ እስራኤላውያን "ዮም ኪፑር" [Yom Kippur] የተባለውን የማስተሥረያ በዓላቸውን በማክበር ላይ ነበሩ። የሶሪያ ሚግ 21 አውሮፕላኖች የእስራኤልን ሚራጅና ፋንቶም አውሮፕላኖችን ይተናኮሉ

ጀመር። እስራኤል ለዚህ በሰጠችው አፀፋ አንድ አውሮፕላን ሲወድቅባት፥ ሶሪያ አሥራ ሦስት አውሮፕላኖችን አጣች። የሶሪያ ፕሬዚደንት ሐፌዝ አልአሳድ [Hafez Assad] እና የዮርዳኖሱ ንጉሥ ሑሴን በግብፁ ፕሬዝደንት አንዋር ሳዳት ሊቀመንበርነት ስብሰባ በማድረግ ላይ ሳሉ ነበር ይህ ግጭት የተደረገው። በጣም የሚገርመው፥ የዓረቦቹ ስብሰባ ለእስራኤል የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ አለማሳለፉ፥ ነገር ግን የውስጥ ግንኙነታቸውን በማደስ ላይ ማተኮሩ ነበር። እያንዳንዱ መሪ በውስጥ ችግሩ ላይ ከማተኮሩ የተነሣ ስብሰባው ምንም ውሳኔ ሳያሳልፍ ተበተነ።

ጥር 6 ቀን 1973 ዓ.ም. ጦርነቱ ሲቀሰቀስ፥ እስራኤላውያን ቤተ ጸሎታቸው ውስጥ ተሰብስበው የዮም ኪፑርን በዓል ያከብሩ ነበር። መንገዶቹ ሁሉ ጭር ብለዋል። ተጠባባቂ የእስራኤል ጦር ሠራዊት በአስቸኳይ ለግዳጅ እንዲሠማራ ጥሪ ቀረበለት። በሰዓታት ልዩነትም ጦርነት መጀመሩን የሚያስተጋባ የአየር ወረራ አደጋ ፉጨት ተሰማ።

## ♦ የዓረቦች ጊዜያዊ ድል

ግብፅ በስዊዝ ካናል [Suez Canal] ላይ ድልድይ ሠርታ በብዙ ችግር በሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮቹዋንና የጦር መሣሪያ በማሳለፍ የሲናን ባሕረ-ገብ መሬት በቁጥጥሯ ሥር አዋለች። የሶሪያ ታጣቂ ኃይሎች በበኩላቸው ጥቂት የእስራኤል ወሰን ጠባቂ ወታደሮችን በማባረር የጎላንን ተራሮች ተቆጣጠሩ። የ1967ቱ ተኩስ አቁም ስምምነት ተጥሶ ሌላ አውዳሚ ጦርነት ይካሄድ ጀመር። ነገር ግን ይሄኛው የተለየ ነበር። ዓረቦች ጦርነቱን ጀመሩ፤ እስራኤል ደግሞ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት አጸፋውን እየመለሰችና እየታገሰች ሁኔታው እንዲታወቅላት አደረገች። ውጊያው ከወታደራዊ ጥቃት አንጻር ሲገመገም፥ እስራኤል ከፉኛ ተጎድታለች፤ ብዙ ወታደሮችም የጦርነቱ ሰለባ ሆነውባታል።

## ♦ የዓለም ኅብረተሰብ አስተያየት

ጦርነቱ አብዛኛውን ዓለም አስደነቀ። ሩሲያና አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ ጦርነት ማንንም ላለመደገፍ የተስማሙ መስለው ነበር። ዓረቦችም ቢሆኑ ችግራቸውን ከጦርነት ይልቅ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ለመፍታት እንዳሰቡ ፍንጭ ያሳዩበት ጊዜ ሆነ። ዓረቦች እስራኤልን ለማጥፋት እንደማይችሉ ቢገነዘቡም፥ የተወሰነ ግዛት መልሰው ለመውሰድ ፈለጉ። እስራኤል አንዳንድ ጉዳዮችን ለቀቅ እንድታደርግ ለማስገደድም ድል አስፈልጓቸው ነበር። ይህ ዓላማቸው ተሳክቶላቸዋል፤ ጦርነቱ ካስከተለባቸው ኪሳራ ወዲህ የተመሠረተው አዲስ ዓረባዊ ኅብረት፥ እንዲሁም ነዳጅ

ዘይታቸውን እንደ ማስፈራሪያ በማድረግ ያገኙት የኢኮኖሚ ማንሰራራት ለሌላ ዕቅድ አነሣሣቸው። ይህ ዕቅድ መካከለኛ ምሥራቅን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር ማድረግና የዓለምን የኃይል ሚዛን ማዛባት ነበር።

## ♦ የጦርነቱ ጉዳት መጠን

ጦርነቱ በተጀመረ ጥቂት ቀናት ውስጥ ግብፅ አብዛኛውን የሲና ባሕረ-ገብ መሬት በቁጥጥሯ ሥር አደረገች። ሩሲያ በዘመናዊና ረቂቅ ጦር መሣሪያዎች አስታጥቃት ስለነበር፥ ወታደሮቿ በምድር ውጊያ "ሳገር" የተባለውን ተወንጫፊ ሚሳይል በመተኮስ የእስራኤልን ታንኮች በአንድ ምት የማጥፋት አቅም አገኙ። አብዛኛዎቹ መሣሪያዎች በአንድ ሰው ኃይል የሚንቀሳቀሱ ሲሆኑ፥ አዲሱ የሶቪየት ሳም 6 ፀረ አይሮፕላን ሚሳይልም የእስራኤልን አይሮፕላኖች ከጥቅም ውጭ የማድረግ ኃይሉ ፍጹም መሆኑ ተረጋገጠ። አልፎ አልፎ የግብፅን አይሮፕላኖች በስሕተት መምታቱ ባይቀርም፥ እስራኤላውያን በጦርነቱ የደረሰባቸው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አልነበረም። ይህ ጦርነት ከ1967ቱ የተለየ ነበር። እስራኤላውያን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እስከ አፍንጫቸው ታጥቀው የመጡትን ወራሪ ኃይሎች በሁለት ግንባሮች በአንድ ወቅት መመከቱ አድካሚ ፈተና ሆኖባቸው ነበር። ዓረቦች ውጊያ ሲጀመር እንደ ወትሮው የሚሸሹ ሆነው አልተገኙም። ይልቁንም ብቁ ተዋጊነታቸውን አስመሰከሩ።

## ♦ በለስ ለእስራኤል ሲቀና

ጦርነቱ ሲጧጧፍ፥ በሥርዓት የታነፀው የእስራኤል ጦር ቀስ በቀስ ድል ያደርግ ጀመር። በዚሁ መሠረት በቅጽበት ወደ ሶሪያ ክልል ዘልቆ በመግባት ወደ ደማስቆ በጣም ተቃረበ። የምዕራቡን የስዊዝ የባሕር ዳርቻም ከግብፃውያን ጦር አጸዳው። የሦስተኛውን የግብፅ ብርጌድ በመከበብም ከሌላው ወገኑ እንዳይገናኝ አደረገው፤ ይህን ማድረጉም፥ በፍጥነት ወደ ስዊዝ ካናል በመሻገር የሲናይን ባሕረ-ገብ መሬት ተቆጣጥሮ የነበረውን የግብፅ ጦር ለመቁረጥ አቅም አገኘ። ሁኔታው እንዲህ ቢቀጥል ኑሮ እስራኤላውያን በምዕራብ ስዊዝ ካናል ዳርቻ ሚሳይል የተጠመደበትን አካባቢ በቁጥጥራቸው ሥር ያደርጉና ሦስተኛውን የግብፅ ብርጌድ ይደመስሱ ወይም እጁን እንዲሰጥ ማድረግ ይችሉ ነበር።

## ♦ የሩሲያ የተኩስ አቁም ግፊት

ዓረቦች በእስራኤል ላይ ጥቃት መሰንዘሩ የማይሆንላቸው መሆኑን ሲያረጋግጡ፥ ለሕልውናቸው በመከላከሉ ላይ ብቻ አተኮሩ። ይህን

ያስተዋለችው ሩሲያ ከገቡበት ችግር ሊታወጣቸው በማሰብ፥ ተኩስ እንዲቆም ተጽዕኖ ማድረግ ጀመረች። በመጨረሻ ጦርነቱ ሲቆም ከስዊዝ ካናል በስተምሥራቅ የነበረው 20 ሺህ የግብፅ ጦር በእስራኤል ሠራዊት ተከብቦ ወደ አገሩ የሚመለስበት መንገድ በማጣት ጭንቅ ውስጥ ነበር። የተኩስ አቁሙ ስምምነት ጉዳይ በተነሣ ጊዜ፥ በጥቂት ቀናት ውስጥ በስዊዝ ካናል ግንባር አስተማማኝና ዘላቂ ድል እንደሚያገኙ እርግጠኛ የነበሩት የእስራኤል የጦር ባለሥልጣኖች ስምምነቱን እጅግ ተቃወሙት።

ይህ ሲሆን ሳለ ሩሲያና አሜሪካ ለየወዳጆቻቸው የጦር መሣሪያና ሌላም እርዳታ ያቀርቡላቸው ነበር። ወዲያው ጦርነቱ እንደተጀመረ አካባቢ፥ ሩሲያ ለሶሪያና ለግብፅ ቀደም ሲል በጦርነቱ የወደመባቸውን የጦር መሣሪያ ትተካ ላቸው ጀመር። አሜሪካም ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰድ የእስራኤልን ጦር በተጨማሪ መሣሪያ አስታጠቀች። በጦርነቱ ማብቂያ ላይ በሁለቱም በኩል ያሉት ተፋላሚዎች የወደመባቸውን መሣሪያ ተክተው ነበር። ይህ ሁኔታ ነበር ለክልሉ እውነተኛ ሰላም ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት አድካሚ ያደረገው። በጥቅሉ ስንመለከተው ግን፥ መካከለኛው ምሥራቅ በሩሲያና አሜሪካ ቁጥጥር ሥር ውሏል። በ1970ዎቹ ዓመታት አሜሪካ ብቸኛዋ የእስራኤል ደጋፊ ስትሆን፥ ሩሲያ ደግሞ የዓረቡን ዓለም ታደራጅ ነበር። የቀረው ዓለም ግን፥ ከዓረቦች ጥላቻ እንዳይደርስበት ስለፈራ፥ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አላሳየም። አክራሪ ፍልስጥኤማውያን ደግሞ፥ ፍልስጥኤም ውስጥ አገር እስኪሰጣቸው ሁከት መፍጠሩንና ደም ማፍሰሱን ገፉበት።

## ♦ የካምፕ ዴቪድ [Camp David] ስምምነት

ከ1973 ዓ.ም. ጦርነት ወዲህ የእስራኤል ታሪክ የታወከ ነበር። በአገርዋ ያሉት አንዳንድ ተቃዋሚ ቡድኖች ምንም እንኳን ብዙ ድጋፍ ባይኖራቸው፥ የተወሰነ የፖለቲካ መሥመር እንዳትከተል እንቅፋት እየሆኑባት ናቸው። ከ1973 የዮም ኪፑር ጦርነት በኋላ የግብፅና የእስራኤልን ፍጥጫ ለማርገብ በመካከላቸው የሠመረ ግንኙነት ተፈጠረ። የግብፅ ፕሬዚደንት አንዋር ሳዳትም ከእስራኤል ጋር የሰላም ውል ለመፈራረም ዝግጁ ሆኑ። ታሪካዊ በሆነው ጉብኝታቸውም ለኢየሩሳሌም ፓርላማ ንግግር ከማድረጋቸው ባሻገር ከእስራኤላዊው አቻቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መናከም ቤጊን [Menachim Begin] ጋርም ተገናኝተው ተወያዩ። ይህን ውጤት መነሻ በማድረግም የአሜሪካው ፕሬዚደንት ጂሚ ካርተር [Jimmy Carter] ከቤጊንና አንዋር ሳዳት ጋር በመስከረም ወር 1978 በአሜሪካ ካምፕ ዴቪድ ተገናኙ። የግንኙነታቸው ውጤትም "የካምፕ ዴቪድ ስምምነት" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ ዓላማውም በግብፅና በእስራኤል፥ በአጠቃላይም በመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ነበር።

የስምምነቱ መጀመሪያ እቅድ ግብ ቢመታም፥ ሁለተኛው ፍሬ ቢስ ሆኖአል። ግብፅና እስራኤል ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ላይ በመጋቢት 1979 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የሰላም ውል በመፈራረም የዲፕሎማቲክ ተወካዮቻቸውን ተለዋወጡ። በውሉም መሠረት እስራኤል በ1973 ከያዘችውና የግብፅ ግዛት ከሆነው ሲና ባሕረ-ገብ መሬት የተወሰነውን ክፍል ትታ ለመውጣት ተስማማች።

ግብፅ፥ እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ ያላትን ሕልውና ከተቀበለች ወዲህ ያካባቢው ወታደራዊ ሁኔታ የተለየ ሆነ። ይህም በመሆኑ ሶሪያና ዮርዳኖስ ራሳቸውን ችለው እስራኤልን ለመውረር የማይቻላቸው ሆነ።

## ♦ የሊባኖስ መወረር

ሁኔታው እንዲህ ቢሆንም፥ ውጥረቱ እንደቀጠለ ሆኖ፥ የፍልስጥኤም ነጻ አውጪ ድርጅት [Palestine Liberation Organization (PLO)] ከ1973ቱ ጦርነት ወዲህ በእስራኤል ላይ የሚሰነዝረውን ጥቃት አባባሰው። በ1964 ዓ.ም. የተመሠረተው ይህ ድርጅት ዓላማው ፍልስጥኤም ውስጥ የዓረብ መንግሥት ለመመሥረት ሲሆን፥ በየጊዜው ከወደ ሊባኖስ በሚሰነዝረው ጥቃት ለእስራኤል ከፍተኛ የራስ ምታት ሆነባት። ስለዚህም እስራኤል በ1978 ዓ.ም. በደቡብ ሊባኖስ ላይ ካደረገችው ወረራ ሌላ እንደገና በ1982 ዓ.ም. ድጋሚ ጥቃት ሰነዘረች። በዚህም ወረራ፥ በስተሰሜን ጥቃት ይፈጽምባት የነበረውን የፍልስጥኤም ነጻ አውጪ ጦር አስወገደች፤ ካምፑንም ደምስሳ ተቆጣጠረች።

በሊባኖስ የተካሄደውን ጦርነት በጊዜው የዘገቡ አንዳንድ ዜና አቅራቢዎች በእስራኤል ላይ ያላቸውን ጥላቻ አሳይተዋል። የፍልስጥኤም ነጻ አውጪ ድርጅት የሚያወጣቸውን ዜናዎች እየተቀባበሉም አናፈሱ። ብዙውን ጊዜ ድርጅቱ ለሚያደርሰው የነፍስም ሆነ የንብረት ጥፋት ተወቃሽዋ እስራኤል ነበረች። አገሪቱ ሊባኖስን ለመያዝ ከፍተኛ የሕይወትና የገንዘብ መሥዋዕትነት ብትከፍልም፥ የያዘችውን መሬት በ1985 ለቃ ወጣች። ሽብር ፈጣሪዎችን በጦር ኃይል መግታትና በቁጥጥር ሥር ማዋሉ አስቸጋሪ እንደሆነም በሚገባ ተረዳች።

በእስራኤል በየጊዜው ድንገተኛ ጥቃቶች መድረሳቸው የተለመደ ነገር ሆነ። በጋዛ ሰርጥና በዮርዳኖስ ወንዝ የምዕራብ ዳርቻ፥ በእስራኤል ላይ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ እየተካሄደ በእስራኤል ወታደሮችና በተቃዋሚ ሰልፈኞች መካከል ግጭት በመፈጠሩ በሁለቱም ወገኖች ለደረሰው የበርካታ ሰዎች ሞት ምክንያት ሆኗል። ይህ ግጭት በ1990ዎቹ ዓመታትም ቀጠለ።

በነዚህ ሁኔታዎችና ግጭቶች ግፊት ነው፥ እስራኤል በወታደራዊ ኃይልና በዘመናዊ ጦር መሣሪያ ይበልጥ የተደራጀችው። የ1990ዎቹ ዓመታት ሲጀመሩ በየትኛውም አቅጣጫ ያለውን ጠላት ለመምታት ብቃት የሚሰጣት፥

የኑክሊየር ባለቤት ሆነች። ታዲያ ይህ መሣሪያዋ በየጊዜው ጥቃት ከሚሰነዝሩባት ተቃዋሚዎቿ ይታደጋት ይሆን? በመካከለኛው ምሥራቅ ድንገት ጦርነት ቢጀመር፥ ፍልሚያው ወዲያውኑ ወደ ኬሚካል ወይም ኑክሊየር ጦርነት እንደሚሸጋገር የታወቀ ነው። ከዚህም የተነሣ እስራኤላውያን ብዙ የሚያሠጋና የሚያስፈራ ችግር አለባቸው።

## ♦ ኢራን- አዲሷ እስላማዊት ሪፐብሊክ

እስራኤል ውስጥ እነዚህ በጣም ጠቃሚ ጉዳዮች በመከናወን ላይ እያሉ፥ በኢራንና በኢራቅ መካከል ደግሞ ግጭት ተፈጠረ። በ1979 በኢራን ውስጥ አብዮት ተካሂዶ አያቶላ ሆሚኒ [Ayatollah Khomeini] ዘውዳዊ አገዛዙን አስወግደው አዲስ የእስላም ሪፐብሊክ መሠረቱ። የእስላም ሕግ ለኢራናውያን ሃይማኖት መሠረት ሆኖ፥ ሆሚኒም የእስላማዊቷ ሪፐብሊክ የመጀመሪያው ገዥ ሆኑ።

ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግም በመቶ የሚቆጠሩ ተቃዋሚዎቻቸውን ይገድሉ ጀመር። እስከ ዕለተ ሞታቸው ማለትም እስከ 1989 ድረስ አገሪቱ በእርሳቸው ቁጥጥር ሥር ነበረች። አገሪቱ በመካከለኛው ምሥራቅና በአውሮፓ የነበሩ ሽብር ፈጣሪዎችን መርዳቷንም አላቋረጠችም።

## ♦ የሳዳም ሑሴን በኢራቅ ውስጥ ሥልጣን መያዝ

ኢራቅና ኢራን በመካከላቸው በተፈጠረው የድንበር ይገባኛል ጥያቄ ምክንያት በ1980 ውጊያ ጀመሩ። ጦርነቱ ለስምንት ዓመታት ቆይቶ በነሐሴ ወር በ1988 በተደረገው ስምምነት ለማቆም ተሞከረ። በውጊያው ከሁለቱም በኩል በሚሊዮን የሚቆጠር ሕይወት ቢጠፋም አሸናፊው አልለየም ነበር። ከሆሚኒ ሞት በኋላ የሥልጣን ሽኩቻ ሲያደርጉ የቆዩት ሐሺም ራፋሳንጃኒ [Hashemi Rafsanjani] በ1989 አዲሱ የኢራን ፕሬዚደንት ሆኑ። ጦርነቱ በነሐሴ ወር 1990 ዓ.ም. እሥረኞችን በመለዋወጥ አቆመ።

ውጊያው የተካሄደው በጥንታዊቷ ባቢሎን፥ ማለት በአሁኗ ኢራቅ በመሆኑ የተነሣ፥ የሀገሪቱ መሪ ሳዳም ሑሴን ራሳቸውን እንደ ናቡከደናፆር በመመልከት አዲስ የባቢሎን መንግሥት ለመመሥረት አቀዱ። ተሰሚነትና ተደማጭነት ለማግኘት የወሰዱት የመጀመሪያ እርምጃ ግን አልተሳካላቸውም። ፍላጎታቸው ጠንካራ መንግሥት በመመሥረት ባሕረ-ሰላጤውን በሙሉ ለመቆጣጠርና የነዳጁን ክምችት በእጃቸው ለማድረግ ነበር። ይህ ተሳክቶላቸው ቢሆን ኖሮ ምናልባት እስራኤልን ለመደምሰስ ይችሉ ነበር።

## ♦ ኢራቅ ኩዌትን ወረረች

በነሐሴ 1990 ዓ.ም. የኢራቅ ወታደሮች ትንሿን፥ ግን በዘይት ሀብት የበለጸገች አገር ኩዌትን ወረሩ። ወረራው በታቀደው መሠረት ተሳክቶ ቢሆን፥ ኢራቅ የመካከለኛው ምሥራቅን የነዳጅ ዘይት እንድትቆጣጠር ይረዳት ነበር። ወታደሮቿ በጀመሩት ፍጥነት ወደ ሳውዲ ዓረቢያ ተንቀሳቅሰው ቢሆን ኖሮ፥ ሳዳም ሑሴን ከዓለም የነዳጅ ክምችት ከመቶ አምሳውን እጅ ለመቆጣጠር ይችሉ ነበር። ይህን የተረዱት አሜሪካና ሌሎች አገሮች የጦር ኃይላቸውን በሦስት ቀን ውስጥ ወደ ሳውዲ ዓረቢያ በመላክ ወደ ምዕራቡ ዓለም የሚጓጓዘው ነዳጅ እንዳይቋረጥ አደረጉ።

ይህን የመሰለው ወታደራዊ ኃይል በመካከለኛው ምሥራቅ መከሠት ከትንቢት አንጻር ትልቅ ክንውን ነበር። ከዚህ አኳያ የኮሪያ፥ የቬትናምና የአውሮፓ ጦርነቶች የመካከለኛው ምሥራቅን ያህል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም። ስለ መጨረሻው ዘመን የተነገሩት ትንቢቶች ለኢኮኖሚ፥ ለፖለቲካና ለወታደራዊ ኃይል አሰላለፍ መካከለኛው ምሥራቅን ነው እንደ ማዕከል የሚያደርጉት። ለበርካታ ዓመታት ከዓለም የነዳጅ ዘይት ፍጆታ 64 በመቶው የሚገኘው ከመካከለኛው ምሥራቅ መሆኑ ሲገለጥ ቆይቷል። ከዚህ ውጪ አካባቢው በፖለቲካና በገንዘብ ነክ ጉዳዮች የዓለምን ኅብረተሰብ ትኩረት የመሳብ አቅሙም ጉልበቱም አይኖራቸውም ነበር። አብዛኛው የነዳጅ ሀብት በመካከለኛው ምሥራቅ መከማቸቱ እግዚአብሔር መካከለኛው ምሥራቅን የመጨረሻው ዘመን ድርጊቶች የሚከሠቱበት ቦታ እንዲሆን ማቀዱ ይሆን? በባሕረ-ሰላጤው የሚካሄደው ጦርነት የትንቢቱ ዋና ክፍል ባይሆንም፥ ከመጨረሻው ትንቢታዊ ክንውን ክፍልና እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከሚከናወኑ ድርጊቶች (በቅድስቲቱ እስራኤል የሚካሄዱትን ዋና ዋና ጦርነቶች ጨምሮ) ጋር የሚቃረን አይደለም።

## ♦ ተአምራዊው የእስራኤል መትረፍ

በመካከለኛው ምሥራቅ መድረክ የሚካሄዱት ሁኔታዎች ከእስራኤላውያን ሕልውናና ጥንካሬ ጋር የተያያዙ ናቸው። ስለ እስራኤላውያን እንደገና መሰባሰብና ለሕልውናቸው መታገል፤ የተሰጡ ተስፋዎችና ትንቢቶች በዚህ መጽሐፍ በ5ኛው ምዕራፍ በሰፊው ተዘርዝረዋል። አንድ ነገር ግልጥ ነው፤ ይኸውም የመጨረሻዎቹ አሥርተ-ዓመታት የእስራኤል ሁኔታ፥ ባለፈ ታሪኳ ላይ በጥልቅ የተመሠረተ ቢሆንም፥ አስገራሚና ተአምራዊ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።

የብሉይ ኪዳን ታሪክ እድገት በአብርሃም ላይ በማተኮር ትውልዶቹ በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች መሆናቸውን ያመለክታል። የተስፋይቱ

ምድር ወራሾች የነበሩና ለዘላለም የሚነግሠው የእግዚአብሔር ሕዝቦች ቤዛ የመሚሑ መገኛ ናቸው።

ብሉይ ኪዳን የአሕዛብ ዘመን በመባል ስለሚታወቀው ክፍለ-ጊዜ የተሰጡ ትንቢቶችንም ያካትታል። አዲስ ኪዳንም ይህንኑ ትንቢት በማረጋገጥ ከማብራራቱም በላይ፥ የአሕዛብ ዘመን ሲባል አይሁድ ያልሆኑ ሕዝቦች በታሪክ ውስጥ ስለሚኖራቸው የበላይነት ብቻ ሳይሆን፥ የቤተ ክርስቲያንንም መመሥረት ጭምር እንደሚያካትት ይገልጣል። በዚህ ዘመን አይሁድም ሆኑ ሌሎች ወገኖች ተስፋ በተገባለት መሚሕ አማካይነት በነጻ የእግዚአብሔር በረከት ተካፋዮች ይሆናሉ።

## ♦ ማስጠንቀቂያ

በመካከለኛው ምሥራቅ የእስራኤል ማቆጥቆጥና ዓለም አቀፋዊ ኃያል ለመሆን የምታደርገው ታጋድሎ፥ የአሕዛብ ዘመን ሊያበቃ ጥቂት ዓመታት ብቻ እንደቀሩት የሚያመለክት ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይችላል። አውሮፓና የምዕራቡ ዓለም ላለፉት ሺህ ዓመታት በታሪክ የበላይነታቸውን ማሳወቃቸው ሐቅ ቢሆንም፥ ይህ ለእስራኤል የተገባላትን ቃል ኪዳን፥ እንዲሁም ያሠቃዩዋትን አሕዛብ አንድ ቀን እግዚአብሔር እንደሚበቀልላት የተሰጣትን ተስፋ አያስቀረውም። ነቢዩ ኤርምያስ የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል:-

> “ስለዚህ የሚውጡህ ሁሉ ይዋጣሉ፥ ጠላቶችህም ሁሉ ይማረካሉ፥ የዘረፉህም ይዘረፋሉ፥ የበዘበዙህንም ሁሉ ለመበዝበዝ አሳልፌ እሰጣለሁ:- እኔ ጤናህን እመልሳለሁ፤ ቁስልህንም እፈውሳለሁ። ይላል እግዚአብሔር ማንም የማይሻት የተጣለች ጽዮን ብለው ጠርተውሻልና” (ኤር. 30፡16-17)።

በአይሁዶችና በክርስቲያኖች ላይ ስደቱ ተጠናክሮ በነበረበት ዘመን እንኳን፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ለእስራኤል የተነገሩት የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ሁሉ ወደፊት እንደሚፈጸሙ ሲናገር፥ “እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን? እላለሁ፥ አይደለም” ብሏል (ሮሜ 11፡1)። ሐዋርያው በመቀጠልም፥ የቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ ዘመን መመሥረትና ፍሬያማ መሆን ምሥጢሩ እስከ አዲስ ኪዳን ዘመን ድረስ እንዳልተገለጠ ካስረዳ በኋላ፥ ለእስራኤል የተሰጣት የተስፋ ቃል መፈጸሙ ስለማይቀር አንባቢያን በዚህ ጉዳይ አላዋቂ እንዳይሆኑ አስጠንቅቋል። ከእስራኤል የደኅንነት ቀን በፊት የሚያስጨንቅ የመከራ ቀን ይሆናል- ታላቅ የመከራ ቀን። የመጨረሻ ደኅንነታቸው ግን፥ “ከጽዮን አዳኝ ለእስራኤል ይመጣል” የተባለው ተስፋ በሚፈጸምበት ጊዜ ነው (ሮሜ 11፡26)።

## ♦ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነቱ እንደገና ተረጋገጠ

የእስራኤል የወደፊት ሁኔታ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን በሰፊው ተገልጧል። ዕጣዋንም አስመልክቶ የተነገረው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት አረጋግጧል። እስራኤል በብዙ መከራ ውስጥ ብታልፍም እና የመዳን ተስፋዋ አነስተኛ ቢሆንም ሕልውናዋ እንደተጠበቀ ነው። ሮማውያን ወድቀዋል፤ አይሁዳውያንን ሲያሳድድ የነበረው የሩሲያ ዛር ወይም አፄ የሌሎች ሰለባ ሆኖአል። የጀርመኑ ራይክ አምባገነን መንግሥት ፈራርሷል። እስራኤል ግን በተአምራዊ ሁኔታ ወደ ርስቷ ተመልሳለች። እነዚህ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ያለፉ አይሁዳውያን የወደፊት ዕጣቸው ምን ይሆን? ዓረቦች ነዳጅ ዘይትን እንደ ማስፈራሪያ መጠቀማቸውስ በእስራኤል ላይ የሚያመጣባት ጉዳት ምን ይሆን? ይህ ሁኔታ ዓለም አቀፉን ፖሊሲ አናግቶ በቅዱሳት መጻሕፍት በተተነበየው መሠረት ዓለምን በመጨረሻው ቀን የሚቆጣጠረው “የሜዲትራኒያን ክልል ኅብረት” እንዲመሠረት ያደርግ ይሆን? ፍጻሜውስ በከፋ ሁኔታ ወደ አሕዛብ ዘመን መጨረሻ ያመራ ይሆን? መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች ብቻ ናቸው ለነዚህ እጅግ አስፈላጊ ጥያቄዎች መልስ ያላቸው።

በመካከለኛው ምሥራቅ በመካሄድ ላይ ያለው ጥቃቅን ጉዳይ ሁሉ፣ የትንቢቱ ክፍል (አካል) ነው ባይባልም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጦርነት ስለሚኖረው ድርሻ እንሥቶ፣ “ጦርነትም የጦርነትም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፣ አትደንግጡ፣ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው” በማለት የተናገረው በትክክል ተፈጽሞአል (ማቴ. 24፡6)። በሌላው የዓለም ክፍል የሚካሄዱት ጦርነቶች ከትንቢታዊ ቃል አኳያ እምብዛም ግምት የማይሰጣቸው ቢሆኑም፣ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚነሡት ውጥረቶች ግን፣ በሁሉም ዘንድ ያለውን ሁኔታ የሚያባብሱና ፍጻሜ ወደሆነው የአርማጌዶን ጦርነት እና ወደ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚያመሩ ናቸው።

# 4

# ነዳጅ ዘይት በማስፈራሪያነት

## ♦ አዲሱ የዓረብ ኅብረት

ከ1967 አስከፊ ጦርነት በኋላ የእስራኤል፥ የግብፅና የሶሪያ ጦር ኃይል በአንጻራዊ መልኩ ማየል የጠቅላላው ችግር አንድ ገጽታ መሆኑ ግልፕ ሆነ። ምንም እንኳን ጦርነቱ በግብፅና በሶሪያ ድል አድራጊነት ባይደመደምና የዓረብ አገሮች በቂ መሣሪያና የሰው ኃይል ቢኖራቸው፥ አንድ ቀን አነስተኛ የሰው ኃይል ያላት እስራኤልን እንዳልነበረች ለማድረግ ወታደራዊ ብቃት እንዳላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ የሆነበት ወቅት ነበር። ሌላው የዓለም ክፍል፥ በተለይም አሜሪካና አውሮፓ፥ እስራኤል በጦርነት ስትወድም ዝም ብለው ይመለከቷት ይሆን? አሜሪካም ሆነች ሩሲያ በአካባቢው ጣልቃ መግባት የማይችሉበትን እና የዓረቡ ዓለም ከሩሲያ እርዳታ ነጻ የሚሆንበትን አዲስ ስልት ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ነበር። ይህ ስልት ቢቻል እስራኤልን ከአጋሮቿ፥ በተለይም ከአሜሪካና ከምዕራብ አውሮፓ ለመነጠል የሚሞክር መሆን ነበረበት።

የ1973 ዓ.ም. ጦርነት ዋና ውጤት፥ ቀደም ብሎ ሊታሰብ ያልተቻለውን አዲስ የዓረብ አገሮች መቀራረብና አንድነት መፍጠሩ ነበር። ምንም እንኳን የዓረቡ አንድነት በከፊል በወታደራዊ ግጭት ቢገለጥ፥ አንድነታቸውና ኃይላቸው እየተጠናከረ የመጣው፥ የዓለምን የነዳጅ ዘይት ሀብት ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ነበር። የዓረቡ ዓለም ለአዲሱ አንድነት መግለጫ በኅዳር ወር 1973 የነዳጅ ዘይት ምርቱን ከቀድሞው ማሳነስና እስራኤልን በሚደግፉ እንደ አሜሪካና ኔዘርላንድስ ባሉ አገሮች ላይ የነዳጅ ዘይት ማዕቀብ መጣል ነበር። ለቤታቸው፥ ለኢንዱስትሪና ለጦር ኃይል የሚውል የነዳጅ ዘይት ለሌላቸው አገሮች የነዳጅ ዘይት አቅርቦት እንዲቀነስ የወጣው አሳብ በመላው ዓለም የድንጋጤ ማዕበል አስነሥቶ ነበር። የዓለምን ኢኮኖሚ የሚያናውጥ አዲስ የኢኮኖሚ ጦርነት ተቀሰቀሰ። መካከለኛው ምሥራቅም ከብዙ ምዕተ ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም ኅብረተሰብ ዋና ትኩረት ሆነች ።

## ♦ የዓለም የኃይል ምንጭ ቀውስ

የዓለም ነዳጅ ዘይት ፍጆታ እጅጉን እየጨመረ መምጣት በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ከተስተዋለ ዓመታት አልፈዋል። ሊያስከትል

የሚችለው ቀውስ እንዳይከሠት የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ግን፥ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ በማለት በዝምታ ታልፎአል። ለፋብሪካ (ኢንዱስትሪ) ፍጆታ ከከሰል ይልቅ፥ የነዳጅ ዘይት ርካሽና ለአሠራርም ምቹ ሆኖ ተገኝቷል። በአሜሪካ፥ በተለይ በምሥራቁ ክፍል፥ አብዛኛው ኤሌትሪክ የማመንጨት አቅሟ የተመሠረተው በነዳጅ ዘይት ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የሥነ አካባቢ አጥኚዎች ከሰል ለኢንዱስትሪዎች ሥራ ጠቃሚነቱ ባይካድም፥ ጪሱ አየር በካይ መሆኑን ያስገነዘባሉ። እየጨመረ የመጣው የአውቶሞቢሎች አገልግሎት፥ በተለይም በአሜሪካ የነዳጅ ዘይት ፍጆታ መጨመር የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዲህ ከሆነ ታዲያ የነዳጅ ዘይት አቅርቦት መቀነስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሽከርካሪዎችን አገልግሎትና መፈብረኪያዎችን ማወኩ ግልጥ ነው። ከስድስት አንዱ ሠራተኛ በተሽከርካሪዎች መፈብረኪያ ውስጥ በተሠማራበት አሜሪካ፥ የቤንዚን አቅርቦት መቀነስ የአገሪቱን የኑሮ ትልምና የምጣኔ ሀብት ልማት ሥጋት ላይ ጥሎታል። አውሮፓና ጃፓን ደግሞ፥ ከውጭ በሚመጣ ነዳጅ ዘይት ይበልጥ የሚጠቀሙ በመሆናቸው የነዳጅ ዘይት አቅርቦት መቀነስ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ታይቶ የማይታወቅ ሥጋትና ሽብር ፈጠረባቸው። በነዚህ ሁኔታዎች ሳቢያ አዲስ ዓለም አቀፋዊ የኃይል አሰላለፍ እየተካሄደ በመሆኑ ስለ ወደፊቱ ማንም በትክክል ለመናገር አይችልም።

## ♦ የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት ዋነኛ ሚና

የዓረቡ ዓለም የተሻሻለውን የነዳጅ ዘይት ክምችት መሠረት በማድረግ ምርትን ለመቆጣጠርና በዚያም በመጠቀም ሌሎቹን አገሮች ሊያንበረክካቸው ችሎ ነበር። የመካከለኛው ምሥራቅና የታወቀው የሰሜን አፍሪካ የነዳጅ ዘይት ክምችት ሁለት ሦስተኛ እጅ በነዚሁ አገሮች በረሃማ ክፍል ይገኛል።

ከዚህም ባሻገር እነዚህ አገሮች ነዳጅ ዘይት ለማውጣትና ለማጣራት የሚያስፈልጓቸውን መሣሪያዎች ከዋና ዋናዎቹ ምዕራባውያን አገሮች በመውሰድ እጃቸው አስገብተዋል። በየአገሮቹ ያሉ ነዳጅ ማውጫ ድርጅቶችም በተፋጠነ እርምጃ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ውለዋል። አንዳንድ የዓረብ አገር መሪዎች ከዚህም አልፈው፥ በመላው ዓለም ያሉ እጅግ ዘመናዊ የነዳጅ ዘይት ማምረቻ መሣሪያዎችንና ተቋማትን ተቆጣጥረዋል። ኃያላን የምዕራብ ባለ ኢንዱስትሪ አገሮች የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ አቅርቦት ቢቋረጥባቸው ኑሮ፥ ለኢንዱስትሪ ውጤቶቻቸው፥ ለትራንስፖርት አገልግሎት፥ ለኤሌክትሪክና ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ኃይል አያገኙም ነበር። በዓለም ከሚመረተው ነዳጅ ዘይት አንድ ሦስተኛውን የምትጠቀምበት አሜሪካ ናት። ይህ እየታወቀ ግን የዓረቦችን ዛቻ ለመቋቋም የወሰደችው እርምጃ አልነበረም። የ1973ቱን የነዳጅ ዘይት ማዕቀብ ለመቋቋም የሞከረችው፥ በተለያየ ዘዴና

ከኢራን የምታስመጣውን ነዳጅ ዘይት መጠን ከፍ በማድረግ ነበር። ይህ ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂ መፍትሔ ሊሆናት አልቻለም። ኢራን ዓረባዊት ባትሆንም እስላማዊት አገር ስለሆነች ከጎረቤቶችዋ ጋር ኅብረት ፈጠረች።

## ♦ የ1973ቱ ማዕቀብ

የ1973ቱ ቀውስ ዛሬ ታሪክ ቢሆንም፥ ጥሎት ያለፈው ጠባሳ ግን፥ የ1990 ዎቹ ዋና ዋና የዓለም ችግሮች መንሥኤ ሆኖአል። የዓለምን ነዳጅ ዘይት ምርት ለመቆጣጠር በሚደረገው ፍልሚያ፥ የዓረብ አገሮች የመጀመሪያው እርምጃ የምርቱን መጠንና ለመላው ዓለም የሚደርሰውን ስርጭት መወሰን ነበር። እስራኤል ከዚህ ቀደም በጦርነቱ ከያዘቻቸው መሬቶች ጓዟን ጠቅላ እንድትወጣ ማድረግ፥ ካልሆነም ኢየሩሳሌምን ማስመለስ፥ ይህ አልሆን ካላቸው ደግሞ፥ ትንሽም ግዛት ብትሆን ከኢየሩሳሌም ቆርሶ መውሰድ ነበር የዓረቦች ዓላማ። በሳውዲ ዓረቢያው ንጉሥ ፋይሳል [King Faisal] መሪነት ዓረቦች ለዓለም፥ በተለይም ለአሜሪካና ለአንዳንድ አገሮች በሚቀርበው ነዳጅ ዘይት ላይ ማዕቀብ ለማድረግ ተስማሙ። በዚህ ገደብ ሳቢያ የነዳጅ ዘይት ዋጋ እየናረ በመምጣቱ ሁኔታው እጅግ አስደንጋጭ ሆኖ ነበር።

ባጭር ጊዜው ጦርነት እንደታየው፥ የዓረቡ ነዳጅ ዘይት ቀውስ ከአሜሪካና ከሩሲያ ይልቅ አውሮፓን፥ ጃፓንንና ጥቂት በኢንዱስትሪ በመበልጸግ ላይ ያሉ አገሮችን ተጠቂ አድርጎአቸዋል። ይህ እስከ 1990ዎቹ ድረስ የታየ ሐቅ ነው። ተጽዕኖው በአውሮፓ የታወቀው ለሙቀትና ለአውቶሞቢሎች የሚውለው ፍጆታ ዝቅ ማለት ሲጀምር ነው። የነዳጅ ዘይት ዋጋ ሲያሻቅብ የሌሎች ዕቃዎች ዋጋም ይገር ጀመር።

ጃፓን በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለነዳጅ ዘይት መግዣ እንድትመድብ በመገደድዋ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ውድቀትና የዋጋ ግሽበት አስከትሎባት ነበር። በአንድ ዓመት ውስጥ ኢጣሊያን፥ ፈረንሳይ፥ ቤልጂግንና ታላቂዋ ብሪታንያን ጨምሮ በብዙ አገሮች የዋጋ ግሽበቱ እጥፍ ሆኖ ነበር። ታላቂ ብሪታንያ ከ1930ዎቹ ወዲህ ይህን የመሰለ የከፋ የኢኮኖሚ ውድቀት ገጥሟት አያውቅም፤ በሰሜን ባሕር አካባቢ ያለ የነዳጅ ምርቷ የኢኮኖሚዋን ሰቆቃ በመጠኑም ቢሆን እስካቃለለላት ድረስ ከፍተኛ ችግር ማጥ ውስጥ ነበረች።

የባሕረ-ሰላጤው የነዳጅ ድፍድፍ ዋጋ ከ1973-74ቱ ቀውስ ወዲህ እንኳን አልቀነሰም። የነዳጅ ዘይት ዋጋ እየጨመረ መሄድ የምዕራቡ ዓለም ኢኮኖሚ እንዲዋዥቅ አደረገ። እንዲሁም በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ አኳኋን የገንዘብ ዝውውርን አስከተለ። በአጋጣሚው ጥቂት የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በከፍተኛ ፍጥነት ሀብት ያካብቱ ጀመር። ይሁን እንጂ፥ ትልቁ ሀብት

በወርቅ ወይም በብር የሚገመት ብቻ ሳይሆን፥ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መልኩ የዓለምን ገጽ መለወጡ ነበር።

## ♦ አሜሪካ ነዳጅ ዘይት የማምረት አቅሟና ዕቀባውን ብቻዋን መወጣቷ

ከ1973ቱ የነዳጅ ዘይት ቀውስ ወዲህ መላው ዓለም የነዳጅ ዘይት ሀብት ፍለጋውን ለማጠናከርና ከቀድሞው ይበልጥ ለማምረት ወሰነ። የነዳጅ ዘይት ዋጋ መጨመር፥ በአሁኑ ጊዜ ለነዳጅ ዘይት ፍለጋና ምርት የሚወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም እየቀጠለ መሄዱን ጠቃሚ አድርጎታል። ነገር ግን ፍለጋውና የማምረቱ ትኩረት ከአሜሪካ ፖለቲከኞች የኃይል ምንጭ ፖሊሲ ጋር የማይስማማና እጅግ አከራካሪ በመሆኑ ተደናቀፈ። አሜሪካ ከነዳጅ ዘይት ላኪ አገሮች እጅ ስላልወጣች በነዳጅ ፍላጎት ራስን መቻል የሚለው መርሕ የፖለቲካ መፈክር ብቻ መሰለ።

የ1970 ዎቹ የነዳጅ ዘይት ዋጋ መጨመር በአሜሪካ የነበረውን ነዳጅ ዘይት የማውጣት ፍላጎት እጅግ ከፍ አድርጎት ነበር። ያም ሆኖ ጥረቱ፥ ፕሩድሆ [Prudhoe] (በአላስካ [Alaska]) በሚባለው የባሕር ወሽመጥ ከተገኘው ነዳጅ ጋር በአንድነት ታስቦ ከ1979-1985 ዓ.ም. የነበረውን የአገሪቱን የነዳጅ ምርት በአራት ከመቶ (4%) ብቻ ነበር ከፍ ያደረገው። ያም ብዙ ሳይቆይ ያሽቆለቁል ጀመር። በ1985 ዓ.ም. ከውጭ ያስመጣችው ነዳጅ ከሚያስፈልጋት ከሠላሳ በመቶ (30%) ያነሰ ሲሆን፥ በ1990 ደግሞ ከሚያስፈልጋት ግማሽ ያህሉን ታስመጣ ጀመር።

በአሜሪካ የነዳጅ ዘይት ፍጆታና በማምረት ዓቅሟ መካከል ያለው ልዩነት ከ1985-1990 ባሉት ዓመታት እየሰፋና እያደገ መጣ። ይህ ደግሞ አገሪቱ ከዓለም ከፍተኛ ነዳጅ አምራቾች ጎራ ልትመደብ አለመቻሏን አሳወቀ። ከዘመመ ችግሯ ለመቅናትም፥ በፕሩድሆ የባሕር ወሽመጥ ካላት ነዳጅ በእጅጉ የሚልቁ ክምችቶች የሚያስፈልጓት መሆኑ ግልጥ ሆነ።

ዓረቦች ማዕቀብ ባደረጉበት ወቅት፥ አሜሪካ ከሌሎች ነዳጅ አስመጪ አገሮች ይልቅ በራስ የመተማመን ብቃትዋን ከፍ ለመድረግ በሚያስችላት ሁኔታ ላይ ያለች መስላ ነበር። ግን፥ ቆራጥና ወሳኝ የኃይል አጠቃቀም ፕሮግራም አውጥቶ መግፋቱ አልተቻላትም። ከውጭ በሚመጣ ነዳጅ መተማመንን ማቋረጡ ቀላል አልነበረም። ኃይል ካልተቆጠበና የሚተካ አማራጭ ከሌለ ምርምር (ፍለጋና) ልማት ብቻውን ችግሩን የሚፈታው አይሆንም። ለመሆኑ አሜሪካ ከውጭ በምታስገባው ነዳጅ ዘይት ተስፋ ማድረግዋን የመተው ፈቃድ አላት? ለምንድነው ልትቆጣጠረው በማትችለው ዓለም አቀፍ ሁኔታ ኢኮኖሚዋ እንዲበላሽ የምትፈቅደው?

## ♦ እስራኤል ማንን ትመን?

ከእስራኤል አንጻር ስንገመግመው ሁኔታው አስደሳች አይደለም። አሜሪካ ራሷ ከባሕረ-ሰላጤው አካባቢ ከፍተኛ የነዳጅ ዘይት ማስመጣት ያስፈልጋታል። ታዲያ፥ የራሷን ፍላጎት እንኳን በሚገባ ሳታረካ፥ የእስራኤልን ጥቅም እስከ መጨረሻ መጠበቅ ትችላለች? ሳውዲ ዓረቢያን ለመከላከልና ወታደራዊ ጦር መሣሪያ በአየር ለማቀበል በ1990 ዓ.ም. ከአገሪቱ መሪዎች ጋር ተስማምታለች። ታዲያ እስከ መቼ ነው የጦር ኃይሏን በክልሉ ለማቆየት የምትፈቅደው? በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችዋ በቪየትናም ጦርነት ተሳትፈው ከሁኔታው አስቸጋሪነት የተነሣ አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ ተገደዋል። ይህ የታሪክ ቁስል ሳይሽር፥ ከባሕር ማዶ ለሚገኝ አገር እንደገና መሥዋዕት ለመክፈል ዝግጁ ትሆናለች?


ይህ በእስራኤልና በዓረብ አገሮች መካከል የተከሠተ ሥነ-ልቡናዊና ፖለቲካዊ ፍልሚያ በእስራኤል ላይ ቀድሞ ያልነበረ ውጥረትና ውስብስብ ችግር አስከትሎባታል። የችግሩን መራራ ጽዋ የምትጎነጨው አገሪቱ ብቻ ሳትሆን፥ በዓለም ዙሪያ ያሉ አይሁዶችም ናቸው። የአሜሪካ መሪዎች አስቸጋሪ ምርጫ ቀርቦላቸዋል። አገሪቱ ከእስራኤል ጋር ያላትን ወዳጅነትና እርዳታ ብታቋርጥ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአይሁዳውያንን ጥላቻ ልታተርፍ ነው፤ ይህን ካላደረገች ደግሞ የዓረቦችንና በኢንዱስትሪ የበለጸጉ አንዳንድ አገሮችን ወዳጅነት ታጣለች።

ያም ሆነ ይህ ምዕራባውያን አገሮች ቁልፍ ከሆኑ ውሳኔዎች ላይ መድረሳቸው የግድ ነው። ውሳኔዎቹም የእስራኤልን ሕልውናና የበላይነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ድርድሮች ይሆናሉ። በመካከለኛው ምሥራቅና በአውሮፓ መሪዎች መካከል የሚፈጠረው አዲስ ኅብረት የኋላ ኋላ የዓለምን የሀብትና የኃይል ሚዛን ያዛባውና፥ እጅግ ተፈላጊ የሆነው ነዳጅ ዘይት ያለምንም ጥያቄ በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ቁጥጥር ሥር ይውላል።

የዓረብ አገሮችና ኢራን ቀድሞ ያልነበራቸውን ኃይል አግኝተዋል። ነዳጅ ዘይት በእጃቸው ነው፤ ከምዕራቡ ዓለም ባለ ኢንዱስትሪ አገሮች ጋርም ኅብረት ፈጥረዋል።

እነዚህ አገሮች ነዳጅ ዘይት ብቻ ሳይሆን፥ ለኢንዱስትሪ ማስፋፊያ የሚውል መዋዕለ ንዋይም ይሰጣሉ። ለሚደርሰው ኪሳራም ድጎማ ያደርጋሉ። ብዙ ጦር መሣሪያ፥ ፋብሪካና ቴክኖሎጂ ገዥዎች እንደመሆናቸው መጠን፥ የመግዛት ወይም የመተው ምርጫቸው የተጠበቀ ነው። የዓረብ አገሮች ለመዋዕለ ንዋይ የሚውልና ከባንክ ባንክ፥ ከአገር አገር፥ የሚንቀሳቀስ ብዙ ገንዘብ አላቸው። ይህ ተቀማጭ ሀብት የዓለምን ገንዘብ ምንዛሪና ንግድ ቀውስ ውስጥ ሊከተው ይችላል።

## የዓለም የነዳጅ ዘይት ምንጭ (በቢሊዮን በርሜል)



የዓረብ አገሮችና ኢራን ለረጅም ጊዜ በሚያገለግል መልኩ ሀብታቸውንም ሆነ ኃይላቸውን አቀናጅተዋል። የኢራን መንግሥት ለብዙ ዓመታት ችግር ውስጥ ቢሆንም፥ ለዓለም ገበያ ነዳጅ ዘይት ማቅረቡን አላቋረጠም። የነዳጅ ዘይት ቀውስ ዓለምን፥ በተለይም እስራኤልን የሚያስከፍለው ዋጋ በገንዘብ ብቻ የሚተመን አይደለም። እነዚህ እውነታዎች ዋና ዋናዎቹን የአውሮፓ መንግሥታትና ከመካከለኛው ምሥራቅ አንዳንድ ኃያላን አገሮችን ይበልጥ እንዲቀራረቡ አስገድደዋቸዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተተነበየው በመጨረሻ ከአሥር በማይበልጡ አገሮች የሚመሠረት ቡድን በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን ችግር የመፍታት አጋጣሚ ይጨብጥና ወሳኝ የፖለቲካ ኃይል ይሆናል።

## ♦ የመጨረሻው ዘመን ትንቢት ሲፈጸም

የአሕዛብ ዘመን ከመፈጸሙ በፊት በሜዲትራኒያን አካባቢ የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ያላቸው የመንግሥታት ኅብረት እንደሚመሠረት መጽሐፍ ቅዱስ አመልክቷል። እስካሁን በሀብትም ሆነ በዓለም አቀፍ ፍላጎት ወደዚህ የኃይል ሚዛን ዝውውር የሚያደርስ ጉዳይ አልተከሠተም። አሁን ግን የአውሮፓ ባለ ኢንዱስትሪ አገሮች አስተማማኝና የማያቋርጥ የነዳጅ ዘይት አቅርቦት ያስፈልጋቸዋል። ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ጋር በኢኮኖሚና በፖለቲካ መስክ በሚደረገው ስምምነት፥ የአውሮፓ ፍላጎት ለነዳጅ ዘይት መግዣ ወደ ዓረቡ ዓለም የተላለፈው ገንዘብ፥ እንዳለ ተመልሶ ለእርሻ ውጤቶችና ቴክኖሎጂ መግዣ አውሮፓ ውስጥ እንዲፈስ ማድረግ ይሆናል። ይህ ጥምር የገበያ ሁኔታ፥ አሜሪካንም ሆነች ሩሲያ በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ከሚያከናውኑት ሊበልጥ ይችላል። የሚያስከትለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ደግሞ፥ የቀድሞ ሮማዊ ኃያል መንግሥት ብዙ መንግሥታትን ባንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ኅብረት አስተባብሮ በሜዲትራኒያን ባሕር አካባቢ ፈጥሮት ከነበረው ሁኔታ የሚያንስ አይሆንም።

የአሁኑ የመካከለኛው ምሥራቅ ገናናነት የሮም አገዛዝ ከፈረሰ ወዲህ በዓለም ታይቶ የማይታወቅ ዓይነት ነው። የመካከለኛው ምሥራቅ መግነንና፥ ዓለም ወደ አርማጌዶን ጦርነት እየገሰገሰች መሆንዋ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት አኳያ ሲታይ አስደናቂ ማስረጃ ነው።

## ♦ የአሜሪካ እና ሩሲያ ማሽቆልቆል

በአሁኑ ጊዜ አሜሪካ እና ሩሲያ በዓለም ሁለት ኃያላን መንግሥታት መሆናቸው የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ፥ ስለ መጨረሻው ዘመን ከተነገረው

ትንቢት አንጻር ሁለቱም ይህን ያህል ትኩረት የሚሰጣቸው አይደሉም። ሩሲያ ከኃያልነት አሽቆልቁላለች። በጀርመንና በምሥራቅ አውሮፓ ከፍተኛ ለውጥ እየተካሄደ ቢሆንም፥ በመጨረሻ ዘመን ሩሲያ ስለሚኖራት ሁኔታ የተነገረ ብዙ ትንቢት የለም። አሜሪካንም ብትሆን፥ ዓለም ወደ አርማጌዶን ጦርነት ሲገሰግስ እሷ የሚኖራት አስተዋጽኦ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው። አሜሪካ በዓለም ተሰሚነት ያላት አገር ብትሆንም፥ በከፍተኛ ዕዳ ውስጥ ስለምትዘፈቅ፥ ሩሲያን ልትረዳት አትችልም።

ዛሬ የዓለም ትርዒት ማዕከል የሆኑት አገሮች፥ ከትንቢት አኳያ ስፍራቸውን በመካከለኛው ምሥራቅ ለሚፈጠረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኃይል ይለቃሉ። የመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ የፖለቲካና የኢኮኖሚ እምብርት ከመሆኑ ባሻገር፥ አዲስና አስደናቂ መሪ የሚነሣበትም ይሆናል። እነዚህ ክንውኖች በቅደም ተከተል ሊመጣ ላለው አዲስና ፈጣን ሁኔታ መረማመጃዎች ናቸው።

## ♦ የመካከለኛው ምሥራቅ ትንቢታዊ ዕጣ-ፈንታ

የአዳምና የሔዋንን መፈጠር ጨምሮ ሥልጣኔ የጀመረው በመካከለኛው ምሥራቅ ነው። ግብፅ፥ አሦር፥ ባቢሎን፥ ሜዶን-ፋርስ፥ ግሪክና ሮምን የመሳሰሉ ታላላቅ መንግሥታት የተነሡትና የወደቁት በዚሁ አካባቢ ነበር። ወደፊትም የዓለም ፖለቲካና ኢኮኖሚ ኃይል ዋና ማዕከል ይሄው አካባቢ ይሆናል። መካከለኛው ምሥራቅ በልማት ኋላ ቀር ሆኖ ሳለ እንዴት የዓለም ታሪክ ማዕከል ይሆናል? ለሚል ጥያቄ፥ መልሱ በከርሠ-ምድሩ በታመቀው የነዳጅ ዘይት ሀብት ክምችት የተነሣ የሚል ይሆናል። መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጡ የሦስት ክፍለ ዓለማት እምብርት አድርጎታል። ወደፊትም በዓለም አቀፍ ከንዋኔና ንግድ ነክ ጉዳዮች ውስጥ ወሳኝ ሚና እንዲኖረው ሆኗል።

## ♦ የሚቀጥለው ቀውስ - ምን ያህል ሩቅ ነው?

የመካከለኛው ምሥራቅ ቀውስ ሩቅ ሊሆን አይችልም። የአካባቢው ነዳጅ ዘይት ከአንድ ትውልድ በኋላ ያከትም ይሆናል። ስለዚህ አካባቢው ወደ ኃያልነት መምጠቅ ካስፈለገው ጊዜው አሁን ነው። የዓረቡም ዓለም ግቡ እንዲሠምርለት ከፈለገ ፈጣን እርምጃ መውሰድ አለበት።

# 5

# ፍልስጥኤም - የተስፋና የጭንቀ ምድር

## ♦ ትንቢት በምድራዊ ሰው ዓይን


በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እስራኤል የተነገሩ ተስፋዎችና ትንቢቶች ውስብስብና የተያያዙ ናቸው። አንዳንዶቹ አጠቃላይ ተስፋዎች ሲሆኑ፥ አብዛኛዎቹ ግን ዘርዘር ያሉና ስለ ወደፊቱ ሁኔታ ጭላንጭል ፈንጣቂዎች ናቸው። ነቢያት የወደፊቱን ሁኔታ ሲገልጡ የተራሮችን ጫፍ አግድምና በርቀት እንደሚመለከቱ ሆነው ነበር*። ነቢያቱ ስለ እነዚህ ተራራዎች ጫፍ በግልጥ ቢያመለክቱም፥ በተራራዎቹ መካከል ያሉትን የጊዜ ሸለቆዎች ግን አልተመለከቷቸውም፥ ወይም እንደሚገባ ለመግለጥ እይታቸው ውስን ነበር። ስለ እስራኤል የተነገሩትን አያሌ ትንቢቶች በሚገባ ካላቀናጀናቸው፥ አንዱን ከሌላው በጥንቃቄ ካላዛመድነውና፥ ከአይሁድ ሕዝብና ታሪክ እንዲሁም ከተስፋይቱ ምድር (ፍልስጥኤም) ጋር ካላነጻጸርናቸው ግራ ሊያጋቡን ይችላሉ። አይሁዶች ሦስት ጊዜ ተበትነው ሦስት ጊዜ ወደ ምድራቸው ተመልሰዋል። የመበተናቸውንና የመመለሳቸውን ትንቢት ከሁነኛ ታሪክ ጋር ማነጻጸር አለብን። ኢየሩሳሌም ብዙ ጊዜ ፈርሳ ነበር። ታዲያ የትኞቹ ትንቢቶች ናቸው የተፈጸሙት? የትኞቹስ በቅርቡ ይፈጸማሉ? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ገና ያልተፈጸሙ ትንቢቶች በእኛ ዘመን ይፈጸሙ ይሆናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች የፍልስጥኤም ያለፈው፥ የዛሬውና የነገው ክስተቶች የወደፊቱን ሁኔታ ለማወቅ ቁልፍ እንደሆኑ ግልጥ ያደርጋሉ።

## ♦ ትንቢታዊ ጥያቄዎች ስለ ተስፋይቱ ምድር


የመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋዎችና ትንቢቶች ስለ ተስፋይቱ ምድር ሲናገሩ፥ የተወሰነ መልከዓ-ምድራዊ ክልል ስላላቸው ስፍራዎች መግለጣቸው ይሆን? በምን መልኩ ነው የተነገረው? ምሳሌያዊ በሆነ አነጋገር፥ ወይስ ግልጥና

---

* የሚቀጥለውን ገጽ ይመልከቱ።



በድሮ ጊዜ አንድ ነቢይ ስለ ወደፊቱ ለማየት የሚችለው



እኛ ዛሬ ስላለፈው ምን ለማወቅ እንደምንችል

ቃል በቃል ሊተረጎም በሚችል ቋንቋ? አይሁዶች ስለ ምድሪቱ የተገባላቸው ተስፋ በእርግጥ መልከዓ-ምድራዊ ስፍራን የሚያመለክት ከሆነ፥ በተገባላቸው ተስፋ መሠረት ምድሪቱን ወርሰዋታል፥ ወይስ ገና ወደፊት ነው እጃቸው የሚያስገቡዋት?

ምድሪቱን ለመውረስ ተስፋ የተገባላቸውና የተተነበየላቸው ለመታዘዛቸው ሽልማት ሲሆን፥ ምናልባት አለመታዘዛቸውና አለማመናቸው ተስፋውን አስቀርቶት ይሆን? ትንቢቶቹስ በአዲስ ኪዳን በድጋሚ ተተንብየው ይሆን? ተስፋዎቹስ በሁኔታዎች ይወሰናሉ?

ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ለእስራኤል ሕዝብ የተሰጡ ተስፋዎችንና የተነገሩ ትንቢቶችን ሰፋ ባለ ሁኔታ አንድ በአንድ መመርመር ያስፈልጋል። ዝርዝር ታሪኩም ከአይሁድ ሕዝቦችና ከተስፋይቱ ምድር ነባር ታሪክ ጋር መነጻጸር አለበት።

## ♦ አብራም - የተስፋ ሰው

ሀያኛው ምዕተ ዓመት ታላቅና አስገራሚ ከሆኑት የዓለም ተአምራቶች አንዱን መስክሯል። እርሱም ጥንታዊያን ሕዝቦች ከብዙ ምዕተ ዓመታት ስደት በኋላ ከተበተኑበት ተሰባስበው ወደ አባቶቻቸው አገር መግባታቸው ነው። የእስራኤላውያን ወደ አገራቸው መመለስ ዑር ከተባለችው የከለዳውያን ከተማ ጋር በተያያዘ ሁኔታ አራት ሺህ ዓመታት ወደኋላ ይመልሰናል። ዑር በባቢሎን አጠገብ የነበረች የሜሶፓታሚያ ከተማ ናት። ታላቅ ተስፋ የተሰጠው ሰው አብራም ይኖር የነበረውም በዚህች የሥልጣኔ ማዕከል ከነበረች ታላቅ ከተማ ውስጥ ነበር። የተወለደባትን የእናት አባቱን አገር ትቶ እግዚአብሔር ወደሚመራው ስፍራ እንዲሄድ ታዘዘ። የአብራም ታሪክ ዘፍጥረት 11፡ 27 ላይ ይጀምርና ዘፍጥረት 25፡ 8 ላይ በሞቱ ይደመደማል። ይህ የዓለምን አፈጣጠር በሦስት ምዕራፎች ብቻ በሚያካትት መጽሐፍ ለአብራም ታሪክ አሥራ አራት ምዕራፎች ሰጥቷል።

አብራም እግዚአብሔርን በከፊል በመታዘዝ ከአባቱ አገር ወጥቶ ወደማያውቀው ስፍራ ተጓዘ። የመጀመሪያዎቹን አንድ ሺህ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትሮች ወደ ሰሜን ምዕራብ ተጉዞ፥ ካራን እተባለው አገር ካረፈ በኋላ፥ አባቱ እስኪሞት ድረስ እዚያው በድንኳን ተቀመጠ። ከዚያም አንድ ሺህ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትሮች ወደ ደቡብ ምዕራብ በመጓዝ ተስፋይቱ ምድር ደረሰ። እስከ ዕለተ ሞቱ የኖረውም እዚያው ነበር።

እግዚአብሔር ለአብራም ትልቅ ተስፋ ሰጥቶታል። ታላቅ ሰው ሊያደርገው ቃል ገብቶለታል (ዘፍ. 12፡2)። ዘሩንም እንደሚባርክ ነገረው

(ዘፍጥ. 12፡2)። በእርሱ አማካይነትም የዓለምን ሕዝብ ሁሉ እንደሚባርክ ቃል ገባለት (ዘፍጥ. 12፡3)።

ታሪክም የዚህን ኪዳን ቃል በቃል መፈጸም ዘግቧል። አብራም የሚለው ስሙም አብርሃም በሚለው ተለውጧል። ትርጓሜውም "የሕዝብ አባት" ማለት ሲሆን፥ የአብርሃም ስም በአይሁዶች፥ በክርስቲያኖችና በእስላሞች ሁሉ ዘንድ ክቡር ነው ። የእስራኤል ነገድ ብቻ ሳይሆን፥ መላው የዓረብ ነገድ ጭምር ከአብርሃም ዘር የተገኘ ነው። እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ መሠረት የአብርሃም ዘር እንደ ምድር አሸዋና፥ እንደ ሰማይ ከዋክብት በዝተዋል (ዘፍጥ. 13፡16፤ 15፡5)። ነቢያት፥ የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጸሐፊዎች እና የዳዊት ልጅ የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን የተገኘው ከዚሁ ከአብርሃም ነው። የአብርሃምን ዘር የባረከ ሕዝብ ሁሉ ተባርኮአል። የአብርሃምን ልጆች የረገመ ሕዝብ ሁሉ ተረግሞአል (ዘፍጥ. 12፡3)። እንደ ግብፅ፥ አሦር፥ ባቢሎን፥ ሮምን በመሳሰሉና እስራኤልን ሲረግሙና ሲጨቁኑ በነበሩ መንግሥታት ላይ እግዚአብሔር ፈርዶባቸዋል። በዘመናችንም ስፔይን፥ ጀርመንና ሩሲያ ከእግዚአብሔር ፍርድ አላመለጡም። የአሕዛብ ዘመን ሲፈጸም ደግሞ የመጨረሻው ፍርድ ይሰጣል።

## ♦ የምድሪቱ ተስፋ

እግዚአብሔር ለአብርሃም ከገባለት ተስፋዎች ዋነኛው ለዘርያዎቹ ርስት እንደሚሰጣቸው የተናገረው ነው። የአብርሃም ሕይወት ታሪክ ባብዛኛው ዑር ከተባለችው የከለዳዊያን ምድር በፈቃደኝነት ለቅቆ ወደ ተስፋይቱ አገር በመሄዱ ላይ ይሽከረከራል። ተስፋው በመንፈሳዊ በረከት ብቻ የሚያከትም አይደለም። አብርሃም ዕድሜውን በስደተኛነት ያሳለፈበት ዋነኛ ምክንያት የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ ነበር።

ተስፋው በማያሻማ ሁኔታ በዘፍጥረት 15 ላይ ሲረጋገጥ እናያለን። አብርሃም የትውልድ አገሩን ለቆ ወደ ተስፋይቱ ምድር በእምነት በመሄዱ ብድራቱን ከተስፋዎቹ ዝርዝር ማብራሪያ ጋር ተቀብሏል። ስለ ተስፋይቱ ምድር መልክዓ-ምድራዊ ክልልና ከዚያ በፊት ይኖሩባት ስለነበሩ ሕዝቦች እንኳን ሳይቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፋ ያለ ገለጣ ተሰጥቷል።

> "በዚያ ቀን እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ ብሎ ቃል ገባለት። ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ትልቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቻለሁ። ቄናውያንን፥ ቄኔዛውያንንም፥ ቀድሞናውያንንም፥ ኬጢያውያንንም፥ ፌርዛውያንንም፥ ራፋይምንም፥ አሞራውያንንም፥ ከነዓናውያንንም፥ ጌርጌሳውያንንም፥ ኢያቡሳውያንንም" (ዘፍጥ. 15፡18-21)።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር ራሱን የቻለ መልከዓ-ምድራዊ ክልል ያለውን ስፍራ ለአብርሃም እንደሚሰጠው እንጂ፥ እንዲሁ በደፈናው በረከትን እንደሚያገኝ ወይም መንግሥተ ሰማይን እንደሚያወርሰው አይደለም የሚያመለክተው። በዘፍጥረት 17 ደግሞ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠውን ተስፋ ይበልጥ ግልጥ ሲያደርግለትና ሲያስረግጥለት እንመለከታለን። ወደፊት የብዙ ሕዝብ አባት ይሆናል። በተሰጠው ተስፋ መሠረትም አብራም የነበረው ስሙ አብርሃም ተብሏል።

የተስፋይቱ ምድር ለእስራኤል የተሰጠችው ለትውልድ ሁሉ ርስት እንድትሆን ነው።

> "ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ፥ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ አምላክ እሆን ዘንድ። በእንግድነት የምትኖርባት፥ የከነዓን ምድር ሁሉ ለዘላለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ አምላክም እሆናቸዋለሁ" (ዘፍጥ. 17፡7-8)።

የዚህ ኪዳን ትርጉም ለአብርሃምና ለቀደሙት አንባቢዎች ግልጥ ነው። በተስፋው የተሰጠቻቸው ምድር ፍልስጥኤም ስትሆን፥ ይህም ከሲና በረሃ አንሥቶ ወደ ሰሜን፥ ከዚያም ወደ ምሥራቅ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለው ምድር ነው። ዛሬ እስራኤል የያዘችውን ግዛት በሙሉና ሊባኖስን፥ የዮርዳኖስን ምዕራብ ዳርቻ፥ እንዲሁም የሶሪያን፥ የኢራቅንና የሳውዲ ዓረቢያን ሰፋ ያለ ግዛት በከፊል ያጠቃልላል። በዘፍጥረት ምዕራፍ 17 ቃል ኪዳን መሠረት የኪዳኑ ተቀባይ የሆነው ሰው መታዘዝና አለመታዘዝ ተስፋውን ሊያፈርሰው እንደማይችል ግልጥ ነው። ቃል ኪዳኑ የዘላለም ነው፤ ስለዚህም ከነዓን የእስራኤል የዘላለም ርስታቸው ናት።

## ♦ ምድሪቱን ከመውረስ መዘግየታቸው

አብርሃም ምድሪቱን በፍጹም አልወረሰም። እግዚአብሔር የተስፋይቱን ምድር ወራሽ የሚሆነውን ልጅ፥ ይስሐቅን በተአምራዊ ኃይሉ ሲሰጠው የመቶ ዓመት ሽማግሌ ነበር። ይስሐቅ ከተወለደ በኋላም አብርሃም ምድሪቱን አልወረሰም፤ ሚስቱን ሣራን እንኳን የቀበራት ራሱ በገዛው መሬት ነበር። ከዚህ ውጪ ምንም ርስት አልነበረውም። ዘሩ ለብዙ መቶ ዓመታት ይህችን ርስት እንደማይወርሳት እግዚአብሔር በግልጥ ነግሮታል። እንዲያውም የተስፋይቱን ምድር ትተው የነሱ ወዳልሆነ አገር እንደሚሄዱ ነው የተነገረው (ዘፍጥ. 15፡13)። ከጊዜ በኋላ ተመልሰውም ምድሪቱን እንደሚወርሱ ተገልጧል።

## ♦ ከምድሪቱ የመጀመሪያው ጉዟቸው

የእስራኤል ልጆች በዮሴፍ ዘመን እንዴት ወደ ግብፅ ምድር እንደሄዱ ከታሪክ መዛግብት መመልከት ይቻላል። በወንድሞቹ ወደ ግብፅ የተሸጠው ዮሴፍ በመጨረሻ የግብፅን ንጉሥ (የፈርዖንን) ትንቢታዊ ሕልም በመተርጎሙ የአገሪቱ ከፍተኛ ሹም ሆኖ ነበር። በሥልጣኑም ቤተሰቦቹን ከግብፅ ሀብት እንዲቋደሱ አደረገ። ቀጥሎም የአብርሃም የልጅ ልጅ የሆነው አባቱ ያዕቆብ፥ ወንድሞቹና ቤተሰቦቻቸው ከረኃብ ለማምለጥ ወደ ግብፅ መጡ። ወደዚያ የገቡት ሰባ ቤተሰቦች ሲሆኑ፥ በኋላ ግን ሁለትና ሦስት ሚሊዮን ሆነው ነበር።

## ♦ እስራኤል በግብፅ

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የግብፅ መንግሥት በመለወጡ ሳቢያ ለአገሩ ባዕድ የሆኑት እስራኤላውያን እዚያ ለመኖር አልቻሉም። እያደርም በፈርዖን ጨካኝ አገዛዝ ሥር በባርነት ቀንበር ሥቃይና መከራ ተቀበሉ። የእስራኤል ወንድ ሁሉ እንደተወለደ እንዲገደል የሚደነግግ ሕግ ወጣ። ሙሴ የተወለደው በዚያ የጭንቅ ዘመን ነበር። የፈርዖን ልጅም በጉዲፈቻ ወስዳ በግብፅ ቤተ መንግሥት እያስተማረች አሳደገችው። ኋላም የእስራኤላውያን አዳኝ ለመሆን ተዘጋጀ።

## ♦ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመጀመሪያው መመለስ

የዘጸአት መጽሐፍ የመጀመሪያውን የእስራኤላውያን ወደ አገራቸው መመለስ ዘግቧል። በጉዟቸውም ወቅት ከእምነታቸው ጉድለት የተነሣ በምድረ በዳ ለአርባ ዓመት ተንከራተቱ። በመጨረሻ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ያለውን ምድር ከነዋሪዎቹ ወረሱ። በዚህ የመጀመሪያ የመልስ ጉዞ እግዚአብሔር ቃል የገባላቸውን ምድር ከሙሴ ዕረፍት በኋላ በኢያሱ አማካይነት እንዲወርሱ በማድረግ ተስፋውን ደግሞ አረጋገጠላቸው። የእግዚአብሔር ትእዛዝ የዮርዳኖስን ወንዝ ዘልቀው እንዲሻገሩ ነበር። "ለእስራኤል ልጆች ወደምሰጣቸው ምድር ይህን ዮርዳኖስን ተሻገሩ" (ኢያሱ 1፡2)። የመሬቷም መልክዓ-ምድራዊ ገለጣ ልክ በዘፍጥረት እንዳለው ነበር። "ከምድረ በዳው ለዚህም ከሊባኖስ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ የኬጢያውያን ምድር ሁሉ. . . እስከ ታላቁ ምዕራብ ባሕር ዳርቻ ይሆናል" (ኢያሱ 1፡4)። በመጨረሻም ከብዙ ዓመት መንከራተት በኋላ፥ ወንዙ ደረቀላቸውና ዮርዳኖስን በተአምር ተሻገሩ። ከዚያም ኢያሪኮን ድል አድርገው "ጋይን" እና ከተስፋይቱ ምድር ብዙውን ማርከው ነበር። የተሰጣቸው ተስፋ በከፊል ሲፈጸም፥ ኪዳኑም በድጋሚ ተረጋገጠላቸው። አስቀድሞ ባደረጉት ውጊያ ግን፥ ቃል የተገባላቸውን ምድር በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር አላደረጉትም።

## ♦ በመታዘዝ ወዲያው ውርስን ማግኘት

የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ የተቀበሉትን ሕግ ካላከበሩ ከም ድራቸው እንደገና ተባረው እንደሚሰደዱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ነበር። እነዚህ ሕዝቦች በመሳፍንት ዘመን በከፍተኛ የሞራል ውድቀት ውስጥ ነበሩ፤ በሳኦልና በዳዊት ዘመን ደግሞ ታላቅ ሕዝብ ሆነው ነበር። በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ለአብርሃም የተገባለት የተስፋ ምድር ከሞላ ጎደል በቁጥጥራቸው ሥር ሆነ። ይህም የግብፅን ወንዝ፥ የግብፅን ድንበር ይዞ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ያለውን ምድር ያጠቃልል ነበር። ይሁን እንጂ፥ ምድሪቱን ሙሉ በሙሉ አልወረሱም። ይህም ሲባል በዘፍጥረት 17፡8 ላይ "የዘላለም ግዛት ይሁንህ" በተባለው መሠረት፥ ምድሪቱን ገና አልተቆጣጠሩም ማለት ነው። የሞራላቸው መውደቅና ምግባረ ብልሹነታቸው ባገኙት ጊዜያዊ ድል ላይ አጠላበት።

የጣዖት አምልኮና የሞራል መዝቀጥ ለመንግሥታቱ መውደቅ ምክንያቶች ነበሩ። ንጉሥ ሰሎሞን ከብዙ አገራባቾቹ ጣዖት አምላኪ ሴቶችን አገባ። ስለዚህም ልጆቹ እውነተኛውን የእስራኤል አምልኮ ትተው ጣዖታትን ማምለክ ጀመሩ። መንግሥቱም ከውጪና ከውስጥ በሚፈጠር ሁኔታ ሳቢያ ይበታተን ጀመር።

ከሱ ሞት በኋላም መንግሥቱ ለሁለት ተከፈለ። አሥሩ ነገዶች በአንድነት ሆኑና በስተሰሜን ያለውን የእስራኤል መንግሥት መሠረቱ፤ ሁለቱ ነገዶች ደግሞ ማለትም ይሁዳና ብንያም ደቡባዊውን የይሁዳ መንግሥት መሠረቱ።

## ♦ ሁለተኛው ጉዞ- ምርኮው

ነቢያት በእስራኤል ላይ የቁጣ ፍርድ እንደሚመጣ አስጠንቅቀው ነበርና በጊዜው መጣ። አሶራዊያን በ721 ዓመተ ዓለም አሥሩን የእስራኤል ነገድ ማረኩዋቸው። ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ፥ በ605 ዓመተ ዓለም በበጋው መጠናቀቂያ ግድም የባቢሎን ጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥና ኋላም ሟች አባቱን ተክቶ የባቢሎን ንጉሥ ሆኖ የተሾመው ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ወረረ። በዚህ ወረራ ብዙ እስራኤላውያን በምርኮ ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። በመጨረሻም በ586 ዓመተ ዓለም ኢየሩሳሌም ምስቅልቅሏ ወጥቶ ወደመች። ሕዝቧ ለስደት ተዳረገ፤ ምድረ በዳም ሆነች።

## ♦ ሁለተኛው የመመለስ ተስፋ

እስራኤል በወደቀችበት ዘመን ይኖር የነበረው ነቢይ ኤርምያስ ግን ሕዝቡ እንደገና ወደ ምድሩ እንደሚመለስ በማመልከት እንዲህ በማለት ትንቢት

ተናግሮ ነበር። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፥ ሰባው ዓመት በባቢሎን በተፈጸመ ጊዜ እጐበኛችኋለሁ፥ ወደዚህም ስፍራ እመልሳችሁ ዘንድ መልካሚቱን ቃሌን እፈጽምላችኋለሁ" (ኤር. 29፡10)።

## ♦ የዳንኤል ጸሎት፥ ሁለተኛው መመለስ

ሰባው ዓመት እንዳበቃ፥ የሰማንያ ዓመቱ አዛውንት ነቢዩ ዳንኤል፥ ትንቢተ ኤርምያስን ያነብ ነበር (ዳንኤል 9ን ይመልከቱ)። ወዲያው ስለ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ለመጸለይና ለመማለድ ልቡ ተነሣሣ። በባቢሎናውያን የወደመችውን ጥንታዊት ከተማ እግዚአብሔር እንዲታደግ፥ እንደገናም የራሱ ክብር መገለጫ አድርጎ ለእስራኤል ዋና ከተማነት እንዲያበቃት በነቢዩ ኤርምያስ የተጻፈውን የተስፋ ቃል በመጥቀስ በጸሎት ጠየቀ። መስኮቱን ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ እየከፈተ በቀን ሦስት ጊዜ የመጸለይ ልምድ ነበረው። የጥንት ሕዝቡንና ከተማውን መልሶ እንዲመሠርት አዘውትሮ ወደ እግዚአብሔር ይማልድ ነበር (ዳን. 6፡10)።

## ♦ ቤተ መቅደሱ እንደገና ተሠራ

የዳንኤል የጸሎት ጥያቄ ተመለሰ፤ የነቢዩ ኤርምያስ ትንቢትም ቃል በቃል ተፈጸመ። አምሳ ሺህ ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር የተመለሰበትን ሁኔታ የዕዝራ መጽሐፍ ይገልጣል። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በ516 ዓመተ ዓለም ቤተ መቅደሱ እንደገና ተሠራ። ከተማዋ ግን እስከ 445 ዓመተ ዓለም ድረስ አልታደሰችም ነበር። ነህምያ የፈረሰውን የኢየሩሳሌም የቅጥር ግንብ ለማደስ ከንጉሡ ፈቃድ ተቀብሎ መጣና ግንቡ እንደገና ታነፀ። ለአምሳ ዓመት ያህል ከተማይቱ እንደገና የእስራኤል ፖለቲካ፥ ሃይማኖትና ብሔራዊ ሕይወት ዋና መዲና ሆነች።

## ♦ ቤተ መቅደሱ በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ

ዓመታት አለፉ። በ20 ዓመተ ዓለም የሮም መንግሥት እስራኤልን ወክሎ በ516 ዓመተ ዓለም የተሠራውን ቤተ መቅደስ ያድስ ጀመር። በዚያን ጊዜ ቤተ መቅደሱ ከተሠራ 500 ዓመት ሆኖታል። በእስከፊ ደረጃ ላይ ስለነበር እድሳት አስፈለገው። እድሳቱ ክርስቶስ ሲወለድም ሆነ ሲሞት ገና አልተጠናቀቀም ነበር። ይህ በኢየሩሳሌም ከተማ ከመሬት በታች ይገኝ ከነበረ ድንጋይ ማምረቻ ውስጥ በሚገኝ ቁሳቁስ የታነፀ ታላቅ ቤተ መቅደስ በ64ኛው ዓ.ም. ተጠናቀቀ።

## ♦ የቤተ መቅደሱ መፍረስ

ይሁን እንጂ፥ ቤተ መቅደሱ በዚያ ውበቱ ብዙ አልቆየም። ከስድስት ዓመት በኋላ ማለትም በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም እንደገና በጦር ተከበበች። የሮም ወታደሮች ለበዓል የተመለሱትን አይሁድ እንደ ከብት አረዱዋቸው። ከተማይቱም ወደመች፤ ቤተ መቅደሱ የተሠራበትም ድንጋይ አንድ በአንድ ተለቅሞ በደቡባማው ምሥራቅ ኢየሩሳሌም ሸለቆ ውስጥ ተጣለ። ዛሬ ከእነዚያ ድንጋዮች ጥቂቶቹ በሥነ-ምድር ተመራማሪዎች ቁፈራ ተገኝተዋል።

## ♦ ሦስተኛው ጉዞ

በኢየሩሳሌም የደረሰው እልቂትና የቤተ መቅደሱ መፍረስ እስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር ለመቆጣጠር የነበራቸውን ተስፋ አጨለመው። በቀጠሉት ዓመታት ደግሞ ብዙ ከተሞች ወደሙ፤ ሕዝቦቹም ከአገራቸው ተገፍተው በዓለም ዙሪያ ተሰደዱ። ለእግዚአብሔር ሕግጋት ካልታዘዙ ይህ ሁሉ እንደሚደርስባቸው ሙሴ አስጠንቅቆአቸው ነበር።

> "እግዚአብሔር በጎ ያደርግላችሁ ዘንድ ያበዛችሁም ዘንድ ደስ ይለው እንደነበረ፥ እንዲሁ እግዚአብሔር ሲያጠፋችሁ ሲያፈርሳችሁም ደስ ይለዋል፤ ትወርሷትም ዘንድ ከምትገቡባት ምድር ትነቀላላችሁ፤ እግዚአብሔርም ከምድር ዳር እስከ ዳርቻዋ ድረስ ወዳሉ አሕዛብ ሁሉ ይበትንሃል፤ ከዚያም አንተና አባቶችህ ያላወቃችኋቸውን ሌሎችን አማልክት ዕንጨትና ድንጋይን ታመልካለህ" (ዘዳ. 28፡63-64)።

ይህ ጥንታዊ ትንቢት እስራኤላውያን በዓለም ሕዝቦች መካከል ሲኖሩ ስደት፥ ሥጋት፥ ፍርሃትና ሁከት እንደሚገጥማቸው ያስረዳል።

## ♦ ለመጨረሻ ጊዜ ስለመመለሳቸው የተነገረ ትንቢታዊ ተስፋ

ኢየሱስ ይህ በዘመኑ የነበረ ቤተ መቅደስ ጨርሶ እንደሚፈርስ ተንብዮ ነበር (ማቴ. 24፡2)። ይህ ስለ ኢየሩሳሌም ዕጣ-ፈንታና በሕዝቡም ላይ ስለሚደርሰው እልቂት የተነገረ ትንቢት መልእክቱን በሰሙ ትውልድ ዘመን ተፈጽሞአል። ቤተ መቅደሱ ፈረሰ፤ አይሁዳውያንም በስደት ተበተኑ። እስራኤል ለአንዴና ለመጨረሻ አብቅቶላት ይሆን? እግዚአብሔርስ የሰጠውን ተስፋ ዘንግቶ ይሆን? ራሱ እስራኤላዊ የሆነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለነዚህ ጥያቄዎች የሰጠው መልስ "በፍጹም!" የሚል ነበር። "እግዚአብሔር ሕዝቡን ጠላቸውን? እላለሁ፥ አይደለም" (ሮሜ 11፡1)።

ዘላለማዊው ቃል ኪዳን ይፈጸም ይሆን? በተስፋው መሠረት እስራኤል መልክዓ-ምድራዊ ክልሏን አስከብራ የርስቷ ባለቤት ትሆን ይሆን?

የዕብራውያን ጸሐፊ ለአብርሃም የተሰጠውን ተስፋ እንደገና ያነሣዋል። ተስፋው በእስራኤል መታዘዝ ወይም አለማመን የሚጸና ወይስ የሚፈርስ ነበር? በፍጹም! በእነርሱ መታዘዝ ወይም አለመታዘዝ የሚወሰን አይደለም። እግዚአብሔር የሰጣቸው ተስፋ የማይሻርና የማይለወጥ ነው።

> "እግዚአብሔርም ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ በራሱ ማለ...። ስለዚህም እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለፈቀደ፥ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ በመሐላ በመካከል ገባ። ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን" (ዕብ. 6፡13፥ 17-19)።

ብሉይና አዲስ ኪዳን እስራኤላውያን በመጨረሻ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደሚመለሱ አስረግጠው ያመለክታሉ። ይህ እንደገና የመመለሳቸው ተስፋ በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ትግላቸው ወቅት ከፍተኛ መጽናናት ሆኖአቸዋል። ተስፋው የመፈጸሙ ዕድል የመነመነ ቢሆንም የትንቢቱን ቃል የተረዱ ክርስቲያኖች ግን ለብዙ ምዕተ ዓመታት ሲጠባበቁት ኖረዋል።

## ♦ የተበተኑት እስራኤላውያን ስደት

ቀጣዮቹ ምዕተ ዓመታት ለአይሁዳውያን እጅግ አስጨናቂ ነበሩ። ከአስከፊው ስደት የተነሣ በርካታ የነበረው ቁጥራቸው በአንድ ጊዜ ወደ አንድ ሚሊዮን ዝቅ አለ። በስመ-ክርስቲያናትም ሆነ፥ በአረማውያን እኩል ተጠሉ። ከአገር ወደ አገር አሳደዷቸው፤ ዕረፍት አሳጧቸው። ለአጭር ጊዜ ካልሆነ በቀር፥ "የእኛ ነው" የሚሉት ርስትም ሆነ ብልጽግና አልነበራቸውም።

በሰብአዊ አእምሮ ሲገመገም እስራኤል ወደፊት ተስፋ ያላት አትመስልም ነበር። በስምንተኛው ምዕተ ዓመት ዓረቦች ጥንታዊውን የእስራኤል ምድር የራሳቸው አድርገውት ነበር። በአሥራ ሁለተኛው ምዕተ ዓመትም የክርስቲያን የመስቀል ጦረኞች በፍልስጥኤም ለጥቂት ጊዜ ተቋቋሙ፤ በኋላ ግን በ1187 ዓ.ም. በሳላዲን [Saladin] ተሸነፉ። በ1517 ዓ.ም. ምድሪቱ በቱርኮች እጅ ወደቀች፤ አስገራሚ ለውጥ መከናወን የጀመረው ግን በአንደኛው የዓለም ጦርነት በ1917 ዓ.ም. እንግሊዛዊው ጄኔራል አለንቢ [General Allenby] ኢየሩሳሌምን ከቱርክ እጅ በመውሰድ በቁጥጥራቸው ሥር ካደረጉዋት በኋላ ነበር። በዚሁ ጊዜም ፍልስጥኤም በእንግሊዞች ይዞታ ሥር መሆን ጀመረች።

## ♦ የሦስተኛው መመለስ ጅማሬ

እስራኤላውያን ወደ ምድራቸው ለመመለስ የተለያዩ ችግሮች ቢገጥሟቸውም፥ ከ1871 ዓ.ም. ጀምሮ ጥቂቶች ለመመለስ ችለው ነበር። በዚሁ መሠረት እስከ 1881 ድረስ ሀያ አምስት ሺህ አይሁዶች ወደ ምድራቸው ለመስፈር በቁ። ወደ ተስፋይቱ ምድር የመመለሳቸው ጉዳይ ሕጋዊ መልክ የያዘው ግን ቴዎዶር ሐርዚል [Theodore Herzl] በ1897 ዓ.ም. የመጀመሪያውን የጽዮናውያን ኮንግሬስ ከመሠረቱ በኋላ ነበር። ምንም እንኳን በጊዜው ሊፈጸም የማይችል ተስፋ ቢመስል፥ አይሁዳውያን አገራቸውን እንደገና እጃቸው ለማስገባት የሚያስችላቸው አዲስ የተስፋ ጭላንጭል አይተዋል።

## ♦ የ1917ቱ የባልፎር መግለጫ

ወደ አገራቸው የመመለሳቸው ክንውን እጅግ አዝጋሚ ነበር። በ1914 በምድሪቱ ሰማኒያ ሺህ አይሁዶች ብቻ ነበሩ። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ጸሐፊ አርተር ጄ. ባልፎር [Arthur J. Balfour] ከአይሁድ ድጋፍ ለማግኘት ሲል የባልፎር ዲክላሬሽን [Balfour Declaration] በመባል የሚታወቀውን መግለጫ ኅዳር 2 ቀን 1917 ዓ.ም. አወጣ። ይህ መግለጫ የእስራኤልን ዓላማ ይደግፋል። "የንጉሡ ነገሥቱ መንግሥት አይሁዳዊያን በፍልስጥኤም መሬት ለእነርሱ ተለይቶ የሚከለል አገራዊ መኖሪያ እንዲኖራቸው ይደግፋል" የሚል ቃል ነበረው። ይሁንና ለእስራኤል የመኖሪያ ቦታ መስጠቱን የማይደግፈው የዓረቡ ዓለም ግፊትና እንግሊዝ ከዓረቦች ጋር ለመወዳጀት የምታደርገው ጥረት ተደምሮ የእስራኤልን በተስፋይቱ ምድር መኖር በእጅጉ አዘግይቶት ነበር። በ1939 ዓ.ም. ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲቀሰቀስ ግን መጠነኛ እድገት ታየበት። ምንም እንኳን በአይሁዳውያን ፍልሰት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግና አይሁዳውያን ርስት እንዳይኖራቸው የሚከለክል ሕግ በማውጣት ከፍተኛ ተጽዕኖ ቢደረግባቸውም፥ እስከ 1939 ዓ.ም. ድረስ አራት መቶ ሺህ አይሁዶች ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመመለስ ቻሉ።

## ♦ በ1948 የእስራኤል መንግሥት መመሥረት

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዶች የናዚ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ሰለባ መሆን ከዓለም ሕዝብ ኃዘኔታን አተረፈላቸው። በእርግጥ ተንከራታቹ አይሁድ የራሱ የሆነ አገር ሊኖረው ይገባል። በ1945 ዓ.ም. በፍልስጥኤም ምድር እስራኤል መመሥረትዋን የሚቃወም አንድ የዓረቦች ማኅበር ተቋቋመ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በዩናይትድ ስቴትስና ሩሲያ አጽዳቂነት የዓለም መንግሥታት ድርጅት አይሁዳውያን በፍልስጥኤም ምድር መኖሪያ እንዲያገኙ ወሰነ። መመሪያውም

ፍልስጥኤም በአይሁድና በዓረብ መንግሥት እንድትከፈል የሚያደርግ ሲሆን፥ ገና በመቋቋም ላይ ለነበረችው ታዳጊ እስራኤል የተሰጣት ክልል ግን አምስት ሺህ ስኩዌር ማይል (ስምንት ሺህ ስኩዌር ኪሎ ሜትር) ነበር።

## ♦ የእስራኤልና የዓረቦች ጦርነት (1948-1949)

በግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም. እንግሊዝ በአካባቢው የነበራት የበላይነት ሲያበቃ እስራኤል ከብዙ ምዕተ ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻ መንግሥት ሆነች። የነጻይቱ አዲስ አገር ሕዝብ ስድስት መቶ አምሳ ሺህ አይሁዶችና በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዓረቦችን ያጠቃለለ ነበር። ይሁን እንጂ፥ ይህ የሕዝብ አሰፋፈር በዓረቦች ዘንድ ተቀባይነት አጣ። እስራኤል በሁሉም አቅጣጫ ማለትም በግብፅ፥ በዮርዳኖስ፥ በኢራቅ፥ በሶሪያ፥ በሊባኖስና በሳውዲ ዓረቢያ ትጠቃ ጀመር። ያም ሆኖ የመከላከያ ኃይሏ እንደ ጠላቶቿ የተበታተነ ሳይሆን የተጠናከረና አስተማማኝ ነበር። በጦርነቱ ብዙ ሺህ ዜጎችዋ ቢወድቁባትም፥ ጥር 7 ቀን 1949 ዓ.ም. የጦርነት ማቆም ስምምነት ሲደረግ፥ አብዛኛውን የደቡብ በረሃማ ምድር፥ ኔጌቭን [Negev] ጨምራ በመያዝ ግዛቷን ከአምስት ሺህ ወደ ስምንት ሺህ ስኩዌር ማይል (ወደ 13,000 ኪሎ ሜትር ገደማ) አስፍታው ነበር። ከዚያ እስከአሁን ያለው የእስራኤል ታሪክ የማያቋርጥ መከራና ጦርነት የበዛበት ቢሆንም፥ መንግሥቷ ግን እየተጠናከረ መጥቷል።

## ♦ ትንቢቶቹ ተፈጽመው ይሆን?

ከአብርሃም ጀምሮ እስራኤል የተሰጣት ተስፋና በረከት ገና ሙሉ በሙሉ ፍጻሜ አላገኘም። ሕዝቧ ሦስት ጊዜ ተበትኖ ሦስት ጊዜ ወደ ምድሩ ተመልሷል። ይህ ሁኔታ ነው ታሪኳን አስገራሚ ያደረገው። እጅግ አስገራሚው ግን፥ ወደፊት የሚሆነው ነው። የአሁኑ የእስራኤል መመለስ፥ የመጨረሻ መሰብሰቢያዋ መጀመሪያ ይሆን? ወይስ ለአሕዛብ ዘመን ማብቂያ ጥርጊያ የሚያዘጋጅ አንድ ተጨማሪና ወቅታዊ ድርጊት? ምንም እንኳን አይሁድ ያልሆኑ አገሮች የከብር ስፍራ ለመያዝ በመሽቀዳደም ላይ ቢሆኑ፥ የአሕዛብ ዘመን ካከተመ በኋላ ግን እስራኤል ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ የተሰጣት ተስፋ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚሆንላት ማወቅ ተገቢ ነው።

## ♦ በቀላሉ የሚገኝ ክብር የለም

አይሁድ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ፍልስጥኤም ምድር እንደገና ለመመለስ የሚያደርጉት ጉዞ ቀላል አይሆንም። በመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም ለማስፈን የተደረጉ ድርድሮች ሁሉ እስከዛሬ ዘላቂ ውጤት አላመጡም። ሰላም ወዳድ

እስራኤላውያን የኢኮኖሚ ብልጽግና ለማግኘት ከመንጓጓታቸው የተነሣ፥ ጸጥታቸውን የሚያደፈርስባቸውን የሰላም ውል ያደርጋሉ። ከአርባ ዓመታት በላይ ራሷን በጀግንነት የተከላከለች አገር ዓለም አቀፋዊ ዋስትና የሚያስገኝ የሐሰት የሰላም ውል ማድረግዋ የሚያሳዝን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ "የያዕቆብ መከራ ዘመን" (ኤር. 30፡7) የሚለው ይህንኑ ሲሆን፥ ይህም ለመጨረሻው ዘመን ምንም የማይረዳ ነው ።

ከመጀመሪያው መመለስ በኋላ እስራኤል የይስሙላ የሰላም ጊዜ ይኑራት እንጂ፥ የኋላ ኋላ የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ ይከዳትና በደም ባሕር ትዋኛለች። በፍልስጥኤምና በአይሁድ ሕዝቦች መካከል ያኔ እግዚአብሔር ጣልቃ ባይገባ ሁለቱም ሕዝቦች ከምድረ-ገጽ ይጠፉ ነበር። ስለ ኢየሩሳሌም የወደፊት ዕጣ የሚገልጡ ዝርዝር ትንቢቶች በሚቀጥሉት ሁለት ምዕራፎች የሚካተቱ ይሆናሉ።

የኤርምያስ ትንቢት የያዕቆብን የመከራ ዘመን በግልጥ ያሳያል። ይህ ሦስት ዓመት ተኩል የሚፈጅ የመጨረሻው የመከራ ዘመን ወደ ፍጻሜው ጦርነት የሚያመራ ይሆናል። የአርማጌዶኑ ጦርነት የሚጀምረውም የይስሙላው የሰላም ድርድር በሚዲትራኒያው ኅብረት መሪ ሲጣስ ነው።

ይህ የታሪክ ወቅት በዙውን ጊዜ "ታላቁ የመከራ ዘመን" በመባል ይታወቃል (ራእይ 7፡14፥ ተመሳሳዩ ማቴ. 24፡21)። ይህ ጊዜ የአሕዛብ ዘመን ማከተሚያ እንደሚሆን በዮሐንስ ራእይ ሰፋ ባለ ማብራሪያ የተገለጠ ሲሆን፥ የአሕዛብ ዘመን ማብቂያ በመባል ይታወቃል። ፍልስጥኤም፥ ኢየሩሳሌምና በሰላሙ ዘመን እንደገና የተሠራው ቤተ መቅደስ "ለአሕዛብ ይሰጣል። እነርሱም አርባ ሁለት ወር የተቀደሰችውን ከተማ ይረግጧታል" (ራእይ 11፡2)።

የመመለሱ ተስፋ ከተፈጸመ በኋላ ስለሚሆነው ስለዚህ ጉዳይ ኤርምያስ፡-

> "የሚያስፈራ ድምፅ ሰምተናል፤ የፍርሃት ነው እንጂ የሰላም አይደለም። ጠይቁ፥ ወንድ ይወልድ እንደሆነ ተመልከቱ፤ ስለ ምን ሰው ሁሉ እንደ ወላድ እጁን በወገቡ ላይ አድርጎ ፊቱም ሁሉ ወደ ጥቁረት ተለውጦ አየሁ? ወዮ! ያ ቀን ታላቅ ነውና፥ እርሱንም የሚመስል የለምና፤ ያ የያዕቆብ መከራ ዘመን ነው፥ ነገር ግን ከእርሱ ይድናል። በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ቀንበርን ከአንገትህ እሰብራለሁ፥ እሥራትህንም እበጥሳለሁ፥ ከእንግዲህ ወዲህ ለሌላ አትገዛም፤ ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር ለማስነሣላቸው ለንጉሣቸው ለዳዊትም ይገዛሉ እንጂ ሌሎች አሕዛብ እንደገና አይገዙአቸውም" በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል (ኤር. 30፡5-9)።

## ♦ የመመለሱን ተስፋ የሚፈጽመው አዲስ መንግሥት ይሆናል

በዳዊት ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ የተነገረለት ኢየሱስ ከተመለሰ በኋላ፥ በአሕዛብ ላይ በመፍረድ እስራኤላውያንን ይታደጋል። ከዚህ በኋላ ነው የመመለሳቸው ሂደት ለመጨረሻ ጊዜ የሚፈጸመው። ስለ እስራኤል መመለስ የተነገረው ትንቢት በዘመናችን በመፈጸም ላይ ነው። የመመለሳቸው ተስፋ ሙሉ በሙሉ የሚፈጸመው ግን በሕይወት ያሉ እስራኤላውያን ሁሉ ተሰብስበው (በታላቁ መከራ ዘመን አይሁዳውያን በብዛት ስለሚያልቁ ቁጥራቸው በጣም ይቀንሳል)፥ በሺህ ዓመቱ ግዛት የሰላምና የብልጽግና ዘመን በፍልስጥኤም ከተመሠረተ በኋላ ነው። ብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን ነቢያትም ስለዚህ ዘመን ተናግረዋል።

ነቢዩ ኤርምያስ አይሁድ ባልሆኑ ሕዝቦች ላይ ስለሚከተለው ፍርድ ከተነበየ በኋላ፥ ከእስራኤል አምላክ የተቀበለውን መልእክት እንዲህ ሲል አመልክቷል፦

> "የመንጋዬንም ቅሬታ ካባረርኋቸው ምድር ሁሉ ወደ በረታቸው ሰብስቤ እመልሳቸዋለሁ። እነርሱም ያፈራሉ፤ ይበዛማል። የሚጠብቋቸውን እረኞች አስነሣላቸዋለሁ፤ ዳግመኛም አይፈሩምና አይደነግጡም። ከእነርሱም አንድ አይጎድልም፥ ይላል እግዚአብሔር ።
>
> "እነሆ፥ ለዳዊት ጻድቅ ቁጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፤ እርሱም እንደ ንጉሥ ይነግሣል፤ ይከናወንለታልም፤ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል። የሚጠራበት ስም እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው" (ኤር. 23፡3-6)።

የመጨረሻው የእስራኤል መመለስ የሚፈጸመው ፍርድ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ ነቢዩ ሕዝቅኤልም በተመሳሳይ ትንቢቱ ተናግሯል። ትንቢቱ፥ ይህ በመጨረሻ የሚጠናቀቀው ልክ ከፍርድ ጊዜ በኋላ እንደሆነ እና የመመለሱ ፍጻሜም በሕይወት ያሉ አይሁዳውያንን ሁሉ ወደ ምድሩ እንደሚያመጣቸው ግልጥ አድርጓል። "እኔም ወደ አሕዛብ አስማርኬአቸዋለሁና፥ ወደ ገዛ ምድራቸውም ሰብስቤአቸዋለሁና፥ እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው እንደሆንሁ ያውቃሉ፤ በዚያም ከእነርሱ አንድ ሰው ከእንግዲህ ወዲህ አልተውም" (ሕዝ. 39፡28)።

## ♦ መድረኩ ሲመቻች

የአሁኑ የእስራኤል ወደ ምድሯ መመለስ ወደፊት በተከታታይ ለሚፈጸሙ ሁኔታዎች መድረክ እያመቻቸ ነው። እስራኤል የአሕዛብ ዘመን

ከማብቃቱ በፊት እንደገና መንግሥትዋን እንደምትመሠርት ትንቢቶች በግልጥ ያሳያሉ። ነገር ግን አይሁድ ያልሆኑ ሕዝቦች የእስራኤልን ዕጣ-ፈንታ እስከ መጨረሻው የፍርድ ሰዓትና የመከራ ጊዜ እንደሚቆጣጠሩ ተገልጧል። ኢየሱስም "የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች" ብሎ አስጠንቅቆ ነበር (ሉቃስ 21፥24)።

ቀጣዩ አስገራሚ ሂደት ደግሞ፥ ኢየሩሳሌምን ለመቆጣጠርና ጥቂት ምድር ለፍልስጥኤም ዓረቦች ለማስለቀቅ የሚደረገውን ውጣ ውረድ ያካትታል። ሦስት ሚሊዮን በሚያህሉት የተፈናቀሉ ፍልስጥኤማውያን ምክንያት፥ ይህ ትግል ሊፈነዳ ይቃረባል። ብዙዎቹ ባጎራባች ዓረብ አገሮች ለስደትና ለግዞት ተዳርገዋል። የፍልስጥኤም ሽምቅ ተዋጊ ቡድኖች ከስደተኞች ጎራ በመውጣት ጥቃት መፈጸማቸው፥ ሰላም ፈላጊና ለዘብተኛ የሆኑ ዓረቦች ለሰላም መፍትሔ ለማግኘት ድርድር እንዳያደርጉ እንቅፋት ሆኖባቸዋል።

የዓረብ መሪዎች ከፍልስጥኤም ጋር ያልተረጋጋ ኅብረት ቢያደርጉም፥ ከብጥብጥ ነጻ ሆነው አያውቁም። በጥቅምት ወር 1974 ዓ.ም. በራባት [Rabat] የተሠየመው የዓረብ ጉባኤ ለአንድነት ሲባል መፍትሔ አቅርቦ ነበር። በኃይል የተያዘው የምዕራብ ዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ነጻ የፍልስጥኤም አገር ሆኖ በፍልስጥኤም ነጻ አውጪ ድርጅት (ፒ.ኤል.ኦ.) እንዲተዳደር ወስነው ነበር። ከእስራኤል ጋር ለመደራደር ያመች ዘንድም በ1975 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ የስደት መንግሥት እንደሚመሠረት ተስማሙ።

ከ1974 ዓ.ም. ጀምሮ የምዕራቡ ዳርቻ ተደጋጋሚ ግርግር የታየበትና እስከ 1990ዎቹ ዓመታት ድረስም የብዙዎችን ትኩረት የሳበ ክልል ሆኖ ቆይቷል። እስራኤል አዳዲስ መንደሮች መመሥረቷን ስትገፋበት ፍልስጥኤሞች ደግሞ ተቃውሟቸውን አላቋረጡም። እስራኤል ምዕራባዊውን የዮርዳኖስ ዳርቻ የያዘችው በ1967 ጦርነት እንደነበር ይታወሳል። ስለሆነም እንደ ሕጋዊ መብቷ አድርጋ ነው የምትመለከተው። አብዛኛው ዓለም፥ አሜሪካንን ጨምሮ፥ የምዕራቡን ዳርቻ ለሌላ መንግሥት እንድትሰጥ ጫና ሲያደርጉባት ቢቆዩም፥ ጥረቱ ለችግሩ ውል ያለው መፍትሔ ሊሆን አልቻለም።

ፍልስጥኤምንና ኢየሩሳሌምን ለመቆጣጠር የሚደረገው ትግል በግልጥ እንዲቀጥል መድረኩ ተከፍቷል፤ ቢሆንም ሽምቅ ተዋጊዎች የሚያደርሱት አልቂትና የበቀል እርምጃ በመካከለኛው ምሥራቅ አዲስ ጦርነት እንዲነሣ ምክንያት ሊሆን ሲችል፥ እስራኤል ከግብፅ ጋር ያላት የሰላም ውል ለጊዜውም ቢሆን ጦርነቱ እንዳይነሣ ተከላክሏል። ሳዳም ሑሴን በነሐሴ 1990 ኩዌትን የወረሩበት ምክንያትም እዚያ፥ ማለት ኩዌት ሆነው እስራኤልን ለማጥቃት ነበር።

ምናልባት ለዘብተኛ ዓረቦችና አውሮፓውያን አጋሮቻቸው ሀብትና ኃይላቸውን አስተባብረው የሚወስዱት የኃይል እርምጃ ብቻ ይሆናል፥ እንዲያ ያለ ብቸኛ መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለው። ይህን ሰላም ተግባራዊ የሚያደርጉ አዳዲስ መሪዎችም ይነሣሉ። ይህ የይስሙላ ሰላምና ብልጽግና፥ ዓለም እስከዛሬ ላላየችው አረመኔ መንግሥት መነሣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

# 6

# የነቢያት ከተማ

## ♦ የተከበሩ ትዝታዎች

ዓለም ለመጨረሻ ጊዜ በሚያደርገው ትግል ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ አገሮች ኒውዮርክ፥ ሞስኮ፥ ፓሪስ፥ ፔኪንግ ወይም ካይሮ አይደሉም፤ ኢየሩሳሌም ናት። አደባባዮችዋም ሆኑ የተቀደሱ ስፍራዎቿ ትዝታ ቀስቃሾች ናቸው። ዘመናዊቷ ኢየሩሳሌም የተመሠረተችባቸው ድንጋዮችና ፍርስራሾች ያለፉ ወረራዎችን ያሳስቡናል፤ ወደፊት ሊኖር የሚችለውን የጦርነት ሥጋትም ያስገነዝቡናል። ያም ሆኖ እስራኤል የከበረ ተስፋ አላት። ወርቃማዎቹ የዳዊትና የሰሎሞን ዘመን ትዝታዎችና የነቢያት መልእክቶች ዛሬም በቅድስቲቱ ከተማ ያስተጋባሉ። ስለሚመጣው ኅዘንና ስለ አይሁድ ሕዝብ መበተን የተነገረው ትንቢት ተፈጽሞአል፤ የልቅሶ ግንብ በሚባለው ስፍራ እያነቡ መታሰቢያውን አሁንም ይዘክሩታል። ኢየሱስ ራሱም ቢሆን ከተማይቱን ስለሚጠብቃት ጥፋት በትንቢቱ ተናግሮ ነበር። ስለሚደርስባት መፈራረስም አልቅሶላታል። እነዚህ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች የወደፊቱን ዓለም ሁኔታ ለመረዳት ዓይነተኛ ቁልፎች ናቸው።

## ♦ የፍጻሜው ከተማ

በክርስቲያኖች፥ በአይሁዶችና በዓረቦች የምትከበረው ኢየሩሳሌም የዓለምን ስሜት የሳበች የሃይማኖት ማዕከል ሆናለች። ይህ ኢየሱስም ሆነ ነቢያት አስቀድመው የተነበዩት ነገር ነው። እንግዲህ ከእነዚህ ትንቢቶች አንጻር ስንመለከተው፥ ዘላቂ ሰላምን በኢየሩሳሌም ለማስፈን የሚደረገውን ድርድርና ውይይት ምክንያት መረዳቱ አያዳግተንም። ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊ፥ ኅላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በአንድነት የተጣመሩ ሲሆኑ፥ እነዚህም ለመካከለኛው ምሥራቅ ሰላምን ለማስፈን ኢየሩሳሌምን ማን ይቆጣጠር የሚለውን ጥያቄ በጣም ወሳኝ አድርገውታል። ይህ ሁኔታ ነው ከተማይቱን ለመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም ወሳኝ ስፍራ እንድትሆን ያደረጋት። ምንም እንኳን አልፎ አልፎ

ትኩረት ቢሰጣቸው፥ የሲና ባሕረ-ገብ መሬት፥ የጎላን ኮረብታ፥ ወይም ምዕራባዊ ዳርቻ ይህን ያህል አንገብጋቢ ስፍራዎች አይደሉም።

በኢየሩሳሌም ላይ የሚነሣው ጦርነት እንደ ሰደድ እሳት ዓለምን ሁሉ ሊያዳርስ ይችላል። ምናልባትም ዓለም አቀፍ የሰላም ድርድር ማድረግና በአካባቢው ያሉ ኃይላት እንዲቀበሉት ማስገደድ ብቸኛው መፍትሔ ይሆናል። ተቃራኒ የአሳብ ፍጭቶችን ጸጥ ማድረግ የሚቻለውም በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ኢየሩሳሌምን ለመቆጣጠር በየጊዜው የሚደረገው ሃይማኖታዊ ግጭትም ከመጨመሩ ባሻገር ዓረቦች መቅደሱ የነበረበትን ስፍራ እጃቸው ለማግባት ተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርበዋል። በእስራኤል በኩል ደግሞ፥ የጥንቱን ቤተ መቅደስ እንደገና ለመሥራት ሙከራ እንደሚደረግ ትንቢቱ ይጠቁማል። የመካከለኛው ምሥራቅን ወቅታዊ ሁኔታ በተጨባጭ ለመረዳት፥ ታሪክንና ትንቢትን በጥምር ማወቅና ሂደቱን ማገናዘብ ይገባል። የነቢያት ከተማ የሆነችው ኢየሩሳሌም በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የተተነበዩትን የዳንኤልንና የኢየሱስን ትንቢቶች ለመረዳት ቁልፍ ሚና አላት። በትንቢት ወደተወሰነላት ፍጻሜ መዳረሻ በመገስገስ ላይም ትገኛለች።

## ♦ ጥንታዊው የኢየሩሳሌም ታሪክ

የኢየሩሳሌም ከተማ ምሥረታ ባለፉት የዘመናት ምሥጢር የተሸፈነ ነው። ሳሌም የተሰኘው ስሟ መጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጠቀሰው በዘፍጥረት 14፡18 ውስጥ ነው። መልከ ጼዴቅ የዚህች ከተማ ንጉሥ ነበር። በግብፅ የተገኘው የቴል ኤል አማርና ሰሌዳ [Tell Amarna Tablets] ይህን ያረጋግጥላታል። ሳሌም የተሰኘው ስሟ በኋላ "ኢየሩ" ከሚለው ጋር ተጋጥሞ በዚህ ስም መጠራት ከጀመረች የአራት ሺህ ዓመታት ታሪክ አላት። ኢየሩሳሌም ከማንም የዓለም ትልቅ ከተማ ይልቅ በብዙ ሰዎችና ትውልዶች ስትታወቅ ኖራለች።

## ♦ የእስራኤል ሕይወትና ተስፋ ማዕከል

በይሁዳ ኮረብቶች ላይ የተመሠረተችውና በሜዲትራኒያን ባሕር ዳርቻና በዮርዳኖስ ወንዝ መካከል የምትገኘው ኢየሩሳሌም፥ ለቁጥር የሚታክት ሁከት የታየባትና ያስተናገደች ከተማ ናት። ከተማዋ ዝናን ማግኘት የጀመረችው በአሥረኛው ዓመተ ዓለም የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ዳዊት መዲናው ካደረጋት ጊዜ አንሥቶ ነበር። የገናናዎቹ ነገሥታት፥ የዳዊትና የሰሎሞን ግዛቶችም ድንቅ ውበትና ሀብት ወደ ከተማይቱ እንደ ጎርፍ አመጡ። ከዚህ ሁሉ እጅግ ጎልቶ የሚነገርለት፥ ዝነኛው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ተሠርቶ ያለቀበት ዘመን ነበር።

ሃይማኖታዊ መነቃቃትና ውድቀት ሲከሡትባት ወደኖረችው ወደዚህች ከተማ ነበር፥ ነቢያት የተግሣጽ መልእክታቸውንና የሚጠብቃትን ከቡር ተስፋ ለማወጅ የመጡት።

ይህች ጥንታዊት ከተማ በተደጋጋሚ የጦርነት ማዕበል ተመታለች፤ ሙሉ በሙሉ ወድማም እንደገና አንሰራርታለች። ወራሪዎቿ የታወቁ ጥንታዊ መንግሥታት ጭምር ነበሩ። አውራ ጎዳናዎቿ በግብፃውያን፥ አሦራውያን፥ ባቢሎናውያን፥ ፋሪሳውያን፥ ሰሉሲዳውያን፥ ሮማውያን፥ በመስቀል ጦርነት ተዋጊ ክርስቲያኖች፥ ሳራሰናውያን፥ ማመሉካውያን፥ እና በኦቶማን ቱርኮች ሲረገጡ ኖረዋል። እንዲህ በሚያስደንቅና ልብ በሚነካ ትዝታ የተሞሉ ከተማዎች ምናልባት ቢኖሩ በጣም ጥቂት ይሆናሉ።

## ♦ ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጣው መሢሕ

አይሁዶች የመሢሑን መምጣት ለምዕተ ዓመታት ሲጠባበቁ ኖረዋል። የእስራኤልና ዓረቦች አባት የሆነው አብርሃም በተሰጠው ትልቅ ተስፋ መሠረት የምድሪቱ ወራሾች የልጅ ልጁ የሆነው የያዕቆብ ዘሮች ሊሆኑ ይገባ ነበር። ምድሪቱ ወዲያውኑ የሚወርሷት ባትሆንም፥ ለብዙ ምዕተ ዓመታት በስደት ከኖሩ በኋላ ተመልሰው ይኖሩባታል። ይህ የተፈጸመው ያዕቆብና ቤተሰቡ ወደ ግብፅ ከሄዱና ታላቅ ሕዝብ ከሆኑ በኋላ ነበር።

እስራኤላውያን ከግብፅ ወጥተው ተስፋ የተገባላቸውን ምድር በከፊል እጃቸው ማድረጋቸው በመጀመሪያዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተገልጧል። የእግዚአብሔርን ሕግጋት ባለመጠበቃቸው ዳግመኛ ከአገራቸው እንደሚሰደዱም ነቢያት ተንብየው ነበር። አሦራዊያን ከአሥራ ሁለቱ ነገድ አሥሩን በምርኮ ወሰዱ። ከአንድ መቶ ሀያ አምስት ዓመት በኋላ ደግሞ፥ ባቢሎናውያን የቀሩትን ሁለት ነገዶች ወሰዱ፤ ኢየሩሳሌምንም አፈረሷት። ነገር ግን ነቢያት እንደተነበዩት ሁሉ በስድስተኛው ዓመተ ዓለም እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ቤተ መቅደሱና ከተማዋ እንደገና ተሠርተው፥ እንደ ወትሮው እስራኤል የሃይማኖትና ፖለቲካ ሕይወት ማዕከል ሆነች። ቅን የሃይማኖት ሰዎችና አይሁዶች በብሉይ ኪዳን ነቢያት የተነገረውን በመረዳት በእግዚአብሔር የተመረጠላቸው መሢሕ፥ አዳኝና መሪ አንድ ቀን ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣል ብለው ያምኑ ነበር።

በ63 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በሮማውያን እጅ ከወደቀች ወዲህ ለእስራኤላውያን አዲስ የጭቆናና የስደት ምዕተ ዓመታት ተጀመሩ። የሮማውያን ወረራ አስጨናቂ ቀንበር ሆነባቸው። በሃይማኖት መሪዎቻቸው መካከል መከፋፈል ቢኖርም፥ በነቢያቱ ትንቢት መሠረት ንጉሣቸው የሆነው መሢሕ

መጥቶ በዳዊት ዙፋን ላይ በመንገሥ ሕዝቡን ከጠላቶቻቸው የሚታደግበትን ዘመን በናፍቆት መጠበቃቸው አልቀረም።

በአዲስ ኪዳን ወንጌላት እንደተገለጠውና ነቢዩ ሚልክያስም እንደተነበየው ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ በምትገኘው ቤተልሔም ከተማ ተወለደ (ሚክ. 5፡2)። በአይሁድ ሥርዓት መሠረት የኢየሱስ እናት ማርያምና ዕጮኛዋ ዮሴፍ የሙሴ ሕግ የሚጠይቀውን መሥዋዕት ሁሉ አሟልተው ሕፃኑን ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት።

የልጅነት ጊዜውን በናዝሬት ካሳለፈ በኋላ፥ 12 ዓመት ሲሆነው ከቤተሰቡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሄዶ በጊዜው የነበሩትን ምሁራንና የሃይማኖት መሪዎች በሥነ-መለኮት እውቀቱ አስደነቀ።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ ወደ ናዝሬት በመመለስ የነቢይነት ተልዕኮውን እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ማንም ሳያውቀው በግምት ለሀያ ዓመታት ያህል ኖረ።

## ♦ ተቀባይነት ያጣው ንጉሥ

ነቢያት የተናገሩለት መሢሕ እርሱ መሆኑ በመጥምቁ ዮሐንስ ከገለጠ በኋላ ኢየሱስ የብዙዎችን ትኩረት ስቦ ነበር። የእስራኤል ሃይማኖት እምብርት በሆነችው ኢየሩሳሌም የነበሩ ሊቀ ካህናትና መሪዎች ግን፥ ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረውን በጥርጣሬ ነበር የተመለከቱት። በትምህርቱና በአስገራሚ ተአምራቱ የተደነቁ ተራ ሰዎች ግን በብዛት ተከተሉት። በኢየሱስና በአይሁድ መሪዎች መካከል የከረረ ክርክር የማይቀር ነበር። ለሦስት ዓመታት እየተዘዋወረ ባስተማረ ጊዜ፥ በእርሱና በእስራኤል የሃይማኖት መሪዎች መካከል ብርቱ ቅራኔና አለመጣጣም ተፈጥሯል።

በብሉይ ኪዳን በተነገረው ትንቢት መሠረት ወደ ኢየሩሳሌም የሚገባበትን የአህያ ውርንጭላ እንዲያመጡለት ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው። በእሷ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም ሲገባ፥ ከዘመናት በፊት በነቢዩ ዘካርያስ፡-"አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በይ፤ እነሆ፥ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያይቱ ግልገል በውርንጭላይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል" (ዘካ. 9፡9) ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ።

ልክ ዘካርያስ እንደተነበየው ኢየሱስ ኢየሩሳሌም በክብር ገባ። የተከተሉት ሕዝቦች፥ ከኢየሩሳሌም ውጪና ከከተማም የመጡት፥ በእስራኤል ላይ የሚነግሠው የተተነበየለት መሢሕና ተስፋ የተገባላቸው የዳዊት ልጅ እርሱ መሆኑን በደስታ እየጮኹ ተቀበሉት። የማቴዎስ ወንጌል ይህን አስደናቂ ትዕይንት ሲገልጥ፡-

"የሚቀድሙትም ሕዝብ የሚከተሉትም ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር። ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ መላው ከተማ ይህ ማን ነው? ብሎ ተናወጠ። ሕዝቡም ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ" ይላል (ማቴ. 21፡9-11)።

የእስራኤላውያን ኢየሱስን ነቢይና መሢሕ አድርጎ በክብር መቀበል የሃይማኖት መሪዎችን አስደንግጧቸው ነበር። ከዚህም የተነሣ "ደቀ መዛሙርትህንና 'ንጉሥ ነው' እያሉ የሚያውጁልህን ዝም እንዲሉ ንገራቸው" ብለው ኢየሱስን ጠየቁት። እርሱ ግን "እላችኋለሁ፥ እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ" በማለት የግሣጼ መልስ ነበር የሰጣቸው (ሉቃስ 19፡40)።

## ♦ ኢየሱስ የሃይማኖት መሪዎችን ተቃወመ

የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን መጥላታቸው ይበልጥ ይፋ ሆነ። ከእነርሱ ይልቅ ተወዳጅነትን በማግኘቱ ቀንተው ሊገድሉት ዕቅድ ያወጡ ጀመር። እርሱ ደግሞ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በአደባባይ ልታይ ልታይ ማለታቸውን ግብዝነት ነው በማለት ነቀፋቸው። ከማቴዎስ 23 ለመረዳት እንደሚቻለው "ግብዞች" እና "ዕውሮች የምትመሩ ዕውሮች"፥ "በውጭ አምረው የሚታዩ፥ በውስጥ ግን በሙታን አጥንትና ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮች"፥ "የነቢያት ሁሉ ገዳዮች" አላቸው። "እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?" (ቁ. 33)። "ደንቆሮዎችና ዕውሮች" (ቁ. 17) በማለት በተደጋጋሚ ነቀፏቸው ነበር። እናከብረዋለን የሚሉትንም ሕግ ራሳቸው ያፈርሱት እንደነበር በግልጥ ነገራቸው። ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ በማልቀስ ነበር ግሳጼውን የጨረሰው፡-

> "ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ! ነቢያትን የምትገድል፥ ወደ እርሷ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶቿን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም? እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል። እላችኋለሁና በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም" (ማቴ. 23፡37-39)።

## ♦ የኢየሩሳሌምን መጥፋት ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ

ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ በክብር መግባት እና ይፋ በመውጣት ላይ የነበረውን የአይሁድ መሪዎች ጥላቻ ተመልክተው ነበር። ሰዎችንና ከተማይቱን ከልብ ይወዳቸው እንደነበርም ተረድተዋል።

ቅድስቲቱ ከተማ በቅርቡ እንደምትጠፋ አውቆ ወደ እሷ እየተመለከተ እንዲህ በማለት አለቀሰላት።

"ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ፥ አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል፤ ወራት ይመጣብሻልና፥ ጠላቶችሽም ቅጥር ይቀጥሩብሻል፤ ይከቡሻልም በየበኩሉም ያስጨንቁሻል፤ አንቺንም በአንቺም ውስጥ የሚኖሩ ልጆችሽን ወደ ታች ይጥላሉ፤ በአንቺ ውስጥም ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተውም፤ የመጎብኘትሽን ዘመን አላወቅሽምና" (ሉቃስ 19፡42-44)።

ይህ ትንቢት አርባ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተፈጸሟል። በአይሁድና በሮማውያን መካከል ለብዙ ዓመታት ብጥብጥና ጦርነት ከተካሄደ በኋላ የሮማውያን ወታደሮች ወደ ኢየሩሳሌም ገስግሰው፥ ዙሪያዋን በመክበብ እጃቸውን እስከሚሰጡ ሕዝቡን አስራቡ፤ ድልም አደረጓቸው፤ ከተማይቱንም አቃጠሏት፥ ዘረፏት፤ በዚያ ዘመን እስከ ሚሊዮን የሚደርስ ሕይወት እንደጠፋ ተገምቷል። ከዚህም በላይ የእስራኤል ጠላቶች በሄሮድስ ከስድስት ዓመታት በፊት ተጠናቅቆ የነበረውን ቤተ መቅደስ ብርቅና ድንቅዬ የሆኑ ድንጋዮች ከኢየሩሳሌም ደቡብ ምሥራቅ ባለው ሸለቆ ውስጥ ጣሉ። የከርሠ-ምድር ተመራማሪዎች [አርኪዮሎጂስቶች] ዛሬም የቤተ መቅደሱን ፍርስራሽ ድንጋዮች በማግኘት ላይ ናቸው። በ70 ዓ.ም. ሌላ ዓይነት አስጨናቂ ስደት በተንከራታቾቹ አይሁዳውያን ላይ ቀጥሎ እስከ ሀያኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ተሠቃዩ።

## ♦ የደቀ መዛሙርቱ ጥያቄዎች

ደቀ መዛሙርቱ ምን እንደሚሆንና ኢየሱስ ምን ለማለት እንደፈለገ በሚገባ አልተረዱም ነበር። እንዲሁም የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን ባለመቀበላቸው ግራ ገብቷቸው ነበር። የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ኢየሱስን ንጉሣቸውና አዳኛቸው አድርገው ቢያቀርቡትም፥ በአንጻሩ ደግሞ የመሪዎቹ አለመቀበል ከትንቢቱ ጋር አልጣጣም አላቸው። ወደ ኢየሩሳሌም በክብር ከመግባቱ አንጻር የአይሁድ መሪዎች ተቃውሞ መከፋቱ ለደቀ መዛሙርቱ እንቆቅልሽ ሆነባቸው።

ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም በመውጣት የቄድሮንን ሸለቆና የደብረ ዘይትን ተራራ አቋርጦ ወደ ምሥራቅ ከሄደ በኋላ አራቱ ደቀ መዛሙርት ማለት፥ ጴጥሮስ፥ ያዕቆብ፥ ዮሐንስና እንድርያስ ለብቻቸው መጥተው እንዲህ በማለት ጠየቁት፥ "ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? ይህስ ሁሉ ይፈጸም ዘንድ እንዳለው ምልክቱ ምንድር ነው?" (ማር. 13፡3-4)። ጥያቄያቸው ስለ መጨረሻው ዘመን እንደነበረ የማቴዎስ ወንጌል እንዲህ በማለት ጨምሮ ይገልጣል፥ " ይህ መቼ

ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው?" (ማቴ. 24፡3)። በእርግጥ፥ ሁለት ጠቃሚ ጥያቄዎችን ነበር ያቀረቡለት። የመጀመሪያው ኢየሩሳሌም መቼ ትጠፋለች? የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ፥ ይህ ዘመን መቼ አብቅቶ መንግሥትህ ለእስራኤል ይመጣል? የሚሉ ነበሩ።

ደቀ መዛሙርቱ ስለ ትንቢት ያላቸውን አመለካከት እያገናዘቡ በማስተካከል ስለ ኢየሱስ የተነገሩ ትንቢቶች በሙሉ መጀመሪያ በመጣበት ወቅት እንዳልተፈጸሙ እየተረዱ ሄዱ። መከራና ሥቃይ ነበር ያኔ ኢየሱስን የጠበቀው። ኢየሩሳሌም በቅርቡ የምትፈርስ ከሆነ ያ ታላቅ የክብር መንግሥት እንዴት ሊመጣ ይችል ይሆን? አሕዛብ አይሁዳውያንን ማሠቃየታቸውን ይቀጥላሉ ማለት ነው? ይህ ሁሉ እንዴት ያበቃል?

## ♦ ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄዎች የኢየሱስ መልሶች

ኢየሱስ የሰጣቸው መልስ በማቴዎስ፥ በማርቆስና ሉቃስ ወንጌሎች እንደሰፈረው፥ በጥንቃቄ ሲጠና ስለ ሁለት በተለያዩ ጊዜያት ማለትም፥ ወደፊት በኢየሩሳሌም ውስጥ ሊከሠቱ ስለሚችሉ ድርጊቶች እንደተናገረ ግልጥ ይሆናል። የመጀመሪያው ትንቢት የተፈጸመው በሉቃስ 21፡5-24 በተነገሩት ማስጠንቀቂያዎች መሠረት በ70 ዓ.ም. ቤተ መቅደሱ በፈረሰ ጊዜ ነበር። የሁለተኛው ክፍል ትንቢቶች የሚያመለክቱት፥ ቤተ መቅደሱ ከፈረሰ ጀምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ወደ ምድር እስከሚመጣ ድረስ በዚህ ዘመን ብዙ ተአምራዊ ምልክቶች እንደሚፈጸሙ ነው (ሉቃስ 21፡25-28)።

ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም መውደም የተናገረው ትንቢት የተፈጸመ መሆኑን ዛሬ በቀላሉ እንረዳለን። ኢየሱስን ያልተቀበሉ የአይሁድ መሪዎች ለኢየሩሳሌም መጥፋት ምክንያት ሆነዋል። የሮማውያን ወታደሮች ከተማይቱን ይከቧታል፤ ሕዝቧን ይገድላሉ፤ ከተማይቱን ያቃጥሉና ቤተ መቅደሷን ያፈርሱታል። ይህ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ እንደገና ለአዲስ ስደትና መከራ የሚዳረግበት ይሆናል። የዘመኑን ሁኔታ ዝርዝር ኢየሱስ በማቴዎስና በማርቆስ ወንጌል ገልጦታል።

## ♦ የአሁኑ ዘመን በኢየሱስ አገላለጥ

በማቴዎስ 24፡4-14 ኢየሱስ የዚህን ዘመን ዘጠኝ ዋና ዋና ባሕርያት በጥቅሉ ተናግሯል። እነርሱም፦

1. ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚሉ ይመጣሉ፤ እነዚህ ሰዎች ሐሰተኞችና አስመሳዮች ናቸው፥ 2. "ጦርነቶችና የጦርነት ወሬዎች"፥ 3. ረኃብ፥ 4. "ቸነፈር" (ማቴ. 24፡7)፥ 5. የምድር መናወጥ፥ 6. የብዙዎች

ሰማዕት መሆን፥ 7. ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፥ 8. ከዓመፅም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር ይቀዘቅዛል፥ 9. የእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች (ወንጌል) በዓለም ሁሉ ይሰበካል። ያለፉት አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዓመታት የዚህን ትንቢት ትክክለኛነት መስክረዋል። ኢየሱስ የሚናገረውን ያውቅ ስለነበር ትንቢቶቹ እውነት ናቸው።

ክርስቶስ በትክክል እንደተነበየው ዘመናችን የሃይማኖት ትርምስና ማታለል የሞላበት ነው። ተደጋጋሚ ጦርነት የደረሰ ከመሆኑም ሌላ አሁንም ቢሆን የዘመኑ ትውልድ በማያቋርጥ የጦርነት ፍርሃት ተጨንቋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች በረኃብና በወረርሽኝ ሞተዋል። ይህ የሀያኛው ምዕተ ዓመት ረኃብ ምናልባት ከምንጊዜውም የከፋና ብዙ ሰዎችን ለእልቂት የዳረገ ሳይሆን አይቀርም። በተለይ በአይሁድ ላይ የጠነከረው የሃይማኖት ሥቃይ የእነዚህ ዓመታት መታወቂያ ነው። ቤተሰቦች በእምነት ምክንያት ሲከፋፈሉ፥ በሥልጣን ላይ ያሉ ገዥዎችም የማይስማማቸውን እምነት ከምድረ-ገጽ ለማጥፋት አያሌ ሙከራ አድርገዋል። በዚህ ጠንቅ ነው ባለፉት አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዓመታት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች የተጨፈጨፉት።

## ♦ የኢየሱስ ትንቢቶች ትክክለኛነት

በየዘመኑ የተነገሩ ትንቢቶችን በዝርዝር ስናጠና በትክክል መፈጸማቸው ያስደንቀናል። ማንም ቢሆን እግዚአብሔር ካልገለጠለት የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመታት የሚደርሱትን ሁኔታዎች መተንበይ እጅግ ያዳግተዋል። የኢየሱስ ትንቢቶች ግን ታሪክ እንዳረጋገጠው ፍጹም ናቸው። ይህ ማለት ግን የተናገራቸው ትንቢቶች ሁሉ ተፈጽመዋል ማለት አይደለም። የዘመን መጨረሻ ወደፊት እንደመሆኑ፥ የተፈጸሙት የኢየሱስ ትንቢቶች ቃል በቃል መከናወናቸውን ካረጋገጥን፥ ስለ ወደፊቱ የተናገራቸውን ትንቢቶች ፍጻሜስ መጠበቁ ያዳግተናል? እነዚህ ጥያቄዎች ዛሬም በአስተዋይና አርቆ አሳቢ ሰው አእምሮ ይጉላላሉ። ታዲያ ትንቢቶቹ ላይ አለመመሥረት ወደፊት የሚሆነውን ነገር በግምት ብቻ መናገር ይሆናል። ለሚሆነው ሁሉ ብቸኛው የእውነት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የዓለም የወደፊት ዕድል ምንድነው? የኢየሩሳሌምና የአይሁድ ዕጣ-ፈንታስ? ኢየሱስ ዝርዝር ትንቢቶችን ተናግሮ፥ ሰሚዎቹ ኢየሩሳሌምን በአንክሮ እንዲመለከቱ አስጠንቅቋቸዋል።

# 7

# ኢየሩሳሌምን በአንክሮ ተመልከቱ

## ♦ የኢየሩሳሌም የወደፊት ዕጣ ምንድነው?

ከአንድ ትውልድ በፊት የነበሩ አንዳንድ ሰዎች እስራኤል እንደገና እንደ መንግሥት ለመቋቋም ያላት ዕድል ያበቃለት እንደሆነ አስበው ነበር። አይሁዶች በግላቸው በመንፈስ ቢነቃቁም ወደ መሬታቸው በፍጹም አይመለሱም፥ ኢየሩሳሌምንም አይዙም፤ የገናናዎቹ ነቢያት ትንቢቶችም በፍጹም አይከናወኑም ብለው ነበር። አይሁዶች መሲሓቸውን ስላልተቀበሉት እነርሱንም እግዚአብሔር አይቀበላቸውም የሚል ነበር የእነዚህ ሰዎች ድምዳሜ።

ዛሬ ግን ስለ እስራኤል የተነገረው ተስፋ በጭራሽ አይፈጸምም ለማለት አንችልም። ሐቁ እንደሚያሳየው እስራኤል ወደ ምድሯ ተመልሳ የራስዋን ሉዓላዊ መንግሥት መሥርታለች። ጥንታዊ መዲናዋን ኢየሩሳሌምንም ለመቆጣጠር በቅታለች። ይሁን እንጂ የኢየሩሳሌም የወደፊቱ ዕጣ ምን ይሆናል? ወደ ፍጻሜው ስለማምራታችን የትንቢት ቅደም ተከተል የሚጠቁመንስ ምንድን ነው?

ብዙዎች፥ እስራኤል መንግሥቷን በከፊል ብታስመልስም፥ ገናናው የሰላምና የጽድቅ መንግሥት ገና በምድር እንዳልተመሠረተ ያመለክታሉ። አይሁዶች ኢየሱስን እንደ መሢሕ ስላልተቀበሉት ሰላም፥ ደኅንነትና የኢኮኖሚ ብልጽግና አላገኙም ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ፥ አስደናቂው የእስራኤል ወቅታዊ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይዛመድም ሲሉ፥ ሌሎቹ ትንቢቶቹ ዛሬ ተፈጽመዋል ይላሉ። የቱ ነው እውነታው? የኢየሩሳሌምና የእስራኤል የወደፊት ዕጣስ ምንድን ነው?

## ♦ የ1967 ዓመተ ምሕረቱ ጦርነት

እስራኤል በ1948 ዓ.ም. በነጻ መንግሥትነት ከተመሠረተች ወዲህ ምናልባት የ1967 ዓመተ ምሕረቱን የስድስት ቀን ጦርነት የሚመስል አስገራሚ

ሁኔታ አልገጠማትም ማለት ይቻላል። የጥንቷ የአይሁድ ከተማ ኢየሩሳሌም፥ ከ70 ዓ.ም. በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በአይሁዶች እጅ ገባች። እስራኤል ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ ያለውን ግዛት በማከል ተስፋፋች። ይህ አስደናቂ እድገት ለእስራኤል መንግሥት ምሥረታ አስፈላጊነቱ የቱን ያህል ነው?

ብዙዎች በሉቃስ 21፡24 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን አስገራሚ ትንቢት ማስተዋል ጀምረዋል። በዚህ ክፍል፥ "የአሕዛብም ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች" ያለው ስለዚህ ዘመን ነበር። እንደሚታወቀው እስራኤል ጥንታዊት ከተማዋን እጅዋ አድርጋለች። ታዲያ በአሁኑ ጊዜ የአሕዛብ ዘመን ተፈጽሟል ማለት ነው?

ከ1967 ዓ.ም. ወዲህ እንኳን የተከሡቱት ድርጊቶች እስራኤል ኢየሩሳሌምን የያዘቻት ለጊዜው መሆኑን ያመለክታሉ። የገናናው መንግሥቷ ዘመን ገና አልደረሰም። የአሜሪካ መንግሥት ባይረዳት ኖሮ ዙሪያውን የከበባት የዓረብ ዓለም ባሕር ውስጥ ያስምጣት ነበር። በ1973 ዓ.ም. ጦርነት ከጥፋት ልትተርፍ የቻለችው በጊዜው አሜሪካ የጦር መሣሪያ ስላቀበለቻት ነበር። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት፥ የእስራኤል የመጨረሻ የድል ሰዓት የሚሆነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ ሕዝቡን በመታደግ የጽድቅና የሰላም መንግሥት በምድር ሲመሠርት ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሩሳሌምና እስራኤል የወደፊት ዕጣ ምን ያስተምራል? ይህስ በመጨረሻው ዘመን ዓለምን ሁሉ ከሚያሳትፈው ጦርነት ጋር ምን ግንኙነት አለው? የብዙዎች ጥያቄዎች መልስ በነቢዩ ዳንኤል ትንቢት ውስጥ ይገኛል። የሰው ዘር ታሪክ አስደናቂ ፍጻሜ እንዲኖረው የተወሰነ ስለሚመስል፥ እነዚህን ትንቢቶች ማወቅና መረዳት ይህን ፍጻሜና የዓለማችንን ወቅታዊ ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል።

## ♦ የዓለም ታሪክ ንድፈ-አሳብ ከዳንኤል ትንቢት አንጻር

የባቢሎን ጦር አዛዥ የነበረው ናቡከደነፆር በ605 ዓመተ ዓለም በበጋው ወራት ኢየሩሳሌምን ድል አድርጎ ሲይዛት ነቢዩ ዳንኤል ገና ለጋ ወጣት ነበር። ናቡከደነፆር በጊዜው የበርካታ ግዛቶች ንጉሥ እንደመሆኑ፥ በልዩ ችሎታቸው እንዲያገለግሉት የእስራኤልን ወጣቶች እየመረጠ በምርኮ ወደ ባቢሎን መውሰድ ጀምሮ ነበር። ዳንኤልም በዚህ አኳኋን ተወስዶ በባቢሎን ትምህርት ቤት ለተወሰኑ ዓመታት ከሠለጠነ በኋላ ከምርኮኞቹ መካከል ለናቡከደነፆር ግዛት አስተዳዳሪነት ብቁ ሆኖ ተገኘ።

አንድ ቀን ናቡከደነፆር አስፈሪ ሕልም ዓለመ። በሕልሙም ታላቅ ምስል በአልጋው አጠገብ እንደ ሐውልት ተገትሮ አየ። ምስሉም፥ ራሱ ወርቅ፥

ደረቱና ክንዶቹ ብር፥ ሆዱና ወገቡ ነሐስ፥ ጭኖቹ ብረት፥ እግሮቹም እኩሉ ብረት እኩሉ ሸክላ ነበሩ። ናብከደነፆርም ሕልሙ አንዳች መልእክት እንዳለው እርግጠኛ ስለነበር ታወከ።

ሕልም ፈቺዎችንም በፍጥነት አስጠራ። የሕልሙን ፍቺ ብቻ ሳይሆን፥ ያየውንም ትንቢት ጭምር እንዲነግሩት ጠየቃቸው። ይህን ያደረገው ሕልሙ ጠፍቶት ይሁን ወይም እነርሱን ለመፈተን አስቦ፥ እርግጠኞች አይደለንም። የባቢሎን ጠቢባን ሕልሙንም ሆነ ፍቺውን ሊነግሩት ባለመቻላቸው እጅግ ተቆጣ። ሁሉም እንዲገደሉ አዘዘ። ለጊዜው በስፍራው ያልነበረው ዳንኤልም ከጠቢባኑ አንዱ ስለነበር ተፈልጎ እንዲገደል ተወሰነበት።

ዳንኤልና ሁለቱ ጓደኞቹ ይህን ትእዛዝ ሰምተው ቢደነግጡም፥ ዳንኤል ሕልሙንና ፍቺውን ለመናገር እንደሚችል ገልጦ ጊዜ እንዲሰጠው ጠየቀ። ወዲያውም እግዚአብሔር የናቡከደነፆርን ሕልም ከነፍቺው አስታወቀው።

ታላቁ ምስል፥ አራት ታላላቅ የዓለም መንግሥታትን የሚወክል ነበር። በወርቅ የተመሰለው ራስ የናቡከደነፆርን መንግሥት፥ ከእርሱ በኋላ ደግሞ በብር የተመሰለው ሌላ መንግሥት፥ በናስ የተመሰለው ታችኛው ክፍል ደግሞ ሦስተኛውን መንግሥት፥ እግሮቹ እኩሉ በብረት፥ እኩሉ በሸክላ የተመሰሉት ደግሞ አራተኛውን መንግሥት ይወክላሉ። በራእዩ (በሕልሙ) መሠረት ናቡከደነፆር ድንጋዩ የእግሮቹን ምስል ሲመታውና ሲፈጨው አይቶ ነበር። በመከርም ጊዜ በአውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ፤ ነፋስም ወሰደው። ዳንኤል በመጨረሻ በፊቱ የነበረውን ሁሉ የሚያጠፋና ምድርን የሚሞላ አምስተኛ መንግሥት በመንግሥተ ሰማያት እንደሚኖር አመልክቷል። ናቡከደነፆር፥ ዳንኤል በሰጠው የሕልም ፍቺ በመደነቅ እሱንና ጓደኞቹን የመንግሥቱ ከፍተኛ ሹማምንት አደረጋቸው።

ናቡከደነፆር ከሞተ በግምት ከአርባ ዓመት በኋላ ዳንኤል ራሱ ሕልም አየ። በሰባተኛው ምዕራፍ እንደተዘገበው ትንቢቱ በአራት አውሬዎች ተመስሎ በቅደም ተከተል ቀርቧል። ባቢሎን በአንበሳ ሲመሰል፥ ሁለተኛው ሜዶን-ፋርስ ግዛት በታላቅ ድብ፥ ሦስተኛው የታላቁ እስክንድር ግዛት አራት ራሶችና ክንፎች ባሉት ነብር፥ አራተኛው እጅግ አስፈሪና የበረታም የብረት ጥርሶች ባሉት አውሬ ተገልጧል። የሦስቱን መንግሥታት ማንነት ዳንኤል ራሱ በዝርዝር ገልጧል፥ የትንቢቱንም ፍጻሜ አመልክቷል። በጣም የሚያስገርመውና ልዩ ትኩረትም ሊሰጠው የሚገባው ግን፥ አራተኛው መንግሥትና ፍጻሜው ሲሆን፥ ይህንንም ዳንኤል 7፡7-28 ላይ መመልከት ይቻላል።

ነቢዩ (ከምዕራፍ 7-8) በትክክል እንደተነበየው፥ የባቢሎን መንግሥት በሜዶን-ፋርስ ተተካ። ሜዶን-ፋርስም በታላቁ እስክንድር (ግሪክ) መንግሥት

ተተካ። ስለ ሮም አወዳደቅ ታሪክ አይዘግብ እንጂ ስለ አነሣሡ ብዙ ተናግሯል። እነዚህ ትንቢታዊ ዘገባዎች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ ይቀርባሉ።

ሆኖም በዳንኤል ትንቢት ውስጥ ሁለት ያልተፈቱ እንቆቅልሾች አሉ። አንደኛ፥ የአራተኛው መንግሥት መጨረሻ በታሪክ አልተዘገበም። ሁለተኛ፥ አምስተኛውና ከሮም ግዛት የሚቀጥለው መንግሥት ከሰማይ የሚመጣ መሆኑ፥ ተተንብዮ ነበር። እንደ መጀመሪያው ሁሉ፥ የዚህም ፍጻሜ በታሪክ አልታየም። እስከዛሬ ያሉት የነቢዩ ትንቢቶች በትክክል ከተፈጸሙ፥ የወደፊቶቹም ሊፈጸሙ እንደሚችሉ መቀበሉ ያዳግተን ይሆን?

## ♦ በዳንኤል ትንቢታዊ ራእይ ውስጥ ያለው የጊዜ ክፍተት*

እንደ ሌሎቹ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ሁሉ፥ የዳንኤል ትንቢትም እስከ ክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት ድረስ ያለውን ጊዜ ይገልጥና እስካለንበት ዘመን ማብቂያ ያለውን ክፍት ይተውዋል። በድምሩ ከአንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዓመታት በላይ መሆኑ ነው። ክርስቶስ መጀመሪያ እንደመጣ (እንደተወለደ) ትንቢቱ በብዙ መልኩ የተፈጸመና ያበቃ መስሎ ነበር። ያልተፈጸሙ ትንቢቶች ከክርስቶስ ዳግም ምጽዓት በፊት የሚደረገውን ክንውን የሚገልጡ ተደርገው ተወሰዱ። የዚህ ምክንያቱ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የአሁኑን ዘመን ሁኔታ በዝርዝር አለመመልከታቸው ነው። ክርስቶስ ግን እንደ ነቢይነቱ በማቴዎስ 13 እና በማቴዎስ 24፥3-14 ባለው ክፍል በማብራራትና ግልጥ በማድረግ፥ የአሁኑ ዘመን ክንውን ሂደት ሲያከትም፥ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ትንቢት እንደሚፈጸም ገልጧል። ይህ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍጻሜ ክፍተት ጉዳይ ደቀ መዛሙርቱ ጥያቄዎች እንዲያነሡ አድርጓቸው፥ ኢየሱስም ተገቢውን መልስ ሰጥቷቸዋል።

ስለ አሁኑ ዘመን የሰጠው ገለጣ በማቴዎስ 24፥3-14 ባለፈው ምዕራፍ ተዘርዝሯል። ታዲያ ትንቢቱ ስለ ዘመኑ ፍጻሜ ምን አለ? በዮሐንስ ራእይ ከተገለጠው የዘመናችን ከፍተኛ ትንቢታዊ ክንውን ጋርስ እንዴት ይጣጣማል?

## ♦ የዳንኤል ትንቢቶች ማረጋገጫ በዮሐንስ

የራእይ መጽሐፍ ከምዕራፍ አራት እስከ አሥራ ስምንት ባለው ክፍል የዘመኑን ማብቂያና አውዳሚ ድርጊቶች ያስረዳል። ከፍተኛ ችግር እንደሚኖርና ያም ሁኔታ ዓለምን ለታላቅ ጦርነት እንደሚዳርጋት በአጠቃላይ ገለጣ ያስረዳል።

ሐዋርያው ዮሐንስ፥ ዳንኤል ከኖረበት ዘመን ስድስት መቶ ዓመታት በኋላ ነበር ራእዩን የጻፈው። ይሁን እንጂ ስለ ዘመን መጨረሻ ተጨማሪና ተመሳሳይ ዝርዝር ራእዮችን ተመልክቷል። በራእይ ምዕራፍ 13 ላይ

* ገጽ 52 ላይ የቀረበውን ሥዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ።

የተመለከተው፥ ታላቅ የዓለም መንግሥት፥ የዓለም መሪ እና ፍጻሜ በዳንኤል ከተገለጠው ጋር አንድ ነው። ፍጻሜው በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ከመንግሥተ ሰማያት በሚመጣው መንግሥት ይሆናል። እንደ ዳንኤልና ዘካርያስ ያሉ የብሉይ ኪዳን ነቢያትና ሐዋርያው ዮሐንስ እንዳመለከቱት፥ ኢየሩሳሌም የውዝግቦች ሁሉ ማዕከል ትሆናለች። የመጨረሻው የዓለም ጦርነት ማዝገሚያና ትኩረትም ናት። ይህን በቅድሚያ በዝርዝር የገለጠው ኢየሱስ ነበር።

## ♦ የቅድስቲቱ ከተማ ርኩሰት

ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፥ የዘመን መጨረሻ ምልክትና የመጪው መንግሥትህ ሁኔታ እንዴት ነው? ብለው ጠይቀውት ነበር (ማቴ. 24፡3)። በማቴዎስ 24፡1-14 ላይ ስለ ሁኔታው ጠቅለል ያሉ ምልክቶች ከሰጠ በኋላ ኢየሩሳሌም ራሷ የጌታ ዳግም ምጽአት በደጅ መሆኑን የምትጠቁም መሆኗን እንዲህ በማለት ገልጧል፥ "እንግዲህ በነቢዩ ዳንኤል የተባለውን የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ" ብሏል (ማቴ. 24፡15-16)።

በነቢዩ ዳንኤል "የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ይቆማል" የተባለውና ኢየሱስ የጠቀሰው ይህ ገለጣ ምን ማለት ነበር? ይህን ርእስ ዳንኤል በሦስት ክፍሎች መድበ እንዲህ በማለት አስተዋውቋል። "ከእርሱም ጋር ሠራዊቶች ይቆማሉ፥ መቅደሱንም ግንቡንም ያረክሳሉ፥ የዘወትሩንም መሥዋዕት ያስቀራሉ፥ የጥፋትንም ርኩሰት ያቆማሉ" (ዳን. 11፡31)። ብዙ ተርጓሚዎች እንደሚስማሙበት፥ ይህ ትንቢት ዳንኤል ከሞተ ከሦስት መቶ አምሳ ዓመት በኋላ ከ175 እስከ 164 ዓመተ ዓለም በሶሪያዊው መሪ በአንቲዮካስ ኤፒፌኔስ [Antiochus Epiphanes] ተፈጽሟል። ይህ ሰው አይሁድን ያሠቃየና ያሳደደ ከመሆኑም በላይ እምነታቸውንም ለመደምሰስ ሞክሮ ነበር። ቤተ መቅደሳቸው ውስጥ በመሠዊያቸው ላይ አሳማ ሠዋበት። በተቀደሰው ስፍራም የግሪኮችን ጣዖት አስቀመጠ። ይህን በማድረጉ ከተቃወሙት አይሁዳውያን አሥር ሺህ ያህሉን ገደለ። ያን ለመግለጥ ነበር፥ "የጥፋትንም ርኩሰት በተቀደሰች ስፍራ ያቆማሉ" ያለው። እንግዲህ ከዚህ ፍጻሜ ካገኘ የዳንኤል 11፡31 ትንቢት በመነሣት፥ ወደፊት የሚፈጸም ተመሳሳይ ሁኔታን የሚገልጡ ሁለት የዳንኤል ትንቢቶችን ለመረዳት ይቻላል።

በዳንኤል 9፡27 የተገለጠው የወደፊቱ የዓለም ገዥ "መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል"። በተጨማሪም "በቤተ መቅደሱ አስጸያፊ የጥፋት ርኩሰት ያስቀምጣል! እስከተቆረጠውም ፍጻሜ ድረስ መቅሠፍት በአጥፊው ላይ ይፈስሳል"።

እንደገናም በዳንኤል 12፡11 "የዘወትሩም መሥዋዕት ከቀረና የጥፋትም ርኩሰት ከቆመ ጀምሮ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ቀን ይሆናል" ብሎ ይተነብያል። እነዚህን ክፍሎች በጥንቃቄ ስናጠና ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በግምት ሦስት ዓመት ተኩል ቀደም ብሎ የሚዲትራኒያኑ አምባገነን መሪ የአይሁድን የቤተ መቅደስ ሥርዓት ያረክሳል፤ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሥዋዕታዊ አምልኮ እንዳይደረግ ይከለክላል። እነዚህ ድርጊቶች የፍጻሜው ዘመን ለመቅረቡ ልዩ ምልክቶች፥ እንዲሁም የእስራኤልና የዓለም የመከራ ዘመን ወዲያው ለመከሠቱ ማስረጃዎች ናቸው። ይህ ድርጊት የሚፈጸመው ኢየሩሳሌም ውስጥ ስለሆነ፥ ስለ መጨረሻው ዘመን ከንውኖች ኢየሩሳሌምን በጥንቃቄ ልንመለከት ይገባናል። የትንቢቱ ቁልፍ ምልክትነትም እዚህ ላይ ነው።

የዳንኤል ትንቢት ወግ አጥባቂ አይሁዳውያን ቤተ መቅደሳቸውን ኢየሩሳሌም ውስጥ ለመሥራትና በሙሴ ሕግ መሠረት ጥንታዊውን መሥዋዕት ለማቅረብ ፍላጎት እንዳላቸው ያመለክታል። ርኩሰቱን የሚፈጽመው የመካከለኛው ምሥራቅ መሪ (የዓለም መሪ የመሆን ሚና የሚያገኝም ይመስላል)፥ የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ሥልጣንም ይኖረዋል። የሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ "የያዕቆብ መከራ ዘመን" ይባላል (ኤር. 30፡7)፤ ይህ ጊዜ በእስራኤል ላይ ታላቅ ስደትና ዓለም አቀፋዊ ውጥረት የሚያመጣበት ይሆናል። በዓለም ላይ ስለሚመጣውም ጠቅላላ ጥፋት ማስጠንቀቂያ ነው። አዲሱ የዓለም መሪ የአይሁድን አምልኮ ሥርዓት ለማገድ በሚያደርገው መከራ፥ ራሱን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚተካ ሰይጣን አድርጎ የሚያቀርብ ሲሆን፥ አንዳንዱም የክርስቶስ ተቃዋሚ ተብሎ ይጠራል።

## ♦ የኢየሩሳሌም አይቀሬው ትንቢት

በፍጻሜው ዘመን በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ ሁኔታዎች ሁሉ፥ በኢየሩሳሌም ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸውን ስለ እርሷ የተነገሩ ትንቢቶች ያመለክታሉ። ዛሬ በመፈጸም ላይ ያሉትን አብዛኛዎቹን ድርጊቶች ኢየሱስ አስቀድሞ ተናግሯቸው ነበር። ይህን በማድረጉም ነቢዩ ዳንኤል ኢየሩሳሌምንም ሆነ የቀረውን ዓለም አስመልክቶ የተናገረው ትንቢት ትክክል እንደሆነ አረጋግጧል። መካከለኛው ምሥራቅ እንደገና የዓለምን ሕዝብ ትኩረት ስቧል፤ ሁኔታዎችም በፍጥነት በመከናወን ላይ ናቸው። ይህ ሁሉ ሁኔታ የሚያስረዳው የትንቢቶቹ ፍጻሜ ሩቅ አለመሆኑን ነው።

ምናልባት ያለነው በአሕዛብ ዘመን ማከተሚያ ወቅት ይሆናል። ዓለም አቀፍ የኃይል ሚዛን ወደ አውሮፓና ሚዲትራኒያን አገሮች እያጋደለ ነው።

ትግሉ ለአዲስ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ኅብረት፥ ሁኔታው ደግሞ ለአዳዲስ መሪዎች መነሣት ተመቻችቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በእስራኤልና በፍልስጥኤም ዓረቦች መካከል የሚካሄደው ትግልና ጦርነት የኢየሩሳሌምን ትኩረት ሳቢነት ከፍ አድርጎታል። በአካባቢው የሚያይለው ሃይማኖታዊ ስሜት እውነተኛ ሰላም ለማምጣት እንቅፋት ይሆናል። በመጨረሻም እስራኤልንና ዓረቦችን በማስገደድ ኢየሩሳሌም ዓለም አቀፍ ከተማ እንድትሆን እንዲስማሙ ያደርጋቸው ይሆናል።

ኢየሱስ በዮሐንስ 14 ላይ በተናገረው መሠረት፥ ዳግመኛ የሚመጣበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። በብዛት በመፈጸም ላይ ያሉት ምልክቶችም ይህንኑ ይጠቁማሉ። የእግዚአብሔር የአሁኑ ዕቅድ አሕዛብም ይሁኑ፥ አይሁድ በኢየሱስ እንዲያምኑና አንድ የምዕመናን አካል እንዲሆኑ ጥሪ ማቅረብ ነው። ይህም ዕቅድ ከተፈጸመ በኋላ የመካከለኛው ምሥራቅ ፌዴራላዊ አንድነት የሚመሠረትበትንና በእስራኤልና በዓረቦች መካከል ያለው ውጥረት የሚፈታበትን ሁኔታ የሚሻ መሪ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ትንቢቶቹ በኢየሩሳሌም ዕጣ-ፈንታ ላይ ስለሚያተኩሩ፥ እኛም ወደፊት የሚሆነውን ለመረዳት በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ ማትኮር አለብን። ከተማይቱ ለፍጻሜው ሁኔታ በመዘጋጀት ላይ ናት።

በትንቢቶቹ መሠረት የዓለም አጠቃላይ ሁኔታ በመለወጥ ላይ ሲሆን፥ ተዋናዮቹና መድረኩ ተዘጋጅቷል። በዚህ ድራማ ኢየሩሳሌም የምትጫወተው ቁልፍ ሚና አለ።

## ከባቢሎን ምርኮ ጀምሮ ትንቢታዊ ክንውኖች፥ በታሪክ

605 ዓ. ዓ. የኢየሩሳሌም መፍረስ (መውደቅ) የባቢሎን ምርኮና የአሕዛብ ዘመን መጀመር (ኤር. 25፡9-11፤ ሉቃስ 21፡24)።

586 ዓ.ዓ. የኢየሩሳሌምና የሰሎሞን ቤተ መቅደስ መፍረስ (ኤር. 52፡12-13)።

539 ዓ.ዓ. የባቢሎን መውደቅ፥ ሁለተኛው መንግሥት በሜዶንና ፋርስ መጀመር (ዳን. 2፡39፤ 5፡1-31፤ 7፡5)።

538 ዓ.ዓ. አይሁዶች ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቅድስት አገር መመለሳቸው (ዕዝራ 1፡1-2፡70)።

515 ዓ.ዓ. የመቅደሱ እንደገና በኢየሩሳሌም መሠራት (ዕዝራ 3፡1-13፤ 4፡21-24፤ 5፡1-6፡18)።

445 ዓ.ዓ. የኢየሩሳሌም ከተማ የቅጥር ግንብ መሠራት (ነህ. 1፡1-6፡16)።

445-396 ዓ.ዓ. የኢየሩሳሌም ከተማ ዳግም መሠራት (ዳን. 9፡25)።

331 ዓ.ዓ. የሦስተኛው መንግሥት በግሪክ መጀመር (ዳን. 2፡39፤ 7፡6፤ 8፡1-22)።

242 ዓ.ዓ. የአራተኛው መንግሥት በሮም መጀመር (ዳን. 2፡40፤ 7፡7)።

63 ዓ.ዓ. የሮማውያን ኢየሩሳሌምን ድል ማድረግ።

20 ዓ.ዓ. ሮማውያን የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ እንደገና ለመሥራት መጀመር።

6 ዓ.ዓ. የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት (ኢሳ. 7፡14፤ 9፡6-7፤ ሚክ. 5፡2፤ ሉቃስ 2፡4-11)።

30-33 ዓ.ም. የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ (መዝ. 16፡19፤ 22፡1-21፤ ኢሳ. 53፡3-12፤ ማቴ. 6፡21፤ 17፡22-23፤ 20፡18-19፤ 27፡33-50፤ 28፡1-10)።

64 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሥራ መፈጸም።

70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌምና የቤተ መቅደሱ መፍረስ፤ የአይሁዶች በዓለም ዙሪያ መበተን (ዘዳ. 28፡63-68፤ ማቴ. 24፡1-2፤ ሉቃስ 21፡20)።

1897 ዓ.ም. የጽዮናዊ ንቅናቄ መጀመር- እስራኤል በጥንት ምድሯ መኖሪያ አገር መፈለጓ።

1945 ዓ.ም. የሩሲያ መነሣትና የኮሚኒዝም ማየል።

1946 ዓ.ም. የዓለም መንግሥት መጀመር፥ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መመሥረት።

1948 ዓ.ም. የእስራኤል መንግሥት በይፋ መቋቋም፤ የአይሁዶች ለሦስተኛ ጊዜ ወደ አገራቸው መመለስ።

1948 ዓ.ም. የዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን መጀመር፤ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ [World Council of Churches] መመሥረት።

1956 ዓ.ም. የእስራኤል ግዛቷን ማስፋፋት።

1967 ዓ.ም. የእስራኤል ግዛቷን ከዮርዳኖስ ወንዝ እስከ ስዊዝ ካናል፥ ኢየሩሳሌምን ጭምር ማስመለስ።

1973 ዓ.ም. የእስራኤል ወደ ግብፅና ሶሪያ ዘልቃ ግዛቷን ማስፋፋት፤ ከስዊዝ ካናል ለቅቃ ለመውጣትም መደራደር።

1975 ዓ.ም. የግብፅ ስዊዝ ካናልን እንደገና መክፈት።

1979 ዓ.ም. የካምፕ ዴቪድ ስምምነት፤ ከግብፅ ጋር ሰላም።

1982 ዓ.ም. የእስራኤል ፒ.ኤል.ኦን (የፍልስጥኤም ነጻ አውጭ ድርጅትን) ሊባኖስ ውስጥ ዘልቃ ማጥቃት።

1985 ዓ.ም. የእስራኤል ከሊባኖስ መውጣት።

1990 ዓ.ም. የሳዳም ሑሴን እስራኤልን ለመውጋት በሚያደርጉት ዝግጅት ኩዌትን መያዝ።

መላው ዓለም፥ የባሕረ-ሰላጤውን የነዳጅ ዘይትና የመካከለኛውን ምሥራቅ ዓለም አቀፍ ጠቀሜታ በመገንዘብ በኩዌት መያዝ አጸፋውን መለሰ።

# 8

# የዓለም የሃይማኖት ማዕበል ከፍ እያለ መሄድ

## ♦ የሃይማኖት ሚና በመጨረሻው ሰዓት

የምዕራቡ ዓለም ሥልጣኔ እስከዛሬ በሳይንስ እድገቱ እና ስለ ዓለም አፈጣጠር በሚሰጠው የአዝጋሚ ለውጥ [Evolution/ኢቮሉሽን] ትንታኔ ረክቶ ነበር የኖረው። አሁን ግን ነገሮች ተለዋውጠዋል። ሥጋት የሌለበትና እስተዋዩ ዓለም መፈራረስ እየጀመረ ነው። ኮከብ ቆጠራ፥ ጥንቆላና ሌሎችም አጋንንታዊ አሠራሮች የዘመናችንን ሰው አስተሳሰብ ይማርካሉ ብለን አስበንም ገምተንም አናውቅ ነበር። ክርስትናም አዳቅሎና ሽቃቅጦ ያቀረበው "የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ" የብዙዎችን ስሜት ለመማረክ ችሏል።

እንዲህ ዓይነቱ የአመለካከት ለውጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተማሪዎችን ሊያስደንቅ አይገባም። ስለ መጨረሻው ሰዓት የተነገሩ ትንቢቶች እንደሚያመለክቱት፥ የዓለም መጨረሻ ዘመን ሲቃረብ የሐሰት ሃይማኖቶች እየበዙ የሚሔዱ ክስተቶች ናቸው። ክርስቶስም ቢሆን የሐሰት ሃይማኖቶችና በሃይማኖት ስም ብዙ ማታለል የሚሠሩ የውሸት ነቢያት እንደሚነሡ፥ ብዙዎችንም እንደሚያስቱ አስጠንቅቆናል። እነዚህ ሁሉ ለዓለማችን ችግር ሃይማኖታዊ መፍትሔ እንሰጣለን በማለት አንዳንድ ሞኞችን ያስታሉ።

በዓለም ታሪክ ውስጥ ሃይማኖት በተደጋጋሚ ግዙፍ ሚና ተጫውቷል። ባለፉት ዘመናት የተደረጉ ጦርነቶች፥ እንዲሁም የታላላቅ ታሪካዊ ክንዋኔዎች መንሥኤ የሃይማኖት ግጭቶች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት እንደሚያመለክተው፥ ያለንበት ዘመን የመጨረሻው ቢሆንም፥ በዚህም ጊዜ ሃይማኖት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል።

## ♦ የመካከለኛው ምሥራቅ የሃይማኖት ውጥረት

በመካከለኛው ምሥራቅ የሚታየው ውጥረት ሥረ-መሠረት ሃይማኖታዊ ይዘት አለው። እስራኤል ጥንታዊ መሬቷን እንድትይዝ

የሚያነሣሣት ሃይማኖት ብሔራዊ ስሜትና ፖለቲካዊ ምኞት ነው። ዓረቦች አይሁድን የሚጠሉበት ከፊል ምክንያት ዘረኝነት ቢሆንም፥ ከገሃዱ እውነት የምንረዳው ግን ኢየሩሳሌምን የራሳቸው ለማድረግ ያላቸው ሃይማኖታዊ ቅንዓት የጎላ መሆኑን ነው።

አሁን እስላሞች መስጊዳቸውን የሠሩት ጥንት የአይሁድ ቤተ መቅደስ እነበረበት ሥፍራ ላይ ነው። በዚህም የተነሣ አይሁዳዊያን ቤተ መቅደሳቸውን እንዳይሠሩ በስፍራው ያለው መስጊድ እንቅፋት ሆኖባቸዋል። ምንም እንኳን የጥንቱ ቤተ መቅደስ የነበረው አሁን መስጊዱ ካለበት በስተሰሜን አንድ መቶ ሃምሳ ሜትር እልፍ ብሎ እንደነበር የከርሠ-ምድር ተመራማሪዎች ቢያረጋግጡም፥ አይሁዶች በዚሁ ቦታ ላይ መቅደሳቸውን ለመሥራት ያላቸው ፍላጎት አልተገታም። ሆኖም ጥንታዊውን "የለቅሶ ግንብ" ጨምሮ ይህን ስፍራ በእጅ ማድረጋቸውና ወደ ቦታውም ለመቅረብ መቻላቸው የ1967ቱ ጦርነት ዋና የሆነና የተቀደሰ ክንውን ተብሎ ይቆጠራል። እንግዲህ በእስራኤልና በዓረቦች መካከል ያለው ዋና ችግር ይኸው ሃይማኖታዊ ጉዳይ መሆኑ ነው።

## ♦ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ላይ ያላት የይገባኛል ጥያቄ

እስራኤልና ዓረቦች በኢየሩሳሌም ላይ ዋናዎቹ ተፎካካሪዎች ቢሆኑም፥ በሚሊዮን የሚቆጠሩና በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ክርስቲያኖችም ኢየሩሳሌምን ቅድስት ከተማ አድርገው የሚያስቧት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። የፕሮቴስታንት፥ የካቶሊክና፥ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ደጋፊዎች በኢየሩሳሌም ላይ ያላቸው ስሜት ከፍተኛ በመሆኑ፥ ምዕራባውያን መሪዎች የኢየሩሳሌምን የወደፊት ዕጣ በቸልታ ለማለፍ አይችሉም። ክርስቲያኖች፥ እስላሞችና አይሁዶች ምንጫቸው መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ መሆኑ ይታወቃል። እነዚህ በአንድ አምላክ ብቻ የሚያምኑ ሃይማኖቶች ከኢየሩሳሌም ከተማና እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሰጠው ተስፋ ጋር ቁርኝት አላቸው። የመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢን ውጥረት ለማርገብ የሚወሰደው እርምጃ አይሁዶችንና እስላሞችን ብቻ ሳይሆን፥ በዓለም ዙሪያ ያሉትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችንም የሚያረካ መሆን አለበት። እስራኤልና ዓረቦች ብቻ የኢየሩሳሌምን ዕጣ ሲወስኑ፥ ክርስቲያኖች ዝም ብለው አይመለከቱም። እንግዲህ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው፥ ለኢየሩሳሌም ችግር መፍትሔ ሊሆን የሚችለው የሦስቱ ሃይማኖቶች የተባበረ ውሳኔ ይሆናል።

## ♦ የተባበረ የዓለም ሃይማኖቶች ጥረት ሊኖር ይችል ይሆን?

እስከ ሀያኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ድረስ የአይሁድ እምነት፥ እስልምናና ክርስትና በመሠረቱ የማይታረቁ መስለው ነበር የታዩት፤ የተወለዱትም በከባድ

ጥረት ነው። ብዙ ስደትና ተቃውሞ ቢገጥሟቸው እንኳን ያን ሁሉ አልፈው እዚህ ደርሰዋል። መካከለኛው ምሥራቅንም ሆነ ዓለምን የወል በሆኑ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ለማስማማት የማይቻል መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይጠቁማል።

የክርስትና እምነት የተወለደው የፖለቲካ ብጥብጥ በሰፈነበትና ምንም ዓይነት ድርጅታዊ መዋቅር በሌለበት ሁኔታ ነበር። በመጨረሻ ቤተ ክርስቲያን ፖለቲካዊ እውቅና ስታገኝ በፍጥነት መደራጀት ጀመረች። ጳጳሳትን በመምረጥ የቤተ ክርስቲያን መማክርቶች ስብሰባ አካሄደች። ፖለቲካ በሚመሰቃቀልበት ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን ለመደራጀትና መላው መካከለኛው ምሥራቅን ለማረጋጋት ችላለች።

ይሁን እንጂ፣ በ11ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ቤተ ክርስቲያን በምሥራቅና በምዕራብ ተከፋፈለች። የምሥራቁ ኦርቶዶክስ፣ የምዕራቡ ደግሞ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያኖች ሆኑ።

ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላም በሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሌላ ክፍፍል ተፈጠረና የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ሕልውናዋን አገኘች። እርሷም በበኩሏ በመላው ዓለም በመቶ በሚቆጠሩ የሃይማኖት ወገኖች ተከፋፈለች። በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ-ዘመን የተለያዩ ቤተ ክርስቲያኖችን ማስተባበር፣ የአይሁድ፣ የእስልምናና የክርስቲያን እምነቶችን ኅብረት የመፍጠርን ያህል የማይቻል መስሎ ነበር የሚገመተው።

## ♦ ሁሉን አቀፍ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ጅማሬ

በሀያኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ታላቅ ለውጥ ተደረገና ዓለም አቀፋዊቷን ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት በፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንቅስቃሴ ተጀመረ። በ1925 ዓ.ም. እና በ1927 ዓ.ም. በተደረጉት ቅድመ ስብሰባዎች ውጤት በ1938 ዓ.ም. ጊዜያዊ የመማክርት ኅብረት ተፈጠረ። ከዚያም በ1948 የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መማክርት በአምስተርዳም ተመሠረተ። በዚህ አዲስ ኅብረት መሠረትም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ያሏትና አንድ-ወጥ የሆነች ሁሉን አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ስምምነት ተደረገ። ከጅምሩም የእምነት ክፍሎችን ሁሉ፣ ማለትም የፕሮቴስታንት፣ የካቶሊክንና የኦርቶዶክስን አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ጥላ ሥር ያሰባስባል በማለት ተስፋ ተጥሎበት ነበር። የኋላ ኋላ ግን፣ ይህን ኅብረት ለማጠናከር ሲባል ቀድሞ ከነበራቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት እና ቀጥተኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት መራቅ ጀመሩ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተማሪዎችም ይህን ዓለም አቀፍ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት እንቅስቃሴ ስለ መጨረሻው ዘመን ሃይማኖት ከተነገሩት ትንቢቶች ጋር አያያዙት።

## ♦ ትንቢታዊ ማስጠንቀቂያ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት

የአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መሪ የነበረው ሐዋርያው ጴጥሮስ በሰማዕትነት ከመሞቱ ትንሽ ቀደም ብሎ ይህን ጽፏል፦

> "ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ፤ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ። እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ። ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል፤ በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል" (2ኛ ጴጥ. 2፡1-2)።

ጴጥሮስ ግልጥ እንዳደረገው፥ ችግሩ ቀላል በሆኑ ሥነ-መለኮታዊ ልዩነቶች ላይ ብቻ ያተኮረ አልነበረም። ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነ፥ ምን እንዳደረገና ለምን በመስቀል ላይ እንደሞተ የሚያብራሩ ነጥቦችን ይመለከት ነበር። እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ የክርስትና እምነት መሠረቶች ናቸው። ጴጥሮስ ስለ እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት ሲጽፍ ዓመፀኞች፥ ሥነ-ምግባር የጎደላቸውና ሃይማኖታዊ ካባ የደረቡ ግብዞች፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት በተነገረው እውነት ላይ የሚዘብቱ እንደሆኑም አመልክቷል (2ኛ ጴጥ. 3፡ 3-4)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በተመሳሳይ ሁኔታ ሰማዕት ከመሆኑ ቀደም ሲል በጻፈው መልእክቱ ጢሞቴዎስን እንዲህ በማለት አስጠንቅቆታል፦

> "ቃሉን ስበክ፤ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ ዝለፍና ገሥጽ፤ ምከርም። ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና። ነገር ግን ጆሮዎቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ" (2ኛ ጢሞ. 4፡2-4)።

የይሁዳ መልእክት በሙሉ እንዲሁ ከሐሰተኛ አስተማሪዎች እንድንጠበቅ የሚያስጠነቅቅ ነው።

ሥነ-መለኮታዊ ትምህርትን አስመልክቶ የሚነሣ ክርክር አዲስ ነገር አይደለም። ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እምነት ማፈንገጥ በየዘመናቱ በተደጋጋሚ ተከሥቷል። በሀያኛው ክፍለ-ዘመን ግን ከመቼውም በላቀ ሁኔታ ከመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት የወጣ የሥነ-መለኮት ለውጥ ታይቷል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚለው የጋራ አቋም ዛሬ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። የሥነ-መለኮት ምሁራን ለመጀመሪያ ጊዜ "እግዚአብሔር ሞቷል" ብለው ዓወጁና በእምነት ፋንታ የክህደት ትምህርት ተስፋፋ። ዓለም ወደ የትንቢቶች ፍጻሜ

በምትገሰግስበት ወቅት በሃይማኖት ጉዳዮችም ሁኔታው ለዚሁ ፍጻሜ በመመቻቸት ላይ ነው።

## ♦ የመናፍስት ትምህርት መስፋፋት

ሐዋርያው ጳውሎስ ከተናገራቸው ዋና ዋና ትንቢቶች አንዱ፥ "በመንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ" በማለት ለጢሞቴዎስ የጻፈው ነው (1ኛ ጢሞ. 4፡1)። ትንቢቱ በመጨረሻው ዘመን ሰዎች የክርስትና እምነታቸውን ብቻ ሳይሆን፥ አጋንንትና አጋንንታዊ ትምህርቶችንም ጨምሮ እንደሚከተሉ አስመልክቶአል። ይህ ከመጨረሻ ዘመን ምልክቶች አንዱ ሲሆን፥ ሰዎች ውሸቱን እውነት ነው ብለው እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል።

ባለፈው ትውልድ የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነተኛነት የሚቀበሉ ክርስቲያኖች ካልሆኑ በቀር የዘመናችን ሰው በመናፍስት ወይም በአጋንንት ሕልውና ያምናል ብሎ መገመት አዳጋች ነበር። ዛሬ ግን ይህ ትምህርት ለመጽሐፍ ቅዱስ ደንታ በሌላቸው ብዙ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል።

ያለ ድምፅ አዕምሮ ለአዕምሮ መግባባት ዛሬ ሳይንሳዊ እውነታ ሆኖአል። ተጨማሪ የመግባቢያ ስሜቶች ምርመራ ግኝቶች፥ ጠንቋዮች ከሙታን መናፍስትና ከሕያዋን ጋር ልዩ ግንኙነት ማድረግ እንደሚችሉ ይነግሩናል። የሞቱ ሰዎች መናፍስት ተመልሰው ስላለፈው፥ ስለ አሁኑ ጊዜና ስለ ወደፊቱ ልዩ ምሪት እንደሚሰጡ ያስረዳሉ።

መናፍስት ሰዎችን ሊረዱ ወይም ጠቃሚ መመሪያ ሊሰጡ ይችላሉ የሚለው እምነት ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ ነው። ይህ የመናፍስት ትምህርትና ሃይማኖት [Spiritism/ስፒሪቲዝም] ከምን ጊዜውም ይልቅ በመስፋፋት ላይ ነው። ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል እንዳላቸው የሚያውጁ አዳዲስ የሃይማኖት መምህራን ተነሥተዋል። ብዙ ሰዎችም ከመናፍስት፥ ማለትም ከአጋንንታዊው ዓለም ጋር የመገናኘት ፍላጎት እንዳላቸው ይናገራሉ። መምህራኖቹም በትምህርታቸው ታዋቂነትን አግኝተዋል።

ምንም እንኳን ይህ ሁኔታ በአብዛኛው የሚታየው ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች አካባቢ ቢሆን፥ ከመናፍስት ጋር መገናኘትና ከእነርሱም መመሪያ ማግኘት አለብን የሚለው ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያንም ዘልቋል። መጻሕፍትና ጋዜጦች ለዓመቱ የሚሆነውን ትንቢት በየዓምዶቻቸው ያወጣሉ። የመናፍስት አገልጋዮች ተወዳጅና ታላላቅ ሰዎች ሆነዋል። የአጋንንትን ኃይል የሚያሳየውና፥ "አጋንንት አውጪው" ["The Exorcist"/"ዘ ኤግዚርሲስት"] የተሰኘው ፊልም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተመልካቾችን ስሜት ለመማረክ ችሏል።

ከማይታዩ ነፍሳት ጋር ለመለማመድ የሚደረገው ሙከራ በአደንዛዥ እፅ የተደገፈ ሲሆን፥ ይህ ጠቅላላ ድርጊትም አስፈሪ የሰይጣን ማታለል ነው። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የመጨረሻውን ጊዜ የትንቢት ቃል የሚከተሉ አስገራሚ እድገቶች ናቸው። የክርስትና እምነትና ግብረገብነት ከብዙዎች ዘንድ የተወገደ በመሆኑ፥ ወደ መናፍስት ትምህርትና ጥንቆላ የሚያመራው አዲስ አዝማሚያ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትናን በሰይጣን እንደሚተካ ግልጥ ነው።

## ♦ ቀጥሎስ ምን ይሆናል?

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን መቅረብ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-12 መልእክቱ አስጠንቅቋል። የተሰሎንቄ ሰዎች በሐሰተኛ ነቢያት ትምህርት ግራ መጋባታቸውን በመረዳትና ስለ መጨረሻው ጊዜ በማስመልከትም አራት ነገሮችን በቅደም ተከተል ገልጧል። ነጥቦቹ የአርማጌዶን ጦርነት ከምንጊዜውም ይልቅ መቅረቡን ለአዋቂዎችና አስተዋዮች ያመለክታሉ።

በመጀመሪያ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለማመንና ከእምነት መራቅ ስለመብዛቱ ይህን ጽፏል፡-

> “ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን፥ በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ፥ በአእምሮአችሁ እንዳትናወጡ፥ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን። ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፥ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደርስምና” (2ኛ ተሰ. 2፡1-3)።

ጳውሎስ፥ ዓመፅ ሲል “ከእምነት ማፈግፈግ” ማለቱ ነው። ክሃዲ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ዓመፅ ከሚለው ግሪክኛ የተወሰደ ነው።

ሁለተኛ፥ በአማኞች አድሮ በዓለም ያለውን ክፉ ነገር የሚቃወመው መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያኖች ከተነጠቁ በኋላ በዚህ ምድር አይኖርም። በዓለም ዙሪያ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ውስጥ ያለው መንፈስ መጥፋት፥ ዓለም አይቶት የማያውቀው ዓይነት የክፋትና የዓመፅ ሥራ እንዲስፋፋ ያደርጋል። ይህም የዓለም ቤተ ክርስቲያን ምንም የክርስትና እምነት በሌላቸው ሰዎች እጅ እንድትወድቅ፥ እንዲሁም ሌሎች እርኩስ ኃይላት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የሚያግዳቸው ነገር እንዳይኖር ያደርጋል።

ሦስተኛ፥ በዚህ ጊዜ የዓመፅ ሰው ጊዜውን ጠብቆ ይገለጣል። ጳውሎስ ስለዚሁ ሲጽፍ የሚከተለውን ብሏል፡-

"በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ። የዓመፅ ምስጢር አሁን ይሠራልና። ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል። ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች፥ በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው" (2ኛ ተሰ. 2፡6-10)።

ይህ የዓመፅ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲተካ በሰይጣን የታቀደ ነው። ይህም የተለያዩ ሰይጣናዊ ሥራዎች መጀመር ምልክት ሲሆን፥ ዓለምን በሞላ ያሳስትና በመጨረሻ ሰዎች እንደ አምላክ እንዲያመልኩት ያስገድዳቸዋል።

አራተኛ፥ የዓመፅ ሰው የሚያካሂደው ክፉ ሥራ ክርስቶስ በዓለም ላይ ለመፍረድና ክፋትን ለማጥፋት በሚመጣበት ጊዜ ያከትማል። ይህ ድርጊት ከአርማጌዶን ጦርነትና ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መጥቶ በምድር ከሚዳኝበት ጊዜ ጋር ይገጣጠማል።

## ♦ ሁሉን አቀፍ የሆነች ቤተ ክርስቲያን መከሠት

በመነጠቅ ["Rapture"] ጊዜ እውነተኛ ክርስቲያኖች ከምድር ሲሰወሩ፥ ፍርሃትና ሽብር ይከተላል (1ኛ ተሰ. 4፡13-18)። ይህም የሃይማኖትን ብጥብጥ አስወግዶ ሥርዓት ለማስያዝ ይቻል ዘንድ የዓለምን ሃይማኖታዊ ድርጅት መኖር አስፈላጊነት ያጎላዋል። ከብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች መሰወር፥ ከተፈጥሮ አደጋ፥ ከአጋንንት ኃይል መጨመር፥ ከሐሰተኛ ነቢያት ምልክትና ተአምር ማድረግ የተነሣ ዓለም አስተማማኝ የሆነ ነገር ለመጨበጥ ትሻለች፤ ሕዝቦቿም ግራ በመጋባትና እርዳታ በመፈለግ ፊታቸውን ወደ ዓለማዊቱ ቤተ ክርስቲያን ይመልሳሉ።

እውነተኛ አማኞች በሌሉበት የካቶሊክ፥ የፕሮቴስታንትና የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በጋራ አንድ ብርቱ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ተቋም ይፈጥራሉ። ይህች ሁሉን አቀፍ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ብዙ መቶ ሚሊዮን አምላኪዎችን ለመቆጣጠር ኃይል ይኖራታል። የሚቃወሟትን ሁሉ የማጥፋት ችሎታ አላት (ራእይ 17፡6)። ከመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ባለ ሥልጣናት ጋርም ኅብረት ይኖራታል። ይህ ክንውን ሁኔታዎችን አመቻችቶ በዓለም ፍጹም አምባገነን መንግሥት ያስነሣል።

ያልተቀደሰው ኅብረት በራእይ 17 ላይ በቀይ አውሬ በምትጋልበው ጋለሞታ ተመስሏል። የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች ጋለሞታዋ ሴት የመጨረሻውን ዘመን ሃይማኖት፥ ቀዩ አውሬ ደግሞ በሚዲትራኒያን ውህደት

የሚመሠረተውን መንግሥት የሚወክሉ ናቸው ይላሉ። ይህ ኅብረታቸው ጊዜያዊ መረጋጋት ቢያመጣም፥ ሰዎች ከእውነተኛ ሃይማኖት እንዲርቁ፥ እግዚአብሔርንም እንዲሰድቡ ያደርጋል።

የጥምር ኃይላቸው አንዱ ውጤትም እስራኤልን አስገድዶ ለሰላም ማዋዋል ነው (ወደ ኋላ እንመለስበታለን)። የአይሁድ ሃይማኖት ማንሰራራት እንደተጠበቀ ሆኖ የሰላም ውሉ እስካልተደፈረ ድረስ ለጥቂት ጊዜ የሚቆይ ይሆናል። ይህን የፖለቲካና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውህደት ተከትሎ በሌላው ክፍለ ዓለም ስደትና ሰማዕትነት የሚጀምር ቢሆንም፥ የመጨረሻው የዓለም ሃይማኖት የሚከሠተው ግን ዘግይቶ ነው።

## ♦ እግዚአብሔርን አለማመን ለመጨረሻው የዓለም ሃይማኖት ቁልፍ መሆኑ

ከሀያኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ክሥተት አንዱ የኮሚኒዝም መነሣትና እግዚአብሔር የለም በሚለው ትምህርቱ [Atheism/ኤቲይዝም]* የዓለምን አንድ ሦስተኛ ሕዝብ ለመቆጣጠር መቻሉ ነበር። ምንም እንኳን ኮሚኒዝም በመጨረሻው ዘመን ፖለቲካ ወሳኝ ሚና ባይኖረው፥ ከክህደት ትምህርት [ኤቲይዝም]፥ ከ“ማቴሪያሊዝም” [Materialism] እና ከወታደራዊ ኃይል ጋር የተሳሰረ በመሆኑ፥ ዓለም አቀፍ የአምልኮ ድርጅት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል።

የቤተ ክርስቲያንና የመካከለኛው ምሥራቅ የፖለቲካ መሪዎች ከእስራኤል ጋር የሰላም ድርድር በሚያደርጉበት ዘመን፥ ሐዋርያው ዮሐንስ ጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን ከሜዲትራኒያኑ አምባገነን ጋር ግንኙነት ባላቸው አሥር ነገሥታት ተቃጥላ እንደምትጠፋ ገልጧል። ይህም ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ ሦስት ዓመት ከግማሽ በፊት ይሆናል። የመጨረሻው ዘመን ሃይማኖት በክህደትና በራስ ወዳድነት እንደሚሞላ የእግዚአብሔር ቃል ይገልጣል። በባህርዩም ራሳቸውን ክበው እንደ አምላክ አምልኩን ካሉት ሮማውያን ነገሥታት ጋር ተመሳሳይነት አለው።

---

* “ኤቲይዝም” በቀላሉ ሲተረጎም እግዚአብሔር የለም የሚል እምነት ነው። ሆኖም ይህ እምነት ሃይማኖቶች ስሕተት ናቸው ብሉ የሚያስተምር ብቻ ሳይሆን፥ ለአንድ ሕዝብ ደኅንነት ጎጂ በመሆናቸው መጥፋት ይኖርባቸዋል ብሉ እስከማለትም ይደርሳል። በዚህ ረገድ ኤቲይዝም ሌሎችን በማሳመን ሳይሆን፥ በግድ ሃይማኖታቸውን ለማስቀየር የሚፈልግ ራሱን የቻለ ሃይማኖት ይሆናል። ይህ ዓይነቱ ኤቲይዝም ባለፉት ጥቂት አሠርተ-ዓመታት በሩሲያና በሌሎች አገሮች እንደታየው የማርክሲስት ኮሚኒዝም ነው።

ኮሚኒዝም በዓለም ላይ ተቀባይነትን እያጣ ቢሆንም፥ የክህደት ትምህርቱ ግን ወደፊት ለምትቋቋመዋ የአምልኮ ድርጅት መሠረት ሊሆን ይችላል። በዳንኤል 11፡36-38 እንደተጻፈው የመጨረሻው የዓለም ገዥ አማልክትን ይንቃል፤ በዚህ ፋንታ ግን "የአምባዎቹን አምላክ" ያከብራል። በግልጥ እንሚታየው ይህ አምላክ ወታደራዊና የገንዘብ ኃይል ነው። የመጨረሻው ዘመን የዓለም ሃይማኖት በሰይጣን ኃይል ለተሞላውና የዓለም መሪ ለሚሆነው መሰገድ ይሆናል። ይህ መሪ ኢየሱስን እንዲተካ በሰይጣን የተዘጋጀ ነው። የዓለም ቤተ ክርስቲያን ንቅናቄ ቀደም ብሎ በመጀመር፥ ለዓለም ቤተ ክርስቲያን ብቅ ማለት ጥርጊያ ጎዳናውን እያመቻቸ ነው። ኮሚኒዝምም ዓለምን ለመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ክህደት ያዘጋጃታል። ይህ ሁሉ ሁኔታ የመጨረሻው ዘመን መዳረሻ የሆነው መድረክ ቀደም ብሎ መጀመሩን ያስረዳል።

## ♦ ሆኖም አያውቅ

በዓለም ታሪክ ውስጥ የመጨረሻውን ዘመን ሃይማኖት ትንቢት በተመለከተ እንዳለንበት ዘመን ሁኔታዎች ተሟልተው አያውቁም። በእኛ ትውልድ ብቻ ነው የእስራኤል ማቆጥቆጥ፥ የዓለም ቤተ ክርስቲያን መመሥረት፥ የእስልምና ሃይማኖት መጠናከር፥ የመናፍስት ትምህርት መስፋፋትና የኤቲይስት ፍልስፍና በዓለም መዳረስ ትንቢት በአስደናቂ ሁኔታ ሲፈጸም የታየው። የዓለምን ሃይማኖት በተመለከተ ወደ አርማጌዶን የሚያመራው መንገድ ቀደም ብሎ ተዘጋጅቷል። ወደ ጥፋት በመጓዝ ላይ ያለውም የዘመናችን ትውልድ ይሆን ይሆናል።

# 9

# አውሮፓን መለወጥ

## ♦ አዲስ የዓለም ሥርዓት

የዓለም ኃይል ሚዛን በአሜሪካና በሩሲያ የበላይነት ሥር እስከሆነ ድረስ፥ ከዚያ ውጭ አዲስ ሥርዓት ወይም አዲስ መሪ ሊኖር የሚችለው እንዴት ነው? በብረት መጋረጃ [Iron Curtain] በተከፋፈለችው አውሮፓ እንዴት እንደ ጥንታዊው የሮማ ዓይነት መንግሥት ሊመሠረት ይችላል? አሜሪካና ሩሲያን ሳይጨምር በዳንኤል 7፡7 እና 24 እንደተገለጠው፥ ሥልጣን ወደ አሥሩ መንግሥታት ሊዛወር ይችላል?

እነዚህ ጥያቄዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተማሪዎችን ለዓመታት ሲያወዛግቧቸው ቢቆዩም፥ አሁን ግን የዓለም የወደፊት ሁኔታ ግልጥ እየሆነ መጥቷል። አዲሱ የዓለም ሥርዓት ብቅ እያለ ነው። ሰላምን ማስፈን፥ የነዳጅ ዘይት አቅርቦትን ማረጋገጥና በመካከለኛው ምሥራቅ ሁከትን ማቆም የአዲሱ ሥርዓት ዋነኛ ዓላማዎች ናቸው።

ዓለምን ለመቆጣጠር ኃይላቸውን ሁሉ የሚያስተባብሩትና በኃያልነት የሚነሡት አሥር መንግሥታት እነማን ይሆኑ? አሜሪካም ሆነች ሩሲያ ባልቻሉበት ወይም ፈቃደኛ ሆነው ባልተገኙበት ወቅት በመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም ለማስፈን ቃል የሚገባው ማን ይሆን? የአሜሪካና የሩሲያ ዓለምን የመቆጣጠር ብቃት አዲሱ መሪ ከመነሣቱ በፊት የሚያከትም መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ያለው የኃይል ሚዛን የሚዛባው እንዴት ነው? በቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢት የተነገረላቸው መንግሥታትስ ወደ መድረኩ ብቅ የሚሉት በምን አኳኋን ይሆን? አዲሱ መሪ ሥልጣን ሲይዝ ምን ዓይነት ሁኔታዎች ይከሠታሉ?

## ♦ የሩሲያ በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ላይ ማየል

ከ1945 እስከ 1985 የነበረው የሩሲያ የውጭ ፖሊሲ በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ላይ ያላትን የበላይነት ማጥበቅ ነበር። የስታሊንን አመራርና

አስተሳሰብ ወደ እነዚሁ አገሮች አስገባች። ምንም እንኳን ሽብርና ግለሰብን እንደ ጣኦት የማምለኩ ጉዳይ ከ1953 ወዲህ እየቀነሰ ቢመጣ፥ ኅብረተሰቡን ለጥ ሰጥ አድርጎ ማስተዳደሩ በሩሲያ ወታደሮች አማካይነት ቀጥሎ ነበር። የተከፋፈለችው አውሮፓ፥ ዓለም ዓቀፋዊ እውነታ ሆና ለአሠርት ዓመታት ቆይታለች። ጀርመን በኢኮኖሚና በወታደራዊ ኃይል እንዳትጎለብት ያደርጋታል በሚል እምነት ሶቪየት ኅብረትን ጨምሮ ብዙ አገሮች የአውሮፓን መከፋፈል ይደግፉ ነበር።

የምሥራቅ አውሮፓ ኢኮኖሚ እንደ ሶቪየት ኅብረት በማዕከላዊ ዕቅድ ይካሔድ ነበር። የኢኮኖሚ የአመራር ብልሹነትና የአስተዳደር መዋቅራዊ ችግሮች ተዳምረው ግልጥ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አመጡ። በ1973 ዓ.ም. የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች የነዳጅ ዘይት እገዳን ችግር በከፍተኛ የነዳጅ ምርቷ ከታወቀችው ሶቪየት ኅብረት ጋር የንግድ ስምምነት በመፈራረም ተወጡት። በኋላ በይፋ እንደታየው ግን ሶቪየት ኅብረት ራሷ በነዳጅ ዘይት አቅርቦት እስከፊ የኢኮኖሚ ችግር ፈጥራ ነበር።

የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችም ኃይልን ለመቆጠብ በከሰል ለመጠቀም ተገደዱ። ውጤቱም አስከፊ የአየር ብክለትና የማይሽር የአካባቢ ብልሽት አምጥቷል። ጥፋቱ በዚህም ብቻ አላበቃም።

የ1980ዎቹ ዓመታት እንደተጀመሩ፥ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ኢኮኖሚ አሽቆለቆለ። የየአገሮቹ መዋዕለ ንዋይ እድገት በውጭ ብድር ክፍያ ጫና ተገታ። የሠራተኛው የማምረት ኃይል በማሽቆልቆሉ የምርት መጠን ቀንሶ ለውጭ ገበያ በሚላከው ምርት ላይ ተጽዕኖ አሳደረ።

የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ከውጭ ከሚያስመጡት ኃይል በስተቀር ሌላ ስላልነበራቸው ችግሩ ከፋባቸው። ሶቪየት ኅብረትም ብትሆን ለምታቀርብ ላቸው ነዳጅ በውጭ ምንዛሪ ወይም በቁሳቁስ እንዲከፈላት ከማድረጓም በላይ የምትልከውን ነዳጅ መጠን ቀነሰች። ይህን በመሰለ የክፍያ ጫና ሥር በመውደቃቸው ለኢንዱስትሪ ልማት የሚውለው መዋዕለ ንዋያቸው ተሟጠጠ።

በኤሌክትሪክ ኃይል ለመጠቀሙም ቢሆን ያው ከሶቪየት ጥገኝነት አልወጡም። የችግራቸው መፍትሔ በመስፋፋት ላይ የነበረው የኑክሊየር ኃይል ምንጭ ነበር። የማዕከላዊ ዕቅድ ነዳፊዎች እንደሚሉት 50% (አምሳ ከመቶ) የሚሆነው የምሥራቅ አውሮፓ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ከኑክሊየር ኃይል ሊገኝ ይችላል። ነገር ግን በ1986 ዓ.ም. በሚያዝያ ወር በቼርኖቤል [Chernobyl] (ሩሲያ) የተከሠተው የኑክሊየር ኃይል ማመንጫ አደጋ በኑክሊየር ኃይል ላይ ያለውን መተማመን ቀነሰው። በእነዚህና በሌሎቹም ችግሮች ሳቢያ በሶቪየት ኅብረትና በምሥራቅ አውሮፓ ክልል ፍጹም ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ነበር። ይህ ሁሉ ሁኔታ እንዲህ ባለ ፍጥነት ይከናወናል ብሎ ማን አስቦ ነበር?

## ♦ የሶቪየት ኃይል ማክተም

በመጋቢት 1985 ዓ.ም. ሚካኤል ጎርባቾቭ [Mikhail Gorbachev] የሶቪየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ጠቅላይ ጸሐፊ ሆነው ተመረጡ። እርሳቸው የወረሷቸው ያረጀ ፍልስፍናና ወደ ኋላ የሚጎትቱ አያሌ ችግሮች ብቻ ነበሩ። ቢሮክራሲው፣ የሞራል ውድቀትና የኢኮኖሚ ችግሮችም እንዲህ በቀላሉ የሚታዩ አልነበሩም።

ምንም እንኳን ሩሲያ በምሥራቅ አውሮፓ ላይ ያላት ቁጥጥር ማብቃት እስከ 1989 ዓ.ም. ድረስ ዓቢይ ጉዳይ ሆኖ ባይታይ፣ የለውጡ አጀንዳ የጀመረው፣ አገሪቱ ሥር ነቀል ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ካላደረገች ለሕልውናዋ አሥጊ ሁኔታ የሚፈጠር መሆኑን የራሷ ፖለቲካ ምሁራን ባመኑበት ወቅት ነበር። ነገር ግን የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችን ሶቪየታዊያን ማድረጉ ሳይቆም እንዴት ሶቪየት ኅብረትን አውሮፓዊት ማድረጉ ይቀጥላል?

"የፐሬስትሮይካ" [Perestroika] ፕሮግራም በኅብረተሰባዊነት የተከሠተውን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ውድቀት በኃይል ለማስወገድ የሰፈረ ቢሆንም፣ የቀድሞዎቹ ገዥዎች የአውሮፓ ይዞታቸውን በፈቃዳቸው የሚለቁ አልሆኑም። በምሥራቅ አውሮፓ ላይ አንሰራርቶ የነበረው የሶቪየት የበላይነት የተሰባበረው ጭቆና ባንገፈገፋቸው የየአገሮቹ ዜጎች ቁራጥ ተጋድሎ ሲሆን፣ ይህም የሆነው ከ1989-1990 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነበር።

ነገር ግን በምሥራቁ ክልል ያሉትን የአውሮፓ አገሮች ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምን ዓይነት ውህደት ነው ሊቀርፋቸው የሚችል?

## ♦ አዲስ እውነታ በምሥራቅ አውሮፓ

በ1990ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ላይ አውሮፓ በሽግግር ላይ ነበረች። የበርሊን ግንብ ከምሥራቅ ጀርመን መንግሥትና የፖሊት ቢሮ አባላት ጋር ፈርሷል። በቼኮዝሎቫኪያ አሌክሳንደር ዱብቼክ [Alexander Dubcek] እንደገና የተዋቀረው ፌደራላዊ ጉባኤ ፕሬዚዳንት በመሆን ተመርጠው ነበር። በሶፊያ [Sofia] (በቡልጋሪያ) ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፍ ከተደረገ በኋላ የኮሚኒስት ፓርቲው አምባገነንነት አክትሞ በምትኩ ነጻ ምርጫ ተካሄደ። በሩማኒያ የኒኮላይ እና ኤሌና ቻውቼስኩ [Nicolae and Elena Ceausescu] መገደል ወደ ታላቅ ደም መፋሰስ ሊያመራ የነበረውን የእርስ በርስ ብጥብጥና ጦርነት ለአፍታ ጋብ አደረገው። በፖላንድ ውስጥ የነጻነቱ ንቅናቄ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ነበር።

የምሥራቅ ጀርመኖች በብዛት ወደ ምዕራቡ ክፍል መፍለስ ወደ አንድነት በፍጥነት እንዲያመሩና የምዕራብ ጀርመንን ማርክ (ገንዘብ) የጋራ

መገበያያቸው እንዲሆን አደረገ። በክልሉ በተካሄደው የመጀመሪያ ምርጫ ምሥራቅ ጀርመናዊያን ከመቶ አርባ ዘጠኙ (49%) ውህደቱን ደገፉ። ይሁን እንጂ፥ ሁሉም ነገር እንደተገመተው ቀላል አልነበረም። በሐንጋሪና በፖላንድ የተባባሰው የኑሮ ውድነት፥ ወደ ነጻው ኢኮኖሚ የሚደረገው ሽግግር፥ የዋጋ ንረትን፥ ሥራ አጥነትንና ለደመወዝተኛው የሚደረግለት ጭማሪ ባለበት መገታትን ሊያስከትል እንደሚችል ያረጋግጣል። ነጻው ገበያና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት አሮጌውን የንግድ አግር ብረት ሰባብረው ብርቱ አንድነትን ለመፍጠር ይችሉ ይሆን?

ምሥራቅ አውሮፓስ ነዳጅ በማስመጣቱ ረገድ ያለባትን ጥገኝነት እንዴት ትላቀቀው ይሆን? በ1990 ዓ.ም. ምሥራቅ ጀርመን ብቻ 150,000,000 በርሜል ነዳጅ ዘይት ትፈልግ ነበር። ከዚህ 90% ከሶቪየት ኅብረት የሚመጣ ነው። ዩጎዝላቪያ የሚያስፈልጋትን 120,000,000 በርሜሎች በሙሉ እንዲሁ ከሶቪየት ኅብረት ማግኘት ነበረባት። ፖላንድ 110,000,000 በርሜል ነዳጅ ያስፈልጋታል፤ ከዚህ አብዛኛውን እጅ የምትሸፍንላት ሶቪየት ኅብረት ናት። ሐንጋሪም 62,000,000 በርሜል ነዳጅ ያስፈልጋት ነበር። ሩሲያ በ1990 ዓ.ም. የመካከለኛው ምሥራቅ ብጥብጥ ከመነሣቱ በፊት በአንድ ዓመት ብቻ ከአንድ ቢሊዮን በርሜል በላይ የነዳጅ ዘይት ወደ ውጭ ልካለች። ከዚህም አብዛኛው ወደ ምሥራቅ ጀርመን ነበር የገባው። ሲተነተንም፥ ለምሥራቅ ጀርመን (13%)፥ ለቼኮዝሎቫኪያ (12%)፥ ለፖላንድ (10%)፥ ለቡልጋሪያ (10%)፥ ለኢጣሊያ (9%)፥ እና ለሐንጋሪ (6%)፥ መሆኑ ነው።

## ♦ ነዳጅ ዘይት በብዛት የሚፈልግ ማነው?

አሜሪካንም በ1990 የመካከለኛው ምሥራቅ ብጥብጥ ሲጀምር ከማንኛውም አገር ይበልጥ ነዳጅ ከውጭ ታስገባ ነበር። ወደ አገር ውስጥ የምታስገባው ዓመታዊ ፍጆታ ከ2.4 ቢሊዮን በርሜል በላይ ሲሆን፥ ግማሽ ያህሉ በሥራ ላይ ያሉ መኪናዎቿ የሚንቀሳቀሱትም ከውጭ በሚመጣ ነዳጅ ነበር። ሳውዲ ዓረቢያ ናት ከማንኛውም አምራችና ላኪ አገር ይበልጥ ነዳጅ ታቀርብላት የነበረች።

የጃፓን የኢንዱስትሪ ብልጽግና የተመሠረተው በነዳጅ ላይ እንደመሆኑ መጠን በዓመት 1.2 ቢሊዮን በርሜል ነዳጅ ትፈልግ ነበር። ከዚህ ፍላጎቷ 30% በላይ የሚሆነውን የምታስመጣው ከፋርስ ከባሕረ-ሰላጤ አገሮች ነው። ሆኖም ጃፓን የነዳጅ ዋጋ ቢወደድባትም የመክፈል አቅም ነበራት።

በአጠቃላይ ሲታይ ምዕራብ አውሮፓ ነበረች ከአሜሪካ ይበልጥ ነዳጅ የሚያስፈልጋት። ምሥራቅ አውሮፓም ቢያንስ 442,000,000 በርሜል ነዳጅ

በተጨማሪ ፈልጋለች። በድምሩ የተባበረችው አውሮፓ 2.8 ቢሊዮን በርሜል ነዳጅ ዘይት ከውጭ ማስገባት አስፈልጓታል ማለት ነው። ምዕራብ ጀርመን ከ1970ዎቹ እስከ 1990 ባለው ጊዜ የኃይል አጠቃቀም ብቃቷን ከፍ አድርጋ ስለነበር፥ የውህደቱ ጉዳይ ሲነሣ የነዳጅ ዘይት ዋጋ፥ የኃይል አጠቃቀም ብቃትና የአካባቢ ሁኔታ ዋነኞዎቹ ተጠቃሽ ችግሮች ነበሩ። በሀያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን አውሮፓ ለመበልጸግ ትችል ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ነዳጅ ዘይት ያስፈልጋታል። አህጉሪቱ ጥቂት የነዳጅ ምርትና ለሚቀጥሉት አሥር ዓመታት የሚሆን ጥቂት ቀሪ የኃይል ምንጭ አማራጮች ይኖሯታል።

## ♦ ፋብሪካዎቹ ቢቆሙ

ሽብር ፈጠራ፥ ግልጥ ጦርነት፥ የኬሚካል ወይም ባክቴሪዎሎጂካል ጦርነት ወይም የኑክሊየር ጦርነት የባሕረ-ሰላጤውን ምርት ቢጎዳው ወይም በከፊል ቢያበላሸው ምን ይኮናል? በ1990 ዓ.ም. ኢራቅ፥ ግብፅ፥ ሶሪያ፥ እስራኤልና ኢራን የኬሚካል ጦር መሣሪያዎች አከማችተዋል ተብሎ ይታመን ነበር። የኑክሊየር የጦር መሣሪያዎችን ለማስፋፋትና ሥራ ላይ ለማዋል የሚደረገው እሽቅድምድም የጀመረው በ1980ዎቹ ነው። ሆኖም እስራኤል ኦሲራክ [Osirak] በሚባለው ሥፍራ በመገንባት ላይ የነበረውን የኢራቅ ኑክሊየር ተቋም በ1981 በቦምብ መደብደብዋ የኢራቅን ዕቅድ አዘገየው።

በሚከፈተው ጦርነት ምክንያት የሚደርሰውን የሕይወትና የንብረት ጥፋት ሳንቆጥር፥ የምዕራቡ ዓለም የኢንዱስትሪ ማሽኖችና የትራንስፖርት መስመሮች ቢቋረጡ የሚደርሰው ኪሳራ ምን ያህል ይሆን? ይህ ሁኔታ ቢከሠት የዓለምን የኢኮኖሚ ሥርዓት ወደነበረበት መመለስ ይቻል ይሆን?

ማን ይሆን በይበልጥ የሚጎዳው? የሚጠይቀውን ዋጋ ከፍሎ በጦርነት ጣልቃ የሚገባ ማነው? መቼም ከነዳጅ ዘይት ምርቷና ከእስቸጋሪው ውስጣዊ ችግሯ ጋር ሩሲያ አትሆንም። አሜሪካም ብትሆን ለራስዋ ነዳጅ ዘይት ማምረት ትችላለች። በተጨማሪ የሚያስፈልጋትንም ከናይጄሪያ፥ ከሜክሲኮ፥ ከካናዳና ከቬንዙዌላ ለማስመጣት ስለምትችል አካባቢውን ለቅቃ ትወጣ ይሆናል።

በነዳጅ እጦት ሳቢያ ኢንዱስትሪዎቻቸው ቢቆሙ የሚጎዱት አገሮች ለአዲስ ዓለም ሥርዓት የሚጥሩና ከጥንት ሮማውያን ጋር የተመሳሰለ ብልጽግና እንዲኖራቸው የሚሹ አገሮች ናቸው። ያለ ነዳጅ ለመኖር ምንም አቅም የላቸውም። አዲስ ኅብረት መፍጠር፥ ወታደራዊ ኃይል ማግኘት፥ እና በመካከለኛው ምሥራቅ ሰላምን ለማስፈን ጥረት ማድረግ አለባቸው።

ይህ ሰላምን የማስፈን ጥረት ከሮማውያን አገዛዝ ጀምሮ ያልታየ በአውሮፓና አፍሪካ ታላቅ የኃይል መጠናከር የሚያስፈልገው ነው። በዚህ

አዲስና አሥጊ ጨዋታ የሚወዳደሩ ተሳታፊዎች ተዘጋጅተዋል ማለት ይቻላል። ውድድሩም ልክ መጽሐፍ ቅዱስ በቅድሚያ እንዳሳወቀው ይሆናል።

## ♦ የአሥሩ መንግሥታት ኅብረት መድረክ

በአውሮፓ የታየው ለውጥና የቀዝቃዛው ጦርነት መርገብ ለአውሮፓውያን ትብብር መንገድ ከፍቷል። ከዚህ በፊት ሊሆን አይችልም ሲባል የቆየው የአውሮፓ መንግሥታት ኅብረት በአሁኑ የተካሄደው ለውጥ ውጤት ሆኗል። ይህን ውጤት ጋዜጠኞችም ተንብየውት ነበር። የመካከለኛው ምሥራቅን ሥርዓት ለማስጠበቅ፥ የነዳጅ ዘይትን እንቅስቃሴ በመቆጣጠርና የዓለምን ኢኮኖሚ ለማረጋጋት አሜሪካንና ሩሲያን ያልጨመረ የመንግሥታት ኅብረት አስፈለገ። በአውሮፓና በመካከለኛው ምሥራቅ ባለው ለውጥ ሳቢያ መድረኩ በሚገባ ተዘጋጅቷል፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አሥሩ መንግሥታት ቡድን፥ ስለ አምባገነኑ መሪና ማዕከሉን በመካከለኛው ምሥራቅ ስለሚያደርገው የዓለም መንግሥት የተነበየው እውን እየሆነ ነው። አሁን በዓለማችን የሚታየው ቀውስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ክንውን ነው።

## ♦ ወሳኙ ቁም ነገር

እነዚህ ሐቆች ወደ መንፈሳዊ ጥያቄ ይመሩናል። የመካከለኛው ምሥራቅ መሪ ከመነሣቱ በፊት ቤተ ክርስቲያን የምትነጠቅ ከሆነ፥ ይህ ሁኔታ የሚፈጸመው በጣም በቅርቡ መሆን አለበት። ዓላማችን ከዚህ በፊት በታሪክ ከታየው ይበልጥ ለመጨረሻው ትንቢት ፍጻሜ በመመቻቸት ላይ ናት።

ከእያንዳንዱ ሰው አንጻር ሲታይ የመጨረሻው ወሳኝ ነጥብ የወደፊቱ የትንቢት ክንውን ሳይሆን፥ ያ ሰው ክርስቶስን ለመቀበል ተዘጋጅቷል ወይስ አልተዘጋጀም? የሚል ይሆናል። የመጨረሻው ትንቢት እያንዳንዱ ግለሰብ ክርስቶስን እንደ ፈራጅ ይገናኘዋል ይላል። በክርስቶስ አምኖ መዳኑ ነው ዋናው የሕይወት ቁም ነገር።

የአሁኑ የዓለም ወቅታዊ ሁኔታዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ቃል በቃል እንደተፈጸሙና እንደሚፈጸሙም አመልካችና ጠቋሚዎች ስለሆኑ፥ በክርስቶስ አምኖና ታዞ ለመዳን ወቅቱ አሁን ነው።

# 10

# መጪው የመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም

## ♦ ዓለም ስለ ሰላም የሚያሰማው ሁካታ

ኢራቅ ኩዌትን በ1990 ዓ.ም. ከወረረች ወዲህ አሜሪካና ተባባሪዎቿ ጦራቸውን ወደ አካባቢው አሠማርተዋል፤ ስለሆነም ከዚህ በፊት ያልታየ ሁኔታ በአካባቢው ተከሥቶአል። የሰሜን ቃል ኪዳን አገሮች (NATO/ኔቶ) ኢራቅ ላይ የጣሉት ማዕቀብ አገሪቱን አስጊ ቀውስ ውስጥ እንድትገባ አድርጓታል። ሳዳም ሑሴን በዓረብ መሬት ላይ የሰፈረውን ጦር እከላከላለሁ በማለት እስላሙን ዓለም ለጅሃድ (ቅዱስ ጦርነት) ጥሪ አደረጉ። ፍልስጥኤማውያንና ሌሎች ከቁጥር የማይገቡ ቡድኖች በፍጥነት የኢራቅን አቋም ደገፉ።

ሰዎች ይታገታሉ፤ ሽብርና ግድያም ተስፋፍቶአል፤ በየዕለቱም የጦርነት ሥጋት እንዳንዣበበ ነው፤ ታዲያ፥ ይህን ድርጊት የዓለም ሕዝብ እስከ መቼ ይታገሣል?

ብቸኛውና ትክክለኛው መፍትሔ የተፋጠጡትን ኃይሎች ትጥቅ የሚያስፈታ፥ ቅራኔዎቹን የሚያስወግድ እና አስተማማኝ ዋስትና የሚሰጥ የሰላም ውል ማድረግ ነው። ከዚህ አንጻር አንድ ኃያል መሪ ዓለምን ካለችበት ምስቅልቅል ሁኔታ አወጣታለሁ በማለት በሚያቀርበው መላ፥ የብዙዎችን ትኩረት ይስባል።

## ♦ ሰላምና የመጨረሻው ሂደት

የመካከለኛው ምሥራቅ የሰላም ድርድር ስለ መጨረሻው ዘመን ከተነገሩት ትንቢቶች አንዱና ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው። የሰላም ድርድሩ መፈረም ወደ አርማጌዶን ለመድረስ የተወሰነ ጊዜ ብቻ እንደቀረው ያመለክታል። አዲሱን የዓለም አምባገነን መሪም ያስተዋውቀናል። ያም የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው።

እንደ ዳንኤል 9፡27 ገለጣ፥ ወደ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚያቀርቡት የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት የሚጀምሩት፥ ይህ የሰላም ስምምነት ውል ሲፈረም ነው። በእስራኤልና በአዲሱ መሪ መካከልም ቃል ኪዳን እንደሚደረግ በዚሁ ክፍል ተጽፎአል (ዳን. 9፡26)። ክንውኑ በትኩረት ሲጤን መሪው በ70 ዓ.ም. ከነበረው የሮማውያን መንግሥት እና ኢየሩሳሌምንካጠፏት ሰዎች ጋር መዛመዱን እንረዳለን። የቃል ኪዳኑ ዝርዝር ባይሰጠንም፥ ዓላማው የዓረቦችንና የእስራኤልን አለመግባባት ለመፍታት፥ እንዲሁም ለመካከለኛው ምሥራቅ ውዝግብ ዓለም አቀፍ መፍትሔ ለመስጠት ነው። የሰላሙ ውል አስገዳጅና እስራኤል በጦርነት ያገኘችውን መሬት አስለቅቆ በምትኩ ዓለም አቀፍ ዋስትና፥ ደኅንነትና ብልጽግና የሚሰጣት ይመስል ይሆናል።

## ♦ የሮማውያን አገዛዝ ማንሠራራት

የእግዚአብሔር ቃል ዛሬ የዓለምን ሁኔታ የሚገልጠው፥ ከሰላሙ ስምምነት በፊት ካለው የተለየ አድርጎ አይደለም። ከሰላም ውል በፊት በሜዲትራኒያን አካባቢ ያሉ አሥር መንግሥታት ኅብረት ይመሠርታሉ። እነዚህም መንግሥታት በዳንኤል 7፡7 እና 24 አሥር ቀንዶች ባሉት አውሬ ተመስለዋል። ይህ የዓለምን የመጨረሻ መንግሥት ግዛት የሚወክል ሲሆን፥ እንደገና የሚያንሠራራውን የሮም ግዛት ያመለክታል። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተርጓሚዎች የአውሮፓ የጋራ ገበያ አገሮች ኅብረት [Common Market]፥ የዚህ ትንቢት ፈጻሚ ነው ብለው ያስባሉ። የጋራ ገበያው መሥራች አገሮች አሥሩ መንግሥታት ይሁኑ ወይም ለሌሎች አሥር መንግሥታት ኅብረት ቅድመ ሁኔታ አመቻቺዎች፥ በእርግጠኛነት ለመናገር ያስቸግራል። የመጨረሻው የአሥሩ መንግሥታት ኅብረት የሜዲትራኒያን አካባቢ ለመቆጣጠር የሚያስችል የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኃይል የሚኖረው "የታደሰ የሮም መንግሥት" ይሆናል። የመጨረሻው መሪም ከእነዚህ መንግሥታት ሦስቱን ለመቆጣጠር የሚችል መሆን አለበት።

## ♦ በመለወጥ ላይ ያለችው አውሮፓ ሚና

የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በአውሮፓ አገሮች መካከል ያለውን ውጥረት በመቀነስ ለአውሮፓ አገሮች ኅብረት ምሥረታ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል። ይህም ብዙዎች ለረጅም ጊዜ ሲያልሙት የቆዩት ጉዳይ ሲሆን፥ በመገናኛ ብዙሃንም በሰፊው ሲወራ የቆየ ነው። አንዳንድ የአውሮፓ መንግሥታት ወታደራዊው ችግራቸው የተወገደ ስለሚመስላቸው ወደ ፓለቲካው አንድነት ያመሩ ይሆናል። በትንቢት በተነገሩት አሥር መንግሥታት ኅብረት ውስጥ

ምናልባት የምዕራብ እስያና የሰሜን አፍሪካ አገሮች ይኖሩበት ይሆናል። አብዛኛዎቹ መንግሥታት የሚመጡት ግን ከአውሮፓ ሲሆን፥ ይህም ጣሊያንን፥ የማይናቅ ግምት የሚሰጣት ስፔይንን፥ ፈረንሳይን፥ ግሪክንና ሌሎችንም ይጨምራል። በአውሮፓ የሚታየው ፈጣን ለውጥ፥ ስለ መጨረሻው ዘመን ከተነገሩ ትንቢቶች ጋር በትክክል የሚጣጣም ነው።

በአውሮፓና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚታየው ዓለም አቀፍ ሽኩቻ በአካባቢው ሰላምና የኢኮኖሚ ብልጽግና ያሰፍን ዘንድ የመንግሥታቱ ኅብረት አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል። በዳንኤል ትንቢት በተነገረው መሠረትም ለዚህ ኅብረት ምሥረታ አስፈላጊው ሁኔታ በመመቻቸት ላይ ነው።

## ♦ የእስራኤል ለድርድር ዝግጁ መሆን

የመጨረሻው ሰላም ከመምጣቱ በፊት አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸው እጅግ አስፈላጊ ነው። ውሉ ከመደረጉ በፊትም እስራኤል ወደ ምድሯ መመለስ አለባት። በዚሁ መሠረት በ1948 ዓ.ም. ወደ ምድሯ በመመለስ የራሷን መንግሥት አቋቁማ ፖለቲካዊ ዕውቅና ማግኘቷ አስፈላጊና የመጀመሪያ እርምጃ ነበር። ወታደራዊው ጦርነትና ያላቋረጠው ግርግር ለሰላሙ ስምምነት ሁኔታዎችን አመቻችቷል ለማለት ይቻላል። በዓለም ኅብረተሰብ ታላቅ ግፊት ካልተደረገባት እስራኤል በመግባባት የሰላም ስምምነት እስከ መዋዋል ትደርሳለች ማለት የማይታሰብ ጉዳይ ነው።

የዓረብ አገሮች ነጻነት ጉዳይና ያን ተከትሎ የሚከሠተው ዓለም አቀፍ የነዳጅ ቀውስ ወደ መጨረሻው የሰላም ውል አስገዳጅ ግፊት ያደርጋል። በኢንዱስትሪ የበለጸጉ የምዕራብ አገሮች ዓለም አቀፉን የኢኮኖሚ ቀውስ በመፍራት ማንኛውንም መሥዋዕትነት ከፍለው ዓረቦችና እስራኤሎችን ወደ ስምምነቱ ለማድረስ ይጥራሉ። ይህም አሁን በተግባር የሚታይ ሐቅ ነው።

## ♦ አዲስ የዓለም መሪ ብቅ ማለት

በሁለተኛ ደረጃ የተነገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ከመካከለኛው ምሥራቅ ስለሚነግሠው መሪ ነው የሚያመለክቱት። የመሪው አመጣጥ የሰላሙ ውል ከመፈረሙ ቀደም ብሎ ሊሆን ይችላል። መካከለኛው ምሥራቅ ዛሬ እንዲህ ያለውን የዓለም መሪ ይሻል። እርሱም መካከለኛው ምሥራቅን በዕቅድና በፕሮግራሙ የሚገርክና የሚያስተባብር ብቻ ሳይሆን፥ ዓለምን አጠቃሉ የሚገዛ ይሆናል። ወዲያውኑ ትኩረቱ በአውሮፓና በዓረብ አገሮች በሚደረግ የመሪነት ትግል ላይ ይሆናል። ተልዕኮውን ለመጀመርም ጊዜውን በመጠበቅ ላይ ነው። እርሱ ብቅ ከማለቱ በፊት ግን፥ ክርስቶስ በተስፋ ቃሉ መሠረት ለቤተ

ክርስቲያኑ ይመጣላታል። በመካከለኛው ምሥራቅ የሚካሄደው ዓለም አቀፍ ክንውንም ይህ የቤተ ክርስቲያን መነጠቂያ ጊዜ በጣም መፋጠኑን ያመለክታል።

መጪው የሰላም ስምምነት ምን ቅርፅ ይይዝ ይሆን? ከብዙ አስደናቂ ልምዳችን በመነሣት የሰላሙን ውል ቅርፅ መተንበዩ ያስቸግረናል። እንዲሁም ምን ዓይነት አሠቃቂ ሁኔታዎች ይህን አስገዳጅ የሆነ ስምምነት አስፈላጊ እንዲሆን እንደሚያደርጉ ለመተንበይ ያስቸግራል። ወደፊት ጦርነት የሚደረግ ከሆነ፥ ውጊያው የሚካሄደው በምን ይሆን? በኬሚካል ወይስ በኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች?

የድርድሩ ውጤት ምንም ይሁን ምን እስራኤልን ከተደጋጋሚ ወታደራዊ ጥቃትና ሥጋት የሚያተርፍ መሆን አለበት። ዓለም አቀፋዊው ሰላም ጠባቂ ግብረ ኃይል በአዲሶቹና በአሥሩ መንግሥታት ኅብረት መሠረት ግጭት በተነሣባቸው አካባቢዎች በመገኘት ድንበር ያስከብር ይሆናል። የሰላሙ ስምምነት አንዱ ክፍልም አጠቃላይ ትጥቅ ማስፈታት ሊሆን ይችላል። በድርድሩ ወቅት ኢየሩሳሌም ዓቢይ የመወያያ ነጥብ ስትሆን፥ እስራኤል ደግሞ ከተማይቱን አሉኝ ከምትላቸው ነገሮች ሁሉ አልቃ ነው የምትመለከታት። ያለ ጥርጥር ኢየሩሳሌምን ዓለም አቀፍ ከተማ ለማድረግ ከፍተኛ ፍጭት ይደረጋል። አይሁዶች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችና እስላሞች በከተማይቱ የመጠቀም መብት ያገኙ ይሆናል። ቤተ መቅደሱ ዓለም አቀፋዊ ክልል ሲሆን፥ በአንጻሩም እስራኤል በጦርነት የያዘችው ግዛቷ ይቀንሳል።

ዓረቦች ካላቸው ኃይል አንጻርና፥ አሜሪካም እስራኤልን በመደገፍ ከምታሳየው ተለዋዋጭ ፖሊሲ አኳያ ሲታይ፥ ኢየሩሳሌምን የማይጨምር ማንኛውም ድርድር ዓረቦችን ያረካቸዋል ብሎ ማሰብ የማይቻል ነው።

ይህ የሰላም ስምምነት ቶሎ ይደረግ ይሆን? እዚህ መላ ምት ውስጥ እጁን የሚያስገባ የለም። መደረጉ እንደማይቀር ግን፥ ቅዱሳት መጻሕፍት በእርግጠኛነት ገልጠዋል። በአዲሱ የዓለም ገዥና በእስራኤል መካከል ቃል ኪዳን ይደረጋል (ዳን. 9፡27)። ቃል ኪዳኑም እስራኤል ሃይማኖታዊ ሥርዓቷን መፈጸም እንድትቀጥል፥ ቤተ መቅደሷን እንድትሠራና በአይሁድ እምነት መሠረት መሥዋዕት እንድታቀርብ የሚፈቅድ ይሆናል። ይህ ሁሉ አስቀድሞ በዳንኤል 9፡27፤ 12፡11 የተጠቀሰ ሲሆን፥ ኋላም ጠላቶቿ ቃል ኪዳኑን አፍርሰው የዘወትር መሥዋዕቱን እንደሚያስቆሙ በክርስቶስ ተነግሯል (ማቴ. 24፡15)።

## ◆ ቃል ኪዳኑ ሲፈርስ

በአሁኑ ጊዜ የሚደረግ ማንኛውም የሰላም ውል ዘላቂ ሳይሆን፥ እስራኤልን የማጥቂያ አመቺ ጊዜ ለማመቻቸት መሆኑን ከዓረቦች ጉባኤ

የሚነፍሰው ጭምጭምታ ይጠቁማል። ይህ ሴራ ከእስራኤል ጋር ዘላቂ ሰላም የማይፈልጉትን አንዳንድ የፍልስጥኤም አንጃዎች አስደስቷቸዋል። ስለዚህ የሰላሙ ውል ለጊዜው ቢደረግ እንኳን ይፈርሳል። ይህ የሰላም ውል፥ በእግዚአብሔር ቃል የተተነበየና ከሜዲትራኒያን ክልል ኅብረት የሚወጣው መሪ ዓለም አቀፍ እውቅና ለማትረፍ ሲል የሚያደርገው ነው። ስምምነቱ የሚሠራው ለሦስት ዓመት ተኩል ሲሆን፥ መሪው ይበልጥ ዓለም አቀፍ ኃይል ያገኘ ዘንድ እንደ መወጣጫ ይግለገልበታል። በኋላ ግን ሆን ተብሎ ስምምነቱ እንዲፈርስ ይደረግና ለዓለም ታላቅ ጥፋት፥ ለእስራኤልም አስከፊ ስደት የሚያስከትል ሁኔታ ይፈጠራል። የዚህን ቃል ኪዳን አለመከበር ክርስቶስ "ታላቅ መከራ" (ማቴ. 24፡21) ብሎታል። ኤርምያስም "የያዕቆብ መከራ ዘመን" ይለዋል (ኤር. 30፡7)።

## ♦ የሰላሙን አለቃ መጠበቅ

እስራኤላውያን በያዕቆብ መከራ ዘመን በአይሁድ ላይ የሚደርሰውን ስደት በአንክሮ ይመለከቱ ዘንድ ዓይኖቻቸው ይበሩላቸዋል። ከዚህ ቀደም በሰዎች የተገባላቸው ተስፋ ሁሉ ከንቱ እንደሆነ ይገነዘባሉ። የዚህ ትንቢት በግልጥ መሟላት የመሢሑ የመጀመሪያ መምጣት እንደተፈጸመና ዳግም ምጽአቱም መቃረቡን እንዲገነዘቡ ያደርጋል። በሦስት ዓመት ተኩሉ ታላቅ መከራ ወቅት ወደ ጌታ የሚመጡ አዲስ አማኞችም በኢየሱስ ዳግም ምጽአት ተስፋ ላይ ሙጥኝ ይላሉ። ኢየሱስ አይሁዳውያንን አስመልክቶ በተናገረው ትንቢት፥ "በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም" ብሎ ነበር (ማቴ. 23፡39)።

ስለሆነም የሰላም አለቃ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምድርን ሊገዛ በኃይልና በክብር እስኪመለስ ድረስ ዘላቂ ሰላም ሊኖር አይችልም።

# 11

# ያላቋረጠው የሩሲያ ጣልቃ ገብነት ሥጋት

## ♦ የሩሲያ ወረራ ፍርሃት

ባለፈው የመካከለኛው ምሥራቅ ግጭት ታላቁ ሥጋት የሩሲያ ጣልቃ ገብነት ነበር። የአሜሪካ ወታደራዊ ኃይልና ጦር መሣሪያዎች ለእስራኤል ዋስትና እንደሆኗት ሁሉ፥ በሌላ በኩል ሩሲያና ወታደራዊ ኃይሏ በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ ደመና ጥለው ነበር። ይህ ፍርሃት ነበር እስራኤል በ1956 ዓ.ም. ያገኘችውን ድል እንዳትጠቀምበት ያገዳትና በ1973 ዓ.ም. ያገኘችውንም ስትራተጂያዊ ድል ትታ በተኩስ አቁሙ እንድትስማማ ያስገደዳት። የተኩስ አቁም ስምምነቱ አሳብ የመጣው የግብፅ 3ኛ ክፍለ-ጦር ሠራዊት በእስራኤል ሊከበብ በነበረ ጊዜ ነው። እስራኤል ይህን ሠራዊት ብትከብ ኖሮ የምድር ጦርና አየር ኃይሎቿን ግብፅ፥ በመጨረሻም ሶሪያ እንዲገቡ ለማድረግ ያስችላት ነበር። እነዚህ ጦርነቶች እንዳይቀጥሉ ያደረገው፥ እስራኤል ማጥቃቷን ብትገፋበት ኖሮ የሩሲያን ወረራ ያስከትልና፥ ይህም በሩሲያና በአሜሪካ መካከል ወደ ኑክሊየር ጦርነት ሊያመራ የሚችል ቀጥተኛ ግጭት ላይ ያደርሳል የሚል ፍርሃት ነው።

ያለ ምክንያት አልነበረም ይህ ሥጋት። ሩሲያ የዓረብ አገሮችን ለመርዳት ቁርጥ ውሳኔ ስላደረገች ከአገሮቹ አንዱ ሲጠቃ ዝም ብላ መመልከት አትችልም። ፈጣኖቹ የጦር መርከቦቿ በአካባቢው ከመኖራቸውም በላይ፥ ለመካከለኛው ምሥራቅ ያላት መልክዓ-ምድራዊ ቅርበት ለወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላት ነበር። ይህ ወረራ የሚፈጸምበትን ጊዜ ሕዝቅኤል በትንቢቱ እንዲህ በማለት ይገልጠዋል:-

> "አንተ የሰው ልጅ ሆይ ስለዚህ ትንቢት ተናገር! ጎግንም እንዲህ በለው፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በዚያ ቀን ሕዝቤ እስራኤል ሳይፈራ በተቀመጠ ጊዜ አንተ አታውቀውምን? አንተም ከአንተም ጋር ብዙ ሕዝብ ሁላቸው በፈረሶች ላይ የተቀመጡ ታላቅ ወገንና ብርቱ ሠራዊት ከሰሜን ዳርቻ ከስፍራችሁ ትመጣላችሁ። ምድርንም ትሸፍን ዘንድ እንደ ደመና

በሕዝቤ በእስራኤል ላይ ትወጣለህ። በኋለኛው ዘመን ይሆናል ጎግ ሆይ በዓይናቸው ፊት በተቀደስሁብህ ጊዜ አሕዛብ ያውቁኝ ዘንድ በምድሬ ላይ አመጣሃለሁ" (ሕዝ. 38፡14-16)።

## ♦ የሩሲያ ኃይል እየቀነሰ መሄድ

በምሥራቅ አውሮፓ ኮሚኒዝም መፈራረሱና የሩሲያ የገንዘብና የፖለቲካ አቅም ማሽቆልቆሉ የዓለምን ኅብረተሰብ ትኩረት ሳበ። አገሪቱ ዛሬ ባለ ብዙ ወታደርና ኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ብትሆንም፥ እንደ ቀድሞው ለዓለም ሰላም አሥጊ አይደለችም። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለተዳከመች ዓለም አቀፍ ጦርነት ለማካሄድ አቅሙም ሆነ ፍላጎቱ የላትም። ሆኖም ከአካባቢው በቅርብ ርቀት ወጣ ብላ ዳጎስ ያለ ወታደራዊ ኃይል ማኖሯን ትቀጥላለች።

ሩሲያ ባለፉት ዘመናት ለመካከለኛው ምሥራቅ ገንዘብና የተለያየ ወታደራዊ እርዳታ በማድረግ በአካባቢው ተቀባይነት ያገኘች ትሁን እንጂ፥ የነበራት የወሳኝነት ሚና ግን እጅግ ጥቂት ነበር። ዜጎቿ በ1972 ዓ.ም. ከግብፅ እንዲወጡ ቢደረግም እንደገና በ1973 እና 1974 ለሶሪያና ለግብፅ ወታደራዊ እርዳታ በማድረግ በአገሮቹ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ ሆነች። በተጨማሪም ሩሲያ ለሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በአብዛኛው የወታደራዊ ዕቃዎች ግዢ ምንጭ ነበረች።

ዓረቦች በነዳጅ ዘይት ሀብት ሳቢያ የገንዘብ አቅም በማግኘታቸው ከፈለጉት አገር ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን ለመግዛት ችለዋል። ኢራቅና ኢራን ስምንት ዓመታት በፈጀው ግጭታቸው ወቅት ከሌሎች አገሮች ይልቅ ለጦር መሣሪያ መግዣ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ተበድረዋል። ሁለቱም አገሮች ከጦርነቱ ያገኙት ትርፍ የለም፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የጦርነቱ ሰለባ ሆነውባቸዋል። ሁኔታው ዓረብ አገሮች ማንኛውንም ዓይነት ዓለም አቀፍ ጦርነት የማድረግ አቅማቸው ውሱን መሆኑን የሚያመለክት ነው። እንዲሁም ኢራቅ ኩዌትን በወረረችበት ወቅት ከታየው ዓለም አቀፍ ተቃውሞ በተጨማሪ የራሱ ተጽዕኖ ነበረው።

## ♦ የሩሲያ ዲፕሎማሲያዊ ቁማር

ሩሲያ በባሕር ኃይሏ እየተረዳች የንግድና ወታደራዊ እንቅስቃሴዋን ዕድሜ በዓለም ዙሪያ ለማራዘም ባላት ዕቅድ መሠረት በሜዲትራኒያን ክልል፥ በስዊዝ ካናልና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ በመንቀሳቀስ ዓረቦችን ለመቆጣጠር ተስፋ አድርጋ ነበር። የዓለም ኃያል መንግሥት ሆና መቆየት ካሻት ባልቲክ ባሕር [Baltic Sea] ላይ የሚገኙ የጦር መርከቦችዋ፥ በምዕራብ እስከ

አትላንቲክና፥ በምሥራቅ በስዊዝ ካናል አድርገው እስከ ደቡባዊ እስያ ድረስ በነጻነት ለመንቀሳቀስ መቻል ነበረባቸው።

የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች የሩሲያ የቅርብ ጎረቤቶች እስከሆኑ ድረስ፥ ሩሲያ ብሔራዊ ጸጥታ እንዲኖራት አካባቢውን መቆጣጠር ያስፈልጋታል። ይህን በማድረግ ላይ ሳለች በተቃራኒው በአካባቢው የነበራት የገንዘብና ዲፕሎማሲያዊ ዓላማ የማይሳካ ይሆን ጀመር። ስለዚህ ኢኮኖሚዋና ብሔራዊ ደኅንነቷ እንዲህ አደጋ ላይ ከሆነ የአካባቢውን ሁኔታ በቀጥታ በወታደራዊ ኃይል ከመቆጣጠር ሌላ ያላት አማራጭ ጥቂት ነበር።

## ♦ ሩሲያ ወደፊት ከመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮች ውጭ መሆኗ

ከትንቢት አንጻር ሲታይ፥ ሩሲያ ከዓረብ ዓለም ጋር ያላት ግንኙነት አሜሪካ የሚኖራትን ያህል አይሆንም። በአንዳንድ ሁኔታ ሁለቱም ኃያላን መንግሥታት እንደ "አረመኔ" ነው በአካባቢው የሚታዩት። ሩሲያ እስራኤልን እንደምትወራት ትንቢቱ ይናገራል (ሕዝ. 38-39)። ይህ የመጨረሻው ዘመን ድርጊቶች ክፍል ሲሆን፥ ሩሲያ ላይ አስከፊ ውድመት የሚያደርስባትና በመካከለኛው ምሥራቅ ያላትን ተሰሚነት የሚያሳጣትም ይሆናል።

የዓለም የነዳጅ ኃይል እጥረት፥ መንግሥታት በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ ያላቸውን አሰላለፍ እንዲለውጡ አድርጎአቸዋል። ሩሲያና አሜሪካ የራሳቸው የነዳጅ ክምችት ሲኖራቸው፥ አዲሱ የተባበሩት አውሮፓውያን ብልጽግና ኅብረት ግን ነዳጅን በተመለከተ የዓረቦች ጥገኛ ነው። የአውሮፓ መንግሥታት በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርጋቸው ይህ ሁኔታ እንደሚሆን መገመቱ አያዳግትም።

በ1990 ዓ.ም. በኢራቅ ውዝግብ በተነሣ ጊዜ፥ አሜሪካና አውሮፓ ኃይላቸውን አስተባብረው ወረራውን ለመከላከል ጥረት ያደረጉት፥ የባሕረ-ሠላጤውን ነዳጅ ደኅንነት ለማስጠበቅ ነበር።

የባሕረ-ሠላጤው ነዳጅ ለዓለም ወታደራዊና ፖለቲካዊ ደኅንነት፥ በተለይም ለአውሮፓና ለጃፓን ኢኮኖሚያዊ ዋስትና አስፈላጊ ነው።

በአካባቢው በሚደረገው የሰላም ውል ውስጥ አሜሪካም ሆነች ሩሲያ ስለሚኖራቸው ሚና በትንቢት የተነገረ ግልጥ ነገር የለም።

በመጨረሻ ግን ሩሲያ ከመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ እንድትገለል በመደረጓ ተቆጥታ አካባቢውን ለመቆጣጠር ጦርነት ትከፍታለች። ይህ ወረራ ነው በሕዝቅኤል 38ና 39 የተገለጠው። ጦርነቱ የሜዲትራኒያንን ክልል የሰላም ስምምነት የሚያናጋ ከመሆኑም በላይ፥ የዓለም የኃይል ሚዛን ወደ ሜዲትራኒያን ክልል መሪ እንዲያጋድል በማድረግ በአምባገነንነት ያስተዋውቀዋል።

## ♦ ሩሲያ እስራኤልን ለመውረር ስትነሣ

ነቢዩ ሕዝቅኤል ሩሲያ ኃይሏን በማጠናከር በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ ወታደራዊ እርምጃ ስለምትወስድበት ጊዜ ተናግሯል። የትንቢቱ 38ኛ እና 39ኛ ምዕራፎች ለትንቢት ተርጓሚዎች አስቸጋሪ ቢሆኑም፥ ከሰሜን ወገን የሚመጣ የሠራዊት መንጋ እስራኤልን እንደሚወራት በግልፕ ያስረዳሉ። እንዲሁም የመሪው ስም፥ የአገሩ ስም፥ ከተሞቹና በግልፕ የተብራራው የወታደሮች ሁኔታ "ከሰሜን ዳርቻ ከስፈራችሁ" (ሕዝ. 38፡15) የሚለው ሁሉ፥ ዛሬ ሩሲያ በመባል የምትታወቀውን አገር ነው የሚያመለክቱት።

ያን ጊዜ ከእስራኤል ወይም ከማንም ሰላም አስከባሪ ኃይል ተቃዋሚ አለመኖሩ ጦርነቱን ያልተለመደ ያደርገዋል። "ከሰይፍ ወደተመለሰች ምድር" (ሕዝ. 38፡8) ተብላ ነው ምድሪቱ የተገለጠችው። እስራኤል የሰላምና የብልጽግና ጊዜ ይኖራታል፥ ሁሉም "ሳይፈሩ ይቀመጡባታል" (ሕዝ. 38፡8) ተብሎላታል። ሕዝቅኤል በትንቢቱ "በኋለኛው ዘመን" የሚለውን ለመግለጥ ነው ያሰበው (ሕዝ. 38፡16)፤ እስራኤል እንደገና ተሰብስባ ዘላቂ ሰላም ነው በምትለው ጊዜ ደስተኛ ትሆናለች። ሩሲያን ለወረራ ከሚገፋፏት ሁኔታዎች አንዱ፥ አገሪቱ በዚያን ጊዜ በቀላሉ የምትበከል መሆኗ ነው። ይህ ሁኔታ ነው ሩሲያን ለእስራኤል የሰላም ዋስትና ከሰጡ የሜዲትራኒያን ኅብረት አገሮች ጋር ለበላይነት ፍልሚያ እንድትገጥም የሚያደርጋት።

ወራሪው ሠራዊት የተገለጠው እንደ "ታላቅ ወገንና ብርቱ ሠራዊት" (ሕዝ. 38፡15) ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገልጣቸው ኋላ ቀር የጦር መሣሪያዎች፥ ፈረሶችና ፈረሰኞች ወታደራዊ ልብስ (ጥሩር) እንደለበሱ አድርጎ ነው። አንዳንዶች፥ ነቢዩ በጊዜው ዘመናዊ ጦርነቶችን በብዙ ታንኮችና ብረት ልብስ (ጥሩር) ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ጥሩ አማራጮች ናቸው ይላሉ። ትንቢቱ የሚያመለክተው ሌላ ጉዳይ፥ ወደፊት በነዳጅ ኃይል ሳቢያ ውዝግብ ተፈጥሮ ትጥቅ የመፍታት ጉዳይ ሲነሣ ሩሲያ ለአካባቢው ካላት ቅርበት አኳያ በሽምቅ ፈረሰኞች አደጋ እንደምትጥል ነው። ዛሬም ቢሆን ሩሲያ እያሌ ፈረሰኛ ጦር ካላቸው ጥቂት አገሮች አንዷ ናት። በወረራው ወቅት ጦሯ ከሜዲትራኒያኑ ኅብረት በተገለሉና የብልጽግናው ተካፋይ ባልሆኑ አንዳንድ አነስተኛ አገሮች የሚደገፍ ይሆናል።

## ♦ የሩሲያ ውድቀት

ለትርጉሙ ችግር የሚሰጠው መፍትሔ ምንም ይሁን ምን፥ ወሳኙ ጦርነትና ውጤቱ ግልጥ ናቸው። ሰላምና ብልጽግና በሰፈነበት ጊዜ ወራሪው ሠራዊት በሩሲያ ተመርቶ ወደ እስራኤል ይተማል። ዘማቾቹ (ወራሪዎቹ)

በሙሉ በሕዝቅኤል 38፡18-23 ላይ እንደተገለጠው በምድር ነውጥ፥ በማያቋርጥ ዝናብ፥ በበረዶ፥ በእሳትና በእሳተ ገሞራ ፈጽሞ ይጠፋሉ። በምንም ይሁን በምን ሠራዊቱ ይወድማል፥ የሞቱትንም ለመቅበር የሰባት ወር ጊዜ ይወስዳል።

እግዚአብሔር እስራኤልን ለማዳን በቀጥታ ጣልቃ ስለሚገባ በአገሪቱ ውስጥና በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ሕዝቦች ይህ የእርሱ ሥራ እንደሆነ ይገነዘባሉ። ለአንዳንዶች እግዚአብሔርን ለማምለክ በር ከፋች ይሆናቸዋል፤ በእምነታቸውም ምክንያት በሰማዕትነት ይሞታሉ። ለቀሪው ዓለም ደግሞ የጥፋት ማዕበል መጀመሩን ያመለክታል። በዚህ ጊዜ የዓለም የኃይል ሚዛን የሚጠፋ ሲሆን፥ ይህም የሚዲትራኒያኑ ኅብረት መሪ ያለምንም ተቃዋሚ የዓለም አምባገነን ገዥ መሆኑን እንዲያውጅ ያስችለዋል። ይህ መሪ (የክርስቶስ ተቃዋሚ) ባጋጠመው ባዶ የሥልጣን ሥፍራ ሁሉ ጠላቂ ብቻ ሳይሆን፥ እኔ ራሴ ነኝ ወራሪውን ጦር ያጠፋሁት ብሎ ይመጻደቃል።

## ♦ የሩሲያ ወረራ በቅርብ ይፈጸም ይሆን?

በሕዝቅኤል ምዕራፍ 38 እና 39 ትርጉም መሠረት ዋናው ጥያቄ ወደ አርማጌዶን በሚያመራው ሂደት የሩሲያ ወረራ የት (በየትኛው ጊዜ) ይመደባል? የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ በሚሰጠው መልስ፥ ምሁራን የተለያየ አስተያየት ነው ያላቸው። አንዳንዶች ሂደቱ በየትኛውም ጊዜ ሊሆን ይችላል ሲሉ፥ ሌሎቹ የአርማጌዶን ጦርነት አንዱ ክፍል ነው ይላሉ። ጥቂት ተርጓሚዎች ደግሞ፥ የሺህ ዓመት መንግሥት በሚጀመርበት ጊዜ ክርስቶስን በመቃወም የሚሆን ነው ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ በሺህ ዓመቱ መንግሥት [Millennial Kingdom] መጨረሻ የሚከናወን ነው በማለት በራእይ 20፡7-9 ከተዘገበው ጋር ያዛምዱታል።

በሕዝቅኤል ትንቢት መሠረት ወረራው የሚካሄደው እስራኤል በሰላምና ብልጽግና በምትዝናናበት መጨረሻው ዘመን ነው። አገሪቱ በትንቢቱ ውስጥ የተገለጠችው ትጥቅ ፈታ፥ ምድሯ ቅጥር አልባ ሆኖ፥ መንደሮችዋም በሰላም ተዝናንተው (ተረጋግተው) ነው። ይህ ሁኔታ በ1948 ከተመሠረተች አንሥቶ የተለማመደችው ጉዳይ አይደለም። በተጠንቀቅ ነው የኖረችው።

ሰላም መቼ ይመጣል? በትንቢት የተነገረው የሰላም ወቅት የሚመጣው፥ የሚዲትራኒያኑ መሪ የመካከለኛው ምሥራቅን ግጭት ለማስወገድ የሰላሙን ውል ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት ይሆናል። የዚህ መሪ አነሣሥና የወደፊት ሕይወቱ ምን እንደሚመስል በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን። ሩሲያ እስራኤልን የምትወርረው በሚዲትራኒያኑ መሪና በእስራኤል መካከል የሰላም ውል ከተደረገ በኋላ ነው ብሎ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል።

በሕዝቅኤል 38 እና 39 የተገለጡት ሌሎች የትንቢቶቹ አተረጓጎሞች ሁሉ ከባድ ችግር ገጥሟቸዋል። ወረራው የሚፈጸመው ክርስቶስ ዳግም ከተመለሰና የዓለም ጦር ሠራዊቶች ሁሉ፥ በአርማጌዶን ጦርነት ካለቁ በኋላ ነው ብሎ ማሰቡ በጣም ያዳግታል። በሕዝቅኤል 38 እና 39 የተገለጠው ልዩ ወረራ ምንም እንኳን በራእይ 20፡8 "ጐግንና ማጎግን" ተብሎ ቢጠቅስ የክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት መጨረሻ ከሚለው አሳብ ጋር አይሄድም። በክርስቶስ ሺህ ዓመት አገዛዝ ፍጻሜ፥ ሩሲያ ብቻ ሳትሆን መላው ዓለምና ምድር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ያምጻሉ። ከዚህ ዓመፅ በኋላ የአሁኖቹ ሰማይና ምድር ጠፍተው የዘላለም መንግሥት ወዲያው ይጀመራል። ከሕዝቅኤል 38 እና 39 አንጻር ሕይወት ቀጣይ ነው። እንቀጹ ሙታንን ለመቅበር የሚወስደውን ሰባት ወሮችና አገሪቱ ከጦርነቱ የምታገግምበትን ዘመን ሳይቀር በዝርዝር ይገልጣል።


በሕዝቅኤል የተሰጠው የወረራ ዘመን ገለጣ፥ ከአርማጌዶን ጦርነት ጥቂት ቀደም ብሎ ከሚሆነው ታላቅ የመከራ ዘመን ጋር አይጣጣምም። የመከራው መጨረሻ ክፍል ከዚህ በፊት ያልታየ ጥፋት፥ ስደት በአይሁዶችና በእውነተኛ አማኞች እንዲሁም በዓለም ሁሉ አስፈሪ ሁከት ይሆናል። ይህ ወቅት እስራኤል አጥር በሌለው ክልል ተረጋግታ የምትቀመጥበት፥ በወርቅ፥ በብር፥ በከብትና በሌላም ሀብት በልጽጋ የምትኖርበት ዘመን አይደለም። እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች ካየን፥ ጦርነቱ የሚመጣው እስራኤል የሜዲትራኒያኑ መሪ በሚፈራረመው ሐሰተኛ የሰላም ዋስትና ስምምነት ስትታለል ነው። ውሉ የሚፈረመው አሥሩ መንግሥታት በሚፈጥሩት ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ኅብረት ይሆናል። እስራኤል በዚህ ዋስትና ተታልላ ያለ ኃይሏንና ጉልበቷን ከመከላከያ ይልቅ ለብልጽግና ታውላለች። የሰላም ውሉ ግን አራት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይፈርሳል።

## ♦ የሩሲያ ክስረት- የክርስቶስ ተቃዋሚው መጠቀም

በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደሚታየው፥ ሩሲያ አደጋ የምትጥለው እስራኤልን ብቻ ለመምታት አይደለም! በሜዲትራኒያን መሪ የተሰጣትን የሰላም ውል ለመፈታተን ጭምር እንጂ። ከሜዲትራኒያን አገሮች የሚውጣጣው አዲስ ኃይል የሩሲያን ሚና ይወስነዋል። እሷም የሞት ሽረት ውጊያ የምታደርገው በዓለም ኃያላን መንግሥታትና በመካከለኛው ምሥራቅ ያላትን ተደማጭነትና ተቀባይነት መልሳ ለማግኘት ነው።

እስራኤልን መውረር በሩሲያና በአዲሱ የሜዲትራኒያን ኅብረት መሪ መካከል የሚካሄድ ቀጥተኛ ግጭት ሆኖ ይታያል። አሜሪካ ገለልተኛ ትሆንና፥ የኃይል ሚዛኑ የሜዲትራኒያን ኅብረት መሪና የእርሱ ጓዶች በአንድ በኩል፥ ሩሲያና አበሮቹዋ በሌላ ይሆናሉ። ስለዚህም የሩሲያን ሠራዊት መደምሰስ

# የአሕዛብ ዘመን የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት



አስፈላጊ ይሆንና፥ ሥልጣንና ኃይል በአስደናቂ ሁኔታ በሜዲትራኒያኑ መሪ እጅ ይገባል። ይህ ሁኔታ መሪውን በዓለም እጅግ ከፍተኛና ኃያል ያደርገውና ምድርን የሚያናጉ ሁኔታዎች ውስጥ ይከተዋል።

ሩሲያ በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ እጅዋን ለማስገባት ያሰማችው ዛቻ በእርግጥ የሚሆን ነው። በቅርቡ፥ በመካከለኛው ምሥራቅ ያላት የኢኮኖሚ አቋም የአካባቢውን የወደፊት ሁኔታ ለመወሰን ትልቅ ሚና እንዲኖራት የሚያስችላት አይሆንም። ለሥልጣን የምታደርገው መፍጨርጨር በመጨረሻ ወታደራዊ ውድመት ያመጣባታል። እግዚአብሔርን በመካድዋና በመሳደብዋ፥ እንዲሁም በእስራኤል ላይ ጦር በመምዘዝዋ ከእግዚአብሔር አስፈሪ የበቀል ፍርድ ትቀበላለች። እንዳለፉት አያሌ አገሮች ሁሉ፥ እሷም የእግዚአብሔር እርግማን ይደርስባታል። የእርሱን ምርጥ ሕዝቦች የረገመ ይረገማልና።

# 12

# መጭው አምባገነን የዓለም ገዥ

♦ የወራሪዎች የዘመናት ሕልም

በታሪክ የሚታወሱ ብዙ ታላላቅ ሰዎች አንድ ቀን ዓለምን በቁጥጥ ራቸው ሥር የማድረግ ምኞት ነበራቸው። ይህ ምኞት የነበራቸው አያሌ ታላላቅ መንግሥታት በመካከለኛው ምሥራቅ ተነሥተዋል፤ ወድቀዋል። ግብፅ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ15ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን የመካከለኛው ምሥራቅ ኃያል መንግሥት ነበረች። ከዚያም ቀና ከተማዋን ነነዌ ያደረገችው አሶር ተተካች። ታላቁ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር አብዛኛውን ምዕራብ እስያ የሚጨምር ሰፊ ግዛት መሠረተ።

ታላቁ እስክንድር ከክርስቶስ ልደት ሦስት መቶ ዓመት በፊት እስከ ምሥራቅ ሕንድ ድረስ ድል አድርጎ ለጥቂት ዘመን ምዕራብ እስያን፥ ሰሜን አፍሪካንና ደቡብ ምሥራቅ አውሮፓን ገዝቷል። በክርስቶስ ዘመንም የሮማ ቄሣሮች ደቡባዊ አውሮፓን፥ ሰሜናዊ አፍሪካንና ምዕራብ እስያን በቁጥጥራቸው ሥር በማድረግ በዓለም ታሪክ ያልታየ ታላቅ ግዛት ያስተዳድሩ ነበር። ሕልሙ በዋተርሉ [Waterloo] ቢከሽፍበትም በዘመናችን የተነሣው ናፖሊዮንም [Napoleon] ዓለምን ለመግዛት ሞክሮ ነበር። በሀያኛው መቶ ክፍለ-ዘመንም ሂትለር [Hitler] ዓለምን አንድ ቀን በእግሮቼ ሥር አደርጋለሁ ብሎ ተነሥቶ ነበር።

ከነዚህ ሰዎች ውስጥ ማናቸውም ቢሆኑ ዓለምን አጠቃልሎ መግዛቱ አልተቻላቸውም። የጥንት ወታደራዊ ወራሪዎች ከፊል አውሮፓን፥ ሰሜን አፍሪካንና ምዕራብ እስያን መውረራቸው እርግጥ ነው። ነገር ግን የትኛውም ገዢ ቢሆን፥ ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋር የተገናኙትን ሦስቱን ዋነኛ አህጉራት በሙሉ ተቆጣጥሮ አያውቅም። ምዕራቡን ንፍቀ ክበብ፥ ማለትም አሜሪካንም መግዛቱ አልሆነለትም። እስከ እኛ ትውልድ (ዘመን) ድረስ ዓለም አቀፍ መንግሥት ለመመሥረት ምድራችን ምቹ አልነበረችም።

♦ በማነስ ላይ ያለችው ዓለም

የዘመኑ ቴክኖሎጂ ምጥቀት በመገናኛ፥ በትራንስፖርትና በጦር መሣሪያዎች መራቀቅ፥ ዓለማችንን በፍጥነት አቀራርበዋታል። ከአንድ ሥፍራ

ሚሳይል ቢተኮስ ከግማሽ ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የትኛውም ክፍለ ዓለም መድረስ ይችላል። ቴሌቪዥንና ራዲዮ እጅግ ፈጣን ግንኙነት እንዲኖር አስችለዋል። ሰዎች በተወሰነ ርቀት ተገልለው የኖሩባት ዓለም አሁን መልክዓ-ምድሯ አንድ እንደሆነ ነው የሚቆጠረው። ዋና ዋና ድርጊቶችን፥ የነዳጅ ዘይትን እገዳ፥ የኑክሊየር መሣሪያን እድገት፥ ወይም የረኃብ ሥጋት ወዘተ. ዜናዎች በየቤታችን ሆነን መከታተል እንችላለን። የሕዝቦች (መንግሥታት) ተለያይተው መኖር አክትሞአል።

በአንደኛው የዓለም ጦርነትና ከዚያም ወዲህ በነበረው ጊዜ ዓለም አቀፍ ጦርነቶችን ለመከላከልና፥ አንድ ዓለም አቀፍ ኃይል ለማቋቋም ለመጀመሪያ ጊዜ እርምጃዎች ተወስደዋል። ያም ምንም አጥጋቢ ውጤት ያላስገኘውና በጊዜው "የመንግሥታት ሊግ" [League of Nations/ሊግ ኦፍ ኔሽንስ] ይባል የነበረ ነው። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ውጤት ግራ የተጋባው የአሚሪካ መማክርት ጉባኤ (ኮንግሬስ) እንዲህ ባለው ዓለም አቀፍ ጉዳይ መንግሥቱ እንዲካፈል ፈቃደኛ አልነበረም። በሌላ በኩል ደግሞ ከውቅያኖስ ማዶ የሚገኙ አገሮች ተሰባስበው በአውሮፓና በእስያ የሚነሡ ችግሮችን ለመፍታት የሚችል ዓለም አቀፍ ድርጅት መመሥረታቸው የማያስፈልግ መስሎ ነበር። በዚህና በሌላም አኳኋን የዓለም ሕዝብ ከምን ጊዜውም ይልቅ እየተቀራረበ ይሄድ ስለነበር፥ አሜሪካ ያን እየተመለከተች በገለልተኛነቷ ልትገፋበት አልቻለችም። ለዚህም ነው እንደገና የ1941 የዓለም አቀፍ ጦርነት ተካፋይ የሆነችው። በዚህ ተሳትፎዋ ሳቢያ ፐርል ሐርበር [Pearl Harbor] በተባለው ሥፍራ የደረሰባት ጥቃት በዚህች እየጠበበች በመጣችው ዓለም ውስጥ ያላትን ኃላፊነት እንደገና እንድታስብ አደረጋት።

◆ የቦምቡ መምጣት

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ ዓለም አቀፍ መንግሥት መመሥረቱ ይበልጥ አስፈላጊ እየሆነ መጣ። ጦርነቱ አብዛኛውን የዓለም ክፍል ያዳረሰና ከዚያ በፊት ከነበሩት ጦርነቶች ሁሉ የከፋ ከመሆኑም በላይ ያከተመውም ሂሮሺማን [Hiroshima] እና ናጋሳኪን [Nagasaki] በአውቶሚክ ቦምብ አውድሞ ነበር። አውቶሚክ ቦምብ ከተፈለሰፈ ወዲህ የጦርነት አስከፊነት ከመቼም የላቀ በመሆኑ ማንኛውም መንግሥት ወይም ሕዝብ ያለ ፍርሃት መኖራቸው አክትሟል።

የኑክሊየር ሰለባ የሚሆኑት ወታደራዊ ኃይሎች ብቻ ሳይሆኑ ከተሞችና ሲቪሎችም ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የጥቂት ቀናት ወይም ሳምንታት ጦርነት ዓለምን በሙሉ ሊያወድም የሚችል ስለሆነ ይህን ያስወግድ ዘንድ አዲሱ ዓለም አቀፍ ድርጅት ከመቼውም ይልቅ አስፈላጊ ሆኗል።

♦ የዓለም መንግሥት የሰው ልጆች የመጨረሻ ተስፋ

የአውቶማቲክ ቦምብ ጦርነቶችን ለመግታት (ለመቆጣጠር) ሲባል፥ በ1946 ዓ.ም. የተወሰኑ መንግሥታትን ይዞ የተነሣው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በፍጥነት አድጎ ብዙዎችን ለማሰባሰብ ቻለ። ኮሚኒስት ቻይናን የዚሁ ድርጅት አባል ከማድረግ ጋር በርካታ ኃያላንና ትናንሽ መንግሥታት በድርጅቱ ታቀፉ። ያም ሆኖ ድርጅቱ ጦርነትን የማስወገድ አቅም የሌለው ሲሆን፥ በድርጅቱ ታሪክም ድክመቱ በተደጋጋሚ ታይቷል። ድርጅቱ በደቡብ ምሥራቅ እስያ የተከሠተውን ጦርነት ለማስቆምና በመካከለኛው ምሥራቅ ብቅ ብቅ የሚለውን የጦርነት እሳት ለማጥፋት ባለመቻሉ፥ ለዓለም ችግር የመጨረሻ መፍትሔ ሰጪ አለመሆኑን አስገንዝቧል።

ሆኖም በቀላሉ ራሷን በራሷ ልታወድም ለምትችለው ምድራችን፥ አንድ ዓይነት ዓለም አቀፍ መንግሥት መመሥረቱ የመጨረሻ ተስፋዋ ይመስላል። የኑክሊየር ጦርነት፥ የሕዝብ ብዛት፥ ረኃብ፥ የአካባቢ ብክለትና የኢኮኖሚ ውጣ ውረድ ዓለም አቀፍ ችግሮች ናቸው። ትናንሽ አገሮች ሳይቀሩ ዓለም አቀፉን የእርስ በርስ መደጋገፍ ሂደት ሊያናጉት ይችላሉ። ይህ በ1990 ዓ.ም. ኢራቅ ኩዌትን በወረረች ጊዜ ታይቷል። ዓለም አዲስ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አጋጥመዋታል። በኢኮኖሚው ውጥረት ሳቢያ የዓለም ሀብትና የገንዘብ ስርጭት ዓለም አቀፋዊ ቁጥጥር የሚሹ ሆነዋል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት [United Nations]፥ የጋራ ገበያ አገሮች እና የዓለም ባንክ [World Bank] እየጨመረ ለሚመጣው ችግርና ለሚነሡ ጥያቄዎች ጅምር መልሶች ናቸው።

በብዙ የዓለም አቀፍ መሪዎችና ምሁራን ግምት፥ በምድር ላይ የሰው ልጅ ሕልውና እንዲቀጥል ከተፈለገ፥ ጠንካራና አስተማማኝ የዓለም መንግሥት ብቸኛ ተስፋ ነው ብለው ያምናሉ። እነዚህ ዝንባሌዎችና አሳቦች እየገፉ በመጡበት በእኛ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉዳዩ ምን ይላል? ብሎ መጠየቁ አስፈላጊ ነው። የመጨረሻው ዘመን ሲቃረብ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች እንደሚከሠቱ ነቢያት አስቀድመው ተናግረዋል።

♦ ስለ ዓለማችን ታላላቅ መንግሥታት ነቢዩ ዳንኤል የተናገረው ትንቢት

ነቢያት የዘመናዊውን የዓለም መንግሥት አስፈላጊነት ምክንያት ባያስተውሉም፥ ታሪክ የሚያከትመው ዓለም በመጨረሻ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ከተካተተች በኋላ እንደሚሆን አመልክተው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የተነበየው፥ ያለፉትን ዋና ዋና የዓለም መንግሥታት መነሣትና መውደቅ ብቻ አይደለም። በትንቢቱ መሠረት የዓለም ሁኔታ በትክክል ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ወደሚከሠተው ማዕከላዊ የዓለም መንግሥት ምሥረታ እያመራ መሆኑንም ተንብይዋል።

ለምሳሌ ነቢዩ ዳንኤል፥ በመጨረሻ፥ ምድር በዓለም መንግሥት ሥር መጠቃለሏንና፥ የዚህም ሂደት ፍጻሜ የሚሆነው፥ ክርስቶስ ዳግም ሲመለስና ለሕዝቦች ፍርድ ሰጥቶ የራሱን መንግሥት በምድር ሲመሠርት እንደሆነ አመልክቶአል (ዳንኤል 7)። ይህ ብቻም አይደለም፥ በዓለም ስለተነሡት መንግሥታት ቅደም ተከተልም በትክክል ተንብይዋል። በዳንኤል ትንቢት መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰው የባቢሎን መንግሥት ዳንኤል ብላቴና ሳለ ኢየሩሳሌምን የተቆጣጠረ ነበር። እርሱ እንደተነበየው የባቢሎንን መንግሥት መውደቅ፥ የሜዶንና የፋርስን መንግሥታት መነሣት በሕይወት ዘመኑ ተመልክቶ ለመመስከር በቅቷል። ከሁሉም በላይ ጠቃሚው ከክርስቶስ ዳግም መምጣት በፊት የሚነሡና የሚወድቁ መንግሥታትን ዝርዝር መግለጡ ነው። ዳንኤል ገና መንግሥታቱ ሳይነሡ ነበር የትንቢቱን ቅደም ተከተል ዋና አሳብ በመጽሐፍ ያሰፈረው። ይህ ዝርዝር ኢየሱስ ከዳንኤል ትንቢት ጋር አገናዝቦ ስለ መንግሥታቱ የተናገረውን ለመረዳት እጅግ ይጠቅማል።

በዳንኤል ትንቢት መሠረት የዓለም መንግሥታት ዝርዝር የባቢሎናውያን፥ የሜዶንና ፋርስን፥ የግሪክን፥ እና የሮምን መንግሥታት የሚያጠቃልል ነበር። እንዲሁም የሮምን መንግሥት የመጨረሻ ዘመን የተነበየ ሲሆን፥ ይህም ገና ወደፊት የሚመጣ ነው። ይህ በመጨረሻ የሚነሣ አምባገነን መንግሥት ነው ዓለምን ወደ አርማጌዶን ጦርነት የሚመራት። በዚያ የመጨረሻ የዓለም ጦርነት፥ የመንግሥታት ታሪክ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ወቅት ለአንዴና ለዘላለም ያከትማል። በሰዎች የተፈጠሩ ግዛቶችና መንግሥታት በእግዚአብሔር ቀጥተኛ ገዥነት ይተኩና አዲስ ሰማይና ምድር ከመከሠቱ በፊት በምድር ላይ ለሺህ ዓመታት የሚቆይ የሰላም፥ የቅድስናና የብልጽግና ዘመን ይሆናል።

### ◆ የሮም መንግሥት መነሣትና መውደቅ

ዳንኤል የባቢሎንን፥ የሜዶንና ፋርስን፥ እና የታላቁ አሌክሳንደርን ግዛቶች በስም በመጥቀስ አመልክቶ ነበር። የግሪክ መንግሥት ከወደቀ በኋላ የተነሣው፥ ከክርስቶስ ልደት ምዕተ ዓመታት ቀደም ብሎ ሥልጣን ይዞ የነበረው የሮም መንግሥት ነበር። ይህን አራተኛ መንግሥት ዳንኤል በስሙ አልጠቀሰውም። ነገር ግን እንዲህ ሲል ገልጦታል፡- "የምታስፈራና የምታስደነግጥ እጅግም የበረታች ታላላቅም የብረት ጥርሶች የነበሩአት አራተኛ አውሬ ነበረች፥ ትበላና ታደቅቅ ነበር! የቀረውንም በእግርዋ ትረግጥ ነበር" (ዳን. 7፡7)። የሮም ወታደሮች ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ አድቅቀው እንደ ብረት የጠነከረውን የቄሣር ግዛት በደቡብ አውሮፓ፥ ምዕራባዊ እስያና፥ ሰሜን አፍሪካ አስፋፍተው ነበር። ነገር ግን ዳንኤል በመንግሥቱ የመጨረሻ ዘመን ብረቱ

ከሸክላ ጋር እንደሚደባለቅ ያየ ሲሆን፥ ይህም የሚያመለክተው አራተኛው መንግሥት ድንገተኛ ጥፋት እንደሚደርስበትና እንደ ሸክላም እንደሚደቅ ነው (ዳን. 2፡41-45)።

◆ የአራተኛው መንግሥት ማንሰራራት

እንደ ዳንኤል ትንቢት ይህ አራተኛ የቁሣር ግዛት የወደመ ቢመስልም፥ ሙሉ በሙሉ አልጠፋም። በቀድሞው የሮም ግዛት ክልል ውስጥ የሚገኙ አሥር የመንግሥታት መሪዎች ወጥተው አዲስ የሚዲትራኒያን መንግሥት ኅብረት ሲመሠርቱ ይህም መንግሥት የመጨረሻውን ቅርፅና መልክ ይዞ ይነሣል (ዳን. 7፡7)።

በራእዩ መሠረት የሮም መንግሥት በአውሬው ተመስሏል። በአውሬው ላይ ያሉት አሥር ቀንዶች የሚወክሉት ገና ወደፊት የሚነሡ አሥር መንግሥታትን ነው። ከዳንኤል 7፡23-24 እንደምንመለከተው፥ የራእዩ ትክክለኛ ትርጉም ለነቢዩ ተሰጥቶታል፦ "አራተኛይቱ አውሬ በምድር ላይ አራተኛ መንግሥት...። አሥሩም ቀንዶች ከዚህ መንግሥት የሚነሡ አሥር ነገሥታት ናቸው...።"

የመጀመሪያው የሮም ኃያል መንግሥት አነሣሥ፥ የነበረው ኃይል፥ የግዛቱ መከፋፈል፥ ውድቀቱና ገጽታው አሁን የጥንት ታሪክ ሆኗል። የአራተኛው መንግሥት የመጨረሻ ገጽታ ግን ገና አልተገለጠም። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተማሪዎች በሚዲትራኒያን አካባቢ አዲስ የኃይል ክምችት ይከሠታል ብለው እንዲጠብቁ አድርጓቸዋል። የአራተኛው መንግሥት ግዛት እንደገና የሚያንሰራራው በአርማጌዶን ጦርነትና በክርስቶስ ዳግም መምጣት መቃረቢያ ላይ ነው።

የአራተኛው መንግሥት ማንሰራራት የመጀመሪያ እንቅስቃሴ የየዕለቱ ዓቢይ ርእስ ሆኗል። ዛሬም የዓለም ኃይላትና ሀብት እንደገና በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ ያተኩራሉ። አሥር ጠንካራ መንግሥታት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኅብረት እንደሚያደርጉ ሲጠበቅ፥ ያም ለወደፊቱ የሮም ግዛት ማንሰራሪያ የመጀመሪያ እንቅስቃሴ ይሆንና፥ ለሚከሠተው አምባገነን መሪ መድረክ ያመቻቻል።

◆ የመጪው አምባገነን የመጀመሪያ እርምጃ

አዲሱ አምባገነን በመጀመሪያ ራሱን ለዓለም የሚገልጠው በመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም ፈጣሪ (አስታራቂ) በመምሰል ነው። ይህ ድርጊት የሚከናወነው፥ በዳንኤል ትንቢት የተነገረው አራተኛ መንግሥት ማለትም የሮም

መንግሥት እንደገና ማንሰራራት በጀመረ ጊዜ ይሆናል። በምሳሌያዊ አነጋገር ይህ የዓለም መሪ:- "ሌላ ትንሽ ቀንድ ወጣ" ተብሏል። የሚወጣውም ከአሥሩ የሚዲትራኒያን መንግሥታት ኅብረት ነው (ዳን. 7:8)። ዳንኤል የአዲሱን የዓለም ገዥ ወደ ሥልጣን አወጣጥ እንዲህ በማለት ይገልጠዋል፥ "ቀንዶችንም ተመለከትሁ፤ እነሆም በመካከላቸው ሌላ ትንሽ ቀንድ ወጣ፤ በፊቱም ከቀደሙት ቀንዶች ሦስት ተነቃቀሉ፤ እነሆም በዚያ ቀንድ እንደ ሰው ዐይኖች የነበሩ ዐይኖች በትዕቢትም የሚናገር አፍ ነበሩበት" (ዳን. 7:8)።

ሀብትና ኃይላቸውን በማዋሃድ በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ የሚጠናከሩት እነዚህ አሥር መንግሥታት በዚህ በአዲሱ መሪ ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን አምባገነኑ ገዥ በመጀመሪያ ሦስት አገሮችን ወርሮ በቁጥጥሩ ሥር እንደሚያደርግ ይስማማሉ። ሌሎቹ ሰባት መሪዎች ለዚሁ ብርቱ መሪ የሚንበረከኩ ናቸው።

ዳንኤል በራእይ የተመለከተው የመጨረሻ አምባገነን ገዥ፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ መሆኑን ነው የሚያስረዳው። እግዚአብሔርን በመቃወም የሚናገር፥ በእግዚአብሔር የሚያምኑትን የሚያሳድድ፥ ዓለምን ሁሉ ለመቆጣጠር በኃይል እየገነነ የሚሄድና ለአርባ ሁለት ወራት የሚገዛ ይሆናል።

ለዳንኤል የተሰጠው ትርጉም እንደሚለው:-

> "ከእርሱም በኋላ ሌላ ይነሣል። እርሱም ከፊተኞች የተለየ ይሆናል፤ ሦስቱንም ነገሥታት ያዋርዳል። በልዑልም ላይ ቃልን ይናገራል፤ የልዑልንም ቅዱሳን ይሰባብራል፤ ዘመናትንና ሕግን ይለውጥ ዘንድ ያስባል፤ እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ" (ዳን. 7:24-25)።

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ፥ "ዘመን" ማለት "አንድ ዓመት"፥ "ዘመናት" ማለት "ሁለት ዓመታት"፥ "ግማሽ ዘመን" ማለት "ግማሽ ዓመት" እንደሆነ ያምናሉ። እኛም ከዚህ በመነሣት መሪው የነገሠው በአጠቃላይ ለሦስት ከግማሽ ዓመታት ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ እንችላለን (ዳን. 12:11፤ ራእይ 13:15)።

### ♦ የዳንኤልን ሰባ ሱባዔ ለመረዳት

የዳንኤል ትንቢት የመጨረሻውን ዘመን ድራማ ለመረዳት ቁልፍ የሆነ መረጃ ይሰጣል። አዲሱ የሚዲትራኒያን ገዥ በተከታታይ ዓለምን የሚያወድሙ ድርጊቶች እንደሚፈጽም በዳንኤልና በራእይ መጻሕፍት በዝርዝር ተገልጧል። ኢየሱስ ይህን ሰው የገለጠው ኢየሩሳሌምን ወርሮ ቤተ መቅደሱን የሚያረክስ አድርጎ ነበር:- "እንግዲህ በነቢዩ ዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት

በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ሲታይ” (ማቴ. 24፡15)። ኢየሱስ ይህን ድርጊት አስመልክቶ ሌላ ትንቢታዊ ገለጣም አክሏል።

በዳንኤል 9፡24-27 ነቢዩ ስለ “ሰባው ሱባዔ” ማለትም ስለ 490 ዓመታት አመልክቷል። ይህም ኢየሩሳሌምንና የአይሁድን ሕዝብ በሚመለከት ታላላቅ ድርጊቶች የሚከናወኑበት ጊዜ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች 483ቱን ዓመታት ወይም ስድሳ ዘጠኝ “ሱባዔዎች” ይወክላሉ። “ሱባዔ” ተብሎ የተነገረው ቃል ሲተረጐም “ሰባትን” ያመለክታል። ይሁን እንጂ፥ የሚወክሉት ዓመታትን እንጂ ቀናትን አይደለም። ዳንኤል ይህን ዘመን እንዲህ በማለት ይገልጠዋል፡-

> “ስለዚህ እወቅ አስተውልም፤ ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዝ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ መሢሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል፤ እርስዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች። ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሢሕ ይገደላል። በእርሱም ዘንድ ምንም የለም፤ የሚመጣውም አለቃ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ፤ ፍጻሜውም በጐርፍ ይሆናል፤ እስከ መጨረሻውም ድረስ ጦርነት ይሆናል፤ ጥፋትም ተቆጥሮአል” (ዳን. 9፡25-26)።

የዳንኤል ሰባ ሱባዔ የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ የሚጀምረው፥ ኢየሩሳሌምን እንደገና ለመገንባት ዓዋጅ በማወጅ ነው። ዓዋጁም የተሰጠው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ445 ዓ.ዓ. ለነህምያ ነበር። የመጀመሪያዎቹ ሰባት ሳምንታት ወይም አርባ ዘጠኝ ዓመታት ኢየሩሳሌምን እንደገና ለመገንባት የወሰደውን ጊዜ ያመለክታሉ። ስድሳ ሁለቱ ሱባዔዎች (434 ዓመታት) ደግሞ መሲሕ እስከሚገደልበት ድረስ ያለውን ጊዜ ያመለክታሉ። እነዚህን ሁለት የጊዜ ቀመሮች ስንደምራቸው፥ የዳንኤልን አስደናቂ ትንቢት ትክክለኛነት እንገነዘባለን። ኢየሱስ በእስራኤል ሕዝብ ከመወገዙና ከመሰቀሉ በፊት 483 ዓመታት ያለፉ ሲሆን፥ ይህ የሆነው በ33 ዓ.ም. እንደነበር የቅርብ ጊዜው የምሁራን ጥናት ያመለክታል።

አንድ ሱባዔ (ሰባት ዓመት) ገና አልተፈጸመም። በዳንኤል 9፡26 ላይ “የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ” የዚያ ዘመኑ የሮም ሠራዊት ከተማዋንና ቤተ መቅደሱን እንደሚያወድም ያመለክታል። በትንቢቱ መሠረት ይህ በ70 ዓ.ም. ተፈጽሟል። የታደሰው የሮም መንግሥት የሚመጣው አለቃ የተነገረለትን ትንቢት እንደገና የሚፈጽመው ግን በመጨረሻው ሰባት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው። በዳንኤል 9፡26 የተጠቀሰው መሪ የሜዲትራኒያኑን አሥር መንግሥታት ኅብረት የሚቆጣጠር ነው። ይህ መሪ ኃይሉን ካጠናከረ በኋላ፥ ሌላ ተጨማሪና ወሳኝ እርምጃ ይወስዳል። በሰላም ቃል ኪዳን፥ የእስራኤልን ደኅንነት ለማስጠበቅና በመካከለኛው ምሥራቅም ሰላም ለማምጣት ይደራደራል። እንደ

ዳንኤል አባባል፥ ይህ ዋና እርምጃ የሚጀምረው ከተተነበዩት 490 ዓመታት በመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት ውስጥ ነው። ይህ የሚሆነው በዓለም ታሪክ የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት፥ የአርማጌዶን ጦርነት ከመካሄዱና ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ነው። "ያም መሪ ከብዙ ሕዝቦች ጋር እስከ ሰባት ዓመት ድረስ በጠበቀ ሁኔታ ቃል ኪዳን ይገባል፤ የሰባቱ ዓመት እኩሌታ ሲያልፍ መሥዋዕትና ቁርባን ማቅረብን ይከለክላል፤ በቤተ መቅደሱም ማዕከላዊ ስፍራ ላይ አስጸያፊ የሆነ የጥፋት ርኩሰት እንዲቆምበት ያደርጋል፤ ይህም የሚሆነው እግዚአብሔር በወሰነው መሠረት ያ መሪ እስከሚወገድበት ጊዜ ነው" (ዳን. 9፡27፥ በ1980 ዓ.ም. እትም)።

የሜዲትራኒያን ኅብረት መሪው ከእስራኤል ጋር የፈጠረው ጊዜያዊ ሰላም እንደተጠበቀ ሆኖ፥ በሰላም ሽፋን ካግባባ በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ተኩል ጊዜ ወደ አምባገነንነት ይለወጣል። በቀሪው የሦስት ዓመት ተኩል ክፍለ ጊዜ ስምምነቱን በግልጥ ያፈርሳል። ከዚህ ቀደም ባለው ምዕራፍ ለማስረዳት እንደተሞከረው ይህ ሁኔታ፥ ማለት ሩሲያ እስራኤልን ለመውረር የምታደርገው ሙከራ እጅግ ከሚያስገርምና ምሥጢራዊ ከሆነው ውድመቷ ጋር የተያያዘ ነው። የክርስቶስ ተቃዋሚ የዓለም ኃይል ሚዛን ወደ እርሱ በሚያጋድልበትና ዓለም በሩሲያ ውድቀት በአድናቆት ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ፥ እውነተኛ ገጽታውን ይፋ ያደርግና ራሱን የዓለም አምባገነን መሪ ብሎ በመሠየም ተቃዋሚዎቹን ሁሉ ይሰባብራል።

◆ አርባ ሁለት የፍዳ ወራት

የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት በሙሉ ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ያሉት የመጨረሻ ዓመታት ታላቅ የመከራ ጊዜያት እንደሚሆኑ ገልጠዋል። ያኔ ነው አምባገነኑ መሪ "ምድሪቱንም ሁሉ ይበላል፥ ይረግጣታል፤ ያደቅቃትማል" ተብሎ የተነገረለትን ትንቢት የሚፈጽመው (ዳን. 7፡23)። ይህን ነው ኢየሱስ፥ "በዚህን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናል፤ እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር። ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ" (ማቴ. 24፡21-22) በማለት ያመለከተው።

ይህ በራእይ ምዕራፍ 13 የተገለጠው ዘመንና ገኸ ነው። ራእይ 13፡5 የክርስቶስ ተቃዋሚ "ለአርባ ሁለት ወሮች ለመግዛት ኃይልና ሥልጣን ይቀበላል" ሲል፥ ራእይ 13፡7 ላይ ደግሞ "ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፤ በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው" ይላል።

ሰይጣን ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስነሣው ይህ የጥፋት ሰው ለአርባ ሁለት ወራት የዓለም አምባገነን ለመሆን ኃይል ይኖረዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በኃጢአተኛውና ክርስቶስን በናቀው ዓለም ላይ እግዚአብሔር አስፈሪ ፍርዱን ያወርዳል።

ይህን ክንውን ትንቢታዊው የጊዜ ሰሌዳ ለምዕተ ዓመታት ሲናገረው የኖረ ሲሆን፥ የሚከሠቱትም ሁኔታዎች ተወስነዋል። በመጨረሻ መካከለኛው ምሥራቅም ወደ ዓለም አቀፋዊ መድረክነት ይመለሳል። የአሥሩ መንግሥታት መሪዎች በሮም መንግሥት ውድቀት ያጡትን ኃይል እንደገና ያጠናክራሉ። የወደፊቱ የሜዲትራኒያን መሪ ጊዜ ጠብቆ ከእነዚህ መንግሥታት ሦስቱን ያተራምስና የአሥሩን ኅብረት ይቆጣጠራል። ለሦስት ዓመታት ተኩልም የሰላም አለቃ፥ የዓለም አዳኝ ነኝ ብሎ ያታልላል። በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ተኩል ደግሞ በሰይጣናዊ ተአምራቱና ኃይሉ ራሱን አምላክ አድርጎ በመሾም ተቃዋሚዎቹን በጭካኔ መፍጨት ስለሚጀምር፥ በዚያ ዘመን ማክተሚያ ላይ የሚኖሩ የዓለም መንግሥታት በሙሉ ኃይላቸውን ያስተባብሩና ጦርነት ይገጥሙታል። ይህ ታላቅ እልቂትና ጥፋት የሚያስከትል ጦርነት፥ የአርማጌዶን ጦርነት በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ በሚቀጥለው ምዕራፍ በሰፊው እንመለከተዋለን።

- ለዓለም አገዛዝ የሚያገለግሉ ሁኔታዎች ዛሬም አሉ

በሀያኛው መቶ ክፍለ-ዘመናችን ለዓለም አቀፍ መንግሥት ምሥረታ ፍላጎቱ ብቻ ሳይሆን፥ መመሥረቻውም በእጃችን እንደሆነ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። ዓለም አቀፍ መሪ እንዲኖር ፈጣን የመገናኛ ብዙኃን ያስፈልገዋል። ዛሬ በኤሌክትሮኒስ መገናኛ፥ በተለይም በሳተላይት አማካይነት በቴሌቪዥን መጠቀም፥ ከመላው ዓለም ጋር ፈጣን ግንኙነት ለሚያስፈልገው አምባገነን ገዥ ትልቅ መሣሪያ ይሆናል። እንዲሁም ዓለም አቀፋዊው መንግሥት ፈጣን ትራንስፖርት ያስፈልገዋል። ዛሬ ወታደሮችንና መሣሪያዎችን በጥቂት ሰዓታት ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ የሚቻል ሲሆን፥ ይህም በማናቸውም ቀደምት ትውልዶች ሊደረግ የማይቻል ሁኔታ ነበር። አሜሪካ በ1990 ዓ.ም. ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ጦር መሣሪያዎች በአየር ያጓጓዘችበት ሁኔታ የዘመናዊ ትራንስፖርትን ጠቃሚነት ያስገነዝባል።

ወደታለሙበት የዓለም ክፍል በግማሽ ሰዓት ውስጥ ለመድረስ የሚችሉ ሚሳይሎች (ተወንጫፊ ጦር መሣሪያዎች) በአምባገነኑ የዓለም መሪ እጅ አያሌ ተግባራት የሚያከናውኑ ሊሆኑ ይችላሉ። ኑክሊየር ሚሳይል በእጁ ያለው መሪ የትኛውንም የዓለም ክፍል ለመዎታት በማስፈራራትና ብዙዎችንም በማስገደድ እንዲከተሉት ለማድረግ ይችላል። ከዚህ ቀደም በታሪክ የተነሣ ማንኛውም

መንግሥት አመራሩን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ተመቻችተውለት አያውቁም። በእግዚአብሔር ቃል እንደተተነበየው አምባገነኑ ገዥ የዓለምን ኢኮኖሚ በቁጥጥሩ ሥር ያደርጋል። ያለ እርሱ ፈቃድ ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ አይችልም (ራእይ 13፡17)። ዛሬ፥ በኮምፒዩተሮች መፈልሰፍ ምክንያት፥ ይህ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚቻል ነገር ሆኗል። ዓለም አቀፉ መንግሥት፥ የድርጅቶችን የሒሳብ መዝገብ ሊይዝ ይችላል፤ ግዢንና ሽያጭን ሊቆጣጠር ይችላል፤ ስለ ግለሰቦችም የፈለገውን መረጃ ሊያገኝ ይችላል።

አሁን የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂና የኤሌክትሮኒክስ ልውውጥ አድጓል። ይህም አንድ ሰው የዱቤ ሰነድ (ካርድ)፥ ቼክ ወይም ገንዘብ ሳይኖረው የሚፈልገውን ሊገዛና ሊሸጥ ያስቸለዋል ማለት ነው። በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በሚሆነው ኢኮኖሚ አማካይነት ማንኛውንም የንግድ ልውውጥ መቆጣጠር ይቻላል። እያንዳንዱ ግለሰብ በማዕከላዊ ሒሳብ ማስያ (ኮምፒዩተር) ውስጥ በስሙ የተመዘገበ ቁጥር ይኖረዋል። አሠሪው የሠራተኛውን ደመወዝ በሒሳብ መዝገቡ ቁጥር አማካይነት በኤሌክትሮኒክስ ልውውጥ ገቢ ያደርግለታል። ሰውዬው (ሠራተኛው) ማንኛውንም ነገር ለመግዛት ወደ ገበያ አዳራሽ ሲሄድ በገበያ አዳራሹ የሒሳብ ማስያ (ኮምፒዩተር) አማካይነት የሰውዬውን መዝገብ ቁጥር ይጠይቅና የገዛውን ዕቃ ዋጋ ከሒሳቡ ወዲያው ይቀንሳል። አምባገነኑ የዓለም ገዥ ከገንዘብ ልውውጥ ይልቅ እንዲህ ዓይነቱን የመገበያያ ዘዴ ከመረጠ፥ እርሱ ፈቅዶ ቁጥር ካልሰጠ በቀር ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ አይችልም።

◆ የዓለም አምባገነንነት ዛሬም ይቻላል

የዘመናዊው ዓለማችን ዲሞክራሲያዊ መንግሥታት ሁሉ በከባድ ችግሮች መመታታቸው ይቀጥላል። የዓለም ኅብረተሰብ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ችግሮች እየከፉ ሲመጡ፥ የመካከለኛው ምሥራቅን ችግሮች የሚፈታለት ቆራጥና ወሳኝ መሪ እንዲሻ ይገደዳል። ዓለምን በአንድ ጠንካራ ሰው የመምራት ፍላጎቱም ሆነ፥ ያንን ተግባራዊ የማድረጊያ መሣሪያዎች በእጃችን ናቸው። የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎችን፥ የዓለም ፕሮፓጋንዳ ሥርጭትን፥ ዓለም አቀፉን ኢኮኖሚ በኃይል የመምራት አቅም፥ በቀላሉ መገኘት አምባገነኑ መሪ ዓለምን እንደፈለገ ለመቆጣጠር ያስችሉታል። ይህ ከዚህ ቀደም የማይቻል ነበር።

በዓለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለም አቀፍ መንግሥት ምሥረታ ቅድመ ሁኔታዎች በአስደናቂ ሁኔታ ተሟልተዋል። በእግዚአብሔር ቃል የተጠቀሱት ትንቢቶች እውን የሚሆኑበትና የዓለም አቀፍ መንግሥት ምሥረታ ጊዜ ሩቅ አይደለም። ትንቢቶቹ በትክክል ይፈጸማሉ።

# 13

# የዓለም የጥፋት ቀን

### ♦ ሊመጣ ያለው የኑክሊየር መዓት

በዓለማችን ከባድ ጥፋትና እልቂት እያንዣበበ መሆኑን የሚጠቁሙ ብዙ ሁኔታዎች አሉ። የሰው ልጅ እያደጉ በመምጣት ላይ ባሉት የዓለም ችግሮች የተነሣ፥ በአንድ ትውልድ ጊዜ "ራስን ከመቻል" ስሜት ወደ ደካማነት ስሜት ሄዷል። የችግሩ አንድ ምክንያትና መንሥኤ በምዕራብ ኃይላትና በሩሲያ እጅ ያሉት የኑክሊየር አረሮች ናቸው። ከሚኒስት ቻይና፥ ሕንድ፥ እስራኤልና ደቡብ አፍሪካን የመሳሰሉ ሌሎች አገሮችም የራሳቸው ኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች አሏቸው። እንደ ኢራቅ፥ ፓኪስታን፥ አርጀንቲና፥ ብራዚል፥ ሰሜን ኮሪያና ታይዋን ያሉ ትናንሽ አገሮችም የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ባለቤት የመሆን ጥረታቸው እያደገ መጥቷል።

እስካሁን የተከማቸው የኑክሊየር መሣሪያ፥ ለማጥቂያም ሆነ ለመከላከል በሚደረገው ፍልሚያ ዓለም አቀፋዊ ጥፋት ለማድረስ በቂ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ፍልሚያ ቢከሠት ሁለቱም ወገኖች፥ ማለት አጥቂና ተከላካይ በጥቂት ቀናት ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ያጣሉ። የኑክሊየሩ ጥፋት ዓለምን በማዳረስ የተለያዩ ሕዝቦች ላይ ጉዳት ያደርሳል። ሌላውን አጥፊ ኃይል ሳንጨምር የኑክሊየር ጦርነት ብቻውን ሰው ከሚገምተው በላይ የከፋ እልቂት ያስከትላል። በመጨረሻው ሰዓት ዓለማችን የሰው አእምሮ ሊገምተው የማይችል ጥፋት እንደሚገጥማት በራእይ መጽሐፍ በግልጥ ተተንብይዋል። ያም አስከፊ ጥፋት የኑክሊየር ጦርነት ይሆን ይሆናል።

ለራስ መከላከያ በሚል ሰበብ ብዙ የኑክሊየር መሣሪያዎች በዓለማችን ተከማችተዋል። ሩሲያና አሜሪካ በመካከላቸው ተፈጥሮ የነበረው ውጥረት በረገበበት በአሁኑ ሰዓት እንኳን፥ ለእርስ በርስ ጥፋት የሚያበቃ ክምችት አላቸው። ማንኛውም አገር ቢሆን እራሱን ሳያጠፋ በኑክሊየር መሣሪያው ሊጠቀም አይችልም። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የተወሰነ ይሁን እንጂ ሌሎች መንግሥታትም ክምችቱ ያላቸው ሲሆን፥ ለኑክሊየር መሣሪያ መስፋፋትም ምንም ዓይነት መፍትሔ የሚኖር አይመስልም። ሁኔታዎች በጣም እየከፉና እየተወሳሰቡ ነው፤ በድንገት ወይም ሆን ተብሎ በኑክሊየር መሣሪያ የሚደረግ ጥፋት ያንዣብባል። ይዋል ይደር እንጂ ከሳይንሳዊ ጥበብ ምጥቀት የተነሣ፥

የኑክሊየር ባለቤት ከሆኑት መንግሥታት አንደኛው ከሌላው በተሻለ ሁኔታ ጥቅሙን በበላይነት ለማስጠበቅ ይችል ይሆናል፤ ወይም እነዚህ መሣሪያዎች ኃላፊነት በማይሰማቸው ግንፍል ሰዎች እጅ ይገቡ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ በመካከለኛው ምሥራቅ ካለው ውጥረት አንጻር የኑክሊየር ጦርነት ቢደረግ፥ እጅግ አስከፊ እልቂት ይሆንና ዓለም አይታ የማታውቀው ጥፋት ያገኛታል።

## ♦ እየጨመረ የመጣው የአካባቢ ብክለት

የኑክሊየር ጦርነት ልንፈታ ካልቻልናቸው ችግሮቻችን ውስጥ አንዱ ብቻ ነው። በዓለም ዙሪያ እየጨመረ የመጣው ብክለትም፥ ምድራችንን ለመኖሪያ የማትመች ስላደረጋት የውኃ ውስጥ ፍጥረታት በማለቅ ላይ ናቸው፥ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ጤንነትና ደኅንነት በመጎዳት ላይ ነው። አሜሪካ የአየር ብክለትን ችግር ድል ለማድረግ ያደረገችው ጥረት በአርዓያነት የሚጠቀስ በጎ እርምጃ ነው፤ ሆኖም ችግሩ ከሚያሳስባቸው ጥቂት አገሮች አንዷ ናት።

ካለው የነዳጅ እጥረት ቀውስ የተነሣ በዓለም ላይ ያሉ ታላላቅ ኢንዱስትሪዎች በድንጋይ ከሰልና ዝቅተኛ ጥራት ባለው ዘይት እንዲጠቀሙ ተገደዋል። ይህ ድርጊታቸው ደግሞ የአካባቢ ብክለትን አባብሶታል። በምሥራቅ አውሮፓ በመታየት ላይ ያለውም ችግር ይሄው ነው። በመላው ዓለም ኢንዱስትሪዎች የሚያስከትሉት የአየር ብክለት እየጨመረ በመሄድ፥ የሰው ልጅ ሕይወትን ክፉኛ የሚጎዳበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። ነቢዩ፥ ፀሐይ እንደምትጨልም፥ ጨረቃም ደም እንደምትመስል፥ ባሕሮችም እንደሚቀሉና ከዚህም የተነሣ የባሕር እንስሳት እንደሚያልቁ ትንቢት ተናግሮ ነበር። እየጨመረ የመጣው የአየርና የባሕር ብክለት፥ ነቢዩ ከተነበየው ትንቢት ጋር በሚያስፈራ ሁኔታ እየተመሳሰለ እንደሄደ እንረዳለን (ራእይ 16፡3-4)።

## ♦ የሕዝብ ብዛትና ረኃብ

ሌላው ትልቅ ችግር የሕዝብ ብዛት እጅግ መጨመር ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአሜሪካ የሕዝብ ብዛት እድገት መቀነስ የጀመረ ቢመስልም፥ በሌሎች የዓለም ክፍሎች ግን እድገቱ አሁንም በሚያስጨንቅ ፍጥነት ማለት በዓመት ከመቶ ሚሊዮን በላይ እየጨመረ ነው። የማኅበራዊ ኑሮ ዕቅድ አውጪዎች በአወላለድ ሁኔታ ላይ ፈጣን ለውጥ ካልተደረገ በምግብ እጥረት ብቻ በሁለት ሺህ ዓ.ም. በዓለም ዙሪያ ታላቅ መቅሠፍት ሊሆን ይችላል በማለት ያስጠነቅቃሉ። የዓለም ሕዝብ ብዛት ከምድሪቱ የምግብ ምርትና ሥርጭት ሊበልጥ ጥቂት ብቻ የቀረው ስለሆነ ሁኔታው እንዲህ ከቀጠለ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦችን ለረኃብ የሚያጋልጥ መሆኑ እርግጥ ነው።

የኢኮኖሚ ችግር በ1970ዎቹ ዓመታት በመባባስ ላይ ሲሆን በ1980ዎቹ ዓመታት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች በረኃብ ረግፈዋል። በሦስተኛው ዓለም ለዚህ ችግር መባባስ የነዳጅ እጥረት ትልቅ ድርሻ አለው። የነዳጅ ዋጋ ንረት የማዳበሪያ አቅርቦት እንዲቀንስና ዋጋውም እንዲንር በማስገደዱ ታዳጊ አገሮች የመግዛት አቅም አጥተዋል። ድርቅ፥ ዓውሎ ነፋስ፥ ጎርፍ፥ የአየር ለውጥ በዓለም ዙሪያ የሚገኘውን አዝመራ ያወድመዋል።

ምንም እንኳን በ1970ዎቹ ዓመታት መገባደጃ ላይ የአሜሪካን የምግብ ምርት ቢጨምር፥ በብዙ አገሮች ከታዩት ፖለቲካዊ ችግሮች የተነሣ የረኃብና የምግብ አቅርቦቱ ችግር እንደቀጠለ ነው። ከዚህም የተነሣ ሶቪየት ኅብረትን የመሳሰሉ አንዳንድ አገሮች የምግብ እህል በብዛት ለመግዛት ተገደዋል። ሶቪየት ኅብረት ይህ ብቻም አልነበረም ችግሯ፤ በ1990 ዓ.ም. በአገሪቱ የተከሠተው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ብጥብጥ ሳቢያ ያላትን እህል እንኳን በሚገባ ማሠራጨቱ ተስኗት ነበር። ምግብ ባላቸውና በሌላቸው አገሮች መካከል ያለው ውጥረት፥ ከረኃብ ጋር አብሮ የሚከሠተው ቸነፈርና ሕመም ታክሎበት ታዳጊ አገሮችን እያደቀቃቸው ነው። ችግሩ በቀጣዩ ትውልድ እንኳን የሚፈታ አይመስልም።

## ♦ የሥርዓት አልበኛነት ሥጋት

የሰው ልጅ መፍትሔ ካጣላቸው ከነዚህ ችግሮች ጋር ሥርዓት አልበኛነት ምግባረ ብልሹነት እያደር በመጨመር ላይ ናቸው። ፍትሕ አልባነትና ሞራለ ቢስነት በመንግሥታትም ሆነ በግለሰቦች ዘንድ ጎልቶ ይታያል። የምዕራቡን ሥልጣኔ እስካሁን የጠበቀው ሕጋዊ አመራር አጠያያቂ ሁኔታ ገጥሞታል። ፍትሐዊ ሕጎች እንኳን በፍርድ ቤቶች በአግባቡ አይተረጎሙም። “ሰው በሕግ የመተዳደር ችሎታ አለው” የሚለው እምነት በ1960ዎቹ የዓመፅ እንቅስቃሴዎች፥ በ1970ዎቹ የዋተርጌት [Watergate] ቅሌት፥ በ1980ዎቹ እየጨመረ በመጣው በዕፅ የመጠቀም ወንጀልና ብጥብጥ ውድቅ ሆኗል። የ1990ዎቹም የኢኮኖሚ ችግሮች፥ የከተማ ኑሮ መዳሸቅን፥ ድኅነትን፥ ወንጀልን፥ ረኃብን፥ ቤት የለሽነትን በአጠቃላይ ማኅበራዊ ችግሮችን አባብሷቸዋል።

እነዚህ የመጨረሻ ቀናት በመጽሐፍ ቅዱስ ከኖኅ ዘመን ጋር ተነጻጽረዋል። ልክ እንደ ኖኅ ዘመን ሁሉ፥ እያንዳንዱ ሰው ትክክል የመሰለውን ነገር ነው የሚያደርገው። ሕገ ወጥነት፥ ሥርዓት አልበኛነትና ፍርሃት ለዓለም ጠንካራ መሪ አስፈላጊ የመግቢያ ቀዳዳዎች ይሆናሉ። ያም መሪ ሥርዓት አልበኛነት ለሰፈነባት ዓለም ሰላምና መረጋጋት እንደሚያመጣ ቃል ይገባል። ከሁሉም የሰው ሕይወት አቅጣጫ እነዚህ ችግሮች ሲባባሱ እንጂ ሲሻሻሉ አይታዩም። መፍትሔው በቅርቡ ይታያል ማለት አስቸጋሪ ነው።

## ♦ መጪው "የያዕቆብ መከራ" ጊዜ

ይህን የዓለማችንን ሁኔታ ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር በማቀናጀት ስንመለከተው፥ ከዚህ ቀደም ባልታየ ሁኔታ በታላቅ መከራና ችግር አፋፍ ላይ መሆናችንን መገመቱ አይቸግረንም። ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ ትንቢቶች ስለ ያዕቆብና በዘሮቹ ላይ ብቻ ስለሚደርሰው መከራ የተነገሩ ቢመስሉ፥ ችግሩ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ነው።

ይህ የመከራ ዘመን ከመጨረሻው ሰዓትና እስራኤል እንደገና ወደ ጥንታዊት ምድሯ ከምትሰበሰብበት ጊዜ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያመለክታሉ። ይህ ሐቅ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ዛሬ እስራኤል ወደ ምድሯ ስለተመለሰች ነው። ለዚህ የመከራ ጊዜ መድረኩ ተዘጋጅቷል። ነቢዩ ኤርምያስ ይህን ዘግቧል፡- "እነሆ፥ የሕዝቤን የእስራኤልንና ይሁዳን ምርኮ የምመልስበት ዘመን ይመጣልና ይላል እግዚአብሔር። ለአባቶቻቸውም ወደ ሰጠኋት ምድር እመልሳቸዋለሁ እነርሱም ይገዙአታል" (ኤር. 30፡3)።

ትንቢቱ ስለ እስራኤላውያን ወደ አገራቸው መመለስ ካመለከተ በኋላ፥ ወዲያውኑ አገሪቱ ስለሚጠብቃት የመከራ ጊዜ ይናገራል። የእስራኤል መከራ የተገለጠው ምጥ ከያዛት እርጉዝ ሴት ጋር በመነጻጸር ሲሆን፥ ያም ቀን በኤርምያስ 30፡7 ላይ እንዲህ ተገልጧል፡- "ወዮ! ያ ቀን ታላቅ ነውና፤ እርሱንም የሚመስል የለምና፤ ያ የያዕቆብ መከራ ዘመን ነው። ነገር ግን እርሱ ይድናል"። በዚህ ትስፋ መሠረት የድርጊቶችን ሂደት ስንመለከት፥ በመጨረሻው ዘመን እስራኤላውያን ወደ አገራቸው ስለመመለሳቸው፥ ስለሚጠብቃቸው መከራና ክርስቶስ በኃይልና በሥልጣን ለመግዛት በሚመጣበት ጊዜ ከመከራቸው ሁሉ እንደሚታደጋቸው የተነገረ መሆኑን እንረዳለን።

## ♦ የመከራው ወቅት፤ ከዳንኤል እይታ አንጻር

ነቢዩ ዳንኤል፥ በዚህ ዘመን በቅደም ተከተል የሚፈጸሙ ሁኔታዎችን ጠቁሞ ነበር። ከትንቢቶቹ ውስጥ አስፈላጊ ክፍሎችን ከዚህ በፊት ተመልክተናቸዋል። በመጨረሻው ዘመን የሚከሠቱ ድርጊቶችን አስመልክቶ በዳንኤል 11፡40-45 የተሰጠውን ገለጣ ደግሞ፥ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመረምራለን። በዳንኤል 12፡1 ላይ ያለው የነቢዩ መደምደሚያ፥ "ሕዝብህን የሚጠብቀው ታላቁ መልአክ ሚካኤል በዚያን ጊዜ ይገለጣል፤ የሰው ዘር ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ መከራ ይሆናል፤ ነገር ግን ስማቸው በእግዚአብሔር መጽሐፍ የተጻፈ የአገርህ ሕዝቦች ብቻ በዚያን ጊዜ ይድናሉ" የሚል ነበር (በ1980 ዓ.ም. እትም)። ከዚህ ቃል ቀጥሎ ያሉት ቁጥሮች ደግሞ፥ ይህ የሚፈጸመው ኢየሱስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት እንደሆነ ያመለክታሉ።

## ♦ ታላቁ የዓለም የመከራ ዘመን

ታላቁ የዓለም የመከራ ዘመን ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት የሚፈጸም ነው። ይህ የመከራ ዘመን በዳንኤል 12፡11 እንደተገለጠው፥ ለአንድ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ቀናት ወይም ደግሞ በግምት ሦስት ዓመት ተኩል ይቆያል። ይህም በዳንኤል 9፡27 እና በሌሎች ትንቢቶች የሰባት ዓመት ግማሽ የመከራ ዘመን ተብሎ ከተገለጠው ጋር ይስማማል። በራእይ 12፡6 ደግሞ ስለ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ቀናት መከራ ወይም አርባ ሁለት ወራት ይናገራል (ተመሳሳይ ጥቅሶች በራእይ 12፡2፤ 13፡5 ይገኛሉ)። ለጥቂት ጊዜ ይሁን እንጂ፥ ይህ ሦስት ዓመት ተኩል ታላቅ የመከራ፥ የዋይታና ዓለም አይታ የማታውቀው መዓት ዘመን ነው የሚሆነው። እንደ ዳንኤል 7፡7-8 ያሉት ሌሎች የብሉይ ኪዳን ክፍሎችም ተጨማሪ ገለጣ ይሰጣሉ። የዚህም ገለጣ ማብራሪያ በዳንኤል 7፡19-27 ይገኛል። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያመለክቱት፥ ታላቁ የመከራ ዘመን በመታደስና በግንባታ እንደገናም በመቋቋም ይተካል (ኢዩ. 2፡1-11፥ 28-32፤ ሶፎ. 1፡14-18፤ ዘካ. 13፡8-14፡2ን ይመልከቱ)። ብሉይ ኪዳን ስለዚህ ክፉ ዘመን ሲያመለክት፥ በዓለም ታሪክ ውስጥ ሆኖ የማያውቅ መሆኑን በግልጥ ይመሰክራል። ዘመናዊዋን ዓለማችንን የሚያጋጥሟት ችግሮች፥ ለሚመጣው መከራ ቅድመ ሁኔታ (መድረክ) የሚያመቻቹ ናቸው።

## ♦ ስለ ታላቁ መከራ የክርስቶስ ትንቢት

አዲስ ኪዳንም ስለዚህ ዘመን ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጣል። ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ያስተምር በነበረበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ዘመናት ፍጻሜ ጠይቀውት ነበር። የሰጣቸው መልስ ይህንኑ በነቢያት የተነገረ የመከራ ዘመን ይገልጣል (ማቴ. 24-25)። ጌታ ኢየሱስ ይህ ወቅት የመከራ ዘመን እንደሚሆን አልሸሸገም። እንደ ማቴዎስ 24፡15 ገለጣ የመከራው ወቅት የሚጀምረው፦ "... በነቢዩ ዳንኤል የተባለውን 'የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ'" በሚቆምበት ጊዜ ነው። ይህም የሚያመለክተው፥ በመጨረሻው ዘመን በኢየሩሳሌም የሚሠራው ቤተ መቅደስ የሚረክስበትንና የመሥዋዕት ማቅረቡም ሥርዓት የሚቋረጥበትን ጊዜ ነው።

ክርስቶስ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራራዎች እንዲሸሹ መክሯቸዋል (ማቴ. 24፡16)። በቤት ያለውን ሊወስዱ እንዳይመለሱ፥ ነገር ግን በተቻላቸው ፍጥነት እንዲሸሹ አስጠንቅቋቸዋል። ለእርጉዞችና ለሚያጠቡ ታላቅ የፈተናና የመከራ ሰዓት ነው የሚሆነው። ሽሽታቸው በክረምት ሆኖ በቀዝቃዛው አየር ምክንያት መንገዳቸው እንዳይሰናከል፥ ወይም አይሁዶች በሰንበት ጉዞ ስለማያደርጉ በሰንበት እንዳይሆን ይጸልዩ ዘንድ አዟቸዋል።

## ♦ የሰው ዘር እየጠፋ ነው

ክርስቶስ በማቴዎስ 24፡21-22 ላይ "በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህ ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናል። እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር። ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ" በማለት አጠቃሎታል። በዳንኤል 12፡1 ላይም "የሰው ዘር ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ መከራ ይሆናል" (በ1980 ዓ.ም. እትም) የሚል ተመሳሳይ ቃል አለ። እንደ ኤርምያስና ዳንኤል ኢየሱስም ይህን ዘመን፥ እስከዛሬ ድረስ በዓለም ታሪክ ውስጥ ያልሆነ ከእንግዲህ ከቶ የማይሆን ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል ብሏል።

ክርስቶስ የመከራዎቹን ቀናት አስከፊነት ሲገልጥ "ቀኖቹ ባያጥሩ" ማለትም፥ በዳግም ምጽአቱ "ባይቋረጡ" ማንም ይህን አስከፊ ዘመን ሊቋቋመው እንደማይችል አመልክቷል። ነገር ግን "እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉና" ክርስቶስ ይህን ፍዳ ለማቆም (ለማቋረጥ) ከሦስት ዓመት ከመንፈቅ በኋላ መጥቶ በእርሱ የታመኑትን ያድናል። "ለተመረጡት" ሲል እስራኤላውያንን ወይ ከእስራኤልም ሆነ ከአሕዛብ ወገን በዚህ የመከራ ወቅት በክርስቶስ አምነው የሚድኑትን ማለቱ ይሆናል። ለመዳን የተመረጡ ናቸውና ይድናሉ።

## ♦ አስገራሚው የእግዚአብሔር ሕዝቦች መትረፍ

እንደ ሮሜ 11፡26 "እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል። እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈው 'መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፤ ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል።'" እስራኤል እንደ መንግሥትነቷ ከሚያሳድዷት ትድናለች። ሆኖም በሕዝቅኤል 20፡34-38 ላይ እንደተጠቀሰው ፍርድ ይጠብቃታል። ተፈትነው ያለፉት ወደተቀደሰው የሺህ ዓመት መንግሥት ይገባሉ። እነዚያ በመከራው ዘመን ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው በሕይወት የሚተርፉት ወላጆች ክርስቶስ በሚገዛበት ጊዜ ምድርን የሚሞላት ትውልድ አያቶችና ቅድመ አያቶች ይሆናሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ በአሕዛብ ላይ ስለሚጣለው ፍርድ ማቴዎስ 25፡31-46 ሲገልጥ፥ በጎች የተባሉት ጻድቃን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲገቡ፥ በፍየል የተመሰሉ ኃጢአተኞች ደግሞ በሞት እንደሚቀጡ ያስገነዝባል። አስከፊ መዓትና ስደት በሚደርስበት የመከራ ዘመን እንኳን እግዚአብሔር ሕዝቦቹን በተአምራቱ ይታደጋል።

## ♦ የራእይ መጽሐፍ ዝርዝሮች

የዚህ ታላቅ መከራ ዘመን ሰፋ ያለ ዝርዝር የሚገኘው በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ነው። ገለጣው ከምዕራፍ 6 ይጀምርና እስከ አብዛኛው የመጽሐፉ

ምዕራፎች ይቀጥላል። በምዕራፍ 19 በታላቁ መከራ መገባደጃ ላይ በአስከፊው መዓትና ውድመት የብዙ ሰው ሕይወት እንደሚጠፋ በዝርዝር ተዘግቧል። የአጠቃላዩ ሁኔታ ገለጣ ከሰባቱ ማኅተሞች ተራ በተራ መፈታት ጋር ተያይዞ ቀርቧል። እንደ ራእይ ምዕራፍ 4 እና 5 አገላለጥ፥ ዮሐንስ በራእዩ በመንግሥተ ሰማያት የመጽሐፍ ጥቅል አየ። የመጽሐፉ ጥቅል በውስጥና በውጭ የተጻፈበትና በሰባት ማኅተም የታሸገ ነበር። የመጽሐፉ ጥቅል በተዘረጋ ጊዜ የመጀመሪያው ማኅተም ተፈታ፤ ከዚያም ሁለተኛው፥ በተከታታይ ሁሉም ተፈቱ። እነዚህ ድርጊቶችና ሁኔታዎች ዘመኑ ምን እንደሚመስል አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጡናል።

## ♦ ሰባቱ አስፈሪ ማኅተሞች

የመጀመሪያው ማኅተም፥ በታላቁ መከራ ዘመን የሚመሠረተውን በጣም አስደንጋጭና ሰይጣናዊ የዓለም መንግሥት ያመለክታል። ይህ በራእይ ምዕራፍ 13 ላይ በዝርዝር ተገልጧል። ሁለተኛው ማኅተም የሚገልጠው፥ በዘመኑ መገባደጃ ስለሚደርሰውና በዓለም ታሪክ እስከዛሬ ስላልታየው ታላቅ ጦርነት ነው። ሦስተኛው ማኅተም የጦርነትና ምድርን የሚሸፍናት ጥፋት ውጤት ስለሚሆነው ረኃብ ያስረዳል። አራተኛው ማኅተም ከዓለም ሕዝብ አንድ አራተኛው በጦርነት፥ በረኃብና በአራዊት እንደሚጠፉ ያመለክታል። የአምስተኛው ማኅተም መፈታት፥ የዘመኑን ጽኑ ስደትና ብዙዎች በክርስቶስ የታመኑ ምስክርነታቸውን በደማቸው ማኅተም እንደሚያመለክቱ ይገልጣል። ስድስተኛው ማኅተም መጪውን የተፈጥሮ መናወጥ ይገልጣል። ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤ ወራቶችና የተፈጥሮ ሂደቶች ይናጋሉ። ፀሐይ ትጠቁራለች፤ ጨረቃም እንደ ደም ትቀላለች። በሁሉም ስፍራ ታላቅ የምድር መናወጥ ይሆናል። ራእይ ምዕራፍ 6 “የበጉ ቁጣ” በምድር ሁሉ ላይ የሚወርድበት፥ የእግዚአብሔር የፍርድ ሰዓት መሆኑን ያመለክታል (ራእይ 6፡16)።

## ♦ ሰባቱ የጥፋት መለከቶች

ሰባቱ ማኅተሞች የዘመኑ አጠቃላይ ቅድመ ገለጣ ብቻ ነበሩ። ሐዋርያው ዮሐንስ ሰባተኛው ማኅተም ተከፍቶ ባየ ጊዜ፥ ከውስጡ እያንዳንዳቸው የተለየ መዓት የሚወክሉ ሰባት መለከቶችን ተመለከተ። ከነዚህ ብዙዎቹ የምድርን ሰፊ ክፍል የሚያወድሙ ናቸው። ታላቅ ሁከት፥ የተፈጥሮና የአየር መዛባት ያስከትላል። በእግዚአብሔር ተአምራዊ ድርጊት፥ እግዚአብሔር እንደ ኑክሊየር ያሉትን መሣሪያዎች መነሻ በማድረግ፥ ወይም በፀሐይ ዙሪያ በምድር ዋልታ ላይ ሁከት በመፍጠር ከምድር ሲሶው በእሳት ይወድማል። ከባሕር አንድ ሦስተኛው ወደ ደምነት ይለወጣል፤ በውስጡ ከሚኖሩ አራዊትም አንድ ሦስተኛዎቹ ይሞታሉ። የመለከቱ ድምፅ በድጋሚ እንደተሰማ አንዱ

መቅሠፍት ከሌላው እየቀጠለ ምድርን ይመታታል። በራእይ ምዕራፍ 9 እንደተገለጠው የአጋንንት ማደሪያ መሆን ይለመዳል፤ በአጋንንት የተጠቁትም በጊንጥ የተነከሱ ያህል ይሠቃያሉ።

ስድስተኛው መለከት ታላቁን የምሥራቃውያን ሠራዊት ግስጋሴ ያመለክታል። ቁጥራቸውም 200,000,000 ይሆናል (ራእይ 9፡16)። ይህ ታላቅ የእስያ ሠራዊት እንቅስቃሴ ምናልባት በኮሚኒስት ቻይና የሚመራ ይሆናል። ቻይና አስቀድማ 200,000,000 የሚያክል ወታደርና ደጀን የሚሆን የወንድና የሴት ሲቪል ሠራዊት አሠልጥናለች። ይህን የሚያህል ሠራዊት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሲንቀሳቀስ በመንገዱ የሚያገኘውን ሁሉ ያወድማል። እንደ ቁጥሩ ብዛት ሰዎችን የመግደል ኃይሉም አስከፊ ነው። የሥራ ድርሻውም "የሰዎችን ሲሶ (አንድ ሦስተኛ) እንዲገድሉ" ነው (ራእይ 9፡15)። ይህ በሰዎች ላይ ከሚደርሰውና በራእይ 6፡8 ካለው መቅሠፍት ተጨማሪ መሆኑ ነው። የዚህ ጊዜ መቅሠፍቶች ድምር ከዓለም ሕዝብ ብዛት ከግማሽ በላይ የሚሆነውን እንደሚያጠፉ የራእይ መጽሐፍ በሚገባ ግልጥ አድርጎታል።

## ♦ የመጨረሻዎቹ ሰባት የመቅሠፍት ጽዋዎች

የሰባተኛው መለከት ድምፅ እንደተሰማ በራእይ 16 እንደተዘገበው፥ ሌሎች ተከታታይ መቅሠፍቶች ይከተላሉ። እነሱም በእግዚአብሔር ቁጣ የተሞሉ ጽዋዎች ናቸው። የጽዋዎቹ ምሳሌነት የሚያመለክተው፥ የእግዚአብሔር የፍርድ ቁጣ በምድር ላይ እንደሚፈስ ነው። እነዚህ ተከታታይ ጽዋዎች ወደ ምድር ሲፈሱ ምድርን ታላቅ መቅሠፍት ይመታታል። ሰዎች ክፉኛ በሚያሠቃይ ቁስል ይመታሉ፤ በባሕር የሚኖሩ ፍጥረታትን ጨምሮ ሕይወት ያላቸው ሁሉ ይሞታሉ። ወንዞችና የውሃ ምንጮች ወደ ደምነት ይለወጣሉ፤ የምድር ምህዋር በመለወጡ ምክንያት፥ ምድርን ተፈጥሯዊ ያልሆነ ሙቀት ያቃጥላታል። በመጨረሻም ፀሐይ ትጨልማለች፤ ከዚህም የተነሣ ጨለማው ይበረታል፤ የአየር ለውጥ ስለሚሆን ዕፀዋት ይወድማሉ።

ከጽዋዎቹ የሚፈሰው ጥፋት የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመለክታል። ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ የእግዚአብሔር ቁጣዎች ናቸው ብለን ለመተርጎም ብንችልም፥ በሌላም በኩል እግዚአብሔር ፈቅዶት የሚደረግ የኑክሊየር ጦርነት ውጤቶች ናቸው ለማለት ይቻላል። የኑክሊየር ጦርነት አስቃቂ የሕይወት ጥፋት፥ ምድር በምህዋርዋ ላይ የምታደርገውን ዑደትና የተፈጥሮ ሂደት መናጋትንም ሊያስከትል ይችላል። የኑክሊየር ጦርነት ቢደረግ ከሚፈነጥቀው ጨረር የተነሣ ሰዎች ክፉኛ ይሠቃያሉ፤ ከዚህም ባሻገር ውኃዎችና ምግቦች ይመረዛሉ። በጣም አነስተኛ የሆነ የኑክሊየር ልውውጥ እንኳን ተከታታይ የምድር ነውጥ እና ሥነ-ምድራዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል።

ከስድስተኛው ጽዋ መፍሰስ በኋላ ያልተለመደ የአጋንንት ሥራ ይቀጥላል፤ ከምሥራቅ ወደ አርማጌዶን ለሚዘምተው ሠራዊት መንገድ ይዘጋጅለት ዘንድ የኤፍራጥስን ወንዝ ያደርቃል። ከሰባተኛው ጽዋ ጋር የተያያዘው የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ መፍሰስ የሚፈጸመው፥ የምድር ሠራዊት ሁሉ ለአርማጌዶን ጦርነት በሚከማቹበት ወቅት ወይም በሦስተኛው የዓለም ጦርነት ነው። ምድር ታላላቅ ከተሞቿ እስኪወድሙ ትናወጣለች፤ ቅርፅዋ እንኳን ይቀየራል። ደሴቶች ይጠፋሉ፤ ተራሮች ይናዳሉ።

ይህ ክርስቶስን እንደ ጌታና ገዥ ለመቀበል ፈቃደኛ ባልሆነው ዓለም ላይ የሚወርድ የመጨረሻ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። ይህ ጦርነትና ተከታታዮቹ መቅሠፍቶች በሰዎችና በንብረት ላይ ለማመን የሚያዳግት ጥፋት ያስከትላሉ። ክርስቶስ የተናገረው ትንቢት፥ ቃል በቃል ይፈጸማል። ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል። የመከራው ጊዜ በእርሱ ዳግም መምጣት ባያጥር ኖሮ፥ አንድ ሰብአዊ ሕይወት እንኳን አይተርፍም ነበር። ነገር ግን ይህ የመከራ ወቅት እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ለሚያደርገው የመጨረሻና ዋና ግንኙነት መጠነኛ አመልካች ብቻ ነው። ለአርማጌዶን ጦርነትና ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ለሚኖረው ፍርድ መድረክ ያዘጋጃል።

# 14

# አርማጌዶን፥ የዓለም የሞት ሽረት ትግል

## ♦ አዲሱ የዓለም መንግሥት ዓዋጅ

በምፀታዊ አነጋገር የሚዲትራኒያኑ መሪ ዓለም አቀፍ ግዛቱን የሚጀምረው ዓዋጅ በማስነገር ነው። በመካከለኛው ምሥራቅ የሚያገኘውን የኃይል የበላይነት መከታ በማድረግ መሪነቱን ለሚቀበሉ ሁሉ፥ የሰላምና የብልጽግና ወቅት እንደሚሆንላቸው ተስፋ ይሰጣል። መልእክቱም በራዲዮና በቴሌቪዥን ለዓለም ሁሉ በአንድ ቀን ይዳረሳል። “ብልሁና አስተዋዩ መሪ” ራሱን፥ ለተቸገረችው ዓለም መፍትሔ እንዲሁም ሰላምና ብልጽግናን የሚያመጣ አድርጎ ነው የሚያቀርበው።

ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ሥልጣኖችን ሁሉ በእጁ ያደርጋል። የአመራር ብቃቱ ከተፈጥሮአዊ ሰው በላይ ይሆናል። በሰይጣን ሥር ስለሆነና በእርሱም ስለሚመራ በሦስት ዓመት ተኩል የግዛት ዘመኑ ጊዜ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ በጭካኔ ይደመስሳቸዋል። ቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛ ባሕርዩን ሲገልጡ “አውሬው” ይሉታል (ራእይ 13፡1-4)። ሰይጣን ደግሞ በእውነተኛው ባሕሪው “ዘንዶው” ተብሎ ተገልጧል (ራእይ 12፡9፤ 13፡4)። እነዚህ ዓመታት ሰይጣን እንደ እግዚአብሔር ለመመለክ፥ ዓለምን ለመቆጣጠርና ሰዎችም ለእርሱ ፍጹም ታዛዦች እንዲሆኑ የነበረውን ምኞት እውን የሚያደርግባቸው ይሆናሉ።

## ♦ ወደ ፍርድ መጣደፍ

አዲሱ የዓለም አምባገነን፥ እግዚአብሔርን የሚሳዳብና የሚያዋርድ፥ በእግዚአብሔር ሕዝቦችም የሚጠላ፥ በራእይ 6-18 በተገለጠው መሠረት፥ በእርሱ ላይ እጅግ አስከፊ መለኮታዊ ፍርድ እስኪገለጥ ድረስ ክርስቶስን የሚያምኑትን ከመጠን በላይ የሚያሳድድ ይሆናል። ታላቁ የመከራ ዘመን ሲጀምር መቅሠፍቶች በተከታታይ ይወርዳሉ። አምባገነኑ መሪ ሰላምና ብልጽግናን አመጣለሁ ብሎ ለዓለም ቃል ቢገባላትም፥ በተግባር ግን አመራሩ

መዓትና ውድመትን ስለሚያስከትል ዕረፍት ይነሣታል። ድንቅና ተአምራትን በማድረግ እንዲመለክ ስለሚጠይቅ ተቃዋሚዎች ይነሡበታል። እርሱም በተቃዋሚዎቹ ላይ የበለጠ ጭቆናና ስደት ያደርስባቸዋል። ምንም እንኳን ሰፊ ሥልጣን በእጁ ቢይዝ፥ የዓለምን ሁኔታ ማርገብና መቆጣጠር ያቅተዋል። ዋና ዋና የዓለም ክፍሎችም በእርሱ ላይ ዓመፅና ተቃውሞ ይጀምራሉ። በመጨረሻም ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በብዛት መጥተው ሥልጣኑን ለመንጠቅ ይዋጉታል።

## ♦ የሦስተኛው የዓለም ጦርነት ፍንዳታ

በዳንኤል 11፡36-39 ነቢዩ ስለ ፈላጭ ቆራጩና በመጨረሻም አምላክ ነኝ ስለሚለው መሪ ካስተዋወቀ በኋላ፥ የዓለም ሠራዊቶች በተቃውሞ እንደሚነሡበት በማስረዳት ስለ ሁኔታው ሥዕላዊ መግለጫ ሰጥቶ ነበር። በዳንኤል 11፡40 መሠረት፥ "በፍጻሜ ዘመን የደቡብ ንጉሥ ከእርሱ ጋር ይዋጋል፤ የሰሜንም ንጉሥ ከሠረገሎችና ከፈረሰኞች ከብዙም መርከቦች ጋር እንደ ዓውሎ ነፋስ ይመጣበታል፤ ወደ አገሮችም ይገባል፤ ይጎርፍማል፤ ያልፍማል።"

## ♦ ከደቡብና ከሰሜን ዓመፅ

የዳንኤል ትንቢት እንደገለጠው፥ ታላቅ ሠራዊት ከግብፅና ከሌሎቹም የአፍሪካ አገሮች ይነሣሉ። ይህም በሚሊዮን የሚቆጠር ሠራዊት ምናልባት መካከለኛው ምሥራቅን በደቡብ በኩል ይወራል። ልክ በዚሁ ጊዜ የሩሲያና የሌሎችም መንግሥታት ሠራዊቶች ይህን አምባገነን መሪ ለመውጋት ከሰሜን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ይዘምታሉ። ሩሲያ ምንም እንኳን በትንቢቱ መሠረት ከሦስት ዓመት በፊት ከፍተኛ ሽንፈት የሚደርስባት ቢሆን፥ የተበታተነ ጦርዋን እንደገና አደራጅታ ለጦርነት ትዘጋጃለች። ሠራዊቱ ከሚገጥመው ሽንፈትና ከሚያገኘው ድል የተነሣ ወደፊትና ወደኋላ ስለሚዋዥቅ ሦስተኛው የዓለም ጦርነት የመጀመሪያ ገጽታ ለጊዜው ያደናግራል። ዓለም አቀፉ መሪ በመጀመሪያው ውጊያ በተለይ በደቡብ ሠራዊት ላይ ድል የሚያገኝ ይመስላል፤ ከዚያም የግብፅንና የአፍሪካን ሠራዊት ወደመጡበት ይመልሳቸዋል።

## ♦ የኮሚኒስት ቻይና እንቅስቃሴ

አምባገነኑ የዓለም መሪ፥ ሁኔታዎችን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ እንደጀመረ ወሬ ሠራዊት ከምሥራቅ እንደመጣበት ይሰማል (ዳን. 11፡44)። ይህን ሁለት መቶ ሚሊዮን የሠራዊት መዓት ለመግታት (ራእይ 9፡16)፥

ራሱንም ለመከላከል ወታደራዊ ኃይሉን በተለያየ አቅጣጫ ለመከፋፈል ይገደዳል። ከዚያም እንደ ማዕበል የሚገሰግስ ሌላ ሠራዊት ከሰሜን እንደሚመጣ ይሰማል። በዚያን ጊዜ፥ በጦርነት ታሪኮች ተወዳዳሪ የሌለውና በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን የሚያሳትፈው ውጊያ የእስራኤልን ምድር ዋና የጦር አውድማ በማድረግ ይጀመራል። ይህ ውጊያ ሌላ የዓለም ጦርነት ከመሆን ባሻገር፥ ዓለምን ለሚቀጥሉት ተከታታይ ትንቢታዊ ፍጻሜዎች በማዘጋጀቱ ረገድ የተለየ ሚና ይኖረዋል።

## ♦ የሰይጣን ጦር ዕቅድ

በራእይ 16፡13-14 መሠረት፥ የዓለም ወታደራዊ ኃይላት በአጋንንት አግባቢነት ይሰባሰባሉ። የዓለም ገዥ ሥልጣን የያዘው፥ በሰይጣን ረዳትነት ዓለምን በሞላ በመቆጣጠር ቢሆንም፥ አሁን ደግሞ በሰይጣን በተላከ አጋንንት አነሣሽነት በሚመጣ ሠራዊት ይመታል።

ዮሐንስ በራእይ 16፡13-14 ላይ "ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጉንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤ ምልክት ያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ" ተብሎ ተጽፏል። በጓጉንቸር የተመሰሉት ርኩሳን መናፍስት የሰይጣን መልእክተኛ የሆኑትን አጋንንት እንደሚወክሉ ግልጥ ነው። እነርሱ የወጡት፥ ከዘንዶው፥ ከአውሬው፥ እና ከሐሰተኛው ነቢይ አፍ ማለትም ዓለምን ከሚቆጣጠሩ ሦስት የክፋት መናፍስት ነው።

## ♦ ሰይጣናዊ ሥልሳዊነት

የሰይጣን ፕሮግራም ሁልጊዜ ማስመሰል ነው። በክርስቲያኖች እምነት መሠረት አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንዳሉ ሁሉ፥ የክፋት ኃይላትም የራሳቸውን ሦስትነት ይዘው ይቀርባሉ። ሰይጣን በእግዚአብሔር አብ፥ አውሬው የንጉሦች ንጉሥና፥ የጌቶች ጌታ በሆነው ክርስቶስ፥ ሐሰተኛው ነቢይ ደግሞ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተመስለው ይቀርባሉ። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሰዎች ክርስቶስንና አብን እንዲያመልኩ ማድረግ እንደሆነ ሁሉ፥ ሐሰተኛው ነቢይም ሰዎች አውሬውንና ዘንዶውን እንዲያመልኩ ያደርጋል። ከዚህ አንጻር አጋንንት በሰይጣናዊ ተአምራት በመደገፍ ይንቀሳቀሳሉ። እነዚህ ሰይጣናዊ ተአምራቶች የምድር ነገሥታትን ያስቷቸውና ምድራዊውን ሥልጣን ለመቀራመት ሲሉ በዓለም ለሚከሠተው ዓመፅ ተባባሪዎች ይሆናሉ።

## ♦ ታላቁ የእግዚአብሔር ቀን ውጊያ

ነገሥታት እንደ እግዚአብሔር ቃል በአርግጥ ይሰበሰባሉ። “በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ (ራእይ 16፡14)። ለምንድን ነው ሰይጣን የዓለምን ጦር አሰባስቦ የራሱን መንግሥት የሚያበጣብጠው? የሰይጣን ተስፋ የለሽ ዕቅድ ዓለምን በአምባገነን መሪው በኩል ከመቆጣጠር የላቀ ነው። የዓለም መንግሥታት ከራሳቸው አመለካከት አኳያ የተሰበሰቡት ለዓለም ሥልጣንና የበላይነት ፉክክር ቢመስላቸውም፥ ሠራዊት አሰባሳቢው ሰይጣን ግን፥ ያን የሚያደርገው የክርስቶስን ዳግም መምጣት ለማደናቀፍ ካለው ዕቅድ የተነሣ ነው። የዓለም የታጠቀ ኃይል በሙሉ በመካከለኛው ምሥራቅ ተከማችቶ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ሊገጥመው ይዘጋጃል። ተከታታይ ድርጊቶች በግልጥ እንደሚጠቁሙት፥ እንቅስቃሴው ፍሬ ቢስና ከንቱ ነው። የዓለም ሠራዊት በምንም ሁኔታ የሰማይን ሠራዊት የመውጋት አቅም የለውም። ቢሆንም ሰይጣን ነገሥታቱን ለዚህ የመጨረሻ ሰዓት ያሰባስባቸዋል፤ ነገሥታቱም ከሰይጣን ወገን መሆንን ይመርጡና የክርስቶስን ዳግም መምጣት ይቃወማሉ። ሰይጣን ለማድረግ የሚችለው ይህንኑ ይሆናል። እነዚህ ሁኔታዎች ለነገሥታቱ ምርጫ የሚሰጧቸው ሲሆን፥ ሰይጣንም የክርስቶስን ዳግም መምጣት ለመቃወም ተስፋ የለሽ ሙከራውን እንዲያደርግ ያስችሉታል።

## ♦ አርማጌዶን

የዓለም ሠራዊት “በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባለው ስፍራ” ይሰበሰቡና እርስ በርሳቸው ውጊያ ይገጥማሉ (ራእይ 16፡16)። አርማጌዶን የሚለው ቃል ከሁለት የዕብራይስጥ ቃላት የተገኘ ነው፤ “አርም” ማለት “ተራራ” ሲሆን፥ “መጊዶ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው ደግሞ፥ ከፍልስጥኤም በስተሰሜን ያለውን ስፍራ ነው። የመጊዶ ተራራ የሚገኘው በሜዲትራኒያን ባሕር አጠገብ በምሥራቅ ሸለቆ ትይዩ ነው። ይህ ሰፊ ሸለቆ ሀያ ሁለት ኪሎ ሜትሮች ስፋትና ሠላሳ ሁለት ኪሎ ሜትሮች እርዝማኔ ያለው ሲሆን፥ የመጨረሻውና የሦስተኛው የዓለም ጦርነት ተዋጊ ሠራዊት ሰልፍ የሚካሄድበት ዋነኛ መድረክ ነው። ምንም እንኳን ስፍራው በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተዋጊዎችን ለማስተናገድ ባይበቃ፥ የዓለም ፍጻሜ መነሻና የጦርነት ማዕከል ይሆናል። ጦርነቱም የአርማጌዶን ጦርነት በመባል ይታወቃል። ሠራዊቶች የሚሠማሩት በብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች ርቀት፥ ባመቸ አቅጣጫ ማለትም፥ በሰሜን፥ በደቡብና በምሥራቅ መሆኑ ነው።

የዓለም ጦር ሠራዊቶች፥ ለመጨረሻው ጦርነት ወደ አርማጌዶን ሲንቀሳቀሱ፥ ቀድሞ የፈነዳው ጦርነት የሚሊዮኖችን ሕይወት አጥፍቶ ይገኛል።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ጦርነቱ መዋዕል የሚሰጠን ገለጣ በትንሹ ማለትም ስለ ዋና ዋና ድርጊቶች ብቻ ነው። ሠራዊቶች በአርማጌዶን ሸለቆ እንደተሰበሰቡ፥ ዓለም ከሰባተኛው ጽዋ ጋር በተያያዘ የመጨረሻ መለኮታዊ ፍርድ ትናወጣለች።


ሐዋርያው ዮሐንስ ሁኔታውን እንዲህ በማለት ገልጦታል፦ "በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ስፍራ አስከተቱአቸው። ሰባተኛው ጽዋውን በአየር ውስጥ አፈሰሰ፥ ከመቅደሱም ውስጥ ተፈጽሞአል የሚል ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ ወጣ። መብረቅና ድምፅም ነጎድጓድም ሆኑ፤ ትልቅም የምድር መናወጥ ሆነ። ሰው በምድር ከተፈጠረ ጀምሮ እንዲህ ያለ ታላቅ መናወጥ ከቶ አልነበረም፤ ከሁሉ በለጠ። ታላቂቱም ከተማ በሦስት ተከፋፈለች፤ የአሕዛብም ከተማዎች ወደቁ። ታላቂቱም ባቢሎን የብርቱ ቁጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች። ደሴቶችም ሁሉ ሸሹ፤ ተራራዎችም አልተገኙም፤ በሚዛን አንድ ታላንት [አርባ ኪሎ ግራም፥ በ1980 ዓ.ም. እትም] የሚያህል ታላቅ በረዶ በሰዎች ላይ ከሰማይ ወረደባቸው፤ ሰዎቹም ከበረዶው መቅሠፍት የተነሣ እግዚአብሔርን ተሳደቡ፤ መቅሠፍቱ እጅግ ታላቅ ነውና" (ራእይ 16፡16-21)።

## ♦ እግዚአብሔርን ሰድቦ መሞት

ሰይጣን በዓለም ዙሪያ ያሉ ሠራዊቶችን ለመጨረሻ ድሉ እንደ ዕቃ ይጠቀምባቸዋል። በእምባገነኑ መሪ ላይ ያመፁ ነገሥታት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ይሰበሰባሉ። ዓለም መውደሚያዋ ዳር እስክትደርስ ድረስ ጦርነቶችና ጥፋቶች ይጨምራሉ። የምድር መሪዎች ራሳቸውን በትሕትና ዝቅ ከማድረግ ይልቅ፥ እግዚአብሔርን ተሳድበው መሞትን ይመርጣሉ (ራእይ 16፡9፥ 11፥21)። በእግዚአብሔርና በምድር ነገሥታት መካከል የሚደረገው ይህ የመጨረሻ ፍጥጫ አንድ ቀን ይፈጸማል።

ነቢያት እንደገለጡት፥ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የታሪክ መደምደሚያ ለሆነው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቅድመ ክንውኖች ሲሆኑ፥ ከዚያ የሚቀጥለው ክንውን ክርስቶስ መንግሥቱን በምድር የሚመሠርትበትና እርሱ እንዲገዛቸው በማይፈቅዱ ሰዎች ላይ የሚሰጠው ፍርድ ይሆናል።

# የመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት ዘመናት ፍጻሜ ቅደም ተከተል መግለጫ



# 15

# የክርስቶስ ዳግም ምጽአት

## ♦ ከግርግም ወደ ሥልጣንና ክብር

ኢየሱስ በመጀመሪያ ምጽአቱ የተወለደው በበረት ውስጥ ነበር፤ መወለዱን ዓለም አላወቀውም። በብሉይ ኪዳን ነቢያት እንደተገለጠው እንደ ባሪያና አዳኝ ሆኖ በዮሐንስ ዓዋጅ ነጋሪነት ነበር የሚመጣው (ኢሳ. 42፡1-4፤ 53፡1-12)። የኖረው አንጻራዊ ሰላም በሰፈነበትና የሮም ነገሥታት ፍልስጥኤምን በሚቆጣጠሩበት ጊዜ ነበር። በኢየሩሳሌም ተከሶ ተፈርዶበታል። በአይሁድ መሪዎች ከሳሽነት በሮም ወታደሮች በመስቀል ተቸንክሮአል። በባሪያ መልክ የመጣው መሲሕ በእስራኤል ስፍራ አልነበረውም። በትንሣኤው ለብዙዎች ከታየ በኋላ ኢየሩሳሌም አጠገብ ካለው ደብረ ዘይት ተራራ ወደ ሰማይ ዓረገ።

ዳግም ምጽዓቱ ግን እንግዲህ የበረት ትርዒት አይሆንም። አስደናቂና ከዚህ በፊት በዓለም ታሪክ ያልታየ፥ ዓለማትን የሚያናውጥ ክንውን ይሆናል። በኃይልና በክብር ስለሚመጣ የዓለምን ሁሉ ትኩረት ይስባል። በሜዲትራኒያኑ ኅብረት የሚያንሰራራው አምባገነን የሮም መንግሥት ከአርባ ሁለት ወራት በፊት በዓዋጅ ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ይልና በግምት ከሦስት ዓመታት በኋላ ዓለምን ዓመፅና አስከፊ ጦርነት ውስጥ ይከታታል። በዳንኤል 11፡40-45 እና በራእይ 16፡14-16 በተገለጠው መሠረት፥ ከዚያ ቀደም ሲል በሚደረጉ ጦርነቶችና መቅሠፍቶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ይሞታሉ። ታላቅ ሠራዊት ከሰሜን፥ ከደቡብና ከምሥራቅ ከትቶ መካከለኛው ምሥራቅ ይደርሳል። ዋናው ጦረኛም አርማጌዶን ሸለቆ ውስጥ ይከማቻል። አምባገነኑ የዓለም ገዥ መዲና እና ማዕከል የነበረችው ኢየሩሳሌም በጦርነት ትጠቃለች፤ ቤቶችም ይበዘበዛሉ (ዘካ. 14፡2)። የመጨረሻው የምድር ነውጥም ዓለምን እረጭ ያደርጋታል። ይህ ነው የመጨረሻውን የፍርድ ጽዋ መፍሰስ የሚያመለክተው (ራእይ 16፡17-21)። ከዚያም የሰው ልጅ አስፈሪና አንጸባራቂ በሆነ ግርማ ከቅዱሳኑ ጋር ከሰማይ ይወርዳል (ራእይ 19፡11-16)።

## ♦ መብረቅ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ

አዲስ ኪዳን እንደሚያመለክተው፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት በክርስቲያናዊ ትምህርተ-ሃይማኖት ውስጥ ዓቢይና ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው

ትንቢታዊ እውነት ነው። በአዲስ ኪዳን ከሀያ አምስት ቁጥሮች ውስጥ አንዱ ቁጥር ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ወይም ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአትና መንግሥቱን በምድር ስለ መመሥረቱ እንደሚናገር ይገመታል። ክርስቶስ ራሱ ስለ አመጣጡ ሲናገር መብረቅ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በሚታይ አኳኋን እንደሚሆን አመልክቷል (ማቴ. 24፡27)። የእርሱ ዳግም ምጽአት የመከራ ዘመን ማከተሚያ እንደሆነ ሲያመለክትም፦ "ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፤ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፤ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፤ የሰማይም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፤ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፤ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል" አለ (ማቴ. 24፡29-30)። ይህ ሁኔታ በወንጌል ብዙ ስፍራ ተጠቅሷል (ማቴ. 19፡28፤ 23፡39፤ ማር. 13፡24-37፤ ሉቃስ 12፡35-48፤ 17፡22-37፤ 18፡8፤ 21፡25-28)።

መላእክት እንኳን ክርስቶስ ከምድር ባረገ ጊዜ የዳግም ምጽአቱን መሠረታዊ እውነት ለደቀ መዛሙርቱ አጽንተው ሲናገሩ፥ "የገሊላ ሰዎች ሆይ! ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል" ብለዋቸዋል (ሐዋ. 1፡11)። በሌላም የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ብዙ ጥቅሶች ተመልክተዋል (ሐዋ. 15፡16-18፤ ሮሜ 11፡25-27፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡26፤ 2ኛ ተሰ. 1፡6-10፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡3-4፤ ይሁዳ 14፥15)።

## ♦ የመላው ዓለም ድንጋጤ

ስለ ዳግም ምጽአቱ ዝርዝር ገለጣ የሚገኘው በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ነው። ይህ የሚያስረዳው፥ ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ ለመላው ዓለም ራሱን የሚገልጥ መሆኑን ነው። ራእይ 1፡7 እንዲህ በማለት ያብራራዋል፦ "እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዐይንም ሁሉ የወጉትም ሁሉ ያዩታል፤ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን አሜን።"

ከሁሉ ዋና ሆኖ የተገለጠው ግን፥ በራእይ 19፡11-21 ላይ ያለው ነው። ታላቁ መከራና የአርማጌዶን ውጊያ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ሰማያት በእግዚአብሔር ክብር ተሞልተው ይከፈቱና የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ በክብር ይገለጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ክፍሎች እንደተገለጠው፥ ቀደም ሲል በተደረገው የእግዚአብሔር ፍርድ ሰማያት ይጨልማሉ (ማቴ. 24፡29)፤ ነገር ግን፥ በዚያን ጊዜ ምድራዊ ያልሆነ ብሩህ ብርሃን በሰማይ ያበራል፤ መላውን የዓለም ሕዝብም ያስደንቃል።

## ♦ በነጩ ፈረስ ላይ የተቀመጠው

ተፋላሚ ወታደሮች ለጥቂት ደቂቃዎች የእርስ በርስ ውጊያቸውን እንዳቆሙ ሰማያት ይከፈቱና ክርስቶስ በግርማ ወደ ምድር ይመጣል። የዚህ ትንቢት ቃሎች እጅግ አስደናቂ የሆኑና በየትኛውም የዓለም ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ የማይገኙ ናቸው፡-

> “ሰማይ ተከፍቶ አየሁ፤ እነሆም፥ አምባላይ (ነጭ) ፈረስ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል። በጽድቅም ይፈርዳል፤ ይዋጋልም። ዐይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው። በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ። ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው። በደምም የተረጨ ልብስ ተጎናጽፎአል። ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል። በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር። አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፤ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል። እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል። በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት፡- ‘የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ’ የሚል ስም አለው” (ራእይ 19፡11-16)።

በእርግጥ ይህ ትዕይንት አስፈሪ ይሆናል- በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችና መላእክት የእግዚአብሔርን ክብር እያንጸባረቁ የድል ምልክት በሆነው ነጭ ፈረስ ላይ በተቀመጠው ክርስቶስ ሲመሩ መመልከት!

## ♦ የሦስተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ

ይህን ትዕይንት ሲያይ ዓለም በፍርሃት ይርበደበዳል፤ ለታላቁ የዓለም ጦርነት የተፋጠጡ ሠራዊቶችም ልዩነታቸውን አስወግደው በአንድነት የሰማያትን ሠራዊት ለመውጋት ይሞክራሉ። የዚህ ዓመፅ አነሣሽና አቀናባሪ ሰይጣን ራሱ ነው (ራእይ 16፡13-14)። ግን እግዚአብሔርን መቋቋም ራስን በራስ ማጥፋት ነውና ሙከራቸው ከንቱ ሆኖ ይቀራል። ራእይ 19፡15 ደግሞ የሚቀጥለውን ፍርድ ይገልጣል። ከክርስቶስ አፍ ሲወጣ የታየው ስለታም ሰይፍ፥ በክርስቶስ የሚሰጠው ትእዛዝ ምሳሌ ይመስላል። የክፋት ማደሪያዎች ሁሉ ይጠፋሉ። የሚቀጥሉት ቁጥሮች እንደሚያመለክቱት፥ የሰማይ አዕዋፍ ሁሉ መጥተው የነገሥታትንና የብርቱዎችንም ሥጋ፥ የፈረሶችንም፥ በእነርሱም የተቀመጡትን በጦርነቱ የታረዱትን ሥጋ እንዲበሉ ይጋበዛሉ (ራእይ 19፡17-18)። አውሬው፥ ማለትም አምባገነኑ የዓለም መሪና ሐሰተኛው ነቢይ በሕይወት ይማረካሉ። እንደ ዮሐንስ ራእይ 19፡20 አገላለጥ እነዚህ ሁለቱ በቀጥታ ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ።

ነቢዩ ዘካርያስ አርማጌዶንን በተመለከተ የሚፈነጥቀው እውነት አለ። ክርስቶስ ዳግም በሚመጣበት በዚያን ቀን በኢየሩሳሌም የቤት ለቤት ውጊያ ይካሄዳል (ዘካ. 14፡2)። በተጨማሪም የክርስቶስ እግሮች የደብረ ዘይትን ተራራ ሲረግጡ የሚፈጠረው ሁኔታ ገልጧል፡-

> "አሕዛብንም ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ ለሰልፍ እሰበስባለሁ፥ ከተማይቱም ትያዛለች፥ ቤቶቹም ይበዘበዛሉ፥ ሴቶቹም ይነወራሉ፥ የከተማይቱም እኩሌታ ለምርኮ ይወጣል፥ የቀረው ሕዝብ ግን ከከተማ አይጠፋም። እግዚአብሔርም ይወጣል፥ በሰልፍም ቀን እንደተዋጋ ከነዚያ አሕዛብ ጋር ይዋጋል። በዚያ ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ላይ ይቆማሉ። ደብረ ዘይትም በመካከል ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ይሰነጠቃል፤ እጅግም ታላቅ ሸለቆ ይሆናል። የተራራውም እኩሌታ ወደ ሰሜን፥ እኩሌታውም ወደ ደቡብ ይርቃል" (ዘካ. 14፡2-4)።

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የመጨረሻውን የዓለም ጦርነት ባልታሰበ ሁኔታ ስለሚያቆመው፥ የጥፋቱ ማዕበልም ምድርን ከማጥፋቱ በፊት ይገታል። በእርሱ መምጣትም የአሕዛብ መንግሥታት እንደፈለጉ ኢየሩሳሌምን ይቆጣጠሩበትና የእስራኤልን ሕዝብ ይጨቁኑበት የነበረው "የአሕዛብ ዘመን" [Times of the Gentiles] ያከትማል።

የክርስቶስ ዳግም አመጣጥ ሁኔታ፥ ትንቢትን በሚያጠኑ ተማሪዎች ዘንድ በቂ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። በቃሉ ውስጥ ያሉት ገለጣዎች በክርስቶስ ዳግም ወደ ምድር መምጣትና በቤተ ክርስቲያን ከዚያ በፊት መነጠቅ መካከል ያለውን ጥርት ያለ ማነጻጸሪያ ለመገንዘብ ይረዳሉ።

## ♦ በአካል መመለሱ

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት አካላዊ ነው የሚሆነው። ከድንግል ማርያም የተወለደው፥ በመስቀል ሞቶ የተነሣውና ወደ ሰማይ ያረገው ኢየሱስ ሥልጣኑንና ሉዓላዊነቱን በዓለም ሊያሰፍን በአካል ወደ ምድር ይመለሳል። እንደገና የሚመለሰው በአካል እንጂ በመንፈስ ብቻ አለመሆኑ ግልጥ ነው። ዘካርያስ 14፡4 ስለዚህ ሲጠቅስ እንዲህ ይላል፡- "በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ላይ ይቆማሉ።" የክርስቶስ እግሮች በዕርገቱ ጊዜ ከደብረ ዘይት ተራራ እንደለቀቁ ሁሉ፥ እንዲሁ ይመለሳሉ። የዚህ ጊዜ አመጣጡ ግን ሁሉን የማድረግና ገናና ኃይሉን የመግለጥ ይሆናል።

## ♦ ግልጥና በክብር የተሞላ መመለስ

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ገሃድ ከመሆኑ ባሻገር በታላቅ ክብርና ግርማ የተሞላ ነው። ቃሉ "ሁሉም ያዩታል" ይላል (ማቴ. 24፡30፤ ራእይ 1፡7)። የክርስቶስ ዳግም ምጽአት እንደ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በቅጽበት አይሆንም። ሰው ሁሉ በሚያየው አኳኋን ከቅዱሳኑ ጋር በግርማ፥ በክብርና በአጀብ ከሰማይ ይመጣል። ወደ ምድር ሲወርድ አመጣጡ ብዙ ሰዓት ሊፈጅ በሚችል ሰልፍ ይሆንና ምድር በምህዋሯ እስከተሽከረከረች ድረስ ዓለም ሁሉ የሚመለከተው ይሆናል። የጉዞው ማብቂያ እስራኤል ስትሆን፥ ለአርማጌዶን ውጊያ በአካባቢው የከተተውን ጦር ደምስሶ ነው ጽዮን ተራራ ላይ የሚያርፈው።

## ♦ ከሰማይ ሠራዊት ጋር ስለመመለሱ

ቅዱስ ቃሉ እንደሚያመለክተው፥ ክርስቶስ በሰማይ ሠራዊት ታጅቦ ይመለሳል (ይሁዳ 14፤ ራእይ 19፡14)። በታላቁ መከራ መግቢያ ወቅት የተነጠቁትና በሰማይ ከጌታ ጋር የሚገኙ አማኞች በዮሐንስ 14፡1-4 በተጠቀሰው ተስፋ መሠረት ከጌታ ጋር ወደ ምድር ይመለሳሉ፥ መላእክትም ከሰማይ ወደ ምድር በሚደረገው በዚህ ታላቅ ሥርዓተ-ጉዞ ክርስቶስን ያጅቡታል (ማቴ. 25፡31)።

## ♦ ምድርን የሚያናውጥ ምጽአት

የዓለም ወታደሮች አርማጌዶን ላይ ለጦርነት እንደተሰበሰቡ በራእይ 16፡17-21 የተገለጠው የመጨረሻ የቁጣ ጽዋ ይፈሳል። በዚያን ጊዜ፥ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጥቂት ቀደም ሲል፥ መብረቅና ነጎድጓድ ትልቅም የምድር መናወጥ ይሆናል። ከተሞች ይደረመሳሉ፤ ደሴቶች ይሰጥማሉ፤ ተራሮችም ይጠፋሉ። እያንዳንዱ አርባ ኪሎ ግራም ገደማ የሚመዝን የበረዶ ድንጋይ ከሰማይ ይወድቃል። ቀጥሎም ከሰማይ ወደ ምድር የሚደረገው ሥርዓተ-ጉዞ ካበቃና የዓለም ወታደሮች ከወደሙ በኋላ ከኢየሩሳሌም ውጪ በሚገኘው ደብረ ዘይት ተራራ ላይ የክርስቶስ እግሮች ያርፋሉ። ተራራው ሁለት ላይ ይከፈላል። ዛሬ የደብረ ዘይት ተራራ ባለበት ሥፍራ ታላቅ ሸለቆ ይፈጥርና ከታች ካለው የዮርዳኖስ ሸለቆ ጋር ይገናኛል። ይህ አስገራሚ መልክዓ-ምድራዊ ለውጥ ክርስቶስ በምድር ከመንገሡ በፊት በቅድስቲቱ ምድር ከሚከናወኑት ነገሮች አንዱ ነው። በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ የምድር መልክዓ-ምድር በአብዛኛው ይለወጣል።

## ♦ በመንግሥታት ላይ ለመፍረድ መምጣት

እግዚአብሔር በክርስቶስ ዳግም ምጽአት አማካይነት በሰው ልጅ ታሪክ ላይ ያለውን ሥልጣንና የበላይነት ስለሚገልጥበት ሁኔታ የዳዊት መዝሙር ሁለተኛው ምዕራፍ ሲያመለክት እንዲህ ይላል፦ "የምድር ነገሥታት ተነሡ፥ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ እንዲህ ሲሉ ተማከሩ፥ ማሰሪያቸውን እንበጥስ፥ ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል" (መዝ. 2፥2-3)። ዓመፀኛ ነገሥታት ላይ እግዚአብሔር እንደሚሣለቅባቸው ሲያመለክትም፦ "በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፥ ጌታም ይሣለቅባቸዋል። በዚያን ጊዜ በቁጣው ይናገራቸዋል፥ በመዓቱም ያውካቸዋል" (መዝ. 2፥4-5)። የብሉይ ኪዳን ነቢያት፥ እግዚአብሔር በጽድቅ ስለሚፈርድበት ጊዜና ሰዓት ያመለክቱ ነበር። የመጨረሻ ዕቅዱ በመዝሙር 2፥6፥ "እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ፤ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ" ተብሎ ተገልጧል።

ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ሕዝቡ እንደ ርስቱ ይሆናሉ። ፍርዱም ፍጹማዊ ነው የሚሆነው። መዝሙረኛው ሲተነብይ፦ "በብረት በትር ትጠብቃቸዋለህ፥ እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃም ትቀጠቅጣቸዋለህ" ብሏል (መዝ. 2፥9)። ክርስቶስ ዳግም ሲመለስ ስለሚደረገው ፍርድ የሰሙ ሁሉ ጌታን እንዲያገለግሉትና እንዲያመልኩት ታዘዋል (መዝ. 2፥10-12)። እግዚአብሔር በተወሰነው ጊዜ ልጁን ልኮ፥ ምድርን በፍጹም ሰላምና ፍትሕ እንደሚያስተዳድራት ተስፋ ሰጥቷል። የክርስቶስን ዳግም መመለስ ለመከላከል የተቋቋሙት መሪዎችና ጭፍሮቻቸው ይወድማሉ። በአርማጌዶን ጦርነት የተገደሉት ዓመፀኞች ከክርስቶስ ሺህ ዓመት ግዛት በኋላ እስከሚሆነው ሁለተኛ የትንሣኤና የፍርድ ቀን ድረስ በመቃብራቸው ይቆያሉ (ራእይ 19፥17-21)።

## ♦ ጽዮን ላይ ሆኖ ለመግዛት መመለስ

ክርስቶስ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ዳግም የሚመለስበት ዓላማ ኢየሩሳሌምን መናገሻ ከተማው በማድረግ አዲስ መንግሥት ለመመሥረት ነው። እንደገና ሕግ ከጽዮን ይወጣል (ኢሳ. 2፥3)። የክርስቶስ ዳግም መምጣት ኢየሩሳሌምንም ሆነ የእስራኤልን ሕዝብ ከጥፋት ያድናል። እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚያድን፥ በዓለም ዙሪያ የተበተኑትን አይሁዶች እንደሚታደግ፥ አስቀድሞ በዘዳግም 30፥3 ተናግሮ ነበር፦ "አምላክህ እግዚአብሔር ምርኮህን ይመልሳል፤ ይራራልህማል። አምላክህም እግዚአብሔር አንተን ከበተነበት ከአሕዛብ ሁሉ መካከል መልሶ ይሰበስብሃል።"

ብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችም ይህን አሳብ በማብራራት በመጨረሻ የፍትሕ፥ የጽድቅና የሰላም መንግሥት በኢየሩሳሌም እንደሚመሠረት ያውጃሉ። በመዝሙር 24 ኢየሩሳሌም በሮችዋን ከፍታ ንጉሥዋን እንደምትቀበል

ተነግሯል። በመዝሙር 72 ደግሞ ስለሚመጣው ንጉሥ ግዛት፥ ስለሚከተለውም በረከትና ሰላም ተገልጧል። በመጨረሻ ነገሥታት ሁሉ፥ በዚህ መንግሥት ፊት ተደፍተው እንደሚሰግዱና እንደሚያገለግሉት ሲገልጥ (መዝ. 72፡11)፥ በመዝሙር 96 ላይ ደግሞ፥ አመጣጡ ለፍርድ እንደሆነ ያመለክታል፦ "ይመጣልና፤ በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣልና" (መዝ. 96፡13)። መዝሙር 110 እንደሚተነብየው፥ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ ይሆናሉ "በአሕዛብ መካከል ይፈርዳል፥ ሬሳዎችንም ያበዛል፥ በሰፊ ምድር ላይ ራሶችን ይቀጠቅጣል" (መዝ. 110፡6)።

ከብዙ ታላላቅና ታናናሽ ነቢያት ትንቢቶች ጋር በማመሳከር መዝሙረ ዳዊትን ማጠናከር ይቻላል። በኢሳይያስ 9፡6 መሠረት የሚወለደው ሕፃን ኃያል አምላክና የሰላም አለቃ ነው። እርሱ በመጣ ጊዜ፥ "ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል" (ኢሳ. 9፡7)። የኢሳይያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 11 በሙሉ ስለ ክርስቶስ ዳግም መምጣት፥ ስለ ፍርዱና በጽድቁ ምድርን ስለ መግዛቱ ይገልጣል። ብዙ ሌሎች አንቀጾችም ስለ ገናናው የክርስቶስ መንግሥት በምድር መስፋፋት ያብራራሉ።

ሁለተኛ አመጣጡ በዳንኤል 7፡13-14 ላይ እንዲህ በሚል ተገልጧል፦ "በሌሊት ራእይ አየሁ፥ እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፤ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፥ ወደ ፊቱም አቀረቡት፥ ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።"

በተመሳሳይ አገላለጥም ዳንኤል 2፡44 ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ መንግሥቱ በምድር ትመሠረታለች ይላል። "በእነዚያ ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፤ እነዚያንም መንግሥት ሁሉ ትፈጫቸዋለች፤ ታጠፋቸውማለች፤ ለዘላለምም ትቆማለች።"

## ♦ በሕይወት ያሉ አይሁዶች እንደገና ለፍርድ ሲሰባሰቡ

እግዚአብሔር የክርስቶስን መምጣት የሚቃወሙትን ሠራዊት ማጥፋቱ፥ በመንግሥታቱ ላይ የሚያመጣው ፍርድ ይሆናል። የአርማጌዶን ጦርነት ታላቅ እልቂት ካበቃ በኋላ በሚተርፉት የዓለም ሕዝቦች ላይ አንድ በአንድ ይፈረድባቸዋል። የእስራኤል ሕዝብ ቅሬት የሆኑ አይሁዶች ከፍልስጥኤምና ከዓለም ዙሪያ ሁሉ ይሰበሰባሉ (ሕዝ. 39፡28)። እያንዳንዱ

በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ ይቀርባል። ከዚህ ፍርድ ማንም አያመልጥም። ክርስቶስን ዳግም ከመምጣቱ በፊት እንደ መሢሐቸውና እንደ ግል አዳኛቸው ያልተቀበሉ ዓመፀኞች ግን ለሞት ይወሰዳሉ (ሕዝ. 20፡38)። በስደቱና በታላቁ መከራ ውስጥ ያለፉት አማኝ አይሁዶች እንደ መጀመሪያዎቹ የክርስቶስ መንግሥት ወገኖች ሆነው በተስፋይቱ ምድር እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል። የእነርሱ የስደት ሰዓት ለዘላለም ያበቃና ከአብርሃም ጀምሮ ለእስራኤል ልጆች የተሰጠውን የተስፋ በረከት ሁሉ ይወርሳሉ (ኤር. 31፡31-34፤ ሮሜ 11፡26-27)።

## ♦ በሕይወት የተረፉ ሌሎች ሕዝቦችም ለፍርድ ይቀርባሉ

አይሁድ ያልሆኑና ታላቁን የመከራ ዘመን የሚያልፉ ወገኖች ፍርድ በማቴዎስ 25፡31-46 ተገልጧል። ክርስቶስ አሕዛብን ኢየሩሳሌም ውስጥ በሚቋቋመው ዙፋኑ ፊት ይሰበስባቸዋል። ሰዎች ሁሉ በበጎች ወይም ደግሞ በፍየሎች ይመሰላሉ። ንጉሡ ክርስቶስ በጎቹን ወደ መንግሥቱ እንዲገቡ ይጋብዛቸዋል። እነርሱም አይሁዶችን በስደትና በመከራ ዘመናቸው የረዱ ሲሆኑ ታሥረው የጠየቋቸው፥ ተራቁተውም ያለበሷቸው፥ ተርበው የመገቧቸውና ካሳዳጆቻቸው ሸሽገው ከሞት ያዳኗቸው ናቸው።

በዚህ ፀረ-ሴማውያን እንቅስቃሴ በተስፋፋበት ዘመን፥ አይሁዶችን በመከራ ጊዜ መርዳት በእግዚአብሔር የማመን ዋናውና ትልቁ ማረጋገጫ ነው። ይህን ማድረግ በራሱ ደኅንነት ባያስገኝም፥ በዚህ ወቅት የአይሁዶች ወዳጅ መሆን በእውነት የማመንና ቅዱሳት መጻሕፍትን የመረዳት ማረጋገጫ ይሆናል። እነዚህ አማኞች የሚታወቁት በመከራ ወቅት ባደረጉት አስተዋጽኦ ቢሆንም፥ ደኅንነት የሚያገኙት ግን፥ በዘመናት እንደነበሩት አማኞች ሁሉ በእግዚአብሔርና በክርስቶስ የቤዛነት ሥራ በማመናቸው ብቻ ይሆናል።

በአንጻሩም በፍዳው ጊዜ በአይሁዶች ላይ ጭካኔ ያሳዩና በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች በገዛ ክፉ ሥራቸው ይጋለጣሉ። እነዚህ በፍየሎች የተመሰሉ ኃጥአን ሲሆኑ፥ ወደ ዘላለም እሳት በመጣል ይቀጣሉ። የማያምኑ አይሁዶች እንደሚፈረድባቸው ሁሉ፥ የማያምኑ አሕዛብም ይፈረድባቸዋል።

ሌሎች በምድር የሚቀሩ ሕዝቦች ሟች የሆነው ሰውነታቸውን እንደያዙ ለሺህ ዓመት ከክርስቶስ ጋር ይገዛሉ። መንግሥቱ የሚጀምረው የማያምኑትን ሁሉ ከምድር በማስወገድ ነው። በሚመጣው የሺህ ዓመት አገዛዝ ወቅት ሕፃናት ተወልደው የሚያድጉ ሲሆን፥ እያንዳንዳቸው ለማመንም ሆነ ለማመፅ የየራሳቸው ጊዜ ይኖራቸዋል። በዘመኑ መጀመሪያ ላይ ዓማፂያን በሙሉ ይወገዱና ዓለም በአዲሱ ሰላም ራሷን የምትገነባበትና የምትለመልምበት ዘመን ይሆናል።

## ♦ ከጥፋት ወደ ፍጹማዊነት [Utopia/ዩቶፒያ]

ፍጹም የሆነው ዓለም፥ የሰው ልጅ ታሪኩን ለመቆጣጠር ሙከራ ሲያደርግ የደረሰበትን ታላቅ ውድቀት የሚከተል ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች በሦስት ዓይነት ፍርዶች ከዓለም ይወገዳሉ። የዓለም ሠራዊቶች በመካከለኛው ምሥራቅ በሚነሣው ጦርነት ይደመሰሳሉ፥ የማያምኑ አይሁዶች ተፈርዶባቸው ከምድር ገጽ ይጠፋሉ። በግና ፍየል በሚለይበት ፍርድ ወቅት አይሁድ ያልሆኑ የማያምኑ ወገኖች ከምድር ይወገዳሉ። በዚያን ጊዜ በምድር ላይ የሚቀሩት፥ ክርስቶስን በማመን ዳግም የተወለዱ ሕዝቦች ናቸው።

በክርስቶስ አምነው ያለፉ በእርሱ የጽድቅ መንግሥት ድርሻ ይኖራቸዋል። በቤተ ክርስቲያን ዘመን ክርስቶስን በግል ያመኑ የመጨረሻው ሰዓት ከመድረሱ በፊት ይነጠቃሉ። በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደሚገለጠው፥ በመነጠቁ ሰዓት በክርስቶስ የሞቱ ይነሡና በሕይወት ያሉትም ከምድር ይወሰዳሉ። ወደ ክርስቶስ የሚወሰዱት በአዲስ የትንሣኤ አካል ስለሆነ በምድር ላይ ከሚመጣው ፍርድ ይድናሉ። በብሉይ ኪዳን ወይም በታላቁ መከራ ጊዜ የሞቱ አማኞች ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ መንግሥቱን በምድር ላይ በሚመሠርትበት ጊዜ ተነሥተው አዲስ አካል ይለብሳሉ። እነዚህ ቅዱሳን አዲሱ መንግሥት በዚህ ምድር ላይ ሲመሠረት ተመልካቾችና በአስተዳደሩ ሥራ ተሳታፊዎች ይሆናሉ።

ነገሮች ሁሉ ባስገራሚ ሁኔታ ስለተለወጡ የሰው ልጆች ታሪክ የነገሥታት ንጉሥ፥ የጌቶች ጌታ በሆነው አምላክ ቁጥጥር ሥር ይሆናል። ከዚህ ቀደም በሰይጣንና በክፉዎች ትገዛ የነበረችው ዓለም አሁን በጽድቅና በፍትሕ ትመራለች። በጦርነትና በጥፋት የታመሰችው ዓለም ለሺህ ዓመት ሰላም ይሰፍንባታል። የዚያን ጊዜው የዓለም ሕዝብ ወደ ወርቃማው ዘመን በመግባት እውቀቱንና መላ ኃይሉን ለእንደገና ግንባታና ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር ይጠቀምበታል። ሰይጣን ይታሠራል፤ ክፋት ከእግዚአብሔር ቅጽበታዊ ፍርድ ያገኛል። ተፈጥሮም ከእሥራት ይፈታል። እንዲህ በተስተካከለው ሰላማዊ ዓለም አንበሳ ከጥጃ ጋር ይውላል።

## ♦ ለአሁኑ ትውልድ ተገቢ ጥያቄ

በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የመካከለኛው ምሥራቅ ተከታታይ ጦርነት ወደማይቀረው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከሚያመሩት ክንውኖች አንዱ ነው። በእኛ ዘመን የሆነው የመጀመሪያ ትንቢታዊ ክንውን የእስራኤል ወደ ምድሯ መመለስና ከእንግዲህ ወደ ባሕር እንደማትጣል ለዓለም ማስመስከሯ ነው። ሌላውና ሁለተኛው የትንቢት ክንውን የጀመረው፥ አውሮፓና ዓለም ያለ ዓረብ ነዳጅ ዘይት ለመንቀሳቀስ አለመቻላቸውን በተረዱ ጊዜ ነበር። የተለመደው

የኃይል አሰላለፍ ሚዛን በመናጋቱ አዲስ የሚዲትራኒያን መንግሥታት ኅብረት ብቅ ይላል። የእነዚህ ክንውኖች ሂደት ከቀጠለ የአርማጌዶን ጦርነት በደጅ በመሆኑ በማንኛውም ሰዓት ሊጀመር ይችላል። የእኛ ትውልድም እነዚህ በብሉይና በአዲስ ኪዳን የተተነበዩ አስደናቂ ትንቢቶች ሲፈጸሙ ለመመስከር ይበቃ ይሆናል።

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በዚህ ትውልድ ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ሰው ጥያቄ አለን። ጥያቄውም ለጌታ መምጣት ዝግጁዎች ነን? የሚል ነው።

ስላልተፈጸሙ ትንቢቶች አጭር መግለጫ

1. የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ (1ኛ ቆሮ. 15፡51-58፤ 1ኛ ተሰ. 4፡13-18)

2. የሮም ግዛት መታደስ (መነሣት)፤ የአሥሩ መንግሥታት ኅብረት (ዳን. 7፡7፥24፤ ራእይ 13፡ 1፤ 17፡3፥ 12-13)

3. የመካከለኛው ምሥራቅ አምባገነን መነሣት (ዳን. 7፡8፤ ራእይ 13፡1-8)

4. ክርስቶስ መጥቶ መንግሥቱን በምድር ከመመሥረቱ ከሰባት ዓመት በፊት ከእስራኤል ጋር የሚደረግ የሰላም ውል (ዳን. 9፡27)

5. የዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ (ራእይ 17፡1-15)

6. ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ አራት ዓመት ቀደም ብሎ ሩሲያ እስራኤልን መውረሯ (ሕዝ. 38-39)

7. ከእስራኤል ጋር የተደረገው ስምምነት መጣስ፡- የዓለም መንግሥት፥ የዓለም ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት፥ እና የክህደት ሃይማኖት ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ሦስት ዓመት ተኩል ቀደም ብሎ መጀመራቸው (ዳን. 7፡23፤ ራእይ 13፡5-8፥ 15-17፤ 17፡16-17)

8. የብዙ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ሰማዕትነት (ራእይ 7፡9-17፤ 13፡15)

9. የመለኮታዊ ፍርዶች ወደ ምድር መፍሰስ (ራእይ 6-18)

10. የዓለም ጦርነት በመካከለኛው ምሥራቅ መፈንዳት፡- የአርማጌዶን ጦርነት (ዳን. 11፡ 40-45፤ ራእይ 9፡13-21፤ 16፡12-16)

11. የክርስቶስ ዳግም መምጣት (ማቴ. 24፡27-31፤ ራእይ 19፡ 11-21)

12. ፍርድ በክፉዎች ላይ (ሕዝ. 20፡33-38፤ ማቴ. 25፡31-46፤ ይሁዳ 14፥ 15፤ ራእይ 19፡15-21፤ 20፡1-4)

13. የሰይጣን መታሠር (ራእይ 20፡ 1-3)

14. የብሉይ ኪዳንና የታላቁ የመከራ ዘመን ቅዱሳን ትንሣኤ (ዳን. 12፡2፤ ራእይ 20፡4)

15. የሺህ ዓመቱ መንግሥት መጀመር (ራእይ 20፡5-6)

16. ዓመፅ በሺህ ዓመት መንግሥት ፍጻሜ ላይ (ራእይ 20፡ 7-10)

17. ትንሣኤና ፍርድ በከሃዎችና በሰይጣን ላይ፡- በታላቁ የነጩ ዙፋን ፍርድ (ራእይ 20፡ 11-15)

18. የዘላለም መጀመር፡- አዲስ ሰማይ፥ አዲስ ምድር፥ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም (ራእይ 21-22)

# 16

# ሊታወስ የሚገባ ተስፋ

### ♦ ለጭንቀት ቀን አጽናኙ ተስፋ

በመጨረሻ ዘመን የሚፈጸሙ አስደናቂ ትንቢቶች እንዳሉ ቢታወቅም፥ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸውን ተስፋ ያህል ሰውን የሚያበረታታ የለም። በመሠቀያው ዋዜማ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ላይኛው ክፍል ተሰብስበው ሳሉ፥ ትተቻቸው እንደሚሄድና እነርሱም ሊከተሉት እንደማይችሉ ነገራቸው። ከዚህም ሌላ ከእነርሱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠውና አንደኛው ደግሞ እንደሚክደው ሲነግራቸው ደቀ መዛሙርቱ በጣም አዘኑ፤ ተሸበሩ። በዚህ ሁኔታ ሳሉ ነበር፥ የሁልጊዜ ትዝታ ሊሆን የሚገባ ቃል የነገራቸው፦ "ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም እመኑ፤ በአባቴ ዘንድ ብዙ መኖሪያ አለ፤ አለበለዚያ ግን 'የምትኖሩበትን ስፍራ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ' ባላልኋችሁም ነበር። ሄጄ ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፥ እኔ ባለሁበት እንድትኖሩ እንደገና መጥቼ እወስዳችኋለሁ" (ዮሐ. 14፡1-3፥ በ1980 ዓ.ም. እትም)።

### ♦ ከዳግም ምጽአቱ የሚለየው አዲስ ተስፋ

ይህ ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ እንደሆነ የሚጠቀስ ምጽአት ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ትምህርቱ ካስተማረውና ማቴዎስ በ24ኛው ምዕራፍ ከዘገበው በድንቅ ሁኔታ ይለያል። በዚያ ክፍል እርሱ ወደ ምድር ዳግም ከመምጣቱ በፊት ስለሚፈጸሙ ሁኔታዎች ነበር የተናገረው። ኢየሱስ በግልጥ ወደ ምድር የሚመለሰው ከታላቁ መከራ በኋላ የአይሁድ ቤተ መቅደስ ከረከሰና በእስራኤል ሕዝቦች ላይ ተደራራቢና አስከፊ ስደት ከደረሰ በኋላ መሆኑ ግልጥ ነው። ይህ መከራ የሚያከትመው፥ ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት ዳግም በታላቅ ግርማ ሲመጣ ይሆናል። ኢየሱስ በላይኛው ክፍል ተሰብስበው ለነበሩ ደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው ተስፋ ግን የተለየ ነው። አማኞችን በአየር ላይ ለመገናኘት ስለመምጣቱና ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ነበር የሚነግራቸው።

የመነጠቅ ተስፋ ለደቀ መዛሙርቱ የነበራቸውን ተስፋ አሰፋላቸው፥ በጉጉትም የሚጠብቁት ሆነ። ኢየሱስ ወደ ሰማይ የተመለሰው በአባቱ ቤት ቦታ

ሊያዘጋጅላቸውና እንደገናም ወደ ራሱ ሊወስዳቸው ነው። ተስፋው ከመሬት ስለመሄድና መንግሥተ ሰማያት ስለመግባት ቢሆንም፥ ስለ ጉዳዩ ምንም ምልክት አልሰጠም፤ አስቀድሞ መፈጸም ያለበት ትንቢት መኖሩንም አላመለከተም። ነገር ግን በቅርቡ የሚፈጸምና እርሱ ከተለያቸው ቀን አንሥቶ በናፍቆት የሚጠብቁት ተስፋ ነበር።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ፍች ሰጭዎች ይኼኛውን የክርስቶስ ምጽአት መንግሥቱን በምድር ለመመሥረት በሰማይ ሠራዊት ታጅቦ ከሚመጣበት ዳግም ምጽአቱ ጋር አቀናጅተው ለማቅረብ ይሞክራሉ (ራእይ 19)። ሌሎች ብዙ ፍች ሰጭዎች ግን ይህን ክፍልና ተዛማጅ ጥቅሶችን በጥንቃቄ በመመርመር ክርስቶስ ለወገኖቹ የመምጣቱ ትንቢት ሌላ የተለየ ቀዳሚ ድርጊት እንጂ፥ ከመጨረሻ ዘመን ዋና ድርጊቶች የሚቀጥል አለመሆኑን ያረጋግጣሉ።

ክርስቶስ ለታወቡት ደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸውን ተስፋ ዛሬ አማኞች ለእነርሱም የተሰጠ አድርገው ሊተማመኑበት ይችላሉ። በታላቁ የመከራ ዘመን የሚኖረው መሥዋዕትነት በአሁኑ ዘመን ያሉ አማኞች ወደፊት የሚጠብቁት ነገር እንደማይሆን ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጥ ባያመለክቱ ኖሮ፥ ክርስቲያኖች በሁኔታው መታወካቸው አይቀርም ነበር። ዛሬ እውነተኞቹ ክርስቲያኖች ወደፊት በዓለም ላይ ስለሚደርሰው መቅሠፍት መታወክ ወይም መፍራት አይኖርባቸውም። ከዚያ ይልቅ፥ ክርስቶስ በቅርቡ እንደሚመለስና ከእርሱም ጋር ለዘላለም እንደሚሆኑ በማሰብ ደስ ሊላቸው ይገባል።

## ♦ መነጠቅ:- ዋናው የሐዋርያት ትምህርት

ክርስቶስ ይህን ተስፋ ከዓወጀ ከዓመታት በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ገልጦለት ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ስለዚህ ድንቅ ተስፋ ዝርዝር መግለጫ ሰጥቷል (1ኛ ተሰ. 4፡13-18)፤ እርሱም የክርስቶስን ለወገኖቹ መምጣት ተሰሎንቄያዊያን እንዲያውቁት ሲገልጥ፥ እግዚአብሔር የፈለገው እውነት ነው ይላል።

በሐዋርያት ሥራ 17፡1-9 ያለው ክፍል እንደሚያመለክተው ጳውሎስ፥ ሲላስና ጢሞቴዎስ ወንጌልን ለሦስት ሰንበት ያህል በተሰሎንቄ ሰብከዋል። ከዚህም የተነሣ "ብዙ እግዚአብሔርን የሚፈሩ የግሪክ ሰዎች አመኑ" የማያምኑ አይሁዶች ግን፥ የጳውሎስን አገልግሎት በመቃወም እንደሚገድሉት ዛቱ። ስለሆነም ጳውሎስና ተባባሪዎቹ በሌሊት ሸሽተው አመለጡ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጳውሎስ እንደገና ተሰሎንቄያዊያን እንዴት እንደሆኑ ለማወቅ ፈልጎ ጢሞቴዎስን ወደዚያ ላከው። ስለ ተሰሎንቄያዊያን ጢሞቴዎስ ያቀረበውን ዘገባ ጳውሎስ በሰማም ጊዜ ልቡ በደስታ ተሞልቶ ክርስቶስን አከበረ። በዚያ ክልል

እያንዳንዱ ሰው የናዝሬቱ ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ፥ ያመኑበትንም እንደሚያድን ይናገር ነበር።

ጢሞቴዎስ ከተሰሎንቄ ክርስቲያኖች የቀረበና እርሱ መመለስ ያቃተውን ትምህርተ-መለኮታዊ ጥያቄ ይዞ ነበር የመጣው። አንደኛው ጥያቄ ስለ ጌታ ዳግም ምጽአት ነበር። ሙታን የሚነሡት ክርስቶስ በሕይወት ላሉት ከመምጣቱ በፊት ነው? ወይስ በኋላ? ይል ነበር ጥያቄው። የቀረበው ጥያቄ ሲመረመር ጳውሎስ ከዚህ በፊት ለነዚያ ክርስቲያኖች ስለ ጌታ መምጣት አስተምሯቸው እንደነበር ያስገነዝባል። እነዚህ አማኞች የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ (1ኛ ተሰ. 4፡17)፥ በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የተነገረው የመጨረሻ ዘመን ፍርድ ከመምጣቱ በፊት እንደሆነ እርግጠኞች ነበሩ። የእነርሱ ዋና ፍላጎት አስቀድመው የሞቱት ወገኖቻቸው ከእነርሱ ጋር እንደሚሆኑ ማረጋገጥ ነበር።

## ♦ መነጠቁ በጌታ የሞቱትን ክርስቲያኖችም ይጨምራል

እግዚአብሔር ይህን እውነት እንዲረዱ እንደሚፈልግና ተስፋ ቢስ እንደሆኑትና እንደማያምኑ ሰዎች ማዘን እንደማይገባቸው ጳውሎስ በጻፈው መልእክቱ አረጋገጠላቸው። የተስፋቸውን እርግጠኛነት በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡14 ላይ እንዲህ በማለት ያብራራል፡- "ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።" ይህ የክርስቶስ ዳግም መምጣት ተስፋ፥ በሕይወት ላሉትና አምነው ለሞቱት፥ እንዳመኑበትና ተስፋ እንደጣሉበት እንደ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እርግጠኛ ነው።

ጳውሎስ "እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና" ሲል ምን ማለቱ ነበር? በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ላይ ክርስቲያን ሲሞት ነፍሱ ወዲያው መንግሥተ ሰማይ እንደምትገባ የሚያብራ ራውን ቃል ነው የሚገልጠው። ይኸውም "ከሥጋ ተለይተን" ሲል "በጌታ ዘንድ ለማደር" እንደሆነ ስለሚያረጋግጥ (ቁ. 8)፥ ለጥያቄው የተሰጠው መልስ ለመረዳት የሚያስቸግር አልነበረም። ክርስቶስ አማኞችን ለመገናኘት ከሰማይ ሲወርድ እነዚህን (የሙታንን) ነፍሳት ይዞ ይመጣል። በመነጠቅ ጊዜ አካላቸው ከመቃብር ይነሣና ከነፍሳቸው ይገናኛል።

## ♦ የክንውኖችን ቅደም ተከተል መረዳት

ጳውሎስ ክንውኑን እንዲህ ሲል ይገልጠዋል፥ "በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፥ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም። ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ

በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ። ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን" (1ኛ ተሰ. 4፡15-17)።

ይህ አዲስ እውነት በብሉይ ኪዳን አልተገለጠም። ለጳውሎስ በቀጥታ የተገለጠ እውነት ነበር፥ "በጌታ ቃል የምላችሁ ይህ ነውና" (1ኛ ተሰ. 4፡15)። ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ በአካል የምንቀይ በጌታ የሞቱትን ቀድመን አንሄድም።

ይልቁንም ጳውሎስ የጌታን ከሰማይ መውረድ "በከፍታ የትእዛዝ ድምፅ" ብሎ ይገልጠዋል። ክርስቶስ የሞቱት እንዲነሡና ከምድር ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዲዛወሩ ያዛል።

## ♦ ትንሣኤን ለማዘዝ የክርስቶስ ሥልጣን

ይህ ተስፋ ክርስቶስ በምድር ሳለ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ከነገራቸው ጋር ይሄዳል፡- "በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ" (ዮሐ. 5፡28-29)።

መነጠቅ የትንቢቱ ከፊል ፍጻሜ ቢሆንም (በዚህ ዘመን የሚሞቱትን ክርስቲያኖች ትንሣኤ ብቻ የሚመለከት በመሆኑ)፥ ጌታ በመለኮታዊ ሥልጣን የሚናገረው ቃል ነው። ክርስቶስ ትእዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ድምፅ ይሰማል (1ኛ ተሰ. 4፡16፤ ተዛማጅ ጥቅስ ይሁዳ 9)፤ እና በምልክትም "በእግዚአብሔር መለከት" ወይም "የኋለኛው መለከት ሲነፋ" (1ኛ ቆሮ. 15፡52) ለክርስቲያኖች ይህ የመጨረሻ ጥሪ ነው። የወንጌልን የምሥራች ይሰሙና ለጥሪው በእምነት መልስ ይሰጣሉ። የአገልግሎት ጥሪም ደርሶአቸው ልባቸውንና ሕይወታቸውን ለጌታቸው ሰጥተው ነበር። ለእነርሱ ይህ የመጨረሻ ጥሪ ምድራዊው የእንግድነት ኑሯቸው አክትሞ ዘላለማዊ ኑሮ ከጌታቸው ጋር የሚጀምሩበት ይሆናል።

## ♦ በአየር ላይ በአንድነት መገናኘት

የክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ ዳግም መገለጥ በአስገራሚ ሁኔታ ነው የተብራራው፡- "በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ" (1ኛ ተሰ. 4፡16)። "ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን" (1ኛ ተሰ. 4፡17)። እንዴት ያለ ግንኙነት ይሆናል!

አማኞች ሳያዩ የወደዱትን ጌታ ለመጀመሪያ ጊዜ ያዩታል (1ኛ ጴጥ. 1፡8)። በሞት ለተለያዩ እንዴት ያለ የግንኙነት ጊዜ ይሆን! ቤተሰቦችና ጓደኞች እንደገና ይተያያሉ። ከዚያ በኋላ አይለያዩም፤ ለዘላለም ከጌታ ጋር ይሆናሉ።

## ♦ የመነጠቅ መጽናኛነት

ይህን አስደናቂ ተስፋ መሠረት በማድረግ ነው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች እንዲህ እያለ የሚነግራቸው፡- "ስለዚህ እርስ በእርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ" (1ኛ ተሰ. 4፡18)። ይህ ተስፋ በቅርቡ የሚገለጥ በመሆኑ ከሚወዷቸው ተለይተው ያሳለፉት ዘመን አጭር ሆኖ ነው የሚታሰባቸው። ጥቂቶች ብቻ በሚተርፉበት በታላቁ የመከራ ዘመን ውስጥ ማለፍ ቢኖርባቸው ኖሮ፥ ይህ ማጽናናት የማይቻል ይሆን ነበር። ነገር ግን ክርስቶስ ለእነርሱ ብሎ መምጣቱ ከመከራው ዘመን አስቀድሞ የሚፈጸም በመሆኑ አጽናኝ ተስፋ ሆነላቸው።

## ♦ መነጠቅና አዲስ አካል- ለሕያዋን

ጳውሎስ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ስለዚህ ጉዳይ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ ተጨማሪ ገለጣ ሰጥቷል። ግብረገብንና ትምህርተ-መለኮትን አስመልክቶ በአሥራ አራት ምዕራፎች በጻፈላቸው ደብዳቤዎች ላይ ሲያር ማቸው ቆይቶ በምዕራፍ 15 ላይ ታላቅና መሠረታዊ እውነት ይገልጥላቸዋል። ክርስቶስ ለኃጢአታቸው እንደሞተ በመግለጥ ወንጌልን እንደገና አወጀ። ክርስቶስ ከሞት የመነሣቱን ታላቅ እውነት ደገፈ። እንዲሁም የክርስቶስ ትንሣኤ ለአካላችን ትንሣኤ መሠረት መሆኑን አመልክቷል። ለመቃብር የተዘጋጀው የአሁኑ አካላችን በጌታ ፊት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቁ ይሆን ዘንድ መታደስና ሰማያዊውን አካል መልበስ አለበት። በእግዚአብሔር መሠረታዊ ዕቅድ የሕይወት ሂደት፥ ልደት፥ ሞትና በእርሱ ለሚታመኑ ትንሣኤ ነው።

ሐዋርያው በምዕራፉ ማጠቃለያ ላይ በብሉይ ኪዳን ተደብቆ የነበረ፥ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን የተገለጠ አንድ እውነት ያስረዳል (ቈላ. 1፡26)። በአዲሱ መገለጥ መሠረት ከተራው የሕይወት ሂደት ማለትም ከሕይወት፥ ከሞት፥ እና ከትንሣኤ ባሻገር ሌላ ተጨማሪ እውነት ታውቋል፤ እንዲህ በማለትም ይገልጥላቸዋል፡- "እነሆ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችንም አናንቀላፋም። ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና፥ ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ። እኛም እንለወጣለን" (1ኛ ቆሮ. 15፡51-52)።

ጌታ ሲመለስ በሕይወት የሚኖሩ ክርስቲያኖች አካላቸው እንደ ሙታኑ አካል መለወጥ ያስፈልገዋል። ጳውሎስ እንዳስገነዘበው፥ ምድራዊው አካላቸው የሚበሰብስ፥ የሚፈርስ፥ የሚያረጅና የሚታመም ነው። የክርስቲያኖች አካልም ቢሆን ሟች ነው።

ጳውሎስ በሌላ ቦታ እንደገለጠው (ኤፌ. 2፡1-3፤ ፊልጵ. 3፡21)፥ የሰዎች አካል ኃጢአተኛና በቅዱሱ ጌታ ፊት ሊቀርብ የተገባ አይደለም። ለዚህ ነው አስገራሚው ለውጥ ያስፈለገው። የሚለወጠው አካል ከእንግዲህ የማያረጅና ለዘላለም የማይሞት ነው።

ሐዋርያው ይህንኑ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡53 ላይ እንዲህ ሲል ይገልጠዋል፡- "ይኽ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ፥ ይህ የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና። ይህም የሚሆነው ክርስቶስ ለራሱ ወገኖች ሲመጣ ነው። በዚያን ጊዜ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ" (1ኛ ቆሮ. 15፡54)።

## ♦ መነጠቁ ከመጨረሻ ሰዓት ድርጊቶች በፊት ይከናወናል

ክርስቶስ መንግሥቱን በምድር ለመመሥረት የሚመጣ ስለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ሁሉ ይገልጣሉ። ሰማዕታትና በፍዳው ዘመን ያለቁ ሙታንም እንደሚነሡ ይናገራሉ፤ በአንጻሩ ግን በዚያን ጊዜ ስለሚኖሩ ቅዱሳን መለወጥ የሚያስረዱት ነገር የለም። ይህን ያልገለጡት በመከራው ወቅት በሕይወት ያሉ ቅዱሳን ክርስቶስ መንግሥቱን በምድር ለመመሥረት በሚመጣበት ጊዜ ስለማይለወጡ፥ ነገር ግን የሱ አስተናጋጅ ሆነው በተፈጥሮአዊ አካላቸው የሺህ ዓመቱ መንግሥት ተካፋይ ስለሚሆኑ ነው። እንደ ወትሮው ሁሉ በሕይወት ይኖራሉ። ማለትም ይዘራሉ፥ ቤት ይሠራሉ፥ ልጅ ወልደው ምድርን እንደገና በሕዝብ ይሞሏታል። እንዲህ ዓይነቱ ሕይወት፥ የክርስቶስ መንግሥት ሲጀመር ቅዱሳን ሁሉ ከተወሰዱና ሰማያዊ አካል ከተሰጣቸው የማይቻል ይሆናል። ይህ አንዱና ዋናው ምክንያት ነው። ለዚህም ነው መነጠቅ የመከራው ዘመን በዓለም ከመጀመሩ በፊት የሚፈጸመው።

ቤተ ክርስቲያን በምትነጠቅበትና ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት በድል በሚመጣበት ክንውን መካከል ለአዲስ አማኞች፥ ማለትም አይሁድና አይሁድ ያልሆኑ ወገኖች ለመዳን ወደ ክርስቶስ የሚመጡበት በቂ ጊዜ መኖር አለበት። እነዚህ ናቸው በሺህ ዓመቱ አገዛዝ ጊዜ ምድሪቱን የሚሞሏት፤ የተነጠቁትና አካላቸው የተለወጠ አማኞች ዳግም ከክርስቶስ ጋር አብረው ይገዛሉ።

## ♦ በጉጉት መኖር

ጳውሎስ እንደ ተሰሎንቄ ሰዎች ሁሉ፣ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንም የክርስቶስ ምጽአት አይቀሬና ድንቅ ተስፋ መሆኑን ገልጦላቸዋል። በሌሎች ገለጣዎቹ እንዳደረገው ሁሉ፥ እዚህ ላይ ይህ መነጠቅ ምን ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉት አይጠቅስም። እንደ ሌሎቹ ጥቅሶች ሁሉ፥ 1ኛ ተሰሎንቄ 5 የሚያመለክተው "የጌታ ቀን"፥ እግዚአብሔር የሰውን ኃጢአት በቀጥታ የሚቀጣበት ጊዜ ሲሆን ይህም ከመነጠቅ ለጥቆ ወዲያውኑ የሚከናወን መሆኑን ነው። "የጌታ ቀን" የሚጀምረው በዚህ አኳኋን በመነጠቅ ጊዜ መሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያን ወደዚህ ቀን ገብታ የእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ በማያምኑት ላይ ሲፈስ አብራ እንደማትሠቃይ ግልጥ ያደርገዋል (1ኛ ተሰ. 5፡9)። የአንደኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ክርስቲያኖች የኖሩት የክርስቶስን መምጣት በመጠበቅ፥ በሱ የሞቱት የሚነሡበትንና በአካል ያሉትም የሚወሰዱበትን ቀን በጉጉት በመጠበቅ ነበር። ይህ የተባረከ ተስፋችን (ቲቶ 2፡13)፥ ይህ የሚያነጻ ተስፋ (1ኛ ዮሐ. 3፡2-3)፥ ይህ አጽናኝ ተስፋ (1ኛ ተሰ. 4፡18) በእውነት በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ጥልቅ ደስታ ሊሆን ይገባል። በተለይ በነዚህ በጣም ወሳኝ በሆኑ ቀናት ተዘጋጅተን የጌታችንን መምጣት በንቃት መጠበቅ አለብን።

# 17

# የሚቀጥለውስ?

## ♦ ተከታዩን እንቅስቃሴ በአንክሮ መጠበቅ

የመካከለኛው ምሥራቅን ሁኔታ በአንክሮ የሚያስተውሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፥ የሚቀጥለው አስገራሚ ጉዳይ የምዕመናን ሁሉ መነጠቅ እንደሚሆን ይጠብቃሉ። የክርስቶስ መምጣት ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ በክርስቲያኖች ሁሉ ሲጠበቅ የኖረ ታላቅ ተስፋ ሲሆን፥ ተጠራጣሪዎች ግን እስከ ዛሬ መች ተፈጸመ በማለት ይዘብታሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስ በሱ ሕይወት ዘመን እንደሚመለስ ተስፋ አድርጎ ነበር። የጥንት ክርስቲያኖችንም የክርስቶስን መምጣት በማንኛውም ሰዓት ነቅተው እንዲጠብቁ አስተምሯቸዋል።

ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ የሚጠቁም ቅድሚያ ምልክት ሳይሰጥ ለምንድነው ክርስቲያኖች ሁሉ በሕይወት ዘመናቸው ይህ ይፈጸማል ብለው የጠበቁት? ይህንስ ትውልድ በዚህ ጉዳይ ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?

## ♦ የእግዚአብሔር ትክክለኛ ጊዜ

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚገልጡት፥ እግዚአብሔር መለኮታዊ ዕቅዱን ከመፈጸም አይዘገይም። የክርስቶስ ዳግም መመለስ የዘገየ ቢመስልም፥ ጥሩና በቂ ምክንያት አለው። እርግጥ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ተስፋ ከተሰጠ ይኸው አሥራ ዘጠኝ መቶ ዓመታት አልፈዋል። የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ክርስቶስ በሕይወት ዘመናቸው እንደሚመጣ አምነው ነበር። ከሞቱ ወዳጆቻቸው ጋር የሚገናኙበት ጊዜ በጣም ቅርብ መስሎአቸው ተጽናንተውም ነበር። ተስፋው ከተሰጠ ምዕተ ዓመታት አልፈዋል! ትውልዶችም መጥተው ሄደዋል። ዓለም ከአንድ ችግር ወደ ሌላ ስትሸጋገር፥ የክርስቶስ መመለስ የተመቻቸ መስሎን ነበር። ነገር ግን አልሆነም።

ለምንድነው ክርስቶስ በሰጠው ተስፋ መሠረት ያልመጣውና የእርሱ የሆኑትን ወደ ራሱ ያልወሰዳቸው? ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት አኳያ ሲታይ እንደዚህ ያለው የሁኔታዎች መዘግየት፥ የማይጠበቅ ወይም ያልተለመደ አይደለም። ክርስቶስ መጀመሪያ የመጣው ለሺህ ዓመታት ሲጠበቅ ከኖረ በኋላ ነበር። የምዕተ ዓመታት ታሪኮች ለክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት መድረክ

ሲያዘጋጁ ቆዩ። የግሪክ ቋንቋ ዳብሮ የምዕራቡ ዓለም መግባቢያ መሆኑ አዲስ ኪዳን በግልጥና በብዙ ቋንቋዎች እንዲጻፍ ረድቷል።

የሮም ገዥዎች በመካከለኛው ምሥራቅ አንጻራዊ ሰላም መሥርተው ነበር። በፍልስጥኤም የነበሩ አይሁዳውያን በሕይወትና በአምልኳቸው የመሢሑን መምጣት ተዘጋጅተው ጠበቁ። መጥምቁ ዮሐንስም በጊዜው ብቅ በማለት የመሢሑን መምጫ መንገድ አዘጋጅቶ፥ ሕዝቡ ንስሐ እንዲገባ አድርጓል። የሮም ሰላም ['Pax Romana'/ፓክስ ሮማና] የጥንት ክርስቲያኖች ወንጌልን በመላው የሮም ግዛት ብሎም በዓለም ለማስፋፋት እንዲችሉ፥ ለዓለም አቀፍ ንግድና ለሕዝቦች ግንኙነት ሰፊ መንገድ ከፍቷል።

የመጀመሪያው የክርስቶስ አመጣጥ በልዑል እግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ትክክለኛ ወቅቱን ጠብቆ የተፈጸመ ነው። ስለ ዳግም ምጽአቱ የተነገሩ ትንቢቶችም፥ በዚሁ መሠረት ትክክለኛውን ወቅት ጠብቀው ይፈጸማሉ።

## ♦ ለምንድነው ክርስቶስ መምጫውን ያዘገየው?

በሰው አመለካከት ስናየው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የዘገየ ይመስል ይሆናል። ነገር ግን ያለፉ ትንቢቶችን ስንመለከት፥ ከአያሌ ምዕተ ዓመታት ታሪኮችና ክንውኖች በኋላ በትክክለኛው የእግዚአብሔር ጊዜ የተፈጸሙ ነበሩ። ትንቢቶች ይዋሉ ይደሩ፥ ለሰዎችም የዘገዩ ይምሰሉ እንጂ አንዳቸውም ሳይቀሩ ቃል በቃል ተፈጽመዋል።

ቅዱሳት መጻሕፍትም ክርስቶስ ያልተመለሰበትን ምክንያት በሚገባ አብራርተዋል። ጴጥሮስ ስለዚሁ ጉዳይ የሚከተለውን ብሏል:- "ለአንዳንዶች የዘገየ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም። ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል" (2ኛ ጴጥ. 3፡9)። የክርስቶስ መምጣት መዘግየቱ ለምርጦቹ ከሚመነጭ ፍቅር የተነሣ ነው። የርኅራኄ አምላክ ገና ብዙዎች ወንጌል ሰምተው በማመን መልስ እንዲሰጡ በትዕግሥት ይጠብቃል። መዘግየቱ ለእኛ ጥቅም ሲሆን፥ በሌላም በኩል ይህን መልእክት ለሌሎች እንድናዳርስ በቂ ጊዜ እንድናገኝ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው።

ያም ሆኖ ታዲያ እግዚአብሔር ለዘላለም እንደማይጠብቅ ቅዱስ ቃሉ ይናገራል። ክርስቶስ ራሱ ስለሚመሠርተው መንግሥት በምሳሌ ሲያስረዳ የመምጫውን ጊዜ ከኖኅ ዘመን ጋር አነጻጽሮታል። ኖኅ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መርከብ ሲሠራ ከጥፋት ውኃ በፊት ከአንድ መቶ ዓመታት በላይ ቆይቷል። የዘመኑንም ትውልድ ሊያስጠነቅቅ ሞክሮ ነበር፤ እነርሱ ግን አፌዙበት፤ መርከብ ሲሠራ አይተውም ሣቁበት። የተባለው ቀን ግን ደረሰ፤ የመርከቡ ሥራ

ስለተጠናቀቀም እንስሳቱ ወደ መርከቡ ገቡ። የአካባቢው ሰዎች ኖኅና ቤተሰቦቹ መርከቡ ውስጥ ሲገቡ አይተው ነበር። ወዲያውም እግዚአብሔር በሩን ዘጋው (ማቴ. 24፡37-39)። ጊዜው ስላለፈ ከመርከቡ ውጪ የነበሩት በጥፋት ውኃው አለቁ።

ክርስቶስ ዳግም ምጽአቱን በዚህ ምሳሌ እንዳብራራ ሁሉ፥ የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅም ከዚህ አኳያ ማየት ይቻላል። እግዚአብሔር ከሰው በላይ ታጋሽ ቢሆንም፥ ፍርዱን የሚገልጥበት ወቅት ይመጣል።

## ♦ ግልጥ የተስፋ መልእክት

የእኛ ትውልድ ክርስቶስ የሚመጣበትና አማኞች የሚነጠቁበት የመጨረሻው ዘመን ትውልድ ሊሆን ይችላል። እንዲያ ከሆነ ልዩ ሸክምና ልዩ ዕድል አለን። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉት በማንኛውም ጊዜ ቢጠሩ እርሱን በአየር ለመገናኘት ተስፋ አላቸው። በአንጻሩ፥ ይህ ጊዜ በኢየሱስ ያላመኑት የእግዚአብሔር ቁጣ በዓለም ላይ መውረጃ መሆኑን ይረዳሉ።

የትውልዳችን ሸክም የእግዚአብሔርን የማዳን መልእክት ለዚህ ለታወከ ዘመን ግልጥ ማድረግ ነው። ሕያው እምነት ደስታ ይሰጣል፥ ለዕለት ኑሯችንም የሚሆን ትርጉምና እርካታ አለው። ወደ ጥፋት በመገስገስ ላይ ላለውም ዓለም ተስፋ ይሰጣል። እያንዳንዳችን የእግዚአብሔር የማዳን መልእክት ገብቶን መልስ ለመስጠታችን እርግጠኞች መሆን አለብን። ከዚያም ይህን አስቸኳይ መልእክት ለቤተሰቦቻችን፥ ለባልንጀሮቻችን እና ለምንችለው ሁሉ በፍቅር ማዳረስ አለብን።

ሰዎች ወንጌልን በእምነት እንዲቀበሉ በብዙ መንገድ መግለጥ ይቻላል። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እምነት የተጻፉና ለብዙ ሺህ ሰዎች የጠቀሙ አጫጭር ጹሑፎች አሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና መልእክት ለዘመናችን ትውልድ መተላለፉ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ መልእክቱ በመጨረሻ ሰዓት በዓለም ላይ ሊመጣ ስላለው የእግዚአብሔር ቁጣ ያስጠነቅቃልና።

## ♦ ስለ ጌታ መመለስ ምልክቶች አሉ?

የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ አስመልክቶ ምንም የተሰጠ ምልክት የለም። መነጠቅን በናፍቆት እንድንጠብቅ የሚያደርጉ ምንም ዓይነት ምልክቶች አልተሰጡንም። ክርስቲያኖች ባልታሰበ ጊዜ የሚሆነውን የክርስቶስ ዳግም መገለጥ በናፍቆት እንዲጠባበቁ ነበር የተነገራቸው። በዚህ እምነት ነበር የጥንት ክርስቲያኖች የኖሩት። ከጥንት ጀምሮ እስካሁን የቤተ ክርስቲያን ተስፋዋ ይሄው

ነው። ምዕመናን ወደ ክርስቶስ ስለሚነጠቁበት ሁኔታ ምንም ምልክት ካልተሰጣቸው፥ ታዲያ ይህ መነጠቅ በቅርቡ ይሆናል ብለን ለማመን መሠረታችን ምንድነው?

ለዚህ ጥያቄ መልስ የምናገኘው፥ ከመነጠቅ በፊት ከሚከናወኑት ሁኔታዎች ሳይሆን፥ መነጠቅን ተከትለው ከሚፈጸሙት ነው። ታሪክ ለክርስቶስ ልደት ሁኔታዎችን እንዳመቻቸ ሁሉ፥ ለዳግመኛ ምጽአቱም ሂደቱን በማመቻቸት ላይ ነው። ከመነጠቅ በኋላ ስለሚፈጸሙ ሁኔታዎች በዚህ መጽሐፍ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ተመልክተናል። ይህ ከሆነ መነጠቅ የማይቀርና በቅርቡ የሚከናወን ነው ብለን ለማጠቃለል እንችላለን።

## ◆ ሦስቱ ዋና ዋና የትንቢት ክፍሎች

ትንቢትን በጥቅሉ ስናጠና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወደፊቱ የሚገልጠውን በሦስት ዋና ዋና አሳቦች ወይም ክፍሎች ማየት እንችላለን። የተነገሩት ትንቢቶች በጠቅላላው የሚያተኩሩት በቤተ ክርስቲያን፥ በመንግሥታት (ሕዝቦች) ወይም በእስራኤል ታሪክ ላይ ነው።

ስለ ቤተ ክርስቲያን የወደፊት ዕጣ የተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ፥ "በእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን" (በማኅበረ ምእመናን በተመሠረተችው) ወይም እንደ ድርጅት በተዋቀረችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጸሙ ሁኔታዎችንና አቅጣጫቸውን ያመለክታሉ። እንደ ድርጅት ስለተዋቀረችው ቤተ ክርስቲያን የተነገሩት ትንቢቶች ክርስቲያን ነን ባዮችንም ጭምር ያካትታሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ለነዚህ የመጨረሻው ዘመን ክርስቲያን ነን ባዮች ወይም በሃይማኖታዊ ድርጅት መልክ የተደራጁ ክፍሎች ብዙ የሚነግረን አለው። እነዚህ ትንቢቶች ስለ ኃያሊቱ ቤተ ክርስቲያን ተግባርና ሐሰተኛው ነቢይ በታላቁ የመከራ ዘመን (ራእይ 17፡1-18) እና የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነው የመጨረሻ ገዥ እንደ እግዚአብሔር እንዲመለክ መፈለጉን ይገልጣሉ።

የመንግሥታት መነሣትና መውደቅ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ትንቢቶች ዋናው ጉዳይ ነበር። የዛሬው ልዩ ትኩረታችን ግን በመጨረሻዎቹ ዓመታት ከአርማጌዶን ጦርነት በፊት ስለሚኖረው ዓለም አቀፍ ሁኔታ በሚገልጡት ትንቢቶች ላይ ይሆናል። እነዚህ ትንቢቶች ዛሬ ከምናየው የዓለም ሁኔታ ጋር አስደናቂ ተመሳሳይነት ስላላቸው እንደ ጌታ መምጫ ማስጠንቀቂያዎች አድርገን ልንወስዳቸው ይገባል።

ስለ እስራኤልና በተለይም ስለ ኢየሩሳሌም የተነገሩት ትንቢቶች፥ ለትንቢት ሁሉ መግለጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በሀያኛው መቶ ክፍለ-ዘመን

ከተደረጉት ድንቅ ትንቢታዊ ክንውኖች ዋናው፥ አገር የለሽ የእስራኤል ሕዝቦች ወደ ምድራቸው መመለሳቸውና በመንግሥትነት መዋቀራቸው ነው። የመጨረሻ ዘመን ትንቢቶች ሁሉ አይሁዶች ወደ ምድራቸው እንደሚመለሱና ዛሬ ባሉበት ሁኔታ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

ከዚህ ጋር ዓለም የሚጠብቀው፥ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ ሦስት ዓመት ተኩል በፊት የሚመሠረተውን የዓለም መንግሥት ነው።

እንደዚሁም በራእይ ምዕራፍ 17 የተጠቀሰው፥ የዓለም ሃይማኖት ዛሬ በሚካሄደው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ ገሃድ በመሆን ላይ ነው። ይህ የዓለም ሃይማኖት ድርጅት እውነተኛ ክርስቲያኖች ከተነጠቁ በኋላ እርቃኑን ይቀራል።

እነዚህ አሁን የሆኑትና ከአምሳ ዓመት በፊት እውነት ያልነበሩ ዋና ዋና ሁኔታዎች የሚያመለክቱት፥ መነጠቅ በጣም በቅርብ ጊዜ የሚከናወን መሆኑን ነው። ከመነጠቅ ለጥቆ ለሚኖሩት ክንውኖች መድረኩ ተዘጋጅቷል። በሁሉም አቅጣጫ ያሉት ትንቢቶች ተደምረው ታሪክ ትውልዳችንን ለመጨረሻው ዘመን እያዘጋጀው ነው።

በእያንዳንዱ ትንቢት ትኩረት መሠረት ጠቃሚ ትንቢታዊ ክንውኖችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይቻላል። በእያንዳንዱ ዝርዝር፥ ቤተ ክርስቲያንን፥ መንግሥታትን ወይም እስራኤልን በተመለከተ የታሪክ አቅጣጫ በግልጥ እንደሚያመለክተው፥ ዓለም በቤተ ክርስቲያን መነጠቅና በአርማጌዶን ጦርነት መጀመር ዋዜማ ላይ ነው ያለችው።

## ♦ ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገሩ ትንቢቶች ማገናዘቢያ

ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ የተነገረው ትንቢታዊ ክንውን በጊዜ ቅደም ተከተል ሲቀመጥ፥ ዓለም ለክርስቶስ መመለስ በጥንቃቄ የተዘጋጀች መሆኗን ይገልጣል። ይህ ማገናዘቢያ ዋና ዋና ትንቢታዊ ክንውኖችን እንደ ቅደም ተከተላቸው ይመለከታል።

1. የኮሚኒዝም መነሣት፥ ከሀደተ-እግዚአብሔርን በዓለም አስፋፋ።

2. የለዘብተኝነት [Liberalism/ሊበራሊዝም] ንቅናቄ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ጤንነት በአውሮፓ፥ ብሎም በአሜሪካ አቀዘቀዘው።

3. ኃያሏን ቤተ ክርስቲያን የመመሥረቱ ሂደት ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያናት ኅብረትን [Ecumenical Movement/ኤኪዩሚኒከል ሙቭመንት] በመመሥረት ጀመረ።

4. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን መቃወምና ከሃዲነት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገሃድ ሆነ።

5. ከክርስትና ሥነ-ምግባር ፈጽሞ ከመራቅ የተነሣ የምግባረ ብልሹነት ቀውስ (ችግር) ይበልጥ ጎልቷል።

6. የመናፍስት አምልኮ፥ ጥንቆላ፥ እና በአጋንንት ማመን ዓለምን ለሰይጣን የመጨረሻ ሰዓት በማዘጋጀት ላይ ነው።

7. ኢየሩሳሌም የዓረቦችና የክርስቲያኖች የሃይማኖት ውዝግብ ማዕከል ሆናለች፤ በዓለም ዙሪያ ያሉት አይሁዶች ደግሞ ከተማይቱን የአይሁድ ሃይማኖት ማዕከል ሊያደርጓት በማቀድ ላይ ናቸው።

8. እውነተኛ አማኞች በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ከዓለም ይሰወራሉ።

9. ከፉ ድርጊት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መገታቱ ያበቃል።

10. ኃያሏ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ተቃዋሚ ሆኖ የሚነሣው ሰው የዓለም ገዥ እንዲሆን በምታደርገው እገዛ ዋና ዋና ሃይማኖቶችን በማሰባሰብ ለሐሰተኛው ነቢይ እንደ መሣሪያ አድርጋ ትጠቀምባቸዋለች።

11. የክርስቶስ ተቃዋሚ ኃያሊቱን ቤተ ክርስቲያን ያፈርስና መመለክን የሚፈልግ ገዥ ይሆናል።

12. በሺህ የሚቆጠሩ አማኞች በዚህ ዘመን በአስከፊ መከራና ሰማዕትነት ያልፋሉ።

13. ክርስቶስ በታላቁ መከራ ጊዜ በሰማይ ከነበሩት ክርስቲያኖች ጋር ይመለስና የመንግሥታት አገዛዝ በአርማጌዶኑ ጦርነት እንዲያከትም ያደርጋል።

## ♦ ስለ መንግሥታት የተነገሩትን ትንቢቶች ማገናዘቢያ

መንግሥታትን በተመለከተ ትንቢታዊ ክንውኖች ታሪካዊ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ተዘጋጅተዋል። ይህ ዝርዝር ዓለም በታሪክ የመጨረሻዎቹ በሆኑት ሰባት ዓመታት ይፈጸማሉ ለተባሉ ትንቢታዊ ክንውኖች መዘጋጀቷን ያመለክታል።

1. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ምሥረታ ለዓለም መንግሥት ጅምር አንድ እርምጃ ወደፊት ነበር።

2. ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የአውሮፓ እንደገና መገንባት፥ በወደፊቱ የሮም ግዛት ተሐድሶ ወቅት የሚጫወተውን ሚና አመቻቸ።

3. የእስራኤል መንግሥት እንደገና ተመሠረተ።

4. ሩሲያ በዓለም ኃያል መንግሥት በመሆን የዓረብ አገሮች ተባባሪ ሆነች።

5. የጋራ ገበያውና የዓለም ባንክ ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚን በአንድ ማዕከል ለመቆጣጠር ድንጋጌ እንደሚያሻ ጠቆሙ።

6. ኮሚኒስት ቻይና ወደ ኃያል መንግሥትነት ከፍ ብላ በትንቢት እንደተጻፈው 200,000,000 ሠራዊት አዘጋጀች።

7. መካከለኛው ምሥራቅ የዓለም ውዝግቦች ሁሉ ትኩረት ሆነ።

8. የነዳጅ ዘይት ዋጋ መናር፥ አዲሱ የዓለም የኃይል ሚዛንና ሀብት ክምችት በሜዲትራኒያን አካባቢ እንዲያተኩር አደረገ።

9. "የብረት መጋረጃ" (በኮሚኒስትና በምዕራባውያን አገሮች መካከል ያለ መለያ) ወርዶ በአውሮፓ አዲስ ሥርዓት ይመሠረታል።

10. የሩሲያ ኃያልነት ያበቃና በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ ያላት ተጽዕኖ ያከትማል።

11. የነዳጅ ዘይት ዋጋ በተከታታይ በመናሩ፥ በሽብርና በመካከለኛው ምሥራቅ በሚፈጠረው ግራ የተጋባ ወታደራዊ ሁኔታ የተነሣ ዓለም ስለ ሰላም የምታሰማው ዋይታ ይቀጥላል።

12. አሥር መንግሥታት የሜዲትራኒያንን ኅብረት ሲፈጥሩ አራተኛውና የመጨረሻው ትንቢታዊው የዓለም መንግሥት ዘመን ይጀምራል።

13. አንድ አዲስ የሜዲትራኒያን መሪ በአስደናቂ የሥልጣን ሽኩቻ የኅብረቱን ሦስት አባል መንግሥታት በማመሳቀል የአሥሩን መንግሥታት ቡድን ይቆጣጠራል።

14. አዲሱ የሜዲትራኒያን መሪ በመካከለኛው ምሥራቅ "የመጨረሻ" ሰላም ስምምነት ያደርጋል (ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ ይፈርሳል)።

15. የሩሲያ ሠራዊት እስራኤልን ለመውረር ይሞክርና በተአምር ይወድማል።

16. የሜዲትራኒያን ገዥ የዓለም አምባገነን መሪ መሆኑን ያውጃል። ከእስራኤል ጋር የነበረውን የሰላም ስምምነት ያፈርሳል፤ አምላክ ነኝ ይላል።

17. አምባገነኑ መሪ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ያረክሳል።

18. የታላቁ ፍዳ አስከፊ ፍርዶች በዓለም ሕዝቦች ላይ ይወርዳሉ።

19. ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው ሠራዊት መካከለኛው ምሥራቅን በመክበብ አምባገነኑን መሪ ያስፈራራዋል።

20. ክርስቶስ ከሠራዊቱ ጋር ከሰማይ ወደ ምድር ይመለሳል።

21. የዓለም ሠራዊቶች የክርስቶስን መምጣት ለመቋቋም ኅብረት ቢመሠርቱም በአርማጌዶን ውጊያ ይወድማሉ።

22. ክርስቶስ የአሕዛብ ዘመን እንዲያበቃ በማድረግ፥ በምድር ላይ የሺህ ዓመቱን መንግሥት ይመሠርታል።

## ♦ ስለ እስራኤል የተነገረ ትንቢት ማገናዘቢያ

ምንም እንኳን የአይሁድን ታሪክ ከዓለም ታሪክ ገንጥሎ ማየት ባይቻል፥ ስለ አይሁድ ሕዝብና መንግሥት የተነገሩ ትንቢቶች ልዩ የማገናዘቢያ ሁኔታዎች አሏቸው። በዚህ ትንቢታዊ ማገናዘቢያ የቀረቡት መግለጫዎች እንደ ሌሎቹ ድርጊቶች ሁሉ ወደ አርማጌዶን የሚያመሩ አስደናቂ ዝግጅቶች በመከናወን ላይ መሆናቸውን ያመለክታሉ።

1. ከባዱ ሥቃይና ስደት በዓለም ዙሪያ ያሉትን አይሁዶች ፍልስጥኤም ውስጥ መኖሪያ እንዲያገኙ ተጽዕኖ አድርጓል።

2. አይሁዶች ወደ ፍልስጥኤም ተመልሰው በ1948 ዓ.ም. የእስራኤል መንግሥት በይፋ ተመሠረተ።

3. አዲሲቱ የእስራኤል መንግሥት የተሰነዘረባትን ጥቃት እየመከተች ጸናች።

4. ሩሲያ ለእስራኤል ዋና ጠላት ሆና ብቅ ስትል አሜሪካ ደግሞ ከእስራኤል ጎን ቆመች።

5. እስራኤል ጠላቶቿን በጀግንነት ተቋቁማ ኃይሏን በማጠናከር በዓለም ታዋቂ መንግሥት ሆነች።

6. የእስራኤል ወታደራዊ ድል ዓረቦች አብዛኛውን የዓለም የነዳጅ ሀብት በመቆጣጠር በሚያደርጉት ዲፕሎማሲያዊ ፍልሚያ ይጋረዳል።

7. ዓረቦች ያላቸው ደረጃ በማደግ ላይ ባለው ሀብታቸው፥ እንዲሁም በአውሮፓና ቁልፍ በሆኑ የዓረብ አገሮች መካከል ባለው ጥብቅ ግንኙነት ምክንያት ከፍ ይላል።

8. አሜሪካና ሩሲያ ከመካከለኛው ምሥራቅ ገለልተኛ መሆናቸው እየጨመረ በመምጣቱ፥ እስራኤል ተቀባይነት ያለው የሰላም ድርድር ለማድረግ ይበልጥ አስቸጋሪ ይሆንባታል።

9. ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ እስራኤል በአዲሱ የሜዲትራኒያን የመንግሥታት ኅብረት መሪ የሚሰጣትን የግብር ይውጣ የሰላም ዋስትና ለመቀበል ትገደዳለች።

10. አይሁዶች ይህን ዘላቂ መፍትሔ የሚመስል ስምምነት በመቀበል ፈንጠዝያ ያደርጋሉ።

11. በሦስት ዓመት ተኩል የሰላም ዘመን ውስጥ አይሁድነት ያንሰራራል። ጥንታዊ መሥዋዕታቸውንና ሥርዓታቸውን እንደገና በኢየሩሳሌም በሚታነፀው ቤተ መቅደስ ያከናውናሉ።

12. የሩሲያ ሠራዊት እስራኤልን ለመውረር ይሞክርና በምሥጢራዊ ሁኔታ ይደመሰሳል።

13. አዲሱ የዓለም አምባገነን መሪ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ያረክስና በአይሁዶች ላይ ከባድ ስደት ይጀምራል።

14. ብዙ አይሁዶች የተገለጠውን ትንቢታዊ ክንውን በማጤን ክርስቶስን እንደ እስራኤል መሢሕ አድርገው ማመናቸውን ይገልጣሉ።

15. ክርስቲያኖችና አይሁዶች የዓለምን አምባገነን መሪ በመቃወም ሲጨፈጨፉ፥ መልእክቱን በዓለም ዙሪያ የሚያዳርሱ ጥቂት ምስክሮች በመለኮታዊ ኃይል ይተርፋሉ።

16. ክርስቶስ በአርማጌዶን ጦርነት ወቅት ወደ ምድር ሲመለስ፥ አማኝ አይሁዶች መሢሐቸውና አዳኛቸው አድርገው ይቀበሉታል።

17. ከዳዊት ዙፋን የሆነው የሺህ ዓመቱ የክርስቶስ ምድራዊ አገዛዝ ለእስራኤል ሕዝብ የተሰጠውን ትንቢታዊ ተስፋ ከፍጻሜ ያደርሰዋል።

## ♦ የተወሳሰበው የድርጅቶች ገጽታ

ከዚህ በፊት በተመለከትናቸው የዚህ መጽሐፍ ምዕራፎች፥ የትንቢቶችን አጠቃላይ እውነት ከዘመናችን አርዕስተ ዜናዎች ጋር በማዛመድ ለማቅረብ ተሞክሯል። ስለ ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ መንግሥታትና እስራኤል የተነገሩት ትንቢቶች ብዙውን ጊዜ በልዩ ልዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ራእይ ተለያይተው ቢቀመጡም በታሪክ ቁልፍልፍ ተዛምዶ አላቸው። ከእነዚህ የመጨረሻ ዘመን ክስተቶች ውስጥ አብዛኞቹ ከመጀመራቸው በፊት፥ እስራኤል ፍልስጥኤም ውስጥ እንደገና በመንግሥትነት መመሥረት ነበረባት። እንደ መንግሥት ባትኖርና የመካከለኛው ምሥራቅ ችግር ባይፈጠር፥ የሜዲትራኒያን ኅብረት መሪ ከእስራኤል ጋር የሰላም ውል በመፈራረም ዝናና መታወቅን

ባላተረፈ ነበር። የነዳጅ ዘይት አስፈላጊነት ባይንርና እንደ ብረት መጋረጃ የሚቆጠረው የምሥራቅ አውሮፓ ፖለቲካ ባይገለል፥ የአውሮፓ አገሮች ኅብረት በመካከለኛው ምሥራቅ ግጭት ቁልፍ ሚና ሊኖረው አይችልም ነበር። በኢንዱስትሪ የበለጸጉ የአውሮፓ መንግሥታት የነዳጅ ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲሉ በልዩ ልዩ አኳኋን የዓረቦች ጥገኛ ሆነዋል። በሌላ የኃይል ምንጭ ለመጠቀም ቢሞክሩም ከጥገኝነት መላቀቁ አልተሳካላቸውም።

እስራኤል በትንቢቱ መሠረት የሞት ሽረት ፍልሚያ አድርጋ ይፋ መንግሥት መሥርታለች። ቀጣዩ እርምጃ ከጠላቶቿ ጋር የሰላም ስምምነት ማድረግ ይሆናል። የአሥሩ የሜዲትራኒያን መንግሥታት ኅብረት አምባገነን መሪ ብቅ ብሎ ካልፈጸመው በቀር በመካከለኛው ምሥራቅ ዘላቂ ሰላም እንደማይመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። የዚህ የሰላም ውል መፈረም በእስራኤል ትንቢታዊ ዝርዝር ውስጥ ሁለተኛው ክንውን ይሆናል። ይህ ክንውን ከአርማጌዶን በፊት ለሚኖሩት የመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታትም መነሻ ነው። እነዚህ የፍጻሜው ሰባት ዓመታት ክፉ አድራጊው የሚፈታበትና የእግዚአብሔር ፍርድ ጽዋ ወደ ዓለም የሚፈስባቸው ናቸው። የእስራኤል መቋቋም ሦስተኛ ደረጃ የሚጀምረው የሰላሙ ውል እንደተጣሰ ይሆናል። አራተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ክርስቶስ መጥቶ ነጻ ሲያወጣት ይሆናል።

ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገሩት ትንቢቶች የሚያመለክቱት ደግሞ እነዚህ ድርጊቶች ሊፈጸሙ የሚችሉት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ስትወሰድ መሆኑን ነው። የሜዲትራኒያኑ መሪ መነሣት፥ የሐሰተኛው ነቢይ ብቅ ማለት፥ እና የኃያሊቱ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ፥ እውነተኛ አማኞች ከምድር ካልተለዩ ሊገለጡ አይችሉም። ክፋውን የሚቃወመው መንፈስ ቅዱስም በዚህ ጊዜ ከዓለም ይወሰዳል። ሰይጣንም ያለምንም ተቃዋሚ በመዓቱና በማታለሉ እንደፈለገ ይፈነጫል።

የእስራኤል ወቅታዊ ሁኔታ በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ቁም ነገር ያለው ጉዳይ ነው። የእስራኤል ዳግም ምሥረታ ቤተ ክርስቲያን ከምድር እስከምትነጠቅ እውን የማይሆን ከሆነ፥ የዚህ ትርጉሙ ክርስቶስ የርሱ ለሆኑት የሚመጣበት ጊዜ ቀርቧል ማለት ነው። ዓለም በመካከለኛው ምሥራቅ ጦርነት መታወኩ ከቀጠለ በአውሮፓውያንና በዓረብ አገሮች መካከል ብርቱ ኅብረት ይፈጠራል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን እስከምትነጠቅ ድረስ መጪው የዓለም አምባገነን መሪ የራሱን ወሳኝ እርምጃ አይወስድም። ከዚያ በኋላ ነው ሰይጣን ነጻ የሚሆነውና በጥፋት ኃይሎች አማካይነት ታሪክን የሚያመሳቅለው። ስለዚህ ነው በትንቢት አጀንዳ ውስጥ የሚቀጥለው ታላቅ ክንውን የጌታን መምጣት የሚያመለክት መሆኑን የተረዱ ክርስቲያኖች በትጋት የሚጠብቁት።

## ♦ የመጨረሻው መድረክ ዝግጁ ነው።

ዓለም ታላቁን ትርዒት ለማስተናገድ በመዘጋጀት ላይ ናት። ዋና ዋናዎቹ ተዋናዮች ከመድረኩ ግራና ቀኝ ሆነው ታሪካዊ ወቅታቸውን በመጠበቅ ላይ ናቸው። በዋናው መድረክ በትርዒቱ ላይ ተዋናዮቹ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች ዝግጁ ሆነዋል። የመካከለኛው ምሥራቅ ትንቢታዊ ቲያትር ሊጀመር የዓለም መሪዎችን ትኩረት በመሳብ ላይ ነው። ዓለም ዛሬ የፖለቲካውና የኢኮኖሚው ኃይል ያለው የነዳጅ ሀብትን በሚቆጣጠሩ አገሮች እጅ መሆኑን ተገንዝቧል። የአውሮፓ መንግሥታት ከተለዋዋጩ የዓለም ሁኔታ ራሳቸውን ለመጠበቅ አዲስ ኅብረትና ስምምነት ሲሹ፥ የጥንቱ ወዳጅነትና ኅብረት ለዚህ ለውጥ ተገዢ ይሆናል። መካከለኛው ምሥራቅ የዓለም አቀፍ ስምምነት ማዕከላዊ ስፍራ መሆኑ ይቀጥላል።

ዋና ዋናዎቹ ታሪካዊ ድርጊቶች ሁሉ በቀደሙት ዘመናት ተከናውነዋል። የዓለም መንግሥት ምሥረታ ሂደት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በ1946 ዓ.ም. ሲመሠረት ተጀምሯል። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴም በ1948 ዓ.ም. ይፋ ሆኖ እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ለሚኖረው ሃይማኖታዊ ክንውንና ለኋለኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ በመዘጋጀት ላይ ነው።

የመናፍስት አምልኮ፥ ኑፋቄና ለአጋንንት መሠዋት ይቀጥላል። ኮሚኒዝምም በክህደተ-እግዚአብሔር ፍልስፍናው ዓለምን አምባገነኑ መሪ ለሚመለከበት አንድ-ወጥ ሃይማኖት እያዘጋጀት ነው።

የራሷን መንግሥት መሥርታ በመጨረሻው ሰዓት ክንውን የራሷን ሚና ለመጫወት በጉጉት ላይ ያለችው እስራኤልና የዓለም መንግሥታት ለመጨረሻው ትርዒት ተዘጋጅተዋል። በትንቢት እንደተነገረው አገሪቱ የሰላም ቃል ኪዳን ማድረጓ አስፈላጊ ቢሆንም፥ ከፍልስጥኤማዊያን ጥያቄ አንጻር ሲታይ በቀጥታ ውይይት ስምምነት ላይ ልትደርስ የምትችልበት ሁኔታ የለም።

ሩሲያ ከቅድስት አገር (እስራኤል) ጋር ጦርነት ለመግጠም በተጠንቀቅ ላይ ነች። ግብፅና ሌሎች የአፍሪካ አገሮች እስራኤልን በደቡብ በኩል የመውጋት ዓላማቸውን አልተዉም። በራእይ እንደተጠቀሰው ኮሚኒስት ቻይናም በስተምሥራቅ ታላቅ ወታደራዊ ኃይል ለማንቀሳቀስ ትችላለች። እያንዳንዱ መንግሥት በመጨረሻው የታሪክ ሰዓት የራሱን ሚና ለመጫወት ተዘጋጅቷል።

የአሁንዋ ዓለማችን ወደ አርማጌዶን ለሚያመራው ትንቢታዊ ትርዒት በቂ ዝግጅት አድርጋለች። የመድረኩ ለዚህ አስገራሚ ትርዒት መመቻቸት፥

ክርስቶስ የራሱ ለሆኑት (ለወገኖቹ) የሚመጣበትን ቀን በጣም ቅርብ ያደርገዋል። ሰዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላቸውን የግል ግንኙነት ከልብ ማጤን ያለባቸው ዛሬ ነው። እግዚአብሔር ይህን ትውልድ፥ "ለጌታ መምጣት ተዘጋጅ!" ይለዋል።

# ስለ ዘላለም መኖሪያችን እንዴት እርግጠኛ መሆን እንደሚቻል

ብዙ ሰዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደገና ለመመልከት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደኅንነት የሚያስተምራቸውን ነገሮች የሚገልጥ ቀለል ያለ መግለጫ ማግኘቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተውታል። ይህ ማውጫ እያንዳንዱ ሰው ለወደፊቱ በመዘጋጀት ረገድ ሊያውቃቸው የሚገባ አራት ጠቃሚ እውነቶችን የሚያሳይ ነው።

ዓለማችንንና እንደ ግለሰቦች እኛን አስመልክቶ የተገለጠውን ትንቢት በመገንዘብ፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለንን ግንኙነት እንደገና መመልከቱ ጠቃሚ ነው?

# 1. ደስታና ትርጉም ያለው ሕይወት የሚጀምረው ከእግዚአብሔር ጋር ነው።




በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፥ እግዚአብሔር የሚሰጥዎትን ነገሮች ይመልከቱ:-

- ፍቅር- ለእርስዎ ያስብልዎታል።
- ጥበቃ- ከሚያጋጥምዎ አደጋ ይጠብቅዎታል።
- ሰላም- ችግሮችዎን ይቃልልልዎታል።
- ዓላማ- በሕይወት መኖርዎ ዓላማ እንዲኖረው ያደርጋል።
- የዘላለም መኖሪያ- ስለ ወደፊቱ ዕድልዎ ያስባል።

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል:-

"በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና።" (ዮሐንስ 3፡16)

ይህንንም ተናግሯል:-

"እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።" (ዮሐንስ 10፡10)

አውግስጢኖስ ይህን አመልክቷል:-

"እግዚአብሔር ሆይ! ለራስህ ፈጠርከን! የሰው ልብ በአንተ ውስጥ ማረፊያውን እስከሚያገኝ ድረስ እረፍት የለሽ ነው።"


**የሚያሳዝነው ግን. . .**

# 2. ሰውን ኃጢአቱ ከእግዚአብሔር ለይቶታል።

**በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ኃጢአት፡-**

- እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ለመሆን አለመቻላችን
- እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ለማድረግ አለመቻላችን ነው።

ስለዚህ፥ ሁላችንም ኃጢአተኞች መሆናችን ግልጥ ነው። አውቀንም ሆነ ባለማወቅ እግዚአብሔር ላይ አምጸናል።





ይህ ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤ ኃጢአት ከፊቱ እንዲቀርብ አይፈቅድም። እግዚአብሔር በሰው ልጅ ኃጢአት ላይ መፍረድ አለበት፤ ሊያስወግደውም ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

“እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ...” (ኢሳይያስ 53፥6)

“ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች...” (ኢሳይያስ 59፥2)




ኃጢአት ከእግዚአብሔር እስከለየን ድረስ፥ እግዚአብሔር እንዲኖረን በሚፈልገው ደስታና ትርጉም ያለው ሕይወት ልንደሰት አንችልም።

**ደስ የሚያሰኘው...**

# 3. እግዚአብሔር በጣም ይወድዎታል! ኃጢአትዎን ከላይዎ ለማውረድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰጥቶዎታል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

"ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" (ሮሜ 5፡8)

"ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ ሞቶአልና. . .።" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)

እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በሠራው ሥራ ረክቷል። አሁን ፈጽሞ ይቅር ሊልዎትና ትርጉም ያለው ሕይወት ሊሰጥዎ ዝግጁ ነው።




ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ አማካይነት የኃጢአትን ግድግዳ አፍርሷል።

**ሆኖም አንድ ኃላፊነት አለብዎ**

## 4. ደስታና ትርጉም ወዳለው ሕይወት ለመግባት፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአትዎ ይቅርታ እንደሚያደርግልዎ በማመን ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለብዎ።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረንን ይመልከቱ፦

"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" (ዮሐንስ 14፡6)

"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ።" (የሐዋርያት ሥራ 16፡31)

"እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ።" (ሮሜ 5፡1)

### ነገር ግን እምነት ምንድነው?

- በሕክምና ባለሞያ ስንተማመን፥
- በጠበቃ ስንመካ፥
- ወይም ጓደኞችንን ስናምን፥ እምነትን እየተለማመድን እንደሆነ ያመለክታል።

እንዲሁም፥ ለኃጢአትዎ ሥርየት ክርስቶስን ማመን ያስፈልግዎታል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ማለት፥ ኃጢአትዎን ይቅር እንዲልዎና ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖርዎ እንዲያደርግ፥ በእርሱ መተማመን ማለት ነው።



# እንደገና እንመልከተው

እነዚህን ነገሮች ያውቃሉ...

1. ሕይወት ከእግዚአብሔር እንደሚጀምር ፥
2. ኃጢአትዎ ከእግዚአብሔር እንደለየዎ ፥
3. ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአትዎን ዕዳ እንደከፈለልዎ።

## እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የሚጠይቅዎ አንድ ነገር፡-

ደስታና ትርጉም ያለው ሕይወት ይኖሩ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትዎን ይቅር እንዲልዎ፥ በእርሱ እንዲያምኑ ነው።



አሁንም እዚሁ ነዎትን?



ወይስ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትዎን በፍጹም ይቅር እንዲልዎ በእርሱ አምነዋል?

ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትዎን አሁኑኑ ይቅር እንዲልዎ አይፈልጉምን?

ውሳኔዎን ለመግለጥ የሚከተለውን መጸለይ ያስፈልግዎ ይሆናል፡-

‘‘ውድ አባት ሆይ! ኃጢአተኛ መሆኔን ተረድቻለሁ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ሲል እንደሞተ አምኛለሁ። ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ በማመን፥ ያቀረብክልኝን ደኅንነት አሁን ለመቀበል እፈልጋለሁ። ኃጢአቴን ይቅር ስላልከኝ አመሰግንሃለሁ። ከአሁን ጀምሮ ከአንተ ጋር አዲስና ትርጉም ያለው ሕይወት እንድኖር እርዳኝ። አሜን።’’

# ለአዲስ አማኝ አጠር ያለ ምክር

ኢየሱስ የሞተ አዳኝ አይደለም። በሕይወት አለ። የርሱ ኃይል አሁን ቀርቦልዎታል። በክርስቶስ ካመኑ፥ ቃሉን ጠባቂ እግዚአብሔር ሕይወቱን ሊሰጥዎ ቃል ገብቶልዎታል (ዮሐ. 3፡15-16ን ይመልከቱ)።

የክርስትናን ሕይወት ለመኖር የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው! ክርስቲያን እንደመሆንዎ፥ የክርስቶስ መንፈስ በእርስዎም ውስጥ አሁን ይኖራል። ክርስቶስ ሕይወቱን በእርስዎ ውስጥ እንዲኖር በእርሱ መተማመንን በተማሩ መጠን፥ አዲሱ ሕይወትዎ ኃይል ያገኛል (ገላ. 2፡20ን ይመልከቱ)።

ስለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስፈልግዎ። እግዚአብሔር በእርስዎ አማካይነት ሊያደርግ የሚፈልገውን ነገር ለመገንዘብ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ ማጥናት ያስፈልግዎታል (1ኛ ጴጥ. 2፡2ን ይመልከቱ)።

ደስታና ትርጉም ላለው ሕይወት፥ ጸሎት ሌላው ዋና ክፍል ነው። ስለሚያስፈልጉዎ ነገሮች እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ያነጋግሩት (ፊልጵ. 4፡6-7ን ይመልከቱ)።

ሌላ አንድ ነገር አለ። ይኸውም ለብቻዎ ክርስቲያን ለመሆን አለመቻልዎ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጥበት ቤተ ክርስቲያን፥ ከሌሎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ካመኑ ሰዎች ጋር ግንኙነት ይፍጠሩ (ዕብ. 10፡25ን ይመልከቱ)።

# የእንግሊዝኛ ቃላት ዝርዝር


| | | |
|---|---|---|
| ሂሮሺማ | Hiroshima | ገጽ 116 |
| ሂትለር | Hitler | 115 |
| ለዘብተኝነት | [Liberalism/ሊበራሊዝም] | 165 |
| ሐሺም ራፉሳንጃኒ | Hashemi Rafsanjani | 39 |
| ሐፌዝ አልአሳድ | Hafez Assad | 34 |
| መነጠቅ | Rapture | 91 |
| መናከም ቤጊን | Menachim Begin | 37 |
| የመናፍስት ትምህርትና ሃይማኖት | [Spiritism/ስፒሪቲዝም] | 89 |
| የመንግሥታት ሊግ | [League of Nations/ሊግ ኦፍ ኔሽንስ] | 116 |
| ሙሐመድ ጋዳፊ | Muammar Kadafi | 34 |
| ሚካኤል ጎርባቾቭ | Mikhail Gorbachev | 97 |
| ምዕራብ ዳርቻ | [West Bank/ዌስት ባንክ] | 31 |
| ሞሺ ዳያን | Moshe Dayan | 31 |
| ራባት | Rabat | 65 |
| የሰሜን ቃል ኪዳን አገሮች | [NATO/ኔቶ] | 101 |
| ሳላዲን | Saladin | 60 |
| ሳዳም ሑሴን | Saddam Hussein | 11 |
| የስዊዝ ካናል | Suez Canal | 35 |
| ሶፊያ | Sofia | 97 |
| የሺህ ዓመት መንግሥት | Millennial Kingdom | 111 |
| የባልቲክ ባሕር | Baltic Sea | 108 |
| የባልፎር ዲክላሬሽን | Balfour Declaration | 61 |
| ባሕር ሰርጓጅ | [Torpedo/ቶርፒዶ] | 30 |
| የብረት መጋረጃ | Iron Curtain | 95 |
| የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት | United Nations | 117 |
| ቲቶ | Titus | 19 |
| የቴል ኤል አማርና ሰሌዳ | Tell Amarna Tablets | 68 |
| ቴዎዶር ሐርዚል | Theodore Herzl | 61 |
| ቼርኖቤል | Chernobyl | 96 |
| ኒኮላይ እና ኤለና ቻውቼስኩ | Nicolae & Elena Ceausescu | 97 |
| ናፖሊዮን | Napoleon | 115 |
| ናጋሳኪ | Nagasaki | 116 |
| ኔጌቭ | Negev | 62 |

| | | |
|---|---|---|
| ንጉሥ ሑሴን | King Hussein | 29 |
| ንጉሥ ፋይሳል | King Faisal | 45 |
| አላስካ | Alaska | 46 |
| አሌክሳንደር ዱብቼክ | Alexander Dubcek | 97 |
| የአሕዛብ ዘመን | Times of the Gentiles | 144 |
| አርተር ጄ. ባልፎር | Arthur J. Balfour | 61 |
| ኦሲራክ | Osirak | 99 |
| አንጥያኮስ ኤጲፋኖስ | Antiochus Epiphanes | 79 |
| አንዋር ሳዳት | Anwar Sadat | 33 |
| አካባ | Aqaba | 30 |
| የአዝጋሚ ለውጥ | [Evolution/ኤቮሉሽን] | 85 |
| አያቶላ ሆሚኒ | Ayatollah Khomeini | 39 |
| አጋንንት አውጪው | [“The Exorcist”/“ዘ ኤክሰርሲስት”] | 89 |
| ኤላት | Eilat | 30 |
| የከርሠ ምድር ተመራማሪዎች | [Archeologists/አርኪዮሎጂስቶች] | 72 |
| ካምፕ ዴቪድ | Camp David | 37 |
| የክህደት ትምህርት | [Atheism/ኤቲይዝም] | 92 |
| ዋተርሉ | Waterloo | 115 |
| ዋተርጌት | Watergate | 127 |
| የዓለም ባንክ | World Bank | 117 |
| ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያናት ኅብረት [Ecumenical Movement/ኤኪዩሚኒካል ሙቭመንት] | | 166 |
| የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ | World Council of Churches | 82 |
| ዩ ታንት | U Thant | 29 |
| ዮም ኪፑር | Yom Kippur | 34 |
| ጀማል አብዱል ናስር | Gamal Abdul Nasser | 29 |
| ጂሚ ካርተር | Jimmy Carter | 37 |
| ጄኔራል አለንቢ | General Allenby | 61 |
| የጋራ ገበያ አገሮች ኅብረት | Common Market | 102 |
| የፍልስጥኤም ነጻ አውጪ ድርጅት | Palestine Liberation Organization (PLO) | 38 |
| ፍጹማዊነት | [Utopia/ዩቶፒያ] | 149 |
| ፐርል ሐርበር | Pearl Harbor | 116 |
| የሮም ሰላም | [‘Pax Romana’/ፓክስ ሮማና] | 162 |
| ፔሬስትሮይካ | Perestroika | 97 |
| ፕሩድሆ | Prudhoe | 46 |

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማውጫ


**ዘፍጥረት** ገጽ

11፡27 ........ 53
12፡2 ........ 53፥ 54
12፡3 ........ 54
13፡16 ........ 54
14፡18 ........ 68
ም. 15 ........ 54
15፡5 ........ 54
15፡13 ........ 55
15፡18-21 ........ 54
ም. 17 ........ 55
17፡7-8 ........ 55
17፡8 ........ 57
25፡8 ........ 53

**ዘዳግም**

28፡63-64 ........ 59
28፡63-68 ........ 82
30፡3 ........ 146

**ኢያሱ**

1፡2 ........ 56
1፡4 ........ 56

**ዕዝራ**

1፡1-2፡70 ........ 81
3፡1-13 ........ 81
4፡21-24 ........ 81
5፡1-6፡18 ........ 81

**ነህምያ**

1፡1-6፡16 ........ 81

**መዝሙር**

2፡2-3 ........ 146
2፡4-5 ........ 146
2፡6 ........ 146
2፡9 ........ 146
2፡10-12 ........ 146
16፡19 ........ 82
22፡1-21 ........ 82
ም. 24 ........ 146
ም. 72 ........ 147
72፡11 ........ 147
ም. 96 ........ 147
96፡13 ........ 147
ም. 110 ........ 147
110፡6 ........ 147

**ኢሳይያስ**

2፡3 ........ 146
7፡14 ........ 82
9፡6 ........ 147
9፡6-7 ........ 82
9፡7 ........ 147
ም. 11 ........ 147
42፡1-4 ........ 141
53፡1-12 ........ 141
53፡3-12 ........ 82
53፡6 ........ 175
59፡2 ........ 175

**ኤርምያስ**

23፡3-6 ........ 64
25፡9-11 ........ 81
29፡10 ........ 58
30፡3 ........ 128
30፡5-9 ........ 64
30፡7 ........ 63፥ 80፥ 105፥ 128
30፡16-17 ........ 41
31፡31-34 ........ 148
52፡12-13 ........ 81

**ሕዝቅኤል**
ም. 38-39 ....25፥ 108፥ 110፥ 111፥ 112 150
20፡33-38 .......... 150
20፡34-38 .......... 130
20፡38 .......... 148
38፡8 .......... 110
38፡14-16 .......... 108
38፡15 .......... 110
38፡16 .......... 110
38፡18-23 .......... 111
39፡28 .......... 64፥ 147

**ዳንኤል**
2፡39 .......... 81፥ 82
2፡40 .......... 82
2፡41-45 .......... 119
2፡44 .......... 147
5፡1-31 .......... 81
6፡10 .......... 58
ም. 7 .......... 22፥ 77፥ 118
ም. 7-8 .......... 77
7፡5 .......... 81
7፡6 .......... 82
7፡7 .......... 82፥ 118፥ 119
7፡7-8 .......... 129
7፡7፥ 24 .......... 95፥ 102፥ 150
7፡7-28 .......... 77
7፡8 .......... 22፥ 120፥ 150
7፡13-14 .......... 147
7፡19-27 .......... 129
7፡23 .......... 122፥ 150
7፡23-24 .......... 119
7፡24-25 .......... 120
8፡1-22 .......... 82
ም. 9 .......... 58
9፡24-27 .......... 121
9፡25 .......... 81
9፡25-26 .......... 121
9፡26 .......... 102፥ 121
9፡27 .79፥ 102፥ 104፥ 122፥ 129፥ 150
11፡31 .......... 79
11፡36-38 .......... 92
11፡36-39 .......... 136
11፡40 .......... 25፥ 26፥ 136
11፡40-45 .......... 128፥ 141፥ 150
11፡44 .......... 26፥ 136
12፡1 .......... 128፥ 130
12፡2 .......... 151
12፡11 .......... 80፥ 104፥ 120፥ 129

**አሞጽ**
9፡14-15 .......... 28

**ሚክያስ**
5፡2 .......... 70፥ 82

**ኢዮኤል**
2፡1-11 .......... 129
2፡28-32 .......... 129

**ሶፎንያስ**
1፡14-18 .......... 129

**ዘካርያስ**
9፡9 .......... 70
13፡8-14፡2 .......... 129
14፡2 .......... 141፥ 144
14፡2-4 .......... 144
14፡4 .......... 144

**ማቴዎስ**
6፡21 .......... 82
ም. 13 .......... 79

17፡22-23 ... 82
19፡28 ... 142
20፡18-19 ... 82
21፡9-11 ... 71
ም. 23 ... 71
23፡17 ... 71
23፡33 ... 71
23፡37-39 ... 71
23፡39 ... 105፥ 142
ም. 24 ... 153
ም. 24-25 ... 129
24፡1-2 ... 82
24፡1-14 ... 79
24፡2 ... 59
24፡3 ... 73፥ 78
24፡3-14 ... 78
24፡4-14 ... 73
24፡6 ... 42
24፡7 ... 25፥ 74
24፡15 ... 104፥ 121፥ 129
24፡15-16 ... 79
24፡16 ... 129
24፡21 ... 63፥ 105
24፡21-22 ... 122፥ 130
24፡27 ... 142
24፡27-31 ... 150
24፡29 ... 142
24፡29-30 ... 142
24፡30 ... 145
24፡37-39 ... 163
25፡31 ... 145
25፡31-46 ... 130፥ 148፥ 150
27፡33-50 ... 82
28፡1-10 ... 82

## ማርቆስ

13፡3 ... 72
13፡4 ... 72
13፡24-37 ... 142

## ሉቃስ

2፡4-11 ... 82
12፡35-48 ... 142
17፡22-37 ... 142
18፡8 ... 142
19፡40 ... 71
19፡42-44 ... 72
21፡5-24 ... 73
21፡20 ... 82
21፡20-24 ... 19
21፡24 ... 19፥ 65፥ 76፥ 81
21፡25-28 ... 73፥ 142

## ዮሐንስ

3፡15-16 ... 179
3፡16 ... 174
5፡28-29 ... 156
10፡10 ... 174
ም. 14 ... 81
14፡1-3 ... 153
14፡1-4 ... 145
14፡3 ... 25
14፡6 ... 177

## የሐዋርያት ሥራ

1፡11 ... 142
15፡16-18 ... 142
16፡31 ... 177
17፡1-9 ... 154

## ሮሜ

5፡1 ... 177
5፡8 ... 176
11፡1 ... 41፥ 60
11፡25-27 ... 142
11፡26 ... 41፥ 130
11፡26-27 ... 148

## 1ኛ ቆሮንቶስ
11፡26 .......... 142
ም. 15 .......... 157
15፡51-52 .......... 157
15፡51-58 .......... 150
15፡52 .......... 156
15፡53 .......... 158
15፡54 .......... 158

## 2ኛ ቆሮንቶስ
ም. 5 .......... 155
5፡8 .......... 155

## ገላትያ
2፡20 .......... 179

## ኤፌሶን
2፡1-3 .......... 158

## ፊልጵስዩስ
3፡21 .......... 158
4፡6-7 .......... 179

## ቆላስያስ
1፡26 .......... 157

## 1ኛ ተሰሎንቄ
4፡13-18 .......... 24፥ 91፥ 150፥ 154
4፡14 .......... 155
4፡15 .......... 156
4፡15-17 .......... 156
4፡16 .......... 156
4፡17 .......... 155፥ 157
4፡18 .......... 157፥ 159
ም. 5 .......... 159
5፡9 .......... 159

## 2ኛ ተሰሎንቄ
1፡6-10 .......... 142
2፡1-3 .......... 90
2፡1-12 .......... 90
2፡6-10 .......... 91

## 1ኛ ጢሞቴዎስ
4፡1 .......... 89

## 2ኛ ጢሞቴዎስ
4፡2-4 .......... 88

## ቲቶ
2፡13 .......... 159

## ዕብራውያን
6፡13፥ 17-19 .......... 60
10፡25 .......... 179

## 1ኛ ጴጥሮስ
1፡8 .......... 157
2፡2 .......... 179
3፡18 .......... 176

## 2ኛ ጴጥሮስ
1፡1-2 .......... 88
3፡3-4 .......... 88፥ 142
3፡9 .......... 162

## 1ኛ ዮሐንስ
3፡2-3 .......... 159

## ይሁዳ
ም. 9 .......... 156
ም. 14 .......... 145
ም. 14፥ 15 .......... 142፥ 150

## ራእይ

1፡7 ... 142፣ 145
ም. 4 ... 131
ም. 4-18 ... 78
ም. 5 ... 131
ም. 6 ... 131
ም. 6-18 ... 135፣ 150
6፡6-8 ... 25
6፡8 ... 132
6፡16 ... 131
7፡9-17 ... 150
7፡14 ... 63
ም. 9 ... 132
9፡13-21 ... 150
9፡15 ... 132
9፡15-16 ... 26
9፡16 ... 132፣ 136
11፡2 ... 63
12፡2 ... 129
12፡6 ... 129
12፡9 ... 135
ም. 13 ... 78፣ 122፣ 131
13፡1 ... 22፣ 150
13፡1-4 ... 135
13፡1-8 ... 150
13፡4 ... 135
13፡5 ... 120፣ 122፣ 129
13፡5-8፣ 15-17 ... 150
13፡7 ... 122
13፡15 ... 150
13፡17 ... 124
16፡3-4 ... 126
16፡8-9 ... 25
16፡9፣ 11፣ 21 ... 139
16፡12 ... 26
16፡12-16 ... 150
16፡13-14 ... 25፣ 137፣ 143
16፡13-16 ... 25
16፡14 ... 138
16፡14-16 ... 141
16፡16 ... 138
16፡16-21 ... 139
16፡17-20 ... 25
16፡17-21 ... 141፣ 145
ም. 17 ... 91፣ 165
17፡1-15 ... 150
17፡1-18 ... 164
17፡3፣ 12-13 ... 150
17፡6 ... 91
17፡16-17 ... 150
ም. 19 ... 26፣ 131፣ 154
19፡11-16 ... 141፣ 143
19፡11-21 ... 142፣ 150
19፡14 ... 145
19፡15 ... 143
19፡15-21 ... 150
19፡17-18 ... 143
19፡20 ... 143
20፡1-3 ... 151
20፡1-4 ... 150
20፡4 ... 151
20፡5-6 ... 151
20፡7-9 ... 111
20፡7-10 ... 151
20፡8 ... 112
20፡11-15 ... 151
ም. 21-22 ... 151

# የአሳታሚው ማስታወሻ

*“አርማጌዶን፥ የነዳጅ ዘይት እና የመካከለኛው ምሥራቅ ውዝግብ”* ለኅትመት ከታቀዱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍት ውስጥ ሁለተኛው ነው። ይህ መጽሐፍ ከዚህ በፊት ወደ አሥራ ሁለት ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

በመጀመሪያ የታተመው *“የመጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓተ ትምህርት ጥናት”* (በራይሪ/Ryrie) ሲሆን፥ መጽሐፉም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ትምህርቶች ለገል ጥናትና ጥቅም የሚውሉበትን ዘዴ ለማስተማር ይጠቅማል። ይህ መጽሐፍ አሁን በገበያ ላይ ይገኛል።

ጌታ ቢፈቅድ ደግሞ ከዚህ በታች የቀረቡት መጻሕፍት በቅርቡ ተዘጋጅተው ይቀርባሉ። መጻሕፍቱ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተተርጉመው የሚታተሙት በአሁኑ ወቅት በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ የአማርኛ አንባቢዎች ጥቅም እንዲሆኑ ነው።

## *“መንፈሳዊው ሰው”*

(ቼፈር/Chafer)

ጸሐፊው ለእግዚአብሔር ክብር የሚሰጡና እርሱን ደስ የሚያሰኙ፥ ለአማኞች ሰማያዊ ደስታና ሰላምን የሚያስገኙ፥ እና ለክርስቲያን አገልግሎት መሠረት ለሆኑት የኑሮ ዘዴዎች እድገት አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችና እርምጃዎችን በግልጥ አቅርቧል።

## *“መንፈስ ቅዱስ”*

(ዋልቮርድ/Walvoord)

መጽሐፉ ስለ ሥላሴ ሦስተኛ አካል የተደረገ ጥልቅ ጥናት ነው። ይህ ጉዳይ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት የክርስትና እምነት ትምህርተ-ሃይማኖቶች ውስጥ አንዱ ሆኖ ሳለ፥ ነገር ግን በጣም ችላ የተባለና ሰዎችም በሚገባ ያልተረዱት ነው። ጥናቱ ትልቅ ምርምር የተደረገበት ሲሆን፥ ለትምህርት ቤትና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል የታቀደ ነው።

## *“የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ”*

(ሂልደብራንት/Hildebrandt)

አፍሪካ ጌታችን ከተወለደበትና ከሞተበት አገር የቀረበች በመሆኗ፥ ወንጌልን ለመቀበል ቅድሚያ ነበራት። ይህ መጽሐፍ ባለፉት 2000 ዓመታት ውስጥ በመላው የአፍሪካ ክፍለ አህጉር የታየውን የቤተ ክርስቲያን አስደናቂ እድገቶችና አሳዛኝ ውድቀቶች ያወሳል።

## *“መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ለመረዳት”*

(ስቴሬት/Sterrett)

መጽሐፍ ቅዱሳችን ከብዙ ዘመናት ጀምሮ፥ በብዙ ጸሐፊዎችና በተለያዩ ቋንቋዎች ሲጻፍ ቆይቷል። ከቀላል ታሪኮች አንሥቶ እስከ ነቢያት ሕልሞች ድረስ የተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶችን ይዟል። ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ለመረዳት ከባድ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር መጽሐፉ እየገባን እንድናነበው ይፈልጋል! ለሁላችንም የእግዚአብሔር መልእክት ነው። ይህ መጽሐፍ ወጣቶችም ሆኑ በእድሜ የበሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን እንዲረዱ መሠረታዊ መመሪያ ይሰጣቸዋል።